በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የ2004/2005 ኦዲት ዓመት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ሪፖርት

አጠቃላይ ዘገባ

ጥራዝ 2

ሚያዝያ 2005
አዲስ አበባ

ክፍል አንድ

ክፍል ሁለት

ክፍል ሦስት

ማውጫ

ክፍል አንድ

1. መግቢያ 1
2. የ2004 በጀት ዓመት ፋይናንስ እንቅስቃሴ እና የ2004/2005 ኦዲት ሥራዎች ዕቅድና አፈጻጸም 4

ክፍል ሁለት

3. የ2004 በጀት ዓመት ሂሣብ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች 34
3.1 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ ኦዲት..34
3.2 የተሰብሳቢ ሂሣብ...35
3.3 የገቢ ሂሣብ..38
3.4 የወጪ ሂሣብ 50
3.5 የተከፋይ ሂሣብ 58
3.6 የበጀት አጠቃቀም 60
3.7 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ 61
3.8 ተሽከርካሪ...63
4.ልዩ ልዩ...65
4.1. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ 65
5. የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮጀክት ሂሳብኦዲት አስተያየትና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች 68
6. የክዋኔና የአካባቢ ኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሃሣቦች 71
7. የልዩ ኦዲት ስራዎች.. 171
8. ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሰረት እርምጃ ያልተወሰዱ መ/ቤቶች..................... 172
9. መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮች.. 172
10. የመፍትሔ እርምጃዎች... 173
11. ማጠቃለያ 173

ክፍል ሦስት

1. መግቢያ.. 175
2. የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2004 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት 175
3. በ2004 በጀት ዓመት በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች የተሰጠው የኦዲት አስተያየት.. 179
4. ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች.. 180
5. ስለልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች የሂሳብ አያያዝና ንብረት አጠባበቅ በተመለከተ 183
6. በመንግሥትና የልማት አጋሮች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ 188
7. የችግሮቹ ምክንያቶችና መፍትሄያቸው.. 189

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በ2004/2005 የኦዲት ዓመት የተከናወኑ ኦዲቶች ዓመታዊ ሪፖርት እና የመ/ቤቱ እቅድ አፈጻጸም /ከጥር 1/2004 - ታህሣሥ 30/2005

1. መግቢያ

የዋናው ኦዲተር መ/ቤት መንግስት የሀገርቱን ኢኮኖሚ በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘትና በፌዴራል መንግስት መዋቅር ስር ባሉ መ/ቤቶች ውስጥ ተጠያቂነት ግልፅነትና መልካም አስተዳደር ለማስፈን አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 55/1 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል።

- የፌዴራሉን መንግሥት ዕቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በወጡት ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መሰብሰቡን፣ መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፣
- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ላይ የፋይናንስና የክዋኔ ኦዲት፣ የአከባቢ ጥበቃ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች፣ልዩ ኦዲቶች እና ሌሎች ኦዲቶች ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሣብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሣብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩ ለክልልና ለፌዴራል መንግሥት ሠራተኞችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሂሣብ የሚመረመርበትን የኦዲት ደረጃ /ስታንደርድ/ ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው።

1.1 የመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ስልጣን፤ ተግባርና ኃላፊነቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፤
- የፌዴራሉ መንግሥት ለክልል መንግሥታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎች ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- ፌዴራል መንግሥት ከብር 1 ሚሊዮን /አንድ ሚሊዮን ብር/ በላይ የሚጠይቅ ሥራ የግል ሥራ ተቋራጮች እንዲሰሩ በውል የሰጠ እንደሆነ ይህንኑ መንግሥት ነክ የሆነ የግል ሥራ ተቋራጮች ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፤
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የኘሮግራምና የአሠራር ቅልጥፍና ምርመራ ወይም ክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- ለፌዴራል መንግሥቱ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት እና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊው የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ምስክርነት ይሰጣል፣
- ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሣብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል። የፌዴራሉ መንግሥት የኦዲትና የሂሣብ አያያዝ ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፣
- ከክልል መንግሥታት የኦዲት መ/ቤቶች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፣

- ለግል ኦዲተሮችና የሂሣብ አያያዝ ሥራ ለሚያከናውኑ የሂሣብ አዋቂዎች በሥራው መስክ ለመሰማራት የሚያስችላቸውን የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሠርዛል፣
- የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስለመንግሥት በጀት ገቢና ወጪ፣ ሀብትና ዕዳ የሚያቀርበውን ዓመታዊ የሂሣብ ሪፖርት መርምሮ ሃሣብ ይሰጣል፣ ስለሁኔታውም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያቀርበው ዘገባ አስተያየቱን ይገልጻል፣

የሚሉት ናቸው::

1.2 የሪፖርቱ ዓላማ

ሪፖርቱ መ/ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 በአንቀጽ 13/1 እና 2 መሠረት በ2004/2005 የኦዲት ዓመት በአከናወናቸው ኦዲቶች የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች፣ ምክር ቤቱ ለ2004 በጀት ዓመት የፈቀደው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉንና ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘቱን ለማረጋገጥና በሪፖርቱ በቀረበው መረጃ መሠረት ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት እንዲያስችለው፤ እንዲሁም መ/ቤታችን በአዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነትና ተግባር በተሻለና በተጠናከረ ሁኔታ ለመወጣት ባደረገው የስራ እንቅስቃሴ የ2004/2005 የኦዲት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ለማመልከት ነው::

በሪፖርቱ ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሀሳቦች መሠረት ያደረጉት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ፣ የዓለም ባንክ እና ሌሎች ዕርዳታ ሰጪዎች የሚሰጡትን የመሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ ኦዲት ለማስደረግ መንግሥት በገባው ውል መሠረት በብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የወረዳ ፋይናንስና የከተማ መስተዳድር ጽ/ቤቶችን ኦዲት በማድረግ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/1984 የተቋቋሙ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን በተመለከተ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በሌሎች የሙያው ፈቃድ በተሰጣቸው የተፈቀደላቸው የኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ተደርገው የተገኘውን ውጤትና በመ/ቤታችን የተከናወኑ ልዩ ኦዲት ስራዎችን ነው::

የኦዲት ሪፖርቱ የኦዲቱ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ከመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ጋር በሚደረግ የመውጫ ስብሰባ ላይ የተነሱ ሃሳቦችን ያካተተ፣ ለእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊና ተቆጣጣሪ መ/ቤት የኦዲት ሥራው እንዳለቀ እየተላከ፣ በአዋጅ

በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን መልስና አስተያየት ያገናዘበ ነው:: ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች፣ አጠቃላይ ተቀባይነት ያላቸውን የመንግሥት ሂሣብ አያያዝ ስርዓት እና ኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት እና ሰነዶች፣ እንዲሁም የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው::

በዚህ ሪፖርት መ/ቤታችን ባለው የሰው ኃይልና በተመደበለት በጀት በ2004/2005 የኦዲት ዓመት ያከናወናቸው ሥራዎች በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ተለይተው ቀርበዋል:: የመጀመሪያው ክፍል የ2004/2005 የኦዲት ዓመት የመ/ቤቱ ዕቅድና አፈፃፀም፣ በሁለተኛው ክፍል የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ግኝቶች፣ መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮች፣ የመፍትሄ ሃሣቦችና አጭር ማጠቃለያ እና ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በኮርፖሬሽኑና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ ኦዲቶችን የሚመለከት ይሆናል::

በሁለተኛው ክፍል የቀረበውን የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ሥራን በተመለከተ የቀረበው ሪፖርት የልዩ ልዩ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት፣ የአካባቢ እና የክዋኔ ኦዲትን እንዲሁም መንግስት ከአለም ባንክ እና ሌሎች ዕርዳታ ሰጪዎች ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ለክልል መንግሥታት የተሰጠውን ሂሳብ ተከታታይ ኦዲት ያጠቃልላል::

2. የ2004 በጀት ዓመት ፋይናንስ እንቅስቃሴ እና የ2004/2005 ኦዲት ሥራዎች ዕቅድና አፈጻጸም

2.1 ሥራ ላይ የዋለው በጀት

በ2004/2005 የኦዲት ዓመት የተፈጸሙ ሥራዎችን ለማከናወን የተመደበውና ሥራ ላይ የዋለውን በጀት በተመለከተ በመ/ቤቱ አዲስ አሠራር መሠረት

የመ/ቤቱ የኦዲት ሥራ ዓመት ከጥር 1/2004 - ታህሣስ 30/2005 ቢሆንም፤ የ2004 በጀት ዓመት ስራ ላይ የዋለው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የ2004 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም

ተ. ቁ	የወጪ አርዕስት	የበጀት ኮድ	ለ2004 የተፈቀደ በጀት	ከሐምሌ 2003 እስከ ሰኔ 2004 ሥራ ላይ የዋለ	ስራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ
1.	ሰብዓዊ ለሆኑ አገልግሎቶች	6100	12,358,080.05	12,277,312.33	99.40
2.	ለአላቂ እቃዎችና አገልግሎቶች	6200	4,984,300.47	3,773,307.55	75.70
3.	ለቋሚ ንብረቶችና ግንባታ	6300	11,800.00	11,601.00	98.30
4.	ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች መዋጮ	6400	175,000.00	106,597.69	60.94
	ድምር		**17,529,180.52**	**16,168,818.57**	**92.23**

በሰንጠረዡ እንደተመለከተው የበጀት አፈፃፀሙ 92.23% ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ በምክር ቤቱ በተሰየሙ ከክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች በተውጣጣ የኦዲት ቡድን አባላት የመ/ቤቱ የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ቀርቧል፡፡

2.2 የመ/ቤቱ የሰው ኃይል ሁኔታ

ለመ/ቤቱ ተሻሽሎ በተፈቀደው መዋቅር የተያዘው የሰው ኃይል ለኦዲት ባለሙያ 393 እና ለድጋፍ ሰጪ 252 በድምሩ 645 ሲሆን፤ በጥር 2004 ዓ.ም የኦዲት ስራው ሲጀመር በመ/ቤቱ የነበረው የሰው ሀይል 236 ኦዲተሮችና 138 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ 374 ነበር፡፡

በኦዲት ዓመቱ 34 የኦዲት ባለሙያዎችና 19 የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በድምሩ 53 ሰራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን፣ 3 ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉና አንድ በሞት የተለየ፣ 29 ኦዲተሮችና 9 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በራሣቸው ፈቃድ የለቀቁ፣ በድምሩ 42 ሠራተኞች መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡

በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ የነበሩ የኦዲት ባለሙያዎች 161 ወንዶችና 81 ሴቶች በድምሩ 243፤ የድጋፍ ሰጪ 75 ወንዶችና 67 ሴቶች በድምሩ 142 ሠራተኞች ሲሆኑ፤ በአጠቃላይ 385 ሠራተኞችና

ኃላፊዎች በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን፤ 260 የሥራ መደቦች በክፍትነት ተመዝግበው ይገኛሉ፡፡

2.3 የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ዕቅድና ክንውን

መ/ቤቱ በአዲሱ አደረጃጀት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርጉ በአራት ዳይሬክቶሬቶች እና የክልሎች ድጋፍና ድጎማ ሂሳብ ኦዲት በየሚያደርግ አንድ ዳይሬክቶሬት የተዋቀረ ሲሆን፤ ከጥር 1/2004 እስከ ታህሣስ 30/2005፤ የ117 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የመደበኛ ኦዲት ለማድረግ በእቅድ በተያዘው መሠረት የ116 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት ቀርቧል፡፡ አንድ መ/ቤት ሂሳቡን ዘግቶ ባለማቅረቡ ምክንያት የመጨረሻው የሂሳብ መግለጫዎች ማረጋገጥ ስራ ሳይከናወን ከቀረው በስተቀር በዕቅዱ መሠረት የተከናወነው ሥራ 99.14% ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በዕቅድ ያልተያዙ በፍ/ቤቶች ትህዛዝና በተለያዩ አካላት ጥያቄ መሰረት 7 ልዩ ኦዲቶች ተከናውኖ ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው አካለት ቀርቧል፡፡

የመሠታዊ የአገልግሎቶች ማስከበር ኘሮጀክት ተከታተይ ኦዲትን በተመለከተም ለወረዳዎች ከተሰጠው የድጋፍ ሂሣብ ውስጥ የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ በ270 መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች (በወረዳና በክልል ደረጃ)፣ ሂሣቡን ለማስተዳደር የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ብቃት ያለውና አጥጋቢ መሆን ወይም አለመሆኑን ኦዲት ለማድረግ የታቀደ ሲሆን፤ በ2004/5 የኦዲት ዓመት የ283 ወረዳዎች ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርታቸው ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ተልኳል፡፡ ይህም ክንውን ከበጀት ዓመቱ እቅድ ጋር ሲነጻፀር 105% ነው፡፡

በዚሁ መሠረት የ2004 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ መ/ቤታችን 117 በሚሆኑ የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች እና በ283 የወረዳና ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች ላይ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለየመ/ቤቶቹ የላከ ሲሆን፣ በሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባሕርይ አንፃር የተሰጡት የኦዲት አስተያየት ከ2003/2004 ኦዲት ዓመት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ ቁ.	መግለጫ	በፌዴራል መንግሥት ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት		የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ተከታታይ ኦዲት		አጠቃላይ	
		2003	2004	2003	2004	2003	2004
1	አጥጋቢ ሆነው በመኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Clean opinion)	57	49	4	13	63	62
2	ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Except for Opinion)	52	48	266	270	307	318
3	አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለጽ አስተያየትየተሰጠባቸው (Disclaimer of Opinion)	7	6	3	-	8	6
4	የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው (Adverse Opinion)	13	13	3	-	13	13
5	ሂሳባቸውን በወቅቱ ባለመዝጋታቸው አስተያየት ያልተሰጠባቸው	2	1	-	-	2	1
	ድምር	131	117	276	283	393	400

2.4 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች፣ ፕሮጀክቶችና የእርዳታ ሂሣቦች ላይ የተከናወነው የፋይናንስ ኦዲት

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንና በውጭ እርዳታ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን ሂሣብ በሙሉ ኦዲት ለማድረግ የመ/ቤቱ አቅም ውሱን በመሆኑ ላለፉት ጊዜያት የነዚህ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ሂሣብ የኦዲት ሙያ ፈቃድ ከመ/ቤቱ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶችና በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት እየተደረገ በተገኙት የኦዲት ግኝቶች ላይ ኦዲት ተደራጊው ድርጅት

የሥራ አመራር ቦርድ፣ የኘራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ በማሳወቅ መ/ቤቱ ክትትል ከማድረጉም በላይ የግል ኦዲት ድርጅቶችም ሆኑ የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ተፈላጊውን የሙያ ሥነ ምግባር ሳያጓድሉ ሥራውን እንዲያከናውኑ አቅም በፈቀደው መጠን ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት በ2004 በጀት በዓመት በመንግሥት ይዞታ ሥር የሚገኙ የልማት ድርጅቶች 82፣ ፕሮጀክቶች እና የዕርዳታ ሂሳቦች በግል ኦዲት ድርጅቶች 150 ኦዲቶች በድምሩ 232 (ይህ ቁጥር በአንድ በጀት ዓመት የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረገው መ/ቤት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርብ ዓመቱን ብቻ እንደ አንድ በመቁጠር የተወሰደ ነው) የተለያዩ በጀት ዓመት ሂሣቦች የተከናወኑ ሲሆን፣ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑትን ኦዲቶች በተመለከተ በተለይም አቋም መውሰድ ያልተቻለበትና የጎላ ችግር ያለባቸው በመሆኑ ተቀባይነት የሚይሳጣ የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው የልማት ድርጅቶችን ዋና ዋና ግኝቶች በዚሁ ጥራዝ በክፍል 3 ከገጽ 175 ጀምሮ ቀርቧል፡፡

2.5 <u>የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተ</u>

በመንግሥት የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጄክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መወጣታቸውን ለማረጋገጥ መ/ቤቱ የክዋኔ ኦዲት ያከናውናል፡፡ በዚህም መሠረት በ2004-2005 የኦዲት ሥራ ዘመን (Audit Calendar) በሁለቱ ዳይሬክቶሬቶች ከጥር 2004 በፊት ተጀምረው የዝርዝር ኦዲት ስራቸው ወደዚህኛው የኦዲት አመት የዞሩ 5 ኦዲቶች እና ከጥር 2004 በኋላ ተጀምረው እስከ ታህሣስ 30/2005 የሚጠናቀቁ 14፤ እንዲሁም ከሰኔ 2004 በኋላ ተጀምረው የዳሰሣ እና ቅኝት ሥራቸውን በማጠናቀቅ ወደ ሚቀጥለው የኦዲት ዓመት የሚዛሩ 8 ኦዲቶች በድምሩ 27 የክዋኔ ኦዲቶችን ለማከናወን በእቅድ ተይዞ ነበር፡፡

በዚሁ መሠረት የእቅድ ዘመኑ የክዋኔ ኦዲት ኘሮጀክቶች አፈጻፀም ሲታይ ካለፈው ዓመት የዞሩትን 5 ኦዲቶች ጨምሮ በዚህ የእቅድ ዘመን ወጪ መደረግ ከሚገባቸው 19 ኦዲቶች ውስጥ የ17ቱ ሥራ ተጠናቅቆ ሪፖርታቸው

የተላከ ሲሆን የ10 ኦዲቶች ሥራቸው ተጀምሮ በተለያየ የኦዲት ደረጃ ላይ ወደ ቀጣዩ ዓመት ተላልፏል፡፡ ይህም ከእቅድ አንጻር ሲታይ የተጠናቀቀው 89.47% ሲሆን ተጀምረው የዞሩት 10 መ/ቤቶች /በመቶኛ 125%/ በመሆኑ ከአጠቃላይ ዕቅዱ በስኬት መጠናቀቁን ያሣያል፡፡

የኦዲት ስራቸው የተጠናቀቁት 17 የክዋኔና አካባቢ ኦዲቶች ሪፖርቶቹ በም/ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡ /የተጠናቀቁት የክዋኔ ኦዲቶች ዋና ዋና ግኝትና የማሻሻያ ሃሳቦች በዚሁ ጥራዝ ተራ ቁጥር 6 ላይ በዝርዝር ቀርቧል/

<u>ወደ 2005/2006 የኦዲት ዓመት የዞሩ</u>

የኦዲት ስራቸው በየለያዩ ደረጃ ማለትም የደሰሳና የቅኝት ሥራው ተጠናቆ የዝርዝር ኦዲቱ ሥራ ወደ 2005/2006 የኦዲት ዓመት የዞሩ፣

1. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም፣
2. የግል ህክምና መስጫ ተቋማት የሜዲካል ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ፣
3. በማረሚያ ቤቶች የውስጥ ገቢ አስተዳደር
4. የታክስ ኦዲት
5. የታክስ መረጃ አስተዳደር
6. ወይራ ትራንስፖርት
7. የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት
8. ዩኒቨርስቲዎች የቆሻሻ አወጋገድ
9. የበጎ አድራጎት ድርጅትና ማህበራት ኤጀንሲ
10. የከተሞች አረንጓዴ አካባቢ አያያዝና አጠቃቀም

ናቸው፡፡

2.6 <u>አጠቃላይ የመንግሥት ገቢና ወጪ ሂሣብ ኦዲት</u>

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በቀን 21/5/2005 በተላከው የ2004 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዓለም

አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

በዚሁ መሠረት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጀው የ2004 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

2.6.1. <u>የገቢ ሂሣብ</u>

<u>ከመልሶ ማበደር ብር 1,701,470.02 ያልተሰበሰበ ሂሳብ መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

በ2004 በጀት ዓመት ከመልሶ ማበደር ይሰበሰባል ተብሎ በነጋሪት ጋዜጣ በታወጀው በጀት መሰረት መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ የወለድ ክፍያ ብር 24,979,058.00 በጀት ተይዞ የተሰበሰበው ግን ብር 23,277,587.98 ሲሆን በገቡት ውል መሰረት በበጀት አመቱ ብር 1,701,470.02 ያልተሰበሰበ ሂሳብ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

በመልሶ ማበደር ስምምነት የተሰጠ ገንዘብ በስምምነቱ መሰረት በወቅቱ ካልተሰበሰበ መንግስት ያወጣውን እቅድ በወቅቱ እንዳያሳካ እንቅፋት ሊሆንበት ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ምንም እንኳን ከላይ የተመለከተው ሂሳብ በ2005 በጀት አመት ላይ የተሰበሰበ ቢሆንም በመልሶ ማበደር ስምምነት የሚሰጡ ብድሮች በገቡት ውል መሰረት በወቅቱ መከፈል ባለበት በጀት አመት ላይ እንዲከፍሉ ተገቢው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ አስተያየት</u>

የተጠቀሰው የወለድ ገንዘብ በበጀት አመቱ ውስጥ ባይከፈልም በ2005 በጀት አመት የተከፈለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የቀረጥ ተመላሽ ሂሳብን በተመለከተ

ግኝት

በገቢ.ዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል በተለያየ ምክንያት(በዋጋ ወይም በታሪፍ አመዳደብ ወዘተ) በስህተት የተሰበሰበ ቀረጥ ግብር ከፋዩ በስህተት የከፈለ ለመሆኑ ሲታወቅና በኮሚቴ ሲረጋገጥ በስህተት የተከፈለው ቀረጥ ለግብር ከፋዩ ተመላሽ የሚደረግለት ሲሆን ተመላሽ የተደረገው የቀረጥ መጠን ግን በገቢ ተመላሽ መያዝ ሲኖርበት በወጪ ሪፖርት ተመዝግቦ ለሚኒስቴሩ እየቀረበ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ይህንኑ ሂሳብ በወጪ እያጠቃለለ ይገኛል፡፡

ለናሙና ያህል:-

- በአዳማ ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በ2004 በጀት አመት በተለያየ ምክንያት በስህተት ተሰብስቦ የነበረ የቀረጥ መጠን ብር 2,954,828.92 በ2004 በጀት ለባለመብቱ ተመላሽ ቢደረግም ከገቢ ሂሳቡ ላይ ተቀናሽ ሳይደረግ በወጪ ተመዝግቦ በገቢ.ዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሂሳብ ውስጥ ተጠቃሎ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ተደርጓል፡፡

በመሆኑም ባለፈው አመት አሰራሩ አግባብ አለመሆኑን በመጥቀስ እንዲስተካከል ለሪፖርት አቅራቢ.ውም ሆነ ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም አሰራሩ አሁንም አለመስተካከሉ ታውቋል፡፡ይህም በመሆኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያጠቃልለው ሂሳብ ላይ የገቢና ወጪ ሂሳብ ትክክለኛውን ባላንስ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡

ስጋት

ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚያቀርበው የገቢ ሪፖርት ከፍ ያለ (overstated) በመሆኑ ምክንያት የተጠቃለለው የገቢ ሂሳብም በበጀት አመቱ የተሰበሰበውን ትክክለኛውን ገቢ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከገቢ.ዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በጋራ በመሆን በገቢ.ዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል በበጀት አመቱ ውስጥ

በስህተት ተሰብስቦ ነገር ግን በዚያው በጀት አመት ለግብር ከፋዩ ተመላሽ የሚደረግ ሂሳብ በበጀት አመቱ የገቢ ሪፖርት ውስጥ እንዳያካትቱ አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

<u>የስራ አመራሩ አስተያየት</u>

ከላይ በተጠቀሰው መሰረት ማስተካከያ የሚወሰድ መሆኑንና በቀጣይ የሚስተካከል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

2.6.2. ሪፖርት አቅራቢ መስሪያ ቤቶች በዋናው ኦዲተር መ/ቤት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የተስተካከለ ሒሳብ መግለጫ የማያቀርቡ መኖራቸው

<u>ግኝት</u>

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀፅ 59 መሰረት ሚኒስቴሩ ከመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚደርሰውን የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርትና የማእከላዊ ግምጃ ቤትን ሂሳብ በማጠቃለል የፌደራል መንግስትን አመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማዘጋጀት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ሪፖርት አቅራቢ መስሪያ ቤቶች በፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የተስተካከለ ሂሳብ መግለጫ አቅርበው የተስተካከለው ሂሳብ መግለጫም የሚጠቃለል መሆኑንና አመታዊው የገቢና ወጪ ሂሳብ ትክክለኛውን ሁኔታ የሚያሳይ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ለናሙና ያህል ከዚህ በታች በቀረበው ዝርዝር መሰረት ሪፖርት አቅራቢ መስሪያ ቤቶች በተሠጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ሂሳብ መግለጫው ሳይስተካከል ሪፖርት ያቀረቡና ያልተስተካከለውም ሂሳብ መግለጫ በተጠቃለለው የፌዴራል መንግስት አመታዊ ሂሳብ ውስጥ የተካተተ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ በ2004 በጀት ዓመት ወቅት ከውስጥ ገቢ ብር 21,819,664.39 የሰበሰበ ሲሆን ይኸንንም ሂሳብ የገ/ኢ/ል/ሚ ነሃሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርአት መሰረት በገቢ ሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲኖርበት በአደራ የሂሳብ መደብ (5054) የሚመዘገብ በመሆኑ እንዲስተካከል አስተያየት

የተሠጠ ቢሆንም ያልተስተካከለ በመሆኑ የሪፖርት አቅራቢው መ/ቤት እና በገ/ኢ/ል/ሚ የተጠቃለለው ሒሳብ ሪፖርት ላይ የአደራ ሂሳብ (5054) በተሰበሰበው የገቢ መጠን ከፍ ብሎ ከመገኘቱም በላይ በዚሁ የገንዘብ መጠን የገቢ ሂሳቡ ያለአግባብ ዝቅ እንዲል ሁኗል፡፡

- ሁሉም የበጀት አመቱ ሂሳብ እንቅስቃሴ ባለመመዝገቡ ሰኔ 30/2004 በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ የሞጆ ቅ/ጽ/ቤት በባንክ ሂሳብ ቁጥር 551 ላይ የባንክ ሂሳብ (ሂሳብ መደብ 4103-2) በብር 38,768,393.79 ክሬዲት ሚዛን የሚያሳይ ሲሆን ይኸው ሂሳብ እንዲተካከል አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ሂሳቡ ሳይስተካከል በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መስሪያ ቤት በመጠቃለሉ የሪፖርት አቅራቢው መ/ቤት እና በገ/ኢ/ል/ሚ የተጠቃለለው ሒሳብ ሪፖርት ላይ የባንክ ሂሳብና የገቢ መጠን ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡
- አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለዋስትና ሂሳብ (Deposit Account) ሪፖርት የማያዘጋጁና ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንም ሪፖርት የማያቀርብ በመሆኑ እንዲስተካከል አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም አሰራሩ ባለመስተካከሉ የሪፖርት አቅራቢው መ/ቤት እና በገ/ኢ/ል/ሚ የተጠቃለለው ሒሳብ ሪፖርት ላይ የባንክ ሂሳብና የመያዣ ሂሳብ (Deposit account=5051) ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡
- በ2004 በጀት ዓመት በግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ በስሩ ያሉት ኮሌጆችን ማለትም በአላጌ፣አጋርፋ እና አርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሞያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች በተለያዩ አርእስቶች የተሰበሰበው የውስጥ ገቢ እንዲሁም ከገቢ ሂሳብ ላይ በተለያዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች ወጪ የተደረገው በጠቅላላ ሒሳብ ብር 45,685,008.00 የፕሮጀክት ማስተባበሪያው ለየሂሳብ መደቡ አጠቃሎ ለግብርና ሚኒስቴር ሪፖርት ያላደረገ በመሆኑ እንዲስተካከል አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም አሰራሩ ባለመስተካከሉ ግብርና ሚኒስቴር በበጀት አመቱ

መጨረሻ የተጠሪ መ/ቤቶችን ሒሳብ አጠቃሎ ለገ/ኢ/ል/ሚ ሪፖርት ያደረገው የሂሳብ ሪፖርት ላይ ከላይ የተመለከተው ገንዘብ በየአርእስቱ አልተካተተም፡፡ በዚህም ምክንያት በሪፖርት አቅራቢውና በገ/ኢ/ል/ሚ የተዘጋጀው የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ በብር 45,685,008. በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ዝቅ እንዲል አድርጎታል፡፡

<u>ስጋት</u>

ሪፖርት አቅራቢ መስሪያ ቤቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት በተለይ በጣም ጉልህ (material) የሆኑ የኦዲት ግኝቶችን ሳያስተካክሉ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚያቀርቡ ከሆነና ይኸው ጉልህ የሆነ ስህተት ያለው ሪፖርት በአገሪቷ ማጠቃለያ ሂሳቡ ውስጥ የሚካተት ከሆነ የተጠቃለለው ሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ከላይ ለናሙና ያህል በቀረበው መሰረት በየመስሪያ ቤቱ ኦዲት ሲደረግ ለተገኙ ግኝቶች አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የእርምት እርምጃ ሳይወሰድ (ሂሳብ መግለጫው ሳይስተካከል) ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ሪፖርት የሚደረግ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ይህም የሚጠቃለለው የፌደራል መንግስት አመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም በአዋጁ መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እያንዳንዱ ሪፖርት አቅራቢ መስሪያ ቤት በተሠጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ሂሳብ መግለጫውን አስተካክሎ ሪፖርት እያቀረበ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ስርአት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

<u>የስራ አመራሩ አስተያየት</u>

ሪፖርት አቅራቢ መስሪያ ቤቶች የተዘጋ ሪፖርት ሲያቀርቡ የተሰጡ የኦዲት አስተያየት እንዲያቀርቡ በማድረግ በኦዲት አስተያየቱ መሰረት ሂሳብ መግለጫው የተስተካከለ ለመሆኑ የሚረጋገጥ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

2.6.3. የሌተር ኦፍ ክሬዲት ሂሳብን በተመለከተ

ግኝት

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት በስሙ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተለት የመንግስት መስሪያ ቤት የሌተር ኦፍ ክሬዲት እንቅስቃሴውን በየሩብ አመቱ ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጀው ፎርም መሰረት ለሚኒስቴሩ ሪፖርት መቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ከዚህ አንጻር በስሙ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተለት የመንግስት መስሪያ ቤት የሌተር ኦፍ ክሬዲት እንቅስቃሴውን በየሩብ አመቱ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት የሚያቀርቡ መሆኑንና በሚቀርበው ሪፖርት መሰረትም የተዘጉ ወይም ውላቸው የተሰረዘ የሌተር ኦፍ ክሬዲት ዋጋ በወቅቱ ወደ ማእከላዊ ግምጃ ቤት ተመላሽ የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተላቸው መስሪያ ቤቶች እንቅስቃሴውን በተመለከተ ለሚኒስቴሩ የሚያቀርቡት ሪፖርት የሌለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

የተዘጉ ወይም ውላቸው የተሰረዘ የሌተር ኦፍ ክሬዲት ዋጋ በወቅቱ ወደ ማእከላዊ ግምጃ ቤት ተመላሽ ላይደረግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በመመሪያው መሰረት በስሙ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተለት የመንግስት መስሪያ ቤት የሌተር ኦፍ ክሬዲት እንቅስቃሴውን በየሩብ አመቱ እንዲያቀርቡ በማድረግ የተዘጉ ወይም ውላቸው የተሰረዘ የሌተር ኦፍ ክሬዲት ዋጋ በወቅቱ ወደ ማእከላዊ ግምጃ ቤት ተመላሽ እየተደረገ ለመሆኑ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

ከላይ በኦዲት ግኝቱ እንደተጠቀሰው የትኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ከሌተር ኦፍ ክሬዲት እንቅስቃሴው ጋር ያለውን ሪፖርት የሚያቀርቡበት ስርአት ተዘርግቶ እየተተገበረ አይደለም፡፡በመሆኑም ከግኝቱ በኋላ በተሰጠው ምክር መሰረት መወሰድ የሚገባቸውን

የማሻሻያ እርምጃዎች በመውሰድ በመመሪያው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የሌተር ኦፍ ክሬዲት ተጠቃሚ የሆኑ መስሪያ ቤቶችን ሁኔታ የሚያስረዳ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግ ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

2.6.4. <u>የብድር ሂሳብን በተመለከተ</u>

<u>የፀደቀ የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ሰነድ የሌለ መሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 42(1) መሰረት ሚኒስትሩ ተፈላጊውን የገንዘብ መጠን በተገቢው ጊዜ የመበደርን አጠቃላይ አላማ መሰረት ያደረገ እና ወጪ መቀነስን ከተረጋጋ ወጪ ጋር ባመዛዘነ አፈፃፀም ለመምራት እንዲሁም ብድር የእዳ ጫና ሁኔታን እና የመክፈል አቅምን መሰረት ባደረገ አኳኋን መውሰድ የሚያስችል የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ መዘጋጀት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የወቅቱን ሁኔታ ያገናዘበ ወቅታዊ የሆነ የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ሰነድ የተዘጋጀ ለመሆኑና የሚወሰዱ ብድሮችም ከወቅታዊው የብድር ስትራቴጂ ሰነዱ ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸው እየታየ ብድር የሚወሰድ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ምንም እንኳን ወቅታዊ የሆነ ረቂቅ የብድር አስተዳደር እስትራቴጂ ሰነድ የተዘጋጀ ቢሆንም ሰነዱ ገና ያልጸደቀ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

በአዋጁ መሰረት ወቅታዊ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ የተዘጋጀው ረቂቅ የብድር ስትራቴጂ ሰነድ ካልጸደቀ የሚወሰዱ ብድሮች ከወቅታዊው የብድር ስትራቴጂ ሰነድ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማረጋገጥ ያስቸግራል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በአዋጁ መሰረት ወቅታዊ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ የተዘጋጀው ረቂቅ የእዳ አስተዳደር ስትራቴጂ ዶክመንት በሚመለከተው አካል የሚጸድቅበት ሁኔታ ሊፋጠን ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ አስተያየት</u>

የብድር እስትራቴጂውን በተመለከተ ሰነዱ በቅርቡ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የበላይ አመራር የሚቀርብ ሲሆን እንደሚጸድቅም ይጠበቃል፡፡ረቂቅ ሰነዱን በተመለከተ ከዚህ በፊትም እየተወሰዱ የነበሩት ብድሮች በተለያዩ ጊዜያት በተቀረጹ እና በመስሪያ ቤታችን የበላይ አመራር ይሁንታን ያገኙ የብድር እስትራቴጂው ላይ በመመርኮዝ እና የሀገሪቱን የብድር ጫና ትንታኔ Debt sustainability Analysis (DSA) ውጤቱን ከግንዛቤ ባስገባ መልኩ ብድሮች እየተወሰዱ እንደሆነና የቅርብ ክትትልም የሚደረግባቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

<u>በበጀት ታውጆ ያልተሰበሰበ የውጪ ሀገር ብድር መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

በአለም አቀፍ ፋይናንስና ልማት ተቋማት ትብብር ቡድን የስራ አሰራር ስርአት መመሪያ(ነሀሴ 1998 ዓ.ም) መሰረት በፕሮጀክት ሂደት ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን ከለጋሽ ተቋማትና ከአስፈጻሚ አካላት ጋር በመሆን እንዲፈቱ እንደሚደረግ ይገልጻል፡፡ ከዚህ አንጻር ስራዎች የሚሰሩ መሆኑንና ብድሮችም በወቅቱ የሚፈሱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች በቀረበው ዝርዝር መሰረት በናሙና ከታዩት ውስጥ በ2004 በጀት አመት ለተለያዩ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከውጪ ሀገር ብድር ይሰበሰባል ተብሎ በነጋሪት ጋዜጣ ብር 1,288,620,310 የታወጀ ቢሆንም ለፕሮጀክቶቹ የፈሰሰው ግን ብር 692,960,949.01 መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በበጀት ተካትቶ ያልተሰበሰበ ብር 595,659,360.99 መሆኑን ያመለክታል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ነው፡፡

አበዳሪ	የፕሮጀክት ስም (ፕሮግራም)	በ2004 በጀት ዓመት በበጀት የተያዘ	በብድር አስተዳደር መዝገብ መሠረት በ2004 በጀት ዓመት ገቢ የሆነ	በበጀት ተይዞ ገቢ ያልሆነ
IDA	MOWR(Tana-Beles)	258,425,640.00	120,650,914.71	137,774,725.29
IDA	East Africa Agricultural productive programme	130,673,120.00	31,433,701.19	99,239,418.81
ADF	ERA (Wacha-Maji)	100,700,000.00	37,800,103.26	62,899,896.74
ADF	ERA (Jima-Mizan)	242,922,000.00	236,747,526.00	6,174,474
IDA	MoA (AGRICULTURAL GROWTH)	372,059,900.00	181,374,187.97	190,685,712.03
ADF	MoA (Agricultral sector Support Project)	87,026,650	44,830,244.34	42,196,405.66
IFAD	MoA (Small Scale Irrigation Development programme)	58,675,000	22,703,802.82	35,971,197.18
BADEA	ERA (Dembi-Bedele)	7,438 000	1,081,331.67	6,356 668.33
BADEA OFID	ERA(Gore-Gambella)	30,700,000	16,339,137.05	14,360,862.95
ጠቅላላ ድምር		1,288,620,310	692,960,949.01	595,659,360.99

<u>ስጋት</u>

የፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም በተገባው ውል መሰረት ሳይሆን ቀርቶ ወደ አገር መፍሰስ ያለበት ገንዘብ ላይፈስ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በስራ ሂደት ማኑዋሉ መሰረት የውጪ ሀገር ብድሮች በተገባው ውል መሰረት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲፈሱ የፕሮጀክቶችን እንቅስቃሴ በመከታተል እና ከፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም ጋር ለሚያጋጥሙ ችግሮችም በወቅቱ እንዲፈቱ በማድረግ ብድሮች በታሰበላቸው ግዜ እንዲፈሱ

በማድረግ አገሪቷ ለአላስፈላጊ ወጪ /commitment fee/ እንዳትዳረግ ጥንቃቄ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

የችግሩ መንስኤ የተለያየ ሊሆን እንደሚችልና የችግሩን መንስኤ በመለየት በየደረጃው (ማለትም በገንዘብ ሚኒስቴር ደረጃ፣ በአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ደረጃ እንዲሁም በአበዳሪ ድርጅቶች ደረጃ) የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ጥረት የሚደረግ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

2.6.5. በበጀት አመቱ ውስጥ የተሰበሰበ የመንግስት ገቢ በአመታዊ በጀት አዘገጃጀት ላይ ያልተካተተ እና ያልታቀደ መሆኑ፤

ግኝት

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 20(2ሀ) መሰረት አመታዊ በጀት ሲዘጋጅ በበጀት አመቱ ዉስጥ ሊሰበሰብ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ሊይዝ እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንጻር በ2004 በጀት አመት ውስጥ ከአገር ውስጥ ሊሰበሰብ የሚችለው ገቢ ሙሉ በሙሉ በበጀት የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች በቀረበው ዝርዝር መሰረት በበጀት ሳይካተት ብር 81,314,742.57 የተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የገንዘብ ምንጭ	የሂሳብ መደብ	በ2004 በጀት ዓመት በበጀት የተያዘ	በ2004 በጀት ዓመት ገቢ የሆነ
በአገር ውስጥ ከሚመረቱ እቃዎች የሽያጭ ተርን ኦቨር ቀረጥ	1220-1239	-	37,408,185.17
የአገልግሎት የሽያጭ ቀረጥ	1240-1279	-	43,906,557.4
ጠቅላላ ድምር			81,314,742.57

ስጋት

ከተለያዩ የአገር ውስጥ የገቢ ምንጮች ሊሰበሰብ የሚችለውን በአግባቡ ተለይቶ በበጀት ዝግጅት ላይ ካልተካተተና አስቀድሞ ካልታወቀ መንግስት ሌሎች ምንጮችን ተጠቅሞ ለመሰብሰብ በሚያሳልፈው ውሳኔ ላይ የራሱ የሆነ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ለወደፊቱ ባለፉት በጀት አመታት ላይ ከአገር ውስጥ ምንጭ ገቢ የተሰበሰበባቸው የሂሳብ አርእስቶች ሙሉ በሙሉ በበጅት የተካተቱ ለመሆኑ በአግባቡ እየተረጋገጠ የበጀት ዝግጅቱ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

የገቢ ዝርዝር እቅድ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚያዘጋጅ ሲሆን በእቅድ ዝግጅት ወቅት ባለመካተቱ መሆኑን በመግለጽ በቀጣይ ዝርዝር እቅድ ሲያዘጋጁ እንዲያካትቱ ግብረ መልስ የሚሰጣቸውን መሆኑን ገልጸዋል፡፡

2.7 የሌሎች ስራ ክፍሎች አፈፃፀም

2.7.1 የኦዲት ምርመርና ስርፀት ዳይሬክቶሬት

ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ውስጥ በ8 መ/ቤቶች የኦዲት ጥራት ማረጋገጫ ፍተሻ ማካሄድ፣ በየደረጃው ላሉ ኦዲተሮች እና አዲስ ለተቀጠሩ ኦዲተሮች የስልጠና እና የምክር አገልግሎት መስጠት፣ ለኦዲት የሚያስፈልጉ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችን መረጃዎችን አጠናቅሮ በመረጃ ሥርዓት ውስጥ ተመዝግቦ እንዲያዝ ማድረግ፣ ለኦዲት ግኝቶችና ነቀፌታ ያለበት የኦዲት አስተያየት ከተሰጠባቸው ሪፖርቶች መነሻ የሆኑትን ችግሮች በማጥናት መደምደሚያ ላይ መድረስ፣ በስታቲስትክስ አጠቃቀምና በናሙና አወጣጥ በመረጃ ስብሰባና ትንተና፣ በኦዲት ስልት ቀረጻና በክዋኔ ኦዲት ትንተና ስልጠናና የቴክኒክ እገዛ ለማድረግ አቅዶ ለኦዲት ሥራ አጋዥ የሆኑ መመሪያዎች ማሠራጨቱ፣ የማጠናከሪያ ስልጠና መስጠቱ፣

ለ2004/2005 ዓመታዊ እቅድ ዝግጅት የሚረዱ መረጃዎችን ማሰባሰቡን፣ ሁለት ልዩ ኦዲቶች ማከናወኑን፣ የክዋኔ ኦዲት ስልጠና መሰጠቱና፣ በመ/ቤቱ ላይ የኦዲት ጥራት ማረጋገጫ ሪቪው (QAR) ማከናወንና በAFROSAI-E ጥራት ክለሣ ዝግጅት የማስተባበር ሥራ ተሠርቷል፡፡

2.7.2 የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠትን በተመለከተ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ለግል ኦዲተሮች እና ለሂሣብ አዋቂዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፣ የማደስና የመሠረዝ ሥልጣን፤ እንዲሁም በማናቸውም የፌዴራል መ/ቤትና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊ የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5/16 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከጥር 2004 እስከ ታህሣሥ 2005 ባለው ጊዜ ለ8 የግል ኦዲተሮችና 107 የሂሳብ አዋቂዎች አዲስ የሙያ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሰጥቷል። በተጨማሪም የፌዴራል የመንግሥት ልማት ድርጅቶች በጠየቁት መሠረት በየደረጃው ለሚገኙ 25 የውስጥ ኦዲተሮች የሙያ ደረጃ ማረጋገጫ ሰጥቷል፡፡

ቀደም ሲል የሙያ ፈቃድ ለተሰጣቸውም የሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ላይ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የ494 የሂሳብ አዋቂዎችና የ64 ኦዲተሮች ዓመታዊ የሙያ የሰርትፍኬት ዕድሳት ተደርጓል፡፡

እንዲሁም አንዳንድ ግለሰቦች ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸው ወይም ከተፈቀደላቸው የኦዲት ወይም የሂሣብ አገልግሎት ፈቃድ ውጭ አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ የሚል ግምት በመኖሩ የአገልግሎት ተጠቃሚውን ህብረተሰብ ከህገ ወጦች ለመከላከል ሲባል 64 የተፈቀደላቸው ኦዲተሮችና 470 የሂሣብ አዋቂዎች የስም ዝርዝራቸውን በመ/ቤቱ ዌብ ሣይትና፣ በጋዜጣ እንዲወጣ እንደዚሁም አዳዲስ ፈቃድ የወሰዱትን በደብዳቤ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች በመግለጽ ሲሆን ከዚህ ውጪ የሚንቀሳቀሱ ሲያጋጥሙ ለእርምጃ አወሳሰድ እንዲያመች ለመ/ቤታችን ጥቆማ የሚቀርብበትን ሥርዓት ኅብረተሰቡ እንዲያውቀው ተደርጓል፡፡

2.7.3 የመ/ቤቱ የግንዛቤ ማዳበሪያና የኮሙኒኬሽን ሥራዎች

የኦዲት አሠራርና ጠቀሜታ እንደዚሁም፣ ተጠያቂነትን ከማስፈን አንፃር የሚኖረውን ፋይዳ በተመለከተ የተለያዩ የግንዛቤ ማዳበሪያ መድረኮች ቀደም ባሉት ጊዜያት እንደነበረ ሁሉ የተከናወነ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ፤

- በሕዝብ ተወካዮች መ/ቤት የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት በሙሉና ከሌሎች ቋሚ ኮሚቴ ለተወከሉ አባላት ስለኦዲት ሙያ ነፃነት በሚደነግገው የሊማና ሜክስኮ ዲክላሬሽን ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፣

- ሰኔ 1 ቀን 2004 250 ለሚሆኑ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት ስለኦዲት አሠራር፣ በመንግሥት ሂሣብ አያያዝና በበጀት አስተዳደር ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ተሰጥቷል፣

- ከተለያዩ የፍትህ አካላት ከተውጣጡ ባለሙያዎች ጋር የ1 ቀን ውይይት በማድረግ፣ ስለኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች፣ በፍ/ቤት በትህዛዝ እና በጥያቄ የሚቀርቡ ልዩ ኦዲቶች ማሟላት የሚገባቸው ጉዳዮችና ሌሎች በኦዲቱና በህግ አፈጻፀም መካከል ስላለው የሥራ ግንኙነት የምክክርና የግንዛቤ ማስጨበጫ ለ1 ቀን ተሰጥቷል፣

- በተፈቀደላቸው የውጭ ኦዲተሮችና የመንግሥት ኦዲተሮች መካከል ያለውን የሥራ ግንኙነት በተመለከተ የምክክርና የግንዛቤ ማስጨበጫ ለ1 ቀን ተሰጥቷል፣

- የፌዴራልና የክልል ዋና ኦዲተሮች የምክክር መድረክ ለ18ኛ ጊዜ የተካሄደ ሲሆን፣ በዚህ ጉባዔ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ከፌዴራልና ከክልላዊ መንግታስት እንዲሳተፉ በማድረግ በመንግስት ግዥ አፈፃፀም፣ የሂሳብ አያየዝና በኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምጃ አወሳሰድና በኦዲት ሪፖርት የሚጠቀሱ የህግ ጥሰቶችን ለህግ ለማቅረብ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች ዙሪያ በመወያየት በጋራ ሊሰሩ የሚገባቸውን ጉዳዮች፣ በኦዲት ሽፋን፣ ጥራትና ወቅታዊነትን ለማሳደግ በሂደት ላይ ያሉትን የለውጥ ሥራዎችን ለማጠናከር፣ የመንግስት ሀብት አሰባሰብ አጠቃቀምና አስተዳደር የሚያስፈጽሙ

በየደረጃው ያሉ አካላት በመልካም ስነ ምግባርና በአመለካከት በታነፁ አካላት እንዲመራና እንዲፈፀም የበኩላችንን ኃላፊነት በመወጣት መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን የበኩላችንን ጥረት ለማድረግ በሚሉት ዙሪያ በጥልቀት ተወያይቶ ባለ13 ነጥብ የአቋም መግለጫ በመውጣት ተጠናቋል፡፡

2.7.4 የትምህርትና ስልጠና ዳይሬክቶሬት

ዳይሬክቶሬቱ የተቋሙን ራዕይ እና ተልዕኮ ሊያሣካ የሚችል ብቃት ያለው የሰው ኃይል በጥራትና በብዛት እንዲኖር ለማድረግ ሠራተኞች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ስልጠና እንዲያገኙና ትምህርታቸውን እንዲያሻሽሉ አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያደርግ ሲሆን በኦዲት ዓመቱ ውስጥ የሚከተሉት ሥራዎች አከናውኗል፤

- ከሰኔ 14-15 2004 ዓ.ም 200 ለሚሆኑ የመ/ቤታችን ኦዲተሮች በመግሥት ሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ በመንግሥት ግዥ አፈጻፀም እና በኢትዮጵያ ታክስ ሥርዓት ላይ የግንዛቤ ማዳበሪያ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፣
- ከሰኔ 22-23 2004 ዓ.ም 40 ለሚሆኑ የመ/ቤቱ አመራር አካላት በEssentials of leadership ላይ ስልጠና ወስደዋል፣
- ከነሐሴ 14-18 2004 ዓ.ም 23 የመ/ቤቱ ሠራተኞች AFROSAI-E ያዘጋጀውን Performance Audit 3 Module Course ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፣
- 1 የክዋኔ ኦዲት ባለሙያ ከህንድ መንግሥት በተሰጠ ዕድል ኢ.ኤ.አ ከ10/09/2012 - 05/10/2012 በህንድ አገር Audit of public sector Enterprises ላይ ስልጠና ወስዷል፣
- 1 የክዋኔ ኦዲት ባለሙያ AFROSAI-E ያዘጋጀውን "Statistical Course for Performance Auditors" E-learning በሚል ለሁለት ቀናት ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፣
- 3 የመ/ቤቱ ሠራተኞች AFROSAI-E ያዘጋጀውን " Work Shop for IT Capacity Building Programme" በሚል በቦትስዋና ኢ.ኤ.አ ከ10-21 Sep. 2012 ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፣

- 4 የፋይናንሻል ኦዲተሮች AFROSAI-E ከIDI ጋር በመተባበር ከኖቨምበር 5 - ዲሰምበር 14, 2012 ባዘጋጀው "E-learning Course on Risk Based Approach to Financial Audit"ሥልጠና ላይ እንዲሣተፉ ተደርጓል፣
- 1 ኦዲት ዳይሬክተር እና 1 የኦዲት ሥራ አስኪያጅ ከኖቨምበር 12-16, 2012 ኬንያ ሀገር ናይሮቢ ከተማ በተደረገው "Joint World Bank /MEFMI Regional Debt Management Performance Assessment (DEMPA) Workshop" ላይ እንዲሣተፉ ሁኔታዎች ተመቻችቷል፣
- 2 የመ/ቤቱ አመራር አባላት ከኖቨምበር 19-21, 2012 ደቡብ አፍሪካ ደርባን ከተማ በተደረገው "3i Programm (ISSI, Implementation Intiative) Management Meeting Workshop" እንዲሣተፉ አስፈላጊው ሁሉ ተደርጓል፣
- የሁለተኛ ዲግሪ ለመከታተል የተመዘገቡትን ሠራተኞች መረጃዎችን በማሰባሰብና በማወዳደር በኮሚቴው የተመረጡ የ16 ሠራተኞች መረጃዎች ለአ.አ ዩኒቨርስቲ ተልኳል፣
- 1 ሠራተኛ መ/ቤቱን ወክለው AFROSAI-E ያዘጋጀውን ''HR Managers' Experts Workshop'' በሚል እኤአ ከ24-28 Sep. 2012 ሥልጠና እንዲሣተፉ ተደርጓል፣
- 1 ሠራተኛ መ/ቤቱን ወክለው AFROSAI-E ያዘጋጀውን ''Communication workshop for the SAIs" በሚል እኤአ ከ24-28 Sep. 2012 እንዲሣተፉ የተደረገ፤ ቢሆንም ሰራተኛው ስልጠናውን ከወሰዱ በኋላ ወደ ሀገር አልተመለሱም፤
- 3 የመ/ቤታችን ሠራተኞች እና 3 የክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሠራተኞች AFROSAI-E ያዘጋጀውን "7th Annual Technical update & Workshop'' በሚል እኤአ ከ14-16 November 2012 ስልጠና ወስደዋል፣
- 4 የመ/ቤቱ ሠራተኞች AFROSAI-E ከ''IDI'' ጋር በመተባበር ያዘጋጀውን ''ISSAI Certification'' በሚል ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል

- የ"ACCA" ትምህርት በመከታተል ላይ ለሚገኙ የትምህርት ክፍያና የመጽሀፍት ግዥ በማከናወን ድጋፍ የተደረገ ሲሆን፣ ለ8 ሠራተኞች "ACCA" ያዘጋጀውን የ"F-5 F-7 እና F-9 የማጠናከሪያ ትምህርት (Tutorial) እንዲወስዱ ተደርጓል፣
- የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ለሚገኙ 20 ሠራተኞች የትምህርት ክፍያ እንዲፈፀምላቸው ተደርጓል፣
- ሥራቸውን በፍቃዳቸው የለቀቁ 5 ሠራተኞች በገቡት ውል መሠረት መ/ቤቱ ለ"ACCA" ትምህርት የከፈለላቸውን ብር 35,956.00 ለመ/ቤቱ ተመላሽ እንዲያደርጉ ተደርጓል፣
- የመ/ቤቱ ቤተመጻህፍት፣ የንባብ፣ የውሰት የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲሁም ከተለያዩ ተቋማት ለመጡ መረጃ ፈላጊዎች አስፈላጊ መረጃ ሰጥቷል፡፡

2.7.5 <u>በኢንፎርሜሽን ሰርቪስ የተሠሩ ዋና ዋና ሥራዎች</u>

ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ መ/ቤቱን በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የማደራጀት፣ የኮምፒውተር ስልጠናና ድጋፍ መሰጠት፣ ኮምፒውተርና የኮምፒውተር ተዛማጅ እቃዎች ግዥ ሂደት ላይ ሙያዊ ድጋፍ መስጠት፣ የቋሚ ፋይሎች የኦዲት ሪፖርቶችና የተለያዩ ስርኩላሮች ዳታ ቤዝ ማዘጋጀት፣ በኦዲት ሶፍት ዌር ላይ ማጠናከሪያ ስልጠና መስጠት የመ/ቤቱን የኔትወርክ ኢንፈራስትራክቸር ማሻሻል፣ የመ/ቤቱን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሴኩሪቲ ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግና የኢንተርኔት አገልግሎት ለመስጠት ባቀደው መሰረት የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል፡፡

- ኮምፒዩተር ለሌላቸው የመ/ቤቱ ሠራተኞች ተጨማሪ የኮንፊግሬሽን ስራ በማከናወን የኮምፒዩተር ዕደላ ተከናውኗል፣
- የመ/ቤቱን መረጃዎች ለማጠናቀር የሚያስችል የዳታቤዝ ስርዓት ለማዘጋጀት የሚያስፈልገው መረጃ የተሰበሰበ እና ተጨማሪ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ጥረት እየተደረገ ሲሆን የዲዛይኑ ስራ ባለው መረጃ እንዲጀመር ተደርጓል፣

- በ Exchange Server ላይ እና በ Firewall ላይ የኮንፊግሬሽን ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ የ Firewall ስራ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ሲሆን በ Exchange Server ላይ የሙከራ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡
- የመ/ቤታችን የጽረ ገጽ ለማሻሻል የዲዛይን ሥራ ተሰርቶ፣ የመጨረሻ የዲዛይን ሥራው ላይ አስተያየት ተሰጥቶበት ተጠናቅቋል፣
- ከ NAO (ከእንግሊዝ) ከመጡ ባለሙያዎች ጋር በመሆን የIT Strategic ሰነድ የተከለሰ ሲሆን የ Exchange Server 2008 የኮንፊግሬሽን ሥራም እንዲከለስ ተደርጓል፣ ወደ አዲስ ሲስተም 2008 Server System የማሸጋገር ሥራ ተከውኗል፣
- ከፋይናንሻል ኦዲተሮች ጋር በመሆን የመረጃ ቴክኖሎጂ ኦዲት ፕሮግራም ተዘጋጅቷል፡
- በአገር አቀፍ ደረጃ እየተካሄደ ባለው የኔትወርክ ማስተር ፕላን ሥራ ላይ መ/ቤታችን የዚሁ አካል በመሆኑ የሚሠራው የኔትወርክ ሥራ በታቀደው መሠረት መሰራቱን የመከታተልና የማስፈፀም ሥራዎች ተከናውኗል በዚህም መሠረት፡-
  - የዳታ ማዕከሉ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን ስርቨሮችና ሌሎች የኢንፍራስትራክቸር ዕቃዎች እንዲገጠሙ ተደርጎል፣
  - በመ/ቤቱ ህንጻ ላይ የቴትወርክ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን በሶስቱም ህንጻዎች ላይ የማሰራጫ መሣሪያዎች እየተገጠሙ ይገኛሉ፣
  - የቪዲዮ ኮንፈረንስ ክፍል የተጠናቀቀ ሲሆን አንዳንድ የመሣሪያ ተከላዎች ይቀሩታል፣
- የኢንፍርሜሽን ቴክኖሎጂ ኦዲት ለማድረግ እንድንችል ከNAO አንድ ባለሙያ ተመድቦ ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል ድጋፍ የተደረገልን ሲሆን በአካል በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት በመገኘት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተሞክሯል፣

- የVPN (Vertual Private Network) ሥራ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የPublic IP ግዥ ተፈፅሞ፣ የ VPN ኮንፊግሬሽን ሥራ ተጠናቆ የሙከራ ሥራው በተለያዩ ቦታዎች እንዲፈተሽ ተደርጓል፣
- ከየዳይሬክቶሬቱ ለተውጣጡ 76 ኦዲተሮች በ ACL የኦዲት ሶፍትዌር እና 50 ኦዲተሮች የ IBEX አጠቃቀም ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፣
- በየዳይሬክቶሬቱ ውስጥ ለሚገኙ 4 ባለሙያዎች የ Window 2008 server ላይ የመጀመሪያ ዙር ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፣
- በ Teammate Pilot ሥራ ከዳይሬክቶሬቶች ለተውጣጡ ኦዲተሮች ሁለተኛ ዙር ሥልጠና ተሰጥቷል የሁለተኛ ዙር ፖይለት ሥራውም ተከናውኗል፣ የፖይለት ሥራ ላይ የሚሣተፉ የሥራ ክፍሎች ድጋፍ ተሰጥቷቸዋል፣
- በምስራቅና ደቡብ ወኪል መ/ቤቶች ላሉ ኦዲተሮች የIBEX እና የ Advanced Computer ስልጠና ተሰጥቷል፣
- በELM (Electronic library management) ሶፍት ዌር አጠቃቀም ላይ ለ2 የቤተመጽሐፍ እና ለ2 የመዝገብ ቤት ሠራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል፣
- የመ/ቤቱን መረጃዎች ለማጠናቀር የሚያስችል የዳታ ቤዝ ሥርዓት ለማዘጋጀት በተወሰኑ መረጃዎች የዲዛይን ሥራው ተጀምሯል፣
- በቤተመጽሐፍት እና በመሰብሰቢያ አዳራሽ የWireless Network ኮንፊግሬሽን የሙከራ ሥራ ተከናውኗል፣
- ከተለያዩ ክፍሎች በቀረበው ጥያቄ መሠረት የሶፍት ዌር ጥገናዎች ተሠርቷል፡፡

2.7.6 የእቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ

- የመ/ቤቱን የ2004/05 በጀት ዓመት የኦዲት ዘርፍ የሁለተኛ እና የሦስተኛ ሩብ ዓመት የድጋፍ ሰጪው የ2004 በጀት ዓመት አፈጻፀም እና የ2005 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ሪፖርት በማጠናቀር ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተልኳል፣

- የኦዲት ዳይሬክቶሬቶችና የድጋፍ ሰጪ ክፍሎች በየወሩ ያቀዱት እቅድና ያከናወኑትን ሥራዎች በማጠናቀር ያሉበት ደረጃ በመገምገም ማጠቃለያ ተዘጋጅቷል፣
- የመ/ቤቱ የድጋፍ ሰጪ ክፍሎች የ2005 በጀት ዓመት የሥራ እቅድ የማጠናቀር ሥራ ተሠርቷል፣
- የመ/ቤቱን የ2004 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተልኳል፣
- የመ/ቤቱን የ2005 በጀት ዓመት የሥራ መርሀ-ግብር ተዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተልኳል፣
- ለመ/ቤቱ ለ2005 በጀት ዓመት ፀድቆ የመጣውን እንደገና በየዳይሬክቶሬቱ የመደልደል ሥራ ተከናውኗል፣
- የመ/ቤቱ የ2005 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተልኳል፣
- በየዕለቱ በዳሬክቶሬቶች የሚቀርቡ የውሎ አበል ጥያቄዎችን ከተደለደለላቸው በጀት ጋር በማገናዘብ በጀት ስለመኖሩ ማረጋገጫ ተሰጥቶበታል፣
- ባለፉት ዓመታት(ከ1998 በጀት ዓመት ጀምሮ) በመ/ቤቱ የታቀዱ ዕቅዶችና የተከናወኑ ሥራዎችን ከሪፖርቶች በማሰባሰብ በዳታና በመረጃ የማደራጀት ሥራ ተከናውኗል፣
- በልዩ ልዩ ስልጠናዎች ተማትሮ ተደርጓል፣ የማስተባበር ሥራም ተሠርቷል፣
- በDIP እና በDFID አማካኝነት የሚሠሩ የአቅም ግንባታ ፕሮጀክቶችን የማስተባበር ሥራ ተሠርቷል፡፡

2.7.7 <u>የሰው ሀብት ሥራ አመራር</u>

ዳይሬክቶሬቱ መ/ቤቱ በልዩ ልዩ ህጎች ደንቦች እና መመሪያዎች የተሰጡትን የሥራ ኃላፊነትና ግዴታ በሚገባ ለመወጣት የሚያስችለው ብቁና በቂ የሰው ኃይል በማንኛውም ጊዜ እንዲኖረው ለማስቻል ክፍት መደቦችን በቅጥር፣ በደረጃ እደገትና በዝውውር ለመሙላት እና

የእያንዳንዱ ሠራተኛ የሥራ መዘርዝር በአግባቡ በማዘጋጀት የመ/ቤቱን ዓላማ ስኬታማ እንዲሆን እገዛ ለማድረግና ሌሎች አስተዳደራዊ ሥራዎች ለመሥራት ባቀደው መሰረት፤

- ከሐምሌ 2004 እስከ ታህሣስ 30 ቀን 2005 ባለው ጊዜ ውስጥ ለ49 ሠራተኞች /41 ኦዲተሮችና 8 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች/ የደረጃ ዕድገት ተሰጥቷል፣
- የመ/ቤቱ ሠራተኞች የሥራ አፈጻፀም ሪፖርት በወቅቱ ተሞልቶ እንዲቀርብ ክትትል ተደርጓል፣
- በጡረታና በስንብት መ/ቤቱን የሚለቁ ሠራተኞች አስፈላጊውን ፎርማሊቲ እንዲፈጽሙ ተደርጓል፣
- የመ/ቤቱ ሠራተኞች የመ/ቤቱን ሥራ በማይጎዳ መልኩ የዓመት እረፍታቸውን በፕሮግራም መሠረት እንዲወስዱ ክትትል ተደርጓል፣
- የመ/ቤቱን የሰው ኃይል መረጃ በዕድሜ፣በሥራ መደብ፣ በትምህርት ደረጃ በደመወዝ፣ በአገልግሎት ዘመንና በፆታ በማጠናቀር ወቅታዊነቱን እንዲጠብቅ ተደርጓል፣
- ሁሉም የመ/ቤቱ ሠራተኞች የሥራ ሰዓት ማክበራቸውን ቁጥጥር ተደርጎ የሥራ ሰዓት ያላከበሩትና ከሥራ የቀሩ ሠራተኞች የሥራ ክፍላቸው እንዲያውቁት ተደርጓል፣
- በመ/ቤቱ ግቢ ውስጥ ለታዩ የጤና ጠንቅ የሆኑ ጉዳዮች ማጣራት ተደርጎ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ቀርቧል፣
- በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚ/ር በቀረበ ጥያቄ መሠረት በመ/ቤታችን የደረሱ የሥራ ላይ አደጋዎችና በሽታዎች ሪፖርት እንዲሁም ለመ/ቤቱ የተፈቀዱ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሣቁሶች በዝርዝር ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሚኒስትር መ/ቤቱ ተልኳል፡፡

2.7.8 <u>የፋይናንስ ግዥና ንብረት አስተዳደር</u>

- የመ/ቤቱ አብይ ተግባር የሆነውን የኦዲቱን ሥራ በተያዘለት የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ለመፈፀም የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ገንዘብ በወቅቱ ማቅረብ፣ ግዥዎችን በወቅቱ መፈፀም፣ የደመወዝና ሥራ ማስኬጃ ክፍያዎች መፈጸም፣ የሂሣብ ሪፖርት ማዘጋጀት፣ የበጀት ፋላጎት ማዘጋጀት፣ በየሦስት ወሩ ለመ/ቤቱ የሚያስፈልገው፣
- ሥራ ማስኬጃ ማዘጋጀትና ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር በወቅቱ በማምጣት፣ ለወኪል መ/ቤቶች ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ እንዲሁም የመሠረታዊ አገልግሎት ማስከበር (PBS) በጀት ወቅቱን ጠብቆ ማስተላለፍ፣ ገቢና ወጪ የሆኑ ሂሣቦች በተገቢው መንገድ መመዝገብ፣ ግዥዎች በደንቡ መሠረት መፈፀም የመ/ቤቱን ንብረቶች በአግባቡ መመዝገብና የመቆጣጠር ተግባራትን ለመሥራት አቅዶ የተጠቀሱትን ሥራዎች በኦዲት ዓመቱ በአግባቡ አከናውኗል፡፡

2.7.9 <u>የውስጥ ኦዲት</u>

በመ/ቤቱ የተገዙ እቃዎች በደንቡ መሠረት አግባብ ባለው የግዥ ዘዴ መፈፀሙን፣ የመ/ቤቱ እና የወኪል መ/ቤቶች ንብረቶች መንግሥት ባወጣቸው ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መጠበቃቸውን፣ ተመዝግበው መያዛቸውን እንዲሁም ተገቢው አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን፣ የንብረት የጥሬ ገንዘብና የሠነዶች ከወጪ ቀሪ ሂሣብ ትክክል መሆኑን በማረጋገጥ የፈሰስ ሪፖርት ለገ/ኢ/ልማት ሚ/ር ማቅረብ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በተገቢው ሁኔታ መወገዳቸውን፣ የበጀት አዘገጃጀት፣ አጠቃቀምና ዝውውር በአግባቡ መሆኑን፣ በሰው ሀብት ሥራ አመራር የተከናወኑ ሥራዎች በደንብና መመሪያ መፈፀማቸውንና የወኪል መ/ቤቶች ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ ባቀደው መሰረት፤

- በ2004 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የጥሬ ገንዘብ፣ የሰነዶችና የአላቂ እቅዎች ቆጠራ መከናወኑን እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የፈሰስ ሪፖርት ተልኳል፣

- የመደበኛና የእርዳታ የሣጥንና የባንክ ከወጪ ቀሪ ሂሣብ ትክክለኛነት ከመዝገብ ከወጭ ቀሪ ጋር ተመሣክሯል፣
- የዋናው መ/ቤት የ2004 በጀት ዓመት የመደበኛና የእርዳታ /ብድር/ የገቢ ሂሣብ በአግባቡ መሰብሰቡንና መመዝገቡን፤ የደመወዝ የአበል እና የረጅም ጊዜ ብድር ክፍያ በደንቡ መሠረት መፈፀሙና በትክክል መመዝገቡን ተረጋግጧል፣
- በመ/ቤቱ ወጪ የሆኑ ሂሣቦችን ህጋዊነት ያላቸው መሆኑንና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት አገልግሎት መከፈሉን፣ በዋጋ ማቅረቢያና በግልጽ ጨረታ የተገዙ እቃዎችንና አገልግሎቶች በአግባቡና በሥርዓቱ መፈፀማቸውና ገቢ መሆን ያለባቸው ገቢ መሆናቸውንና መመዝገባቸውን የማጣራት ሥራ ተሠርቷል፣
- ለመ/ቤቱ የተፈቀደው የፕሮግራም በጀት የመ/ቤቱን ተልዕኮ፣ ራዕይ አላማና ግብ በአግባቡ ለመወጣት በሚያስችለው መልኩ በተግባር ላይ መዋሉን አፈጻፀሙም የበጀት አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ተከትሎ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ኦዲት ተደርጓል፣
- በመ/ቤቱ የተገዙ አላቂ እቃዎች በናሙናው መሠረት ገቢ መሆናቸውን፣ በስቶክ ካርድና በሌጀር ካርድ በትክክል መመዝገባቸውን አጠቃቀማቸው አያያዛቸውና አጠባበቃቸው በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ተጣርቷል፣
- በንብረት ክፍል ውስጥ የተገኙትን ላፕቶፕና ዴስክቶፕ ኮምፒውተሮችን በመቁጠር ከወጭ ቀሪው ተመሣክሯል፣
- በህግ አገልግሎት ክፍል ተጣርተው እንዲቀርቡ የተጠየቁ ጉዳዮች በተጠየቀው መሠረት በማጣራት ሥራ ተከናውኖ ሪፖርት ቀርቧል፣
- የሰሜን ወኪል መ/ቤትን የ2004 በጀት ዓመት የመደበኛና የPBS የበጀት አጠቃቀም፣ አያያዝና ቁጥጥርን የወጪ ሂሣብና የግዥ ሂሣብ አፈጻፀም እንዲሁም የቋሚ ንብረትና የአላቂ የቢሮ እቃዎች አያያዝና አጠቃቀሙን ኦዲት በማድረግ ሪፖርቱ ለበላይ ኃላፊ ቀርቧል፡፡

2.7.10 የጋራ አገልግሎቶች

የኦዲቱን ሥራ በሚገባ ለማከናወን የሚያስፈልጉ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን የግቢና የንብረት ጥበቃ፣ የውሀ፣ የመብራት፣ የስልክ፣ የመልዕክት፣ የግቢ ውበትና ጽዳት አገልግሎቶችን በመስጠት በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ በሌላም በኩል የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች አስፈላጊውን የሰርቪስ እና ጥገና አገልግሎት በወቅቱ እንዲያገኙ፣ ጥገናቸው በኢንሹራንስ መሸፈን ያለበት አግባብ ባለው አካል በኩል በማስፈፀም፣ የትራንስፖርት ስምሪት አገልግሎት ለተጠቃሚዎች በተቻለ ፍጥነት እንዲቀርብ በማድረግ፣ የተቋረጡ የተሰበሩ የአገልግሎት መስጫ አውታሮች በአፋጣኝ ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

2.8 ሴክተር ዘለል የሆኑ ሥራዎችን በተመለከተ

በሥርዓተ ጾታ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና የአከባቢ ጥበቃ ዙሪያ ከተከናወኑት ተግባራት፤

- በስርዓተ ጾታ ተወካይና በመ/ቤቱ የሴቶች ጉዳይ ኮሚቴ አስተባባርነት ለአራተኛ ጊዜ በመ/ቤታችን የማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን የተለያዩ ትምህርታዊ መልዕክቶችን በማስተላለፍና አዝናኝ ፕሮግራሞችን በማካተት ሠራተኛው የሥርዓተ ፆታ ትምህርት ግንዛቤ እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኞች ልምዳቸውን የሚጋሩበት እና በሥራ ላይ ስለሚያጋጥሟቸው ችግሮች የሚወያዩበትና የመፍትሄ አቅጣጫ የሚያፈላልጉበት የሴቶች የጋራ የምክክር መድረክ ተቋቁሟል፣
- የዓመቱ የአለም የኤድስ ቀን መሪ ቃል "አንድም ሰው በኤች.አይ.ቪ እንዳይያዝ ኃላፊነታችንን እንወጣ!!!" የሚል መልእክት በማስተላለፍና ሠራተኛው የቀይ ሪቫን በደረት ላይ በማድረግ የዓመቱ የዓለም የኤድስ ቀን መሪ ቃል መልዕክት ላይ እርስ በእርስ እንዲወያዩ ተደርጓል፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሥራ ቦታ ላይ ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲያስችል በሽታውን ለመቆጣጠር በመ/ቤታችን መወሰድ ስለሚገባው

እርምጃና በሥራ ቦታ መፈፀም የሚገባቸውን ተግባራት በመጠቆም ጥናት ተደርጓል፣

- በመ/ቤቱ የስራ ዕቅድ በተለይ የክዋኔ ኦዲት በአካባቢ ኦዲት ላይም በማትኮር የሚሰሩት የአካባቢ ኦዲት ስራዎች ለአካባቢ ጥበቃ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡
- የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ግንዛቤ ማስጨበጫ የሚሆን በራሪ ወረቀቶች ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ ሠራተኞች ተሰጥቷል፣
- በመ/ቤቱ ግቢ ውስጥ ለታዩ የጤና ጠንቅ የሆኑ ጉዳዮች ማጣራት ተደርጐ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ቀርቧል፣
- በሶሻልና ኢንቫሮሜንት ኮሚቴ አስተባባርነት የመ/ቤቱ ሰራተኞች የተሳተፉበት የ2004 የችግኝ ተከላ ፕሮግራም በኦሮሚያ ክልል በድሬ ግድብ አከባቢ ተከናውኗል፡፡

3. የ2004 በጀት ዓመት ሂሣብ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች

በዚህ ክፍል የሚነሱ አብዛኞቹ ግኝቶች ባለፉት ዓመታት ሪፖርታችን ደጋግመን ያቀረብናቸው ቢሆንም፣ በርካታ ጉድለት የታየባቸው መሥሪያ ቤቶች በመኖራቸው የሚመለከታቸው አካላት አጥጋቢ እርምጃ ወስደው ባለመገኘታቸው አሁንም ደግመን ለማቅረብ አስፈላጊና ግዴታ ሆኖ በመገኘቱና በጉዳዩ ላይ ተገቢ ትኩረት እንዲሰጠው ለመግለጽ እንወዳለን።

መ/ቤታችን በ2004/2005 የኦዲት ዓመት በ117 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች መደበኛ የፋይናንስና ህጋዊ ኦዲት፣ በክልል መንግሥታት ደግሞ በ283 የወረዳና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች ላይ የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲት ያከናወነ ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት የታዩ ጉልህ የአሠራር ስህተቶችና ግድፈቶች ከመፍትሄ ሃሣቦች ጋር እንደሚከተለው ቀርበዋል።

3.1 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ ኦዲት

3.1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ3 መ/ቤቶች ብር 247,210.19 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት እንደሚገኝ ተውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ - 7 ተመልክቷል/

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል በ2 መ/ቤቶች ቆጠራው በብር 133,466.99 በማነስ እና በ9 መ/ቤቶች በብር 3,433,156.03 በመብለጥ ልዩነት ታይቷል። /ዝርዝሩ በአባሪ - 8 ተመልክቷል/

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና በማነስ/በመብለጥ የታየው ልዩነት ተጣርቶ

እንዲተካ/እንዲስተካከል ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.1.2 <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመት የታባቸው መ/ቤቶች</u>

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፣ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ24 መ/ቤቶች የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር አባሪ - 9 እና አባሪ - 10 እና ዝርዝር ችግሮቹ በልዩ ልዩ የመንግስት መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርት ጥራዝ 1 ከገፅ 4 እስከ 5 እና በየዘርፉ ስር ተመልክቷል/

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፣ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር፣ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በየወሩ እንዲዘጋጅ፣ እንዲሁም በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር ከቆጠራው ጋር ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.2 <u>የተሰብሳቢ ሂሣብ</u>

3.2.1 <u>በየመ/ቤቶቹ የተገኘ ተሰብሳቢ ሂሣብ</u>

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፣ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል። ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ57 መ/ቤቶች ብር 1,369,377,900.98 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል። /ዝርዝሩ በአባሪ - 11 ተመልክቷል/

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የትምህርት ሚኒስቴር ብር 401.75 ሚሊዮን፣ የግብርና ሚኒስቴርና

የግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጠና ብር 220.29 ሚሊዮን፣ ውጭ ጉዳይ ሚ/ር 173.75 ሚሊዮን፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 159.45 ሚሊዮን፣ የሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 86.36 ሚሊዮን፣ በሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና የፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 83.08 ሚሊዮን፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 69.02 ሚሊዮን፣ የፌዴራል ፖሊስ 29.77 ሚሊዮን እና አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 21.39 ሚሊዮን ይገኙበታል፡፡

ይህ የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለለ በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይና የአንዳንድ መ/ቤቶች እየጨመረ የሄደ መሆኑ፣ በአብዛኛው ቀደም ባሉት ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲወራረድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም ሂሳቡ እንዲወራረድ ያልተደረጉ ናቸው፡፡

ስለተሰብሳቢው ሂሳብ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ከሰጡት ምላሽ፣ የሀገር መከላከያ ሚ/ር ለሥራ አመራር ሪፖርት በሰጠው መልስ ብር 18,500,490.05 በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ማለት በመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ብር 11,593,098.46 እና በሌሎች 8 ክፍሎች በድምሩ ብር 6,907,391.59 የወደመ፣ የጠፋና የተሰረቀ መሆኑን እና በፋይናንስ ሕግ መሠረት ከመዝገብ ለማሰረዝ ኮሚቴ መቋቋሙን፣ ለዝቋላ ስቲል ማምረቻ ፋብሪካ በበጀት ዓመቱ በብድር የተሰጠው ብር 45,000,000.00 እና ከ3 ዓመት በፊት ለብራና ማተሚያ ቤት በብድር የተሰጠው ብር 3,000,000.00 በ2005 በጀት ዓመት በሙሉ እንደሚሰበሰብ፣ በአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ በተሰብሳቢ የሚገኘው ውስጥ ብር 4,213,093.82 በተመለከተ የአስተደደር መምሪያው ምን ያህል እንደሰበሰበ ቀሪው ምን ያህል እንደሆነ ከወጪ ቀሪው እንዲሁም እስካሁን እርምጃ ያልተወሰደባቸው ካሉ በማጣራት እንዲሰበሰብ እርምጃ እንደሚወሰድ ሌሎቹ በተለያየ ምክንያት ሊሰበሰቡ ያልቻሉትን በማጣራት ለውሣኔ እንደሚያቀርብ፣ ከተቋራጮች ስለሚፈለገው ብር 10,627,372.19 ከመከላከያ መሠረተ ልማትና ግንባታ ዘርፍ በተሰጠው ምላሽ መሠረት የመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬቱ ክትትል እንደሚያደርግ፣ ትምህርት ሚኒስቴር ለየዩኒቨርስቲዎች ግንባታ የተሰጠውን በርካታ ገንዘብ እንዲወራረድ ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑንና የመንግስት ግዥና ንብረት

ማስወገድ አገልግሎት ከውጭ ሀገር ለመንግስት መ/ቤቶች ተሸከርካሪዎች ግዥ ሂሳብ ሆኖ ተሽከርካሪዎቹ እየገቡ ስለሆነ በቅርቡ እንደሚያወራርድ ሲገልጽ፤ ሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶችን በመጥቀስ ሂሳቡን ለማወራረድ ጥረት እንደሚያደርጉ በመግለጽ ለተላከላቸው የሥራ አመራር ሪፖርት በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቢን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

3.2.2 <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች</u>

- በአብዘኛዎቹ መ/ቤቶች ለእቃ ግዥ ሰራተኞችና ሌሎች ሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ በተደጋጋሚ የሚሰጥ በመሆኑና በእያንዳንዱ የእቃ ግዥ ሰራተኛ ተቀጽላ ሌጀር ባለመኖሩ ማስረጃ ቀርቦለት ያልተወራረደና ከሰራተኛው የሚፈለግ ቀሪ እዳ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥና ለይቶ ኦዲት ለማድረግ አለመቻሉ፤
- በአንዳንድ መ/ቤቶች ገንዘቡ ወጪ ተደርጎ ለመሰጠቱ ማስረጃው ባለመቅረቡ የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- በበርካታ መ/ቤቶች የተሰብሳቢ ሂሳቡ ባልተለመደ ሚዛን /Abnormal balance/ በክሬዲት አቅጣጫ የሚታይ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ መሆኑ፤
- በአንዳንድ መ/ቤቶች የተሰብሳቢ ሂሳብ ተብሎ ቢያዝም የሂሳብ ሠነዱ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑና ከመቼ ጀምሮ የሚፈልግ ሂሳብ እንደሆነ የሚገልጽ ማስረጃ እና ተቀጽላ ሌጀር ያልተቋቋመ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣

ዋና ዋናዎቹ የአሰራር ችግሮች ሲሆኑ፤ በየመ/ቤቶቹ የታየው የተሰብሳቢ ሂሣብ አያያዝ ችግሮች በልዩ ልዩ መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርት ጥራዝ 1 ከገፅ 7 እስከ 10 እና በየዘርፉ መ/ቤቶቹ ስር በዝርዝር ቀርቧል፡፡

እነዚህ የተሰብሳቢ ሂሣብ አያያዝ ችግሮች ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ተመሳሳይ ችግር የተስተዋለባቸው መሆኑን፣ እንዲስተካከሉ በተደጋጋሚ የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ችግሮቹ ሊቀረፉ አለመቻላቸው፣ ለበርካታ ዓመታት ሳይወራረዱ የቆዩና ያለበቂ ማስረጃ በተሰበሳብ ሂሳቦች ስለሚያዙ ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የማይቻልበት ሁኔታ በመኖሩ፣ በቆይታ ብዛትም ሂሳቦቹን የመሰብሰቡ ሂደት ውስብስብና አዳጋች እየሆነ የሚሄድ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

በመሆኑም ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግ እና ባልተሟላ ማስረጃ ሪፖርት እንዳይዘጋጅ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.3 የገቢ ሂሣብ

3.3.1 በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሣብ

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ4 መ/ቤቶችና በ6 የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 29,205,484.95 በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ - 13 ተመልክቷል/

በአዋጁ በመሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፣ ምስራቅ አዲስ አበባ ብር 25.09 ሚሊዮንና ውሃና ኢናርጂ ሚ/ር ብር 1.06 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፣ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ

ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S. Code) እና Custom Procedure Code (C.P Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሳበሳበ የንግድ ትርፍ ግብር እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች ወሳኝ ስለሆነ፣ ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.3.2 <u>ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ</u>

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤትና በስሩ ባሉ ስድስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፣ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው ብር 853,920,158.83 እና በሌሎች 6 መ/ቤቶች ብር 12,250,953.19 በድምሩ ብር 866,171,112.02 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ - 12 ተመልክቷል/

ገቢን በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አ.አ ወጪ እና ሌሎች ዕቃዎች ቅ/ጽ/ቤት ብር 475.95 ሚሊዮን፣ በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት ብር 315.06 ሚሊዮን፣ በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ብር 23 ሚሊዮን፣ ምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ብር 16.19 ሚሊዮን፣ ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 12.03 ሚሊዮን ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት 14.10 ሚሊዮንና በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ብር 6.18. ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

መ/ቤቶቹ ለስራ አመራር ሪፖርታችን በሰጡት ምላሽ፤

- የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት የንብረት መውረስ ደብዳቤ ለድርጅቶቹ ተጽፎ ክትትል እየተደረገ መሆኑን፣
- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት ያለውን ቀሪ ሂሳብ በመመሪያ ቁጥር 69/2004 መሰረት ወደ ንብረት መያዝ ለማስተላለፍ የማጥራት ስራ መጀመሩን፣
- በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግዴታቸውን ባልተወጡ ደንበኞች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ወደ ህግ ማስከበርና ለሚመለከታቸው ክፍሎች ማሣወቃቸውን፣
- የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ለ4 ግብር ከፋዮች የብር 7,035,679.02 የውሳኔ ማስታወቂያ የተላከ መሆኑንና ለቀሪዎችም አስፈላጊውን እርምጃም የሚወስዱ መሆኑን፣
- የሀዋሳ ለ6 ግብር ከፋዮች የብር 563,899.43 የግብር/ታክስ ማስታወቂያ የተላከ መሆኑና የሌሎችን የማጥራት ስራ እየተከናወነ መሆኑን፣
- የምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ለአራት ድርጅት የግብር ማስታወቂያ ወጥቶ ሁለት ድርጅቶች ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቅሬታ አቅርበው በዝርዝር እየታየ ያለ መሆኑንና፣

ሌሎች ድርጅቶችም በቀረበው የኦዲት ግኝት መሰረት የግብር ማስታወቂያ ወጥቶላቸው በውሳኔው ላይ ቅሬታ ቀርቦ በመታየት ላይ ያለ መሆኑንና የተሠጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀበለውት ውዝፍ ገቢውን ለመሰብሰብ የተለያየ ጥረት እያደረጉ መሆኑን ለስራ አመራር ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት ተገቢ እርምጃ በመውሰድ የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ለየመ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.3.3 ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስር ባሉ በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ብር 75,049.27 እና በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 4,888,598.34 በድምሩ ብር 4,963,647.61 የገቢ ደረሰኝ እና የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፤ የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል።

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፤ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

3.3.4 የውስጥ ገቢን ሂሳብ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ መ/ቤቶች

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ5 መ/ቤቶች የሰበሰቡት የውስጥ ገቢ ብር 24,606,079.30 ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ - 15 ተመልክቷል፡፡/

የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱት መ/ቤቶች አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፤ በገንዘብ ያልተገለፀ የውስጥ ገቢ ሂሳብ በሪፖርት የማያካትቱ በ15 መ/ቤቶች /ዝርዝራቸው በአባሪ - 15 ተመልክቷል/ ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች ገንዘብ የሚሰበስቡና ሪፖርትም የማያደርጉ እንዲሁም ያለ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ፍቃድ የገቢ ደረሰኝ አሳትመው ገቢ የሚሰበስቡ 5 መ/ቤቶች ያሉ /አባሪ - 18/ መሆኑ ታውቋል፡፡

ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪም ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስበቸውን ገቢ ሕገዊ በሆነ መንገድ በታተሙ ደረሰኞች ብቻ በመጠቀም እንዲሰበስቡና የገቢን ሂሳብ በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.3.5 የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የወጪ መጋራት ሂሳብ የማይሰበሰቡ መ/ቤቶች

የወጪ መጋራት አሰባሰብ መመሪያ ቁጥር 26/2001 ክፍል 5.2/ሀ መሰረት የተቀጣሪዎች የእፎይታ ጊዜ እንደተጠናቀቀ ከጥቅል የወር ደመወዝ ላይ 10% በአሰሪው እየተቀነሰ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ፈሰስ የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ 3 መ/ቤቶች - የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም፣ የፌደራል ፖሊስ፣ የጅማ ዩኒቨርስቲ እና የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የወጪ መጋራት ሂሳብ የማይሰበስቡ መሆኑ ታውቋል፡፡

መሰብሰብ ያለበት የመንግስት ገንዘብ በወቅቱ ሳይሰበሰብ ሊዘገይ ከመቻሉም በላይ ሳይሰበሰብ ሊቀር የሚችልበትም አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፡፡

በመሆኑም የወጪ መጋራት ሂሳብ በመመሪያው በተቀመጠው ቀነ ገደብ መሰረት እንዲሰበሰብ ተገቢውን ቁጥጥር መደረግ እንዳለበትና ያልተሰበሰበውም ሂሳብ ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.3.6 ከየመኖሪያ ቤት አበል ግብር የማይቀንሱ መ/ቤቶቸ

በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 12/1 እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነፃ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማንኛውም ክፍያ ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት ደንቡ በሚያዘው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ፣ የጅማ ዩኒቨርስቲ እና ህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጽ/ቤት የመኖሪያ ቤት አበል በጥሬ ገንዘብ ከሚከፈላቸውና መኖሪያ ቤት

በአይነት ከተሰጣቸው መምህራንና ሠራተኞች ላይ የገቢ ግብር የማይቀነስ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

መሰብሰብ ያለበት የመንግስት ገንዘብ በወቅቱ ሳይሰበሰብ ሊዘገይ ከመቻሉም በላይ ሳይሰበሰብ ሊቀር የሚችልበትም አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፡፡

በመሆኑም የወጪ መጋራት ሂሳብ በመመሪያው በተቀመጠው መሰረት እንዲሰበሰብ ተገቢው ቁጥጥር መደረግ እንዳለበትና ያልተሰበሰበውም ሂሳብ ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.3.7 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ ተመዝግቦ ስለተገኘው ሂሳብ

የተመዘገበው ሂሳብ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት የሂሳብ መደቡን ጠብቆ መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ:-

በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ከተለያዩ የታክስ አይነቶች የሚሰበሰበው ገቢ በመንግስት የታክስ አስተዳደር (SIGTAS) ላይ በትክክለኛው ሂሳብ መደብ የማይመዘገብ መሆኑንና 2 መ/ቤቶች በተገቢው ሂሳብ መደብ ባለመመዝገቡ በተለያዩ በሂሳብ መደብ በድምሩ ብር 201,109,973.12 በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ - 17 ተመልክቷል/

የገቢ ሂሳብ በተገቢው የሂሳብ መደብ ካልተመዘገበ የሂሣብ ሪፖርት እና የአፈጻጸም ሪፖርት ትክክለኛውን መረጃ እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አወቃቀር መሰረት ትክክለኛውን የሂሳብ መደብ ተከትሎ ሊመዘገብ እና የሂሳብ መግለጫውም ትክክለኛውን የገቢ አፈጻጸም በገቢው አይነቱ እንዲያሳይ ተደርጎ ሊስተካከል ይገባል፡፡

3.3.8 በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል።

3.3.9 በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 66 መሠረት በእቃዎች አያያዝ፣ በታሪፍ አመዳደብ፣ በዋጋ አተማመን ወይም በሌላ የሂሣብ አሠራር ስህተት ምክንያት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ በስድስት ወራት ውስጥ ለከፋዩ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱም ሆነ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በበጀት አመቱ በተለያየ ምክንያት በስህተት ተሰብስቦና በገቢም ተመዝግቦ ነገር ግን ለባለመብቱ ተመላሽ የሚደረግ ሂሳብ ተገቢው ማስተካከያ የማይደረግለት መሆኑ፤
- በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 5/2000 አንቀጽ 5 መሰረት:- የጫት ላኪ ማህበራት ማህበራት በቀን ኮታቸው መሰረት ጫቱን ለሶጂክ የሚያቀርቡ መሆኑንና አገሪቷ ከውጪ ንግዱ ማግኘት ያለባትን የውጪ ምንዛሬ እያገኘች መሆኑን እንዲሁም በቀን ኮታቸው ልክ በመመሪያው መሰረት በማያቀርቡት ላይ ተገቢው እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ማህበራት በልዩ ልዩ ምክንያት በኮታው መሰረት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በቀን ኮታቸው ልክ የማያቀርቡ መሆኑንና በዚህም ምክንያት አገሪቷ በ2004 በጀት አመት ብቻ 3,099,618 የአሜሪካ ዶላር የውጪ ምንዛሬ ያጣች መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ለወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 543/1999 አንቀጽ 11 (9) የጉምሩክ ባለሥልጣን ስሌቱን

የሚሠራው ቫወቸሩ በታደሰ ከ11ኛው ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ሲሆን ስሌቱ በ30 ቀናት ውስጥ መጠናቀቅ እንዳለበትና በአንቀፅ 11(10) ደግሞ አምራቹ የምርት ሥራው እንዳይስተጓጎል ለሦስት ጊዜ ብቻ በኢንሹራንስ ዋስትና እቃዎች ወደ አገር ሊያስገባ ይችላል ብሎ ይደነግጋል፡፡ መመሪያው በትክክል ለመዋሉ ኦዲት ሲደረግ አብዛኛው የቫውቸር ተጠቃሚዎች መጀመሪያ ካስገቡት በተጨማሪ በኢንሹራንስ ዋስትና ዕቃዎች ወደ አገር አስገብተው ሳያወራርዱ ለዓመታት የቆዩ መኖራቸውን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- በታክስ ኦዲተሮች የግብር ውሳኔ መሰረት የሚሰበሰበው ሂሳብ በትክክለኛው የታክስ አይነትና የሂሳብ መደብ እየተመዘገበ የሂሳብ ሪፖርት የሚዘጋጅ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል አንድ ድርጅት ከተለያየ የታክስ አይነት ተጨማሪ የግብር ውሳኔ ሲደርሰው ለየታክስ አይነቱ የክፍያ ስምምነት መግባት ሲኖርበት በጥቅል ስምምነት እንዲገባ የሚደረግ ሲሆን ክፍያ ሲፈጽምም ለተለያዩ የታክስ አይነቶች የከፈለ ቢሆንም የሚመዘገበው ግን በአንዱ የታክስ አይነት ላይ በማጠቃለል በመሆኑ፤ የሚዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን ሁኔታ የማያሳይ መሆኑ፤

- በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 ክፍል 7 አንቀጽ 26 ታክስ ስለማስታወቅና ስለመክፈል ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እያንዳንዱ የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ሂሳቡን ለታክስ ባለስልጣን ማስታወቅ እንዳለበት ያዛል፡፡ ስራው በዚሁ መሰረት የሚሰራ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት/፤

    - ቻይና ጂሊን ፕሮቪንስ ትራንስሚሽን ኤንድ ሰብስቴሽን ፕሮጀክት ካምፓኒ (0000043793) ከ2001 በጀት አመት በኃላ የተጨማሪ እሴት ታክስም ሆነ የንግድ ትርፍ ያላሳወቀ መሆኑ፣

- ፍላወር ፖርት ካርጎ ድርጅት /0005021831/ ከጥር 2004 ጀምሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቀ በመሆኑ፣ ምክንያት ለመንግስት ገቢ መሆን የሚገባው ገንዘብ በወቅቱ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

➢ ከግብር ከፋዩ የሚሰበሰብ ግብር/ገቢ ሙሉ በሲግታክስ (በሲስተም ላይ) የሚመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በአዳማና በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤቶች ከተወሰኑ ግብር ከፋዮች በማኑዋል ደረሰኝ የተሰበሰበ ገቢ በሲግታክስ (ሲስተም ላይ) የማይመዘገብ መሆኑን፣
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በታክስ ኦዲትም ሆነ በዴስክ ኦዲት የሚገኙ (የሚጠየቁ) ተጨማሪ የግብር ዉሳኔዎች በሲግታክስ (ሲስተም ላይ) የማይመዘገቡ መሆኑ፣
- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በኩል ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም የወጪ መጋራት የሚሰበሰበው ገቢ በመንግስት ታክስ አስተዳደር ስርዓት /SIGTAS/ ላይ የማይመዘገብ መሆኑ፣ የግብር ከፋዩን መረጃ በተሟላ ሁኔታ ስለማይገኝ የታክስ ኦዲት በሚሰራበት ጊዜ ዕዳ ያለበትና የሌለበትን በሚለይበት ጊዜ፣ በጊዜው ታክስ ያሳወቁና ያላሳወቁትን ለመለየት የማይቻል መሆኑ፤
- በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ሳጋ ሎጂታ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሐምሌ ወር 2003 ዓ.ም የተጨማሪ እሴት ታክስ ሽያጭ ብር 57,272.70 በነሐሴ ወር 2003 ውስጥ መክፈል ሲገባው ጥር ወር 2004 በመክፈሉ ቅጣትና ወለድ አለመክፈሉ፤
- ስለፌደራል መንግስት አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀፅ 70 መሰረት ማናቸውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለመስሪያ ቤቱ ወይም ለዉጪ ኦዲተሮች ለማናቸዉም ጉዳይ በመረጃነት የሚያስፈልጉትን የፋይናንስ መረጃዎችና መዛግብት ቢያንስ ለአስር አመት ማቆየት እንዳለበት ያዛል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ፡-
  - በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል 67 ዲክላራሲዎኖች ለኦዲት ተጠይቀው ባለመቅረባቸው፣.

- በምስራቅና ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤቶች በኩል በተወሰኑ ግብር ከፋይ ፋይሎች ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች በፋይላቸው ውስጥ ባለመገኘቱ፣
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በዲክላራሲዮን ቁጥር C-827/2011 ለተመዘገበው እቃ ከዲክላራሲዮኑ ጋር በአባሪነት የዋጋ ሰነዱ የሌለ በመሆኑ

• በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል የማስጫኛ ዋጋ (airway bill) አንድ ሶስተኛው ብቻ ለቀረጥ ማስከፈያነት የሚወሰድ ቢሆንም ይህን ስሌት ለመጠቀም የሚያስችል መመሪያ ወይንም ሰርኩላር ለኦዲት ባለመቅረበቸው የተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ብር ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

• በገንዘብ ትልልፍ መመሪያ ቁጥር 22/2001 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት እያንዳንዱ የባለሥልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት የሰበሰበውን የተጨማሪ ዕሴት ታክስና የቅድመ ታክስ ክፍያን ወሩ ባለቀ ከ10/አስር/ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወደ ባለሥልጣኑ ዋናው መ/ቤት የአደራ ሂሳብ/አካውንት መተላለፍ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ሆኖም፤

  - በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ብር 41,589,986.08 እንዲሁም
  - በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ብር 37,163,801.33

በ2004 በጀት አመት የሰበሰቡትን የክልል መንግሥታትና የከተማ አስተዳደሮች የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ቅድመ ግብር ድርሻ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ወደ ዋናው መ/ቤት የአደራ ሂሣብ /አካውንት መመሪያው በሚያዘው መሠረት በወቅቱ ያልተላለፈ መሆኑ ተውቋል፡፡

በመሆኑም የመንግስት ገቢ የወጡትን የገቢ ደንብና መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ እንዲከናወንና ለታዩትም ድክመቶች አስፈላጊውን ማስተካከያዎች በማድረግ በገቢው እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

3.3.10 <u>የሌሎች መ/ቤቶች የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች</u>

ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑና ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ሲጣራ፤

- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የግል ጤና አገልግሎቱ ከሚያገኘዉ ገቢ ዉስጥ በመመሪያው መሰረት የሆስፒታሉን ድርሻ 15% ገቢ ያላደረገ መሆኑ፣
- የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ከተለያዩ የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች ሽያጭ ገቢ የሚሰበስብ ሲሆን፣ ለሚሰበሰበው ገቢ ግን በሚመለከተው አካል የጸደቀ ተመን የሌለው መሆኑ፣
- የማሪታይም ጉዳዮች ባለስልጣን ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚያስከፍለውን ልዩ ልዩ ታሪፍ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሕግ (በደንብ) ሳያጸድቅ ለባህረኛ መታወቂያ ደብተር መስጠትና ማደስ፤ የመርከብ መኮንኖች የብቃት ማረጋገጫ ዕውቅና የምስክር ወረቀት፤ የወችኪፒንግ የምስክር ወረቀት፤ የጤንነት ምርመራ ማረጋገጫ ውጤት ዕውቅና የምስክር ወረቀት፤ እና የመልቲ ሞዳልትራንስፖርት አከናዋኞች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ፤ የንግድ ስራ ፈቃድና የሰነድ መመርመሪያ ክፍያ የምስክር ወረቀት ለሰጠበት ገቢ የሰበሰበ መሆኑ፣

- <u>**የገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ**</u>

  - ኮሌጁ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ለሰበሰበው ገቢ በመረጃ የተደገፈ የገቢ ተመን የሌለው መሆኑ፤
  - ኮሌጁ ከውስጥ ገቢ ከሰበሰበው ገንዘብ ውስጥ ለኮሌጁ ካፌ ብር 100,000.00 በብድር የሰጠ መሆኑ፤
  - ለኦዲት ከቀረበው የገንዘብ መቀበያ ሰነድ ቁጥር 05101-05150 ውስጥ የገንዘብ መቀበያ ሰነድ ቁጥር 05104 ለኦዲት ሥራው ያልቀረበ መሆኑ፤
  - ከቁጥር 06501-06550 እና 05701-05750 የሆኑ ሁለት የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ፓዶች ከዕቃ ግምጃ ቤት ወጪ የተደረጉ ቢሆንም በኦዲት ወቅት ያልቀረቡ መሆኑ፤

- **<u>የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ</u>**

  - ኮሌጁ በ2003 በጀት ዓመት ብር 20,005.16 ከተለያዩ የገቢ ርዕሶች የሰበሰበውን ገቢ ያልመዘገበ፣ ወደ ባንክ ገቢ ያላደረገ እና ለግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ሪፖርት ያላደረገ መሆኑ፤

- **<u>የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ</u>**

  - ከግል ጤና አገልግሎቱ ከሚያገኘዉ ገቢ ዉስጥ በመመሪያው መሰረት የሆስፒታሉን ድርሻ 15% ገቢ ያላደረገ መሆኑ፤

  - የመያዣና የተመላሽ ሂሳብ በመዝገብ (በሌጀር) የማይመዘገብ፤ ከወጪ ቀሪው የማይታወቅ እንዲሁም በፋይናንስ መመሪያው መሰረት በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ እንዲታይ ያልተደረገ መሆኑ ፤

- ጅማ ዩኒቨርሲቲ የሥራ ተቋራጮች በፀደቀ የውል ማራዘሚያ መሠረት ስራቸውን አጠናቀው ማስረከብ ሲኖርባቸው ባለማስረከባቸው እስከ 2004 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በድምር ብር 81,110,000.00 ዩኒቨርሲቲው ከሥራ ተቋራጮች በቅጣት መልክ Liquidation Damage ካሳ ማስከፈል ሲገባው ያላስከፈለ መሆኑ፣ በተጨማሪም አቅራቢዎች በገቡት ውል መሠረት በወቅቱ ንብረቱን ገቢ ባለማድረጋቸው በድምሩ ብር 2,625,402.93 የቅጣት ክፍያ እንዲከፍሉ መደረግ ሲገባው እንዲከፍሉ ያልተደረገ መሆኑ በአጠቃላይ ድምር ብር 83,735,402.93 የቅጣት ክፍያ አልተሰበሰበም፡፡

- ተቋራጮች በገቡት ውል መሠረት የግንባታ ሥራቸውን ባለማጠናቀቃቸው በጠቅላላው ድምር ብር 17,320,938.60 ቅጣት /Liquidation Damage/ መክፈል ሲገባቸው በአማካሪ ድርጅቱም በኩል ሆነ በዩኒቨርሲቲው እንዲከፍሉ ያልተደረገ መሆኑ፣

- የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ከመደበኛ በጀት እንቅስቃሴ የሚገኙ የመልካም አፈጻጸም ዋስትናና ቅጣት ገቢዎች ወደ ውስጥ ገቢ ሂሳብ የሚገቡ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የውስጥ ገቢ በሚሰበሰበው ልክ ወደ ሂሳብ ቋት ብሎም ወደ ሪፖርት በትክክል መወሰዱን ለማረጋጋጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርትና በሂሳብ መመዝገቢያ ቋት መካከል ልዩነት ብር 2,016,742.21 የታየ መሆኑ ታውቋል፡፡
- የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ-ዋናው ግቢ እና የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ-የህክምናና የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የውስጥ ገቢ ደረሰኞች ተፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የገቢው ዓይነት፤ የተከፈለበት ምክንያት፤ የሂሳብ መደብ ባለመያዛቸው፤ የሃዋሳ ዩኒቨርስቲ-የግብርና ኮሌጅ የውስጥ ገቢ ሂሳብ የገቢ ማመንጫዎች የሆኑት የገቢ ዓይነቶች ዝርዝርና የገቢ ማስከፈያ ተመን በዝርዝር የሚገልጽና በሚመለከተው አካል የጸደቀ ዶክመንት የሌለው በመሆኑ እና ለሌሎች 10 መ/ቤቶች /ዝርዝራቸው በአባሪ-16 ተመልክቷል/ በተሟላ መልኩ ምዝገባ ባለመከናወኑ የውስጥ ገቢ ሂሳብ በዝርዝር ኦዲት ማድረግ አልተቻለም፡፡

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ፤ አፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ፤ እንድሁም በገቢ ደረሰኝ አያያዝ ረገድ የሚደረገው ቁጥጥር ሊጠናከር እንደሚገባ በሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

3.4 የወጪ ሂሣብ

3.4.1. የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ22 መ/ቤቶች ብር 13,803,414.08 ማስረጃ

ማይኖረው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል:: /ዝርዝሩ በአባሪ - 21 ተመልክቷል/

ተገቢውን ማስረጃ አለማቅረብ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ስለሚችል ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

3.4.2. የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ13 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 132,364,911.31 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል:: /ዝርዝሩም በአባሪ - 20 ተመልክቷል::/

ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚየሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፤ በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን የሚገልጽ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጎላ ያሉት ናቸው::

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና ያልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጻዋል::

3.4.3. ከደንብና መመሪያ ወጪ አለአግባብ የተፈጸመሙ ክፍያዎች

ክፍያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ21 መ/ቤቶች ብር 137,363,575.83 ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል:: /ዝርዝሩም በአባሪ- 23 ተመልክቷል/

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ከተፈጸሙ ክፍያዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ፣

በጅማ ዩኒቨርሲቲ 77.61 ሚሊዮን፣አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ 34.77 ሚሊዮንና ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ 10.82 ሚሊዮን ሲሆን፣ ከምክንያቶቹም በድምሩ 97.95 ሚሊዮን በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ ዕቃዎች (materials on site) ተብሎ የተከፈለና ሌሎችም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በመፈጸም፣ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈልና የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የሃላፊነት አበል ለዩኒቨርሲቲ የስራ አመራሮች ክፍያ መፈጸሙና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

በተጨማሪም በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የፌዴራል ሲቪል ሠርቪስ ኮሚሽን በቁጥር መ30/ጠ/ጠ13137/820 በቀን 5/13/2001 ዓ.ም ባስተላለፈው ሠርኩላር መሠረት የትርፍ ስዓት ክፍያ ተግባራዊ እንዳይሆን መመሪያ የተላለፈ ቢሆንም፣ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በ2004 በጀት ዓመት ለትርፍ ሰዓት ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ፣ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት መመሪያ የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባብ የተፈከለውም ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲሆን አሳስበናል፡፡

3.4.4. ግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች

የዕቃና አገልግሎት ግዢዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ30 መ/ቤቶች ብር 353,568,759.15 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ - 22 ተመልክቷል፡፡/

ከደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 240.22 ሚሊዮን፣ የኢንፎረሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ 36.19 ሚሊዮን፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ 20.34 ሚሊዮን፣ አርባ

ምንጭ ዩኒቨርሲቲ 14.08 ሚሊዮን ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 8.75 ሚሊዮንና ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 6.74 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ ማስታወቂያ በመግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ኘሮፎርማ/ አማካኝነት መፈጸም ያለበትን የግዥ ውድድር ሳይደረግ መፈጸም እና የውስን ጨረታ የግዥ ዘዴን ተግባራዊ የሚሆነው ግልጽ ጨረታ ሁለት ጊዜ ወጥቶ እቃው በሚፈለገው ጥራትና መጠን ካልተገኘ ቢያንስ አምስት አቅራቢዎች በውስን ጨረታ መጋበዝ የሚለውን ሳያሟሉ ግልጽ ጨረታ ያላወጣና በውስን ጨረታው የግዥ ዘዴ በቂ አቅራቢዎች ሳይጋብዙ ግዥን ማከናወን የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ከመንግስት መመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቶቹን ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፤ የመንግስትን አዋጅ በማያከብሩ የመ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ ሊወሳድ ይገባል፡፡

3.4.5. <u>የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ</u>

በበጀት ዓመቱ መ/ቤቶች የፈጸሙት ክፍያ ትክክለኛነት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶች በተለያየ ምክንያት የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ ብር 3,507,062,927.60 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ - 30 ተመልክቷል/

የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሣብ ውስጥ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 3.16 ቢሊዮን የሠራዊት ደመወዝና ብር 51.98 ሚሊዮን ለመረጃ ግዥ ወጪ ያደረገው፤ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት 187.85 ሚሊዮን፤ እንዲሁም ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 41.28 ሚሊዮን፤ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 29.70 ሚሊዮንና ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ብር 14.00 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የደመወዝ ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ በበጀት ዓመቱ የተቀጠሩ በዝውውር የመጡ በጡረታ የተገለሉ እና በተለያየ ምክንያት የተሰናበቱ የሠራዊት አባላት ስም ዝርዝር እና የተወሰኑ ዓመታት በማገልገላቸው ማበረታቻ የተሰጣቸው አባላት ስም ዝርዝር ለኦዲት ተጠይቆ መ/ቤቱ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን የሠራዊት ደመወዝ ወጪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዳልተቻለ፤ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልገሎትና በሥሩ የሚገኙ ዋና መመሪያዎች ለደመወዝ ወጪ ያደረጉት ሂሣብ ፔሮሉ በኮድ በመቅረቡ ኮዱን የሚገልጽ ማስረጃ ለመሰጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው፤ ሌሎቹ የወጪ ሂሣቦች ለምሳሌ የመኪና ጥገና የነዳጅ ለማጣራት የመኪኖች ታርጋ የስልክ ቁጥሮችና የመሳሰሉት ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑት እንዲቀርቡ ተጠይቆ ከሚስጥራዊነት አንጻር ማቅረብ እንደማይቻል በኦዲት ወቅት መገለፁና የሌሎችም ክፍያ የተፈጸመባቸው ደጋፊ የክፍያ ሰነዶች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር በላከው መልስ ከመረጃው ሚስጥራዊነት አንጻር የተሰው የሰራዊት አባላትና አዲስ የተቀጠሩት ሠራዊት አባላትን ከደህንነት አንጻር ችግር ያለበት በመሆኑ፣ ለወደፊቱም ቢሆን እንደዚህ አይነት ሚስጥራዊ ሰነዶችን አሳልፎ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑ ተገልጿል፡፡

3.4.6. <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆረጠለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ6 መ/ቤቶች በብር 20,240,407.36 የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል:: /ዝርዝሩም በአባሪ - 25 ተመልክቷል/

ከዚህም ውስጥ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 18.87 ሚሊዮን እና መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ብር 1.32 ሚሊዮን ለተገዛው ዕቃና የንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልተቆረጡት ዋና ዋናዎቹ ሲሆን፣ በተጨማሪም በ4 መ/ቤቶች ብር 634,568,430.11 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው

ማስረጃ ያልቀረበላቸው /ዝርዝሩም በአባሪ - 25/1 ተመልክቷል/ ከዚህም ውስጥ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 409.80 ሚሊዮን፣ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 171.00 ሚሊዮንና ውሃና ኢናርጂ ሚኒስቴር ብር 49.83 ሚሊዮን ይገኝበታል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ከውጪ ተገዝተው ገቢ ያልተደረጉ ዕቃዎች፣

- በዩኤስ ዶላር 1,620.76 የተገዛው ቢት ብሬከር 17 1/2 እንዲሁም 10,000.00 ዶላር ከሚያወጣው ስታንዳርድ አክሰሰሪስ ፎር ድሪሊንግ ውስጥ ሁለት አዳብተር ቢት ብሬከር ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ፤
- በዩኤስ ዶላር 812,800.04 የተገዛው የውሃ መቆፈሪያ ሪግ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ፤
- በዩ.ኤስ.ዶላር 3,235.00 የተገዛው የድሪሊንግና ሌሎች ተጓዳኝ መሣሪያዎች መለዋወጫ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ከተገዙት የመለዋወጫ ዕቃዎች ውስጥ በዩኤስ ዶላር 4,600.00 የተገዙት የመለዋወጫ ዕቃዎች ያልመጡ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

የዚህ ዓይነት አሠራር ለንብረት ብክነት ስለሚያጋልጥ አሠራሩ ተገቢ ሆኖ ባለመገኘቱ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ጥንቃቄ ሊደረግና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው ንብረቶች ለየመ/ቤቶቹ አገልግሎት ለመዋላቸው በማስረጃ እንዲረጋገጥ ለመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4.7. <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች</u>

በበጀት በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ12 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ

ክፍያ ብር 546,599,171.27 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ - 24 ተመልክቷል/

ቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል ውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ብር 302.9 ሚሊዮን፣ ጂማ ዩንቨርሲቲ 123.9 ሚሊዮን፣ ትምህርት ሚ/ር 47.98 ሚሊዮን እና ማዕድን ሚኒስቴር 28.68 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፣ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርተችን አሳስበናል፡፡

3.4.8. <u>በብልጫ የተከፈለ ወጪ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፣ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ 7 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግዢዎች ብር 542,220.60 እና ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በ4 መ/ቤቶች ብር 851,589.66 በጠቅላላው ብር 1,393,810.26 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ - 29 ተመልክቷል/

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ዕደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፣ በድገሚ ወጪ በማድረግ ወይም ከተገበው ውል ውጭ በመክፈልና ከውሎ አበል ተመንና የትርፍ ሰዓት ክፍያ በላይ በመክፈል የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የግዢ ስርዓቱን ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው በብልጫ የተከፈለውም ወጪ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.4.9. የወጪ የሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ17 መ/ቤቶች ብር 18,255,126.27 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ - 28 ተመልክቷል/ የወጪ ሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል የኢትዮ. ጂኦሎጂካል ሰርቬይ 11.73 ሚሊዮን እና የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ 2.37 ሚሊዮን እና በሀገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ 1.61 ሚሊዮን ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

3.4.10. የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 34,801,740.53 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2004 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -27 ተመልክቷል/

ይህም የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት አመቱ የተገኘ አገልግሎት ወጪው በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4.11. በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪና የመደበኛ ወጪ ሂሳብ

ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ/ ሁሉም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት የተካተተ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ6 የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች ብር 159,482,075.35 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ/ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ - 26 ተመልክቷል/

ከዚህም በተጨማሪ የውስጥ ገቢ ሂሳባቸውን በሪፖርት የማያካትቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት /አባሪ-15 ይመልከቱ/ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት እንደማያደርጉ ተውቋል፡፡

ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል፣ በተጨማሪም ትክክለኛውን የመ/ቤቶቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.5 <u>የተከፋይ ሂሣብ</u>

3.5.1 <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ</u>

በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ29 መ/ቤቶች ብር 491,128,467.28 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ - 31 ተመልክቷል/

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች ሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 173.82 ሚሊዮን፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 159.33 ሚሊዮን፣ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 64.329 ሚሊዮን፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 25.01 ሚሊዮን እና የግብርናና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማስተባበሪያ ብር 23.12 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ በሌሎች

መ/ቤቶችም የተከፋይ ሂሳቡ የሠራተኞች የጡረታ መዋጮንና በሌሎች የገቢ መሰብሰብ ግዴታዎች ምክንያት ተሰብስበው ለሚመለከተው አካል ያልተከፈሉትን ይጨምራል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሰኔ 30/2004 ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ ተብሎ ሪፖርት የተደረገው ብር 163.50 ሚሊዮን የሠራዊቱ አባላት ደመወዝ ባለመውሰዳቸው ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ሂሣብ የተያዘና ሂሣቡም በወጪ የተመዘገበ መሆኑን /እና ሌላ ብር 10.32 ሚሊዮን ለበርካታ ዓመታት በተከፋይ የተያዘ/ በመጥቀስ አሠራሩ ከመንግሥት የሂሣብ አሠራር ውጭ በመሆኑ እንደማንኛውም የፌደራል መንግሥት መ/ቤት ያልተከፈለ ደመወዝ በቀጣዩ ወር መጀመሪያ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ መደረግ እንዳለበት ደመወዝ ካልተከፈላቸው አባላት ጥያቄ ሲቀርብ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር እየተጠየቀ እንዲከፈልና ሌሎችም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

3.5.2 <u>በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ድክመቶች</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የየመ/ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በርካታ የሂሳብ አያያዝ ችግሮች ያለባቸው ተከፋይ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፤

- ተከፋይ ሂሳቡ ምን ያህል ጊዜ ሳይከፈል እንደቆየ እና ለማን እንደሚከፈል ለማረጋገጥ ሰነዶቹ ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ
- በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5035 ባልተለመደ ዴቢት ሚዛን /Abnormal Balance/ ሪፖርት ተደርጎ የተገኘ ሲሆን ሰነዱም ሆነ ስለሁኔታው የቀረበ አጥጋቢ ምክንያት የሌለ መሆኑ፤
- የተከፋይ ሂሳብ በክሬዲት መታየት ሲገባው በዴቢት የተመለከተ መሆኑ፤
- ተከፋይ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን ተቀጽላ ሌጀር ባለመቋቋሙ ለነማን እንደሚከፈልና ለምን ያህል ጊዜ ሳይከፈል እንደቆየ ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤

- ቀደም ሲል ባለፉት ኦዲቶች አለአግባብ በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ መገኘቱና የተከፋይ ሂሣብ አጠቃላይ ሌጀር በተቀጽላ ሌጀሮች ላይ ከተመዘገቡት ጋር ተመሳሳይ ለመሆናቸው እንዲጣራ አስተያየት ተሰጥቶ አሁንም ችግሮቹ አለመቀረፋቸው፣

በኦዲቱ ወቅት የተገኙ ናቸው /ዝርዝሩ በልዩ ልዩ የመንግስት መ/ቤቶች ሪፖርት ጥራዝ 1 ከገፅ 32 እስከ 33 እና በየዘርፉ ተከፋይ ሂሳብ ስር በዝርዝር ተገልጿል/

በዚህ አሰራር የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል።

3.6 የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

3.6.1 ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ27 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ ብር 212,476,799.01 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ - 32 ተመልክቷል፡፡/

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 40.97 ሚሊዮን፣ ሃዋሣ ዩኒቨርሲቲ ብር 30.49 ሚሊዮን፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 28.21 ሚሊዮን ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ 22.22 ሚሊዮን እና በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር የቀላ ዝንብ ማጥፍያ ፕሮጀክት 21.63 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱም መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙም የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.6.2 በስራ ላይ ያልዋለ በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% ላይ የሆነውን ብቻ በመውሰድ በ84 መ/ቤቶች ብር 2,761,425,768.89 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ - 32 ተመልክቷል፡፡/ ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ትምህርት ሚኒስቴር ብር 657.51 ሚሊዮን፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 234.15 ሚሊዮን፣ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ብር 221.67 ሚሊዮን፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 198.42 ሚሊዮን፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 161.57 ሚሊዮን እና የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ብር 112.74 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም ሌሎች መ/ቤቶች በመንግስት ተፈቅዶላቸው ሊጠቀሙበት የሚችሉትን በጀት እንዳይጠቀሙ ከማድረጉም በላይ የብቃት ማነስን (inefficiency) የሚያመለክት በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.7 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

3.7.1 የቋሚ ዕቃዎችና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች ተገኝተል፡፡

ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	21 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	18 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	12 መ/ቤቶች
ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ	20 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	33 መ/ቤቶች
ተያያዥነት ያለቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	3 መ/ቤቶች

እንደሚገኙ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ - 33 ተመልክቷል/ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች ከፍተኛ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው 10 መ/ቤቶች ያሉ ሲሆን፣ ችግሮቹ በዝርዝር በልዩ ልዩ የመንግስት መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርት ጥራዝ 1 ከገፅ 36 እስከ 47 ተገጿል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ - 33 ተመልክቷል፡፡/

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ባለመሆኑ ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፤ አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንም በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.8 ተሽከርካሪ

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ14 መ/ቤቶች	375 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ18 መ/ቤቶች	287 ተሽከርካሪዎች
በተለያዩ ድርጅቶች ሥም ሊቢሬ ያላቸው ወደ መ/ቤቱ ስም ያልተቀየረላቸው	በ4 መ/ቤት	15 ተሽከርካሪዎች

መኖራቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ - 34 ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ፣ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ/እንዲወገዱ፤ ሊብሬ ያሌላቸው እንዲወጣለቸውና ሊብሬያቸው በሌላ መ/ቤት የሚገኙት ወደ ባለይዞታው መ/ቤት እንዲዞሩ እንዲደረግ ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

3.8.1 የነዳጅና የነዳጅ ኩፖን አጠቃቀም በተመለከተ

የበጀት ዓመቱን የነዳጅ አጠባበቅና አያያዝ ኦዲት ሲደረግ፤

- የብሄራዊ ስነልክ ኢንስቲትዩት ሰነዶች ሊቀርብ ባለመቻሉ ኦዲት ለማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡
- የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-12464 በቀን 30/10/04 ብቻ 326 ሊትር ነዳጅ የቀዳ መሆኑ፣
- ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ የነዳጅ መቆጣጠሪያ ጌጃቸው የሚሠሩ የዩኒቨርሲቲው መኪናዎች ወጥነት ባለው አሰራር የተጓዙበት ርቀት /ኪሎ ሜትር/ እየተሰላ እና እየተቀናነሰ በአግባቡ ነዳጅ መስጠት እንዲያስችል አንድ መኪና በሊትር ስንት ኪሎ ሜትር መሄድ እንሚችል የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

- <u>በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>
  - እያንዳንዱ ተሸከርካሪ ከተገዛበት ጊዜ ጀምሮ የነዳጅ እና ቅባት ፍጆታ እንዲሁም የመለዋወጫ እና የጥገና ወጪን በግልጽ የሚያሳይ የግል ማህደር የሌላቸው መሆኑ፣
  - ተሽከርካሪዎች በሚጓዙበት ርቀት (ኪ.ሜ) ተሰልቶ ነዳጅ የማይሞላ መሆኑ፣
- <u>በግዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>
  - ለእያንዳንዱ ተሸከርካሪ መኪና የነዳጅ እና ቅባት ፍጆታ እንዲሁም የመለዋወጫ እና የጥገና ወጪ በግልጽ የሚያሳይ የግል ማህደር ያልተቋቋመ መሆኑ፤
  - ተሽከርካሪ መኪናዎቹ በሰአት ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደሚሄዱ በተቀመጠው የምርመራ ስታንዳርድ መሰረት በሚጓዙበት ርቀት (ኪ.ሜ) ልክ ተሰልቶ ነዳጅ የማይሞላ መሆኑ፤
- <u>በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

  ለተሽከርካሪዎች በብዛት ነዳጅ ተገዝቶ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦ ገቢ ከተደረገ በኋላ የተጠቃሚዎች የነዳጅ ጥያቄ ሳይኖር ወዲያው ወጪ የሚደረግ ከመሆኑም በላይ ወጪ ከተደረገ በኋላ በየጊዜው ለተጠቃሚዎች ያለምንም ህጋዊ ማስረጃ የሚታደል መሆኑ፤
- <u>የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም</u>
  - የተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም በተመለከተ የሰሌዳ ቁጥር 4-12187 ሱዙኪ ቪታራ ተሽከርካሪ የኪሎሜትር ንባብ የማይሰራ በመሆኑ የተሽከርካሪውን የነዳጅ ፍጆታ መጠን ለመቆጣጠር የሚቻልበት አሰራር አለመኖሩ፤
  - በሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያሉት ተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ለተቋሙ አገልግሎት መዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ተሽከርካሪዎቹ ለሥራ በሚሰማሩበት ወቅት የተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያ እና መዘዋወሪያ ቅፅ የማይዘጋጅ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

የተሽከርካሪው የኪሎ ሜትር የንባብ መሣሪያ የማይሰራ በመሆኑ የፈጀው /የተጠቀሙትን/ የነዳጅ መጠን እና ኪሎ ሜትር ማረጋገጥ የሚቻልበት አሰራር አለመኖሩ፤ የተቋም የነዳጅ አጠቃቀምን ትክለኛነት ማረጋገጥ እንዲቻል የመንግሥት ተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ መጠቀምና የነዳጅ ፍጆታ መቆጣጠር የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4. <u>ልዩ ልዩ</u>

4.1. <u>የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ</u>

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 208/2000 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ሥልጣንና ሃላፊነት መሰረት የሚተላለፉለትን የልማት ድርጅቶች ተሰብሳቢ ሂሳቦችና ዕዳዎችን የሚመለከቱ ሰነዶችን በመረከብ ወደግል ይዞታ በሚዛወሩበት ወይም ወደ አክስዮን ማህበር ወይም ለቀድሞ ባለቤቱ በሚተላለፉበት ወቅት ወደ አዲሱ ባለቤት የማይተላለፉ የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦችን በመያዝ እንደሚያስተዳድርና ትክክለኛ የሂሳብ ሰነዶችንና መዛግብትን በመያዝ ኦዲት ማስደረግ እንዳለበት ያዛል፡፡ በመሆኑም ቦርዱ በዚሁ መሰረት ተፈፃሚ የሚያደርግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ባለአደራ ቦርዱ የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖርት /Consolidations Financial Statement/ የማያዘጋጅ በመሆኑ የድርጅቶችን የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በመሆኑም የቦርዱን የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳብ ትክክለኛ ገጽታ ለማሳወቅ አያስችልም፡፡ እንዲሁም ከ1997 ጀምሮ ስራው በትክክል እንዲሰራ የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በቦርዱ የሚሰጠው ምላሽ ተመሳሳይነት ያለውና እልባት ያላገኘ ጉዳይ መሆኑ አሳሳቢነቱን የጎላ ያደርገዋል፡፡ ስለ መ/ቤቱ የሚመለከታቸው ሃላፊዎች በተደጋጋሚ የሚነሱትን የሰው ሃይልና ሌሎች ችግሮች ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ሥራው የሚከናወንበት መንገድ ሊፈለግ ይገባል፡፡

- በወለጋ ዩኒቨርሲቲ ልዩ ልዩ ሕንጻዎች ግንባታ ወጪ ሆኖ የተመዘገበው ሂሳብ ትክክል መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ለአንድ ኮንስትራክሽን

ድርጅት ከተፈጸመው ክፍያ ሂሳብ ላይ የተቀነሰው መያዣ (Retention) ብር 173,993.71 መያዣ (Retention) በተከፋይ ሂሳብ ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡

- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ በ2003 እና በ2004 በጀት ዓመት መጨረሻ ያልተሰራባቸው የውስጥ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች በሴሪና በቁጥር (ከ-እስከ-ከ) ተለይቶ ቆጠራ ባለመደረጉ በ2004 በጀት ዓመት የውስጥ ገቢ ሂሳብ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ምን ያህል እንደሆኑ ለማወቅ ባለመቻሉ የውስጥ ገቢ ተሰብስቦበት ደረሰኝ ሳይመለስ ሊቀር እና ገንዘቡ ለግል ጥቅም ሊውል ስለሚችል የውስጥ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች በሴሪና በቁጥራቸው እየተቆጠሩ ሁሉም ደረሰኞች መኖራቸው እና በደረሰኞቹ ተሰብስበው ሁሉም ገንዘብ ገቢ መሆኑ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

<u>ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ</u>

- ዩኒቨርሲቲው ከመቋቋሙ በፊት ሀጂ ናስር ደረቅ ቡና መቀሽሪያ የሚሰራበትን ቦታ ለዩኒቨርሲቲው አስረክቦ ሲለቅ ድርጅቱ ሲጠቀምበት በነበረው ቦታ ላይ የቡና ገለባ በመኖሩ ገለባው በዝናብ ምክንያት እየታጠበ ወደ ሾንጋ ወንዝ የሚገባ በመሆኑ ወንዙን የሚበክልበት ሁኔታ እና መጥፎ ጠረን የፈጠረ መሆኑ፣
- በሚዛን ካምፓስ ከተማሪዎች ካፍቴሪያ የሚወጣ ተረፈ ምግብ፣የሽንኩርት ልጣጭ፣የድንች ልጣጭ፣አመድ፣ አጥንት እና የመሳሰሉት በመመገቢያ አዳራሽ አቅራቢያ እና በሾንጋ ወንዝ አካባቢ በአግባቡ ባልተሰራ የቆሻሻ ማስወገጃ እየተደፋ በመሆኑ በአካባቢው ላይ መጥፎ ጠረን እና ወደ ወንዙ የሚገባበት ሁነታ በመኖሩ ወንዙ የሚበክልበት ሁኔታና ለጤና አስጊ ደረጃ ላይ ቢደርስም የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ልብሳቸውንና ገላቸውን እንደሚታጠቡበት ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፣

- በቴፒ ካምፓስ ጊዜአዊ ለተማሪዎች አገልግሎት የሚውል በቆርቆሮ የተሰራ መጸዳጃ ቤት እና ገላ መታጠቢያ አብሮ የተሰራ ሲሆን መጸዳጃው ተማሪዎች ማደሪያ ክፍል/ዶርም/ አካባቢ የሚገኝ በመሆኑ እና መጸዳጃውና ገላ መታጠቢያ አብሮ በመሰራቱ መጸዳጃ ቤቱ ቶሎ ቶሎ በመሙላቱ አካባቢው ላይ መጥፎ ጠረን መፍጠሩና ገላን ለመታጠብ እንደማይቻል በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማየት የተቻለ መሆኑ፣

- ዩኒቨርሲቲው ባጠናው BPR ጥናት መሠረት ሠራተኛ እንደ አዲስ ሲደለደል የሰው ኃብት ልማት አስተዳደር እና የበጀት፣ ፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ኃላፊ ያልተመደበላቸው ሲሆን በቦታው የነበሩ የቀድሞ ኃላፊዎች ያለውክልና እየሰሩ ሲሆን በተለይ የበጀት፣ ፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ባልተመደቡበትና የዩኒቨርሲቲው ውክልና በሌለበት ሁኔታ በቦታው እየሰሩ እና እስከ ብር 50,000.00 ወጪ የሚያጸድቁ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>ሠመራ ዩኒቨርስቲ</u>

- ለኦዲት ሥራ ተፈላጊ የሆኑ ዶክመንቶች ሰነዶችና ልዩ ልዩ መረጃዎች ለኦዲት ሊቀረቡ ባለመቻሉ በ2004 በጀት ዓመት ለኮንስትራክሽንና ለመሠረተ ልማት ግንባታ ማስፈጸሚያ የተመደበው ብር 14,000,000.00 ካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን እንዲሁም የግንባታው ሥራ በተያዘለት የጊዜ ሠሌዳ መሰረት ተጠናቅቆ የሚፈለገውን አገልግሎት መስጠቱን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- የአስተዳደርና የመምህራን ቢሮዎች፣ ወርክሾፕና ላይብረሪ ግንባታ፣ ከፕሮጀክቱ ጠቅላላ ዋጋ ብር 28,332,773.92 ላይ ብር 20,143,721.71 ለተቋራጩ የተከፈለ ሲሆን በውል የተመለከተው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና የማስረከቢያ ቀን ማርች 29/2010 ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ 1657 ቀናት ወይም ከ 4 ዓመት በላይ የዘገየ ከመሆኑ በተጨማሪ የፕሮጀክቱ ሥራ ሙሉ በሙሉ መቋረጡንና አብይ ኃይሉ የተባሉት የፕሮጀክቱ ሥራ ተቋራጭ የግንባታውን ሥራ በማቋረጥ ጥለው መሄዳቸው እንዲሁም ውል ተቀባይ አብይ ኃይሉ የህንጻ ተቋራጭ በብድር የወሰዱት የሲሚንቶ ዋጋ ብር 642,044.88 ተመላሽ አለመደረጉ የተረጋገጠ ቢሆንም የህንጻ ተቋራጩ በገቡት ውል መሠረት ባለመፈጸማቸው በተቋሙ ላይ ለደረሰው ጉዳትና ኪሳራ G.I.Z. በተባለው ድርጅት እና M.H. ተብሎ በሚጠራው የፕሮጀክቱ ተቆጣጣሪና አማካሪ መሃንዲስ ወይም በተቋሙ ማኔጅመንት ምንም ዓይነት እርምጃ አለመወሰዱ ተረጋግጧል፡፡

5. የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮጀክት ሂሳብኦዲት አስተያየትና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች

5.1. መግቢያ

በአሁኑ ወቅት የሚያከናውነው ኦዲት የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS) ፕሮጀክት ተከታታይ (Continuous) ኦዲት ሲሆን፣ ይህም ኦዲት በየሩብ ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር እና ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍናቸው ሴክተሮች የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን ነው፡፡

ስለሆነም የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ሁለተኛ ዙር (PBS II) ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲት ዋና ትኩረት በእነዚህ መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች (በወረዳና በክልል ደረጃ) የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ላይ በመሆኑ፣ በየሩብ ዓመቱ እየተጠቃለለ የሚላከው የተከታታይ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች የሚያተኩረው በገንዘብ መጠን (quantitative amount) ላይ ሳይሆን፣ በዓይነት ላይ (Qualitative) በመሆኑ፣ ዋና ዋና ግኝቶች የሚባሉት በዓይነት እንጂ በመጠን አለመሆናቸውን እንገልፃለን፡፡

በ2004/5 የኦዲት ዘመን ለተከናወኑት ተከታታይ ኦዲቶች የተሰጡት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የኦዲት አስተያየቶችና በየመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች የሚታዩት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በአብዛኛው ተመሣሣይነት ያላቸው በመሆኑ፣ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶችና የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS) ፕሮጀክት የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ውጤቱ ቀርቧል፡፡

5.2. በ2004/5 የኦዲት ዘመን የታዩ ዋና ዋናየውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች

በአሁኑ ወቅት የተወሰነ መሻሻል ቢታይም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በበርካታ የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች ውስጥ በመታየት ላይ ናቸው፡፡ እነሱም;-

ጥሬ ገንዘብ

- በየወቅቱ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የሚደረግ ቢሆንም ቆጠራዉ ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣
- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ አልፎ አልፎ በየወሩ የማይዘጋጅ መሆኑ፣

ተሰብሳቢ ሂሳብ

- የቅድሚያ ሂሣብ ክፍያዎች እና ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ አለመወራረዳቸው እና አለመፈጸማቸዉ፣
- አልፎ አልፎ ለተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሣቦች ዋና እና ተቀጽላ ሌጀሮች አለመቋቋም እና የተቀጽላ ሌጀሮች ምዝገባ ወቅታዊ አለመደረግ፤

ወጪዎች

- የተወሰኑ ክፍያዎች በበቂና አግባብ ባላቸው ማስረጃዎች አለመደገፋቸው፣
- የውሎ አበል ፎርም በአግባቡ አለመሞላት፡

የሂሳብ ሪፖርት

- ወርሃዊ የሂሣብ መግለጫዎች አልፎ አልፎ በወቅቱ እየተዘጋጁ ለሚመለከተው ክፍል አለመላካቸው፣

ንብረት

- የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ መዝገብ በአብዛኛው መ/ቤት አለመቋቋም፣
- ቋሚ ዕቃዎች በአብዛኛው መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎች በወቅቱ የማይወገዱ መሆኑ፤
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር በአብዛኛው የማይመዛዘኑ መሆኑ፣ እና በአብዘኛዉ መ/ቤቶች የመድኃኒት እና የህክምና መገልገያዎችን አለመመዝገብ፡

የክትትል ኦዲት

- ለኦዲት ሥራ ድጋሚ በሚኬድበት ወቅት፣ ባለፈው ኦዲት ወቅት በታዩ ድክመቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ አለመወሰዱ፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከላይ ለተመለከቱት ድክመቶች አለመሻሻልና በወቅቱም እርምጃ ላለመወሰዱ ኦዲት ተደራጊዎች ሲጠየቁ የሰጧቸው መልሶች (Management Responses) ሲጠቃለሉ የሚከተለውን ይመስላሉ፡-

- ከፍተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መኖር፣
- ከፍተኛ የሥራ ጫና መኖር፣
- የግንዛቤ ማነስ፣እና
- ትኩረት አለመስጠት

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

5.3. በ2003/4 የኦዲት ዘመን በተከናወኑ ተከታታይ ኦዲቶች ላይ የተሰጡ የውስጥ ቁጥጥር ኦዲት አስተያየቶች (Audit Opinion)

በ2004/5 የኦዲት ዘመን (ከጥር/2004 እስከ ታህሣሥ/2005) 283 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ሁለተኛ ዙር (PBS II) ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲቶች የተከናወኑ ሲሆን፣ በተከታታይ ኦዲቱ ወቅት በውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች ላይ የተሰጡት የኦዲት አስተያየቶች (Audit Opinion) እንደሚከተለው ተጠቃሎ በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ - 35 (Annex I) በሚል ተመልክቷል/

ተ.ቁ	የተሰጠው የኦዲት አሰትተያየት	የኦዲቱ ብዛት (በቁጥር)	በመቶኛ (%)
1.	ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified) የኦዲት አስተያየት	13	4.5
2.	ነቀፌታ ያለበት (Except for) የኦዲት አስተያየት	270	95.5
3.	ተቀባይነት የሚያሳጣ (Adverse) የኦዲት አስተያየት	-	-
4.	አቋም የማይወስድ (Disclaimer) የኦዲት አስተያየት		
	ድምር	283	100

5.4. የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ፕሮጀክት የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

የመሠረታዊ አገልግሎቶች 'PBS II' ፕሮጀክት የ2004 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሂሳብ መግለጫ (PFS) የዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን በመከተልና በስምምነቱ በተቀመጠው (TOR) መሠረት ኦዲት ተደርጓል፡፡

የኦዲት ስራው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ደረጃ በተዘጋጀው የተጠቃለለ ሂሳብ ላይ የተከናወነ ዓመታዊ ኦዲት ሲሆን የተሰጠው የኦዲት አስተያየት "ነቀፌታ የሌለበት" (Unqualified) ነው፡፡

6. የክዋኔና የአካባቢ ኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሃሣቦች

የክዋኔ ኦዲት መሠረታዊ ተልዕኮ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች የተመደበላቸውን የሰው ኃይል፣ ገንዘብና ቁሳቁስ ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ በመጠቀም እንቅስቃሴአቸውን በብቃት በማከናወን የተሰጣቸውን የሥራ ኘሮግራም ከግብ በማድረስ የሚጠበቀውን ውጤት ማስገኘታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት አካሂዶ የታዩ ድክመቶች እንዲስተካከሉ ለሥራ አመራሩ ተገቢውን የማሻሻያ ሃሣብ ማቅረብና ተፈፃሚነታቸውንም በመከታተል ስኬታማ ውጤት እንዲገኝ መርዳት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ነው::

የመንግሥት መ/ቤቶች ያቀዷቸውን ሥራዎች በተመደበላቸው በጀት ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ እና በቅልጥፍና ማከናወናቸውን እንዲሁም የሥራ ኘሮግራሞቻቸው ስኬታማ መሆናቸውን የፌዴራል ዋናው ኦዲተር አጣርቶ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 4 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ኦዲት አድርጎ፣ ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የታዩ ጉልህ ድክመቶች ጠቅለል ባለ መልኩ ቀጥሎ ቀርበዋል::

6.1. በኢምግሬሽን እና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ በመደበኛ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት በተመለከተ

- የመደበኛ ፓስፖርት የሚፈልግ ማንኛውም ዜጋ አስፈላጊውን መረጃ አሟልቶ ሲቀርብ በዋናው መምሪያ በ 3 ቀናት፣ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በ7 ቀናት ውስጥ የጉዞ ሰነድ ተዘጋጅቶ ሊሰጠው ሲገባ በዋናው መምሪያ እና በናሙና በተመረጡት የደሴ፤ የባህር ዳር እና የሃዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እስከ 90 ቀናት ድረስ የሚያስጠብቅ መሆኑ፤
- በዋናው መምሪያም ሆነ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አገልግሎት ለማግኘት የሚመጡ ባለጉዳዮች መሰረታዊ የሆኑ አገልግሎቶች በተለይም መጠለያ ያለው ወረፋ መጠበቂያ ስፍራ፣ የመጸዳጃ ቤቶች እና የምግብ እና የመጠጥ አገልግሎት የሚያገኙበት ሥፍራ ሊሟሉላቸው የሚገባ ቢሆንም፤
  - በዋናው መምሪያ ለባለጉዳዮች የተዘጋጀ የእንግዳ ማረፊያ አዳራሽ ቢኖርም፣ ከተገልጋዩ ህዝብ ብዛት የተነሳ ወደ አዳራሹ ከመድረሳቸው

በፊት በግቢው ውስጥ ለረዥም ሰዓታት ወረፋ የሚጠብቁበት መጠለያ የሌለ መሆኑ፣

- በናሙና በተመረጡ በደሴ፣ በባህር ዳር እና በሐዋሳ ኢምግሬሽን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለባለጉዳዩች ፎርም ከመሙላት ጀምሮ ገንዘብ አስኪከፍሉ ድረስ ያለውን የሥራ ሂደቶች ለመጀመር ተራቸው እስኪሚደርስ ወይም የተዘጋጀላቸውን ፓስፖርት ለመውሰድ በተቀጠሩበት ቀን ወረፋ የሚጠብቁበት ቦታ (የእንግዳ ማረፊያ ቤት)፤ ለባለጉዳይም ሆነ ለሰራተኛው የሚሆን ደረጃውን የጠበቀ የመፀዳጃ ቦታ የላቸውም፤ ወይም ደግሞ በብልሽት ምክኒያት ለሠራተኛውም ሆነ ለባለጉዳዮች ጤና ጠንቅ እየፈጠሩ መሆኑ፣

- በአጠቃላይ የአገልግሎት አሰጣጡን አስመልክቶ በዋና መምሪያውም ሆነ በናሙና በተመረጡት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እያገኙ ያለውን አገልግሎት ጥራት ደረጃ እና በአጠቃላይ በመስሪያ ቤቱ ቆይታቸው ስላገኙት አገልግሎት አስተያየት ከሰጡን 200 ባለጉዳዮች 189 ባለጉዳዮች (94.5%) የሚሆኑት አለመርካታቸውን የገለፁ መሆኑ፤
- የፓስፖርት አሰጣጥ ሂደቱ ረዥም መሆኑ፤ ለደንበኞች በቂ የሆነ እንክብካቤ አለመኖር፤ ከዝናብና ጸሃይ መከለያና የወረፋ መጠበቂያ ቦታ አለመኖር፤ የመፀዳጃ ቤትና ውሃ አለመኖር፤ የቀጠሮ ቀን አለመከበር፤ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ባለጉዳዮችን የሚረዳ የመረጃ ዴስክ አለመኖር ለደንበኞች አለመርካት እንደምክንያት ከተጠቀሱት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ መሆናቸው፣
- የመደበኛ ፓስፖርት አመልካቾች የመጀመሪያ ቀጠሮ ለመውሰድ መታወቂያቸውን ፎቶ ኮፒ ከዋናው መምሪያ እንዲያደርጉና ኮፒ በተደረገው መታወቂያ ላይ የቀጠሮ ቀን (ፎርም ለመሙላት) ከፊርማ ጋር እንዲወስዱ ለማድረግ የተቀመጠው የአፈጻጸም ደረጃ/ስታንደርድ (performance indicator) በደቂቃዎች ቢሆንም ባለጉዳዮች የመጀመሪያ ቀጠሮ ለመውሰድ ከአንድ ሰዓት እስከ ስድስት ሰአት የሚጠብቁ መሆኑ፣
- ባለጉዳዮች በዋና መምሪያውም ሆነ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ አስተያየት እና ጥቆማ ማቅረብ የሚያስችል እና

የተሰበሰቡት አስተያየቶችም ተተንትነው ተገቢው መፍትሔ ለመስጠት እንዲያስችል የተቀረፀ ስርዓት ቢኖርም፤

- በናሙና በተመረጡ በደሴ፣ በባህር ዳር እና በሐዋሳ እንዲሁም በዋናው መምሪያ ውስጥ የቅሬታ መቀበያ ዴስኮች አለመኖር
- በሐዋሳ እና በባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚገኙት የሀሳብ መስጫ ሳጥኖች ደግሞ በተገልጋዩ ሕብረተሰብ ሊታዩና ሊደረሱ በማይችሉበት ቦታ መቀመጣቸው፣
- በደሴ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደግሞ የሃሳብ መስጫ ሳጥኑ እንደ መቀመጫ እያገለገለ መሆኑን በተደረገው የመስክ ጉብኝት መታወቁ፣

- ከዋና መምሪያው ተልዕኮ አንጻር ውስጣዊ ጥንካሬዎችንና ድክመቶችን እንዲሁም ውጪያዊ ዕድሎችንና ሥጋቶችን ለይቶ ለመረዳት የሚያስችል እና በአገልግሎት አሰጣጥ መስክ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ጥሩ ውጤት ያስገኙ የአሰራር ልምዶች መሰረት ያደረገ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ቢደረግም ጥናቱ በማስተናበሪያና የጉዞ ሰነድ ዝግጅት መምሪያ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- ዋና መምሪያው ለአገልግሎቱ አሰጣጥ የሚረዳው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሲስተም ከተዘረጋ ስምንት ዓመት ያለፈው ቢሆንም አሁን ካለው ከፍተኛ የባለጉዳይ ቁጥር አንፃር የማስተናገድ አቅሙን ለማሳደግ ማሻሻያ (upgrade) ያልተደረገለት መሆኑ፤
- የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ የመስሪያ ቤቱን መረጃ ለማጠናቀር የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሲስተም/Web-site ለመዘርጋት በመሰረታዊ ሂደት ለውጥ ጥናት ከ 2001 ዓ.ም ጀምሮ በጥናቱ ላይ ቢካተተም ኦዲቱ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ ይህን ቁልፍ ተግባር ድረ ገጽ ተዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፣
- ዋና መምሪያው የፓስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚጠቀምባቸው የተለያዩ መሳሪያዎች ሲበላሹ አፋጣኝ ጥገና ተደርጎላቸው ሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባ ቢሆንም፣
  - በሐዋሳ ኢምግሬሽን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የአንድ ወርክ ስቴሽን ካሜራ፣ አንድ የሱፐርቫይዘር ኮምፒውተር፣ አንድ የዕለት ገንዘብ ያዥ ባር ኮድ ሪደር (1D-bare Code)፣

- በደሴ አንድ የኤሌክትሮኒክ መፈረሚያ (signature pad)፣ አንድ የኮምፒዩተር ኃይል መቆጣጠሪያ (UPS) ተበላሽተው አገልግሎት እንደማይሰጡ እና ከሲስተሙ ጋር የማይጣጣም (Not compatible) አንድ የአሻራ መውሰጃ (DFR) መገኘቱ፣
- ደረሰኝ የሚያወጣው ፕሪንተር ሁለት ደረሰኝ በአንዴ እንደሚያወጣ እና ከሁለት ወር በላይ በብልሽት ምክኒያት ተገቢውን አገልግሎት ሊሰጡ አለመቻሉ፣
- መሣሪያዎቹ እንዲጠገኑ በተደጋጋሚ ለዋናው መምሪያ በደብዳቤ ቢያሳውቁም ጥገናው አለመደረጉን፣
- በሓዋሳ፤ በደሴ፤ በባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ደግሞ ከመሳሪያዎች ጥገና እና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዙርያ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚረዳ ድጋፍ ሰጪ አካል አለመኖሩ፤

- ዋና መምሪያው ለሚሰጠው አገልግሎት የሚፈለገውን እና በቅድሚያ ባለጉዳዮች ማሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች የሚፈለጉ መስፈርቶቹን ተገልጋዩ ሊያየው በሚችል ግልጽ ቦታ ላይ ሊለጥፍ እንዲሁም የመረጃ ዴስክ ሊኖር የሚገባ ቢሆንም፣
- በደሴ፤ በባህርዳር እና በሃዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ፓስፖርት ለመጠየቅ እና ለማውጣት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን የሚገልጽ ምንም ማስታወቂያ (መረጃ) አለመኖሩ፣
- ባለጉዳዮች በሂደት ላይ እያሉ ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ መረጃ የሚጠይቁት አካል አለመኖሩን ከባለጉዳዮች እና በመስክ ጉብኝት ወቅት ለመረዳት የተቻለ መሆኑ፣
- በዋና መምሪያው ሆነ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ስለሚሰጡ አገልግሎቶች እና አገልግሎቶቹ የት እንደሚሰጡ የማስተዋወቅ ሥራ ሊሰራ የሚገባ ቢሆንም፣ መጠይቅ ከተደረገላቸው 200 አገልግሎት ፈላጊዎች ውስጥ 120 የሚሆኑት (60%) የፓስፖርት አገልግሎት በሌሎች የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንደሚሰጥ እንደማያውቁ መግለፃቸው፣
- በዋና መምሪያውም ሆነ በቅርንጫፍ መ/ቤቶች የውስጥ ቁጥጥር መርህ በሚያዘው መሠረት፣ የሚሰበሰበው ገንዘብ በእለቱ ወደ ባንክ ገቢ መደረግ ያለበት ቢሆንም፣

- በደሴ፣ በባህር ዳር፤ በሐዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፤ ከመደበኛ ፓስፖርት የሚሰበሰበው የዕለት ገቢ ገንዘብ ምንም አጃቢ ሳይመደብ የግል ትራንስፖርት በመጠቀም ወደ ባንክ በገቢ የሚደረግ መሆኑ፣
- በእለት ገቢ ሰብሳቢዎች የሚሰበሰበው ገንዘብ በየቀኑ ገቢ ሲደረግ አጠቃላይ የሣጥን ገቢ ደረሰኝ እራሳቸው የሚያዘጋጁ መሆኑ፤
- በየእለቱ የተሰበሰበውን ገንዘብ ባንክ ከገባው ጋር ትክክለኛ መሆኑን የማይረጋገጥ መሆ፤
- ገንዘብ ለመሰብሰብ ኃላፊነት ባልተሰጣቸው ሠራተኞች ገንዘብ የሚሰበሰብ መሆኑ፤
- የሚሰበሰበው ገንዘብ በየዕለቱ ባንክ ገቢ የማይደረግ መሆኑ፤
- ገንዘብ ያገሮች ባለፈው ቀን የሰበሰቡትን ገንዘብ ገቢ አድርገው እስኪመጡ ድረስ ባለጉዳዮች በመጠበቅ የሚጉላሉ መሆኑ፤
- የተሰበሰበው ገንዘብ ወደ ባንክ ገቢ ከሆነው ገንዘብና ከደረሰኙ ጋር ገንዘብ ያገሮች እራሳቸው በየዕለቱ የሚያስታርቁ መሆኑ፣

- በዋና መምሪያው የስርዐተ-ፆታ እና የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ጉዳይ ተካቶ (Mainstreaming) በሁሉም የስራ ሂደት ተግባራዊ ሊደረግ ሲገባ፣ በደሴ፣ በባህርዳር እና በሐዋሳ በሚገኙት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሥርዓተ ጾታም ሆነ የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በየሥራ ሂደቱ ተካቶ እንዲሰራ አለመደረጉ፤ በኦዲት ወቅት የታዩ ግኝቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም ከለይ የተመለከቱትን ድክመቶች ለማሻሻል አስተዋጾ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻ ሀሳቦች ለኢሚገሬሽንና ድህንነት ዋና መምሪያ መ/ቤት በላክነው ሪፖርት በማካተት መስሪያ ቤቱ ከሚመለታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲያደርጋቸው አሳስበናል፡፡

6.2. <u>በሀገሪቱ የማዕድን ሀብት ልማት ላይ ለሚሳተፉ አካላት ወጥ የሆነ የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ልማቱ የአካባቢንና የህብረተሰቡን ደህንነት በማይጎዳ ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑን በተመለከተ</u>

- በማዕድን ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ አካላት የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ እና የተዘረጋው ስርዓት ተግባራዊነት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘረጋ ቢሆንም፤ በናሙና ከተመረጡና በሚኒስቴር

መ/ቤቱ የማምረት ፈቃድ ከተሰጣቸው 21 ባለፈቃዶች ውስጥ 14ቱ (67%) የተቀመጠዉን መስፈርት አሟልተው ፍቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ ማስረጃ አለመኖሩ፣

- የማዕድን ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የማዕድን ልማት ፈቃድ የተጠየቀበት አካባቢ ለዱር እንስሳት ጥበቃ ያልተከለለ እና ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሲባል በተለየ ሁኔታ ጥበቃ የማይደረግለት መሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥ እና የታቀደው የማዕድን ልማት በዱር እንስሳት እና በመኖሪያቸው አካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የማያሳድር መሆኑና የአካባቢያቸው ህልውና በዘላቂነት የሚጠበቅ መሆኑን ማረጋገጥ ሲገባ፣
  - የአብጃታ ሶዳ አሽ አክስዮን ማህበር በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሸዋ ዞን አዳሚ ቱሉ ጁዶ ኮምቦልቻ ወረዳ ውስጥ ከአብጃታ ሐይቅ ውስጥ የሶዳ አሽ ማዕድን ለማምረት ፈቃድ ሲጠይቅ፤ የማዕድን ፈቃዱ ከመሰጠቱ በፊት ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተለይም ማዕድኑ የሚገኝበትን ሐይቅ የሚጋራው የአብጃታ-ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክን በባለቤትነት የሚያስተዳደረው የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን አስተያየት ተጠይቆ ኢንቨስትመንቱ ቢቀጥልና ይበልጥም ቢስፋፋ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ከፍተኛ በመሆኑ ፈቃዱ መሰጠት እንደሌለበት አስተያየት ሰጥቶበት እያለ፤ በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካባቢና ማህበረሰብ ልማት ዩኒት ደብዳቤ ተግባራዊነቱ እንዲቀጥል ይሁንታ መሰጠት እንደሌለበት አስተያየት የሰጠ ቢሆንም የአብጃታ ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ ይዞታ ክልልን የጨመረ ከ28,800 ስኩዌር ኪሎ ሜትር በሆነ ቦታ ላይ የሶዳ አሽ እንዲያመርት ለአክስዮን ማህበሩ ፈቃድ የተሰጠ መሆኑ፣
- እንደዚሁም የብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ኢሉ አባቦራ ዞን ያዩ ወረዳ የኮል ፎስፌት ማዳበርያ ኮምፕሌክስ ፕሮጀክት ሊተገበርበት የታሰበበት ቦታ፣
  - በቅርቡ Biosphere Reserve ተብሎ በUNESCO እውቅና ያገኘ የደን ቦታ መሆኑ፣
  - የያዩ ጥብቅ የጫካ ቡና (Yayu coffee forest Biosphere Reserve) ከየትኛውም አካባቢ የጫካ ቡና /wild Arabica coffee/ በብዛት በውስጡ የያዘና በብዝኃ-ሕይወት (Biodiversity) የበለፀገ በመሆኑ፣

- የደን ቦታውን ከአላማው ውጭ ማዋል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ Biosphere Reserve የተቋቋመበትን ቀጣይነት ያለው የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ ጥበቃና እንክብካቤ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ስለሚችል ፈቃዱ ቢሰጥ አካባቢው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት ለማዕድን ሚኒስቴር መ/ቤት አስተያየቱን የገለፀ ቢሆንም ኮርፖሬሽኑ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት አስጠንቶ ሳያቀርብ እንዲሁም ደግሞ ፕሮጀክቱ የበለጠ ጠቀሜታ ያለው ለመሆኑ ትንታኔ (Cost benefit analysis) የተሰራበት ሰነድ አቅርቦ የድንጋይ ከሰል ማዕድን የማምረት ፈቃድ የተሰጠው ስለመሆኑ ማስረጃ አለመቅረቡ፣

- የማዕድን ምርመራ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆየው ለ3 ዓመት ብቻ ሲሆን ከ3 ዓመት በኋላ መቀጠል የሚፈልጉ ካሉ ግን ለተከታታይ 7 ዓመታት በየዓመቱ የስራ ፕሮግራም በማቅረብ የምርመራ ፈቃድን ማሳደስ ያለባቸው ቢሆንም እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ መታደስ ወይም መሰረዝ የነበረባቸው 81 የምርመራ ፈቃዶች ስለመታደሳቸው ወይም እንዲያሳድሱ ማሳሰቢያ ስለመሰጠቱ ወይም ፈቃዳቸው ስለመሰረዙ የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡ፣
- ማዕድን ለማልማት ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት በገቡት ውል መሰረት ስራቸውን ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉ ሲጣራ ድልቢ ኮል ማይኒግ አክስዮን ማህበር
  - በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን ዴዶ ወረዳ ውስጥ የድንጋይ ከሰል ለማምረት የማዕድን ማምረት ፈቃድ ሲወስድ በግንቦት 4 ቀን 2000 ዓ.ም. ዉል ከገባው ግዴታዎች ውስጥ፣ አስራ ሁለት የተለያዩ የመሰረተ ልማት ሥራዎች ከአራት ዓመታት በኃላ እንኳን አለመስራቱ፤
  - የማዕድን መሬት ኪራይ አለመክፈሉ፤
  - እንዲሁም ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተፈጥሮ ሀብት ልማትና የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ግንቦት 08 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የማዕድን ሚኒስቴር አስፈላጊውን የእርምት እርምጃዎች እንዲወስድ የተገለፀ ቢሆንም፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ እርምጃ አለመውሰዱ፣
- የመንግስት ነፃ የአክሲዮን ድርሻ በቀድሞው አዋጅ 2% በአዲሱ አዋጅ ደግሞ 5% እንደሚኖረው የተደነገገ ቢሆንም፣ በኦዲቱ ወቅት የመንግስት

ነፃ አክስዮን ድርሻ የሚያስገኘውን ጥቅም በተመለከተ በማዕድን ሚኒስቴር ፈቃድ በናሙና ከተመረጡ 21 ማዕድን አምራቾች ውስጥ 20 ባለፈቃዶች ክፍያ የማይፈፅሙ መሆኑ፤

- በናሙና ጉብኝት በተደረገባቸው የኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የመንግስት ነፃ የአክስዮን ድርሻ እየተሰበሰበ አለመሆኑ፣
- በክልሎች በባህላዊ መንገድ ከሚመረት ወርቅ ሮያሊቲን ለመሰብሰብ የሚያስችል ህግ አለመውጣቱ፣
- በባህላዊ መንገድ ከሚመረት ወርቅ የሮያሊቲ ክፍያ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል እና በኦሮሚያ ክልል የማይሰበስብ መሆኑ፣
- የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎችና አያያዛቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ መዘጋጀትና መሰራጨት እንዳለበት በማዕድን ፖሊሲ ሰነድ ላይ የተመለከተ ቢሆንም፣ መመሪያው በሚኒስቴር መ/ቤቱ አለመዘጋጀቱ፤
- የማዕድን ፈቃድ ጠያቂዎች ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሊያቀርቡ፣ በፈቃድ ጠያቂዎች የሚቀርቡ የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናቶች ትክክለኛነት ፈቃድ በሚሰጠው አካል የሚረጋገጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግና የጥናቱ ተግባራዊነት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግበት ሲገባ፣ በናሙና ከተመረጡ የማምረት ፈቃድ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ከወሰዱ 21 ባለፈቃዶች ውስጥ 16 ባለፈቃዶች (76%) የሚሆኑት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አቅርበው ፈቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ ማስረጃ አለመቅረቡ፣
- ህብረተሰቡ ከማዕድን ልማቱ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊነቱ የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡ ከአካባቢ ማህበረሰቦች፣ ከማዕድን ስራ ከተሰማሩ ባለሀብቶችና ከክልል መንግስታት ጋር በመተባበር የተቀናጀ የአካባቢ ልማት እቅድ ሊዘጋጅና ለዚህም የሚያስፈልግ ወጪ (ፈንድ) የሚመደብበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊሆን ሲገባ፣
  - በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች እና በኦሮሚያ ክልሎች፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ

ከተሰጣቸው ከ21 ማዕድን አውጪዎች ውስጥ 20 ባለፈቃዶች በአካባቢ ልማት ላይ ትኩረት ባለማድረጋቸው፤

- ከአካባቢው መስተዳድርና ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን የተቀናጀ የአካባቢ ልማት ዕቅድ የማያዘጋጁ መሆኑን፤
- የአካባቢ ልማት እቅድ እንዲዘጋጅ የሚያደርግ የአሰራር ስርዓት ያልተዘረጋና ተግባራዊ አለመደረጉ፣

- በማዕድን አዋጅ ቁጥር 678/2002 መሰረት ለአካባቢ ልማት የሚውል ገንዘብ በየዓመቱ የሚመድቡ ድርጅቶች ገንዘቡን ለማን ማስገባት እንዳለባቸው ባለማወቃቸው ለማዕድን ሚኒስቴር ደብዳቤ ቢፅፉም ምላሽ ባለማግኘታቸው በገንዘቡ የየአካበቢው ህብረተሰብ ተጠቃሚ ሊሆን አለመቻሉ፣
- ቀሪዎቹ ባለፈቃዶች ፈቃድ ሲሰጣቸው በውሉ ላይ ለዚህ ተግባር እንመድባለን ብለው ከሚገልጹት የገንዘብ መጠን በስተቀር ፈንዱን ስለመመደባቸውም ሆነ የሚመደበው ገንዘብ የት መቀመጥ እንዳለበት እና በስራ ላይ ስለመዋሉም ክትትል የሚደረግበት ስርዓት አለመኖሩ፣
- የማዕድን ባለፍቃዶች የአካባቢ ተፅዕኖ መልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ሊመድቡና ለመልሶ ማቋቋሚያ ፈንዱ በስራ ላይ የሚውልበትን የአሰራር ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸው ቢሆንም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች እና በኦሮሚያ ክልል እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር እና ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ከወሰዱት ባለፈቃዶች ለመልሶ ማቋቋሚያ የሚሆን ፈንድ ፈቃድ ሲሰጣቸው በውሉ ላይ ከሚገለጽ የገንዘብ መጠን በስተቀር የተመደበው ገንዘብ የት መቀመጥ እንዳለበትና ስራ ላይ ስለመዋሉ ክትትል የሚደረግበት ስርዓት አለመኖሩ፤
- ለመንገዶች ግንባታና ጥገና አገልግሎት በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና በክልል የገጠር መንገድ ባለሥልጣኖች እንዲሁም በእነርሱ በኩል ጨረታ አሸንፈው ኮንትራት የሚወስዱ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በህግ በተደነገገው መሰረት በነፃ የሚጠቀሙ ቢሆንም በማዕድን አዋጁ መሰረት አካባቢን መልሶ ለማቋቋም የሚያገለግል ፈንድ የማይመድቡ እና የመንገድ ግንባታቸውን ጨርሰው ቦታውን ለቀው ከመሄዳቸው በፊት የመልሶ ማቋቋም ስራዎች የማይሰሩ መሆኑ፣

- በማዕድን ሚኒስቴር የማዕድን ሥራ ጤንነትና ደህንነት መመሪያ ተዘጋጅቶ ለክልል ማዕድን ቢሮዎችም ሆነ የማዕድን ፈቃድ ለተሰጣቸው አካላት ስለመሰራጨቱ ማስረጃ አለመቅረቡ፣
- የሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን ልማት ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ስርዓት በመዘረጋት በማዕድን ልማት ዙሪያ ለሚነሱ ችግሮች በአፋጣኝ ምላሽ መስጠት የሚጠበቅበት ቢሆንም፤
  - የሚድሮክ ወርቅ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበር የሳካሮን የማዕድን ማምረት ፍቃድ ሲያወጣ በካዳስተሩ መሰረት ድንበራቸው እንዲከለልላቸው ለወረዳው፣ ለዞን እና ለክልሉ አሳውቀው መፍትሄ ባለማግኘታቸው ለማዕድን ሚኒስቴር ቢያሳውቁም እስካሁን ድረስ ይዞታቸው እንዲከለል አለመደረጉ፤
  - ፈቃድ የተሰጠበት ቦታ ክልል ውስጥ በአንደኛው ሳይት ላይ ሥራ ከተጀመረ በኃላ በአካባቢው ነዋሪዎች በተተከለው ቡና ተክል ምክንያት ለቁፋሮ የሚሆን ማሽን በቦታው ላይ ተክለው መስራት ያለመቻላቸው፣
  - በለገደምቢ ወርቅ የማምረት ፍቃድ ክልል ውስጥ በሚገኝ የፈንጂ ማከማቻ መጋዘን አካባቢ ከ 500 ሜትር ባነሰ ርቀት የሰፈሩ ነዋሪዎች ማህበሩ ፈቃድ ከመውሰዱ በፊት የነበሩት ነዋሪዎች ካሳ ተከፍሏቸው የተነሱ ቢሆንም፣ እነሱ ከተነሱ በኃላ ሌሎች መጥተው በመስፈራቸው ከሥፍራው እንዲነሱ እንዲደረግ ጉዳዩን ለወረዳው፣ ለዞኑ፣ ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት እና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ቢያሳውቅም እልባት ለማግኘት አለመቻሉ፤
  - በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና በክልል የገጠር መንገድ ባለሥልጣኖች ለመንገድ ግንባታና ጥገና በህግ በተደነገገው መሰረት በነፃ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ለመጠቀም የኮንስትራክሽን ማዕድን ቦታ ሲወስዱ፤
  - የሚኒስቴር መ/ቤቱንም ሆነ የክልል ማዕድን ቢሮዎች/ ኤጀንሲዎች እንዲያውቁ የማይደረግ መሆኑን፣
  - የኮንስትራክሽን ማዕድኑን ከመቼ እስከ መቼ እንደሚጠቀሙ በግልጽ ያልተቀመጠ እና ሥራው ሲጠናቀቅ የማምረቻ ሥፍራውን የማይመልሱ መኖራቸው፣

- የኮንስትራክሽን ማዕድኑን ከተፈቀደላቸው ዓላማ ውጪ ለሌላ ተግባር እንዳያውሉት በማዕድን ቢሮዎችም ሆነ በመንገድ ባለሥልጣኖች በኩል ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግባቸው መሆኑን፣
- በአጠቃላይ ለመንገድ ግንባታ እና ጥገና ተብሎ በተለየ የሚሰጠውን የኮንስትራክሽን ማዕድን የማምረት (የመጠቀም) ፈቃድ አሰጣጥ፣ ቁጥጥር እና አካባቢን መልሶ የማቋቋም ሥራ በቅንጅት የማይከናወን መሆኑ፣

- የማዕድን ሚኒስቴር የማዕድን ፈቃድ መረጃን ለመለዋወጥ የሚረዳ በአገር አቀፍ ደረጃ ሥራ ላይ እንዲውል የካዳስተር ሥርዓት ዘርግቶ በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልሎች ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ ሲጣራ፣ የደቡብ፣ የኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች የካዳስተር ስርዓቱን በክልል ደረጃ እየተጠቀሙበት ቢሆንም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር እና በየክልሎች በሚገኙ ዞኖችና ወረዳዎች ያሉ የማዕድን ፈቃድ የሚሰጡ አካላት ግን የማይጠቀሙበት መሆኑ፤

በኦዲት ወቅት የታዩ ግኝቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም ከለይ የተመለከቱትን ድክመቶች ለማሻሻል አስተዋጾ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻ ሀሳቦች ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በላክነው ሪፖርት በማካተት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲያደርጋቸው አሳስበናል፡፡

6.3. <u>በመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የጡረታፈንድ አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ</u>

ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎችና የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ላይ ኃላፊነት እና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ፣ ከመንግሥት ሠራተኞች የተሰበሰበውም የጡረታ መዋጮ ወደ ጡረታ ፈንድ በወቅቱ ገቢ ሊደረግ ሲገባ፣

- አዋጅ ቁጥር 714/2003 ከመውጣቱ በፊት አሰሪ መ/ቤቶች ከሰራተኞቻቸው ደመወዝ እየቆረጡ የሰበሰቡትን የጡረታ መዋጮ ገቢ ማድረጋቸውን ለመከታተል የተዘረጋ ስርአት አለመኖሩ፣
- አዋጅ ቁጥር 714/2003 ከወጣ በኋላም በተለይ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከሰራተኞቻቸው የሰበሰቡትን የጡረታ መዋጮ ለገቢዎችና

ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ እንዲችሉ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር ውል የተዋዋሉ ቢሆንም፣ መሰብሰብ ያለበትን የጡረታ መዋጮ በውሉ መሰረት ለመሰብሰብ የሚያስችል ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን፣

– ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር በተደረገው የውል ስምምነት ላይም ተጠቃሎ ወደ ጡረታ ፈንድ ገቢ የተደረገውን የጡረታ መዋጮ ገቢ ያደረጉትን እያንዳንዱን የመንግሥት የልማት ድርጅት እና ሰራተኞች ለማወቅ እንዲቻል ዝርዝር መግለጫ በማዘጋጀት ከባንክ ዴቢት አድቫይስ ጋር ገንዘቡ ለጡረታ ፈንዱ በተላለፈበት ወር እስከ ቀጣዩ ወር 30ኛው ቀን ድረስ ለኤጀንሲው መላክ እንዳለበት የተቀመጠ ቢሆንም ባለስልጣኑ በውሉ መሰረት እንዲፈጽም ባለመደረጉ አሰሪ መ/ቤቶች ያስገቡለትን ብቻ ለኤጀንሲው በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ከማድረጉ ውጪ ከየትኛው መ/ቤት፣ ዞን፣ ወረዳ እንደተሰበሰበ ባለመታወቁ የተነሳ የትኛው መ/ቤት የጡረታ መዋጮውን በወቅቱ ገቢ ማድረጉንና አለማድረጉን ለመለየት አለመቻሉ፤

- በናሙና ተመርጠው ከታዩት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አማካኝነት በቀጥታ ለኤጀንሲው ገቢ ስለሚሆን የኤጀንሲው የአዲስ አበባ ሪጅን ጽ/ቤት የጡረታ መዋጮው በትክክል ገቢ መደረጉን የማይቆጣጠር መሆኑን፣
- ከሠራተኞች ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በመቀነስ እስከ 3 ወር ድረስ ወደ ፈንዱ ገቢ ያላደረገ መ/ቤት ክፍያውን ራሱ እንዲፈጽም መደረግ ያለበት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 714/03 የተመለከተ ቢሆንም

  – በናሙና ከታዩት መ/ቤቶች ውስጥ ከሠራተኛው ደመወዝ ቀንሰው ወደ ጡረታ ፈንዱ ሳያስገቡ የቀሩ መ/ቤቶች መኖራቸው፤

  – በሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት እንደሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች ከሰራተኞች ደመወዝ እየተቀነሰ እንዲቀር ባለመደረጉ በአዲሱ አዋጅ መሰረት ከሰኔ/2003 ጀምሮ የጡረታ መዋጮ ያልከፈለ መሆኑ፣

- በሆሳዕና ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት ከሰኔ 2003 ጀምሮ እስከ ነሐሴ 2004 ድረስ እንዲሁም በሆሳዕና ማዘጋጃ ቤት ከሠራተኞች ደመወዝ ተቀንሶ የቀረ የጡረታ መዋጮ ወደ ኤጀንሲው ገቢ አለመደረጉ፣

- በፌዴራልም ሆነ በክልል የጡረታ መዋጮ ከፋይ በሆኑ አሰሪ መ/ቤቶች መሰብሰብ የሚገባው ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ስለመሰብሰቡ ኤጀንሲው ምርመራ በማድረግ እርምጃ መውሰድ ያለበት ቢሆንም፤
  - መሰብሰብ የሚገባው የጡረታ መዋጮ መኖሩን እንጂ ውዝፍ መዋጮ ያለባቸው መ/ቤቶች የትኞቹ እንደሆኑ ተለይተው የማይታወቁ መሆኑ፤
  - ያልተሰበሰበ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ምን ያህል እነደሆነ በትክክል ለይቶ ለማወቅ አለመቻሉ፤
- የሚፈለግባቸውን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ገቢ ያላደረጉ የክልል መንግሥታት በአዋጅ ቁጥር 714/2003 መሰረት የፌዴራል መንግሥት ከሚሰጣቸው የድጎማ በጀት ላይ ተቀንሶ ለኤጀንሲው ገቢ ሊደረግ ሲገባ፣
  - ኤጀንሲው ከአዋጅ ቁ.714/2003 በፊት ያለውን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ በእያንዳንዱ የመንግሥት መ/ቤት ላይ ክትትል አድርጎ አለመሰብሰቡ፣
  - ከመጋቢት 14 እስከ ግንቦት 30 2004 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በቀረበው የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት መሰረት ከተመረመሩት መ/ቤቶች መካከል ለምሳሌ ከመሀል፣ ከአዲስ አበባ እና ከደቡብ ሪጅን ጽ/ቤቶች፣ በድምሩ ብር 118,114,069.00 በአሰሪ መ/ቤቶች ላይ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ መኖሩ ተረጋግጦ መተማመኛ የተሰጠ ቢሆንም ገንዘቡ ገቢ ስለመደረጉ ማስረጃ ያለመቅረቡ፣
- ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በመቀነስ እስከ 3 ወር ድረስ ለፈንዱ ገቢ ያላደረገ መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 714/03 መሰረት ክፍያውን ራሱ እንዲፈጽም ማድረግ ሲገባ፣ በኦዲቱ ወቅት
  - ኤጀንሲው በሚያደርገው የሂሳብ ምርመራ ያልተሰበሰበ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ሂሳብ መኖሩ እየታወቀ በተለይ በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታ ሲዛወሩ ሊከፍሉት የሚገባ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ እዳ ያለባቸው መሆኑ እየታወቀ ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርጉ ለኤጀንሲው የህግ ክፍል በማስተላለፍ እርምጃ እንዲወሰድ አለመደረጉ፣

- ከ2002 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ የህግ ጉዳዮች ዳይሬክተር ክትትል በማድረግ ክስ ከመሰረተባቸው 44 መዝገቦች ውስጥ ውዝፍ የጡረታ ሂሳብን በተመለከተ የተከሰሱት 6 (ስድስት) ብቻ መሆናቸው፣ የተቀሩት በግለሰቦች ላይ የተከፈቱ የተመላሽ አበል ክፍያን የሚመለከቱ ክሶች መሆናቸው፤
- በመሰረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ ጥናት መሰረት ኤጀንሲው የጡረታ ፈንዱን ለመቆጣጠር የሚጠቀምበት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ዘመናዊ ሊደረግ ሲገባ የጡረታ ፈንድን የሚመለከቱ አዋጆች እና ደንቦች በየጊዜው ተሻሽለው መውጣታቸውን ተከትሎ አሰራሩም እየተለወጠ በመምጣቱ በ1992 ዓ.ም የተዘጋጀው እና ከ 13 ዓመት በላይ በአገልግሎት ላይ የቆየው የጡረታ ፈንድ የሂሳብ አያያዝ ማንዋል (መመሪያ) በጥናቱ መሰረት እንዲሻሻል አለመደረጉ፤

- በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት የበጀት አመቱ ባለቀ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ሂሳቡን በመዝጋት የኤጀንሲውን አጠቃላይ የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ (የሂሳብ መግለጫ) በየዓመቱ በማዘጋጀት ኦዲት ሊያስደረግ ሲገባ የ2003 እና 2004 በጀት ዓመትን ሂሳብ ባለመዝጋቱ እና የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ (የሂሳብ መግለጫ) ባለማዘጋጀቱ የጡረታ ፈንዱ ሂሳብ ከ2002 በኋላ ኦዲት ያልተደረገ መሆኑን፣
- ለፈንዱ ኢንቨስትመንት አያያዝና አጠቃቀም በጥናት ላይ የተመሰረተ የቁጥጥር እና የክትትል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ፤ እንዲሁም ለሪል ስቴት ወጪ የተደረገው ገንዘብ ለወደፊቱ እንዲሰበሰብ ተደርጎ የሂሳብ ምዝገባውም ከኢንቨስትመንት ወደ ተሰብሳቢ ዞሮ ሊመዘገብ፤ ቦታውንም ለሚመለከተው የመንግስት አካል ለማስረከባቸው ማስረጃ ሊቀርብ ሲገባ፡-
  - ኤጀንሲው ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉ ህንጻዎች ለመገንባት አሰላ፤ ደሴ፤ ጅማ እና ደብረማርቆስ ለሚካሄድ ሪል ስቴት ልማት ብር 5,301,741.17 ወጪ ተደርጎ ከተከፈለ በኋላ መንግሥት የኤጀንሲውን ኢንቨስትመንት በተመለከተ አዲስ አቅጣጫ በማስቀመጡ ከተጀመረው የሪል ስቴት ልማት እንዲወጣ የተደረገ መሆኑ፣

- በዚሁ ውሳኔ መሰረት ቀደም ሲል በሊዝ ኤጀንሲው የተረከበውን ቦታ ለማስረከብና ውሉ እንዲቋረጥ የተከፈሉ የተለያዩ ወጪዎችም ተመላሽ እንዲሆኑ በ17/09/03 ለጅማ ከንቲባ ጽ/ቤት፣ በ20/11/2003 ለአሰላ ከተማ ከንቲባ ጽ/ቤት፣ በ9/09/2003 ለደሴ ከተማ አገልግሎት እና በ10/09/2003 ለደብረማርቆስ ከተማ ከንቲባ ከተጻፈ ደብዳቤ ውጭ ለሪልስቴቱ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲሆን የተደረገ ክትትል አለመኖሩ እና ደብረማርቆስ እና አሰላ ከተማ የሚገኘውን ቦታ ለከተሞቹ ማዘጋጃ ቤቶች ለማስረከባቸው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን፣

- ኤጀንሲው የመንግሥት ሠራተኞችን ምዝገባ እና የጡረታ ፈንዱን የሚመለከቱ ማስረጃዎች አስተማማኝ እና ወጥ በሆነ የመረጃ አያያዝ ዘዴ በመያዝ እና በመጠበቅ በተፈለጉ ጊዜ ወዲያውኑ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ሲገባ የመንግሥት ሠራተኞች የምዝገባ መረጃ በሁለት አይነት መንገድ ማለትም በኮምፒዩተር መስራት የሚችሉ የኤጀንሲው ሰራተኞች በሶፍት ኮፒ ሲይዙ ኮምፒዩተር መጠቀም የማይችሉ ሰራተኞች ደግሞ በእጅ (Manual) እየመዘገቡ የሚያዙ መሆኑ፣

- ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የምዝገባ ማስረጃ ተሟልቶ ሲቀርብ የማኅበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር በወቅቱ ሊሰጠው ይገባል፡፡
  - ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ሪጅን ጽ/ቤቶች ውስጥ ከ1990 እስከ 2001 ድረስ ለተቀጠሩ ሰራተኞች መለያ ቁጥር እንዲሰጣቸው ከዋናው መ/ቤት መለያ ቁጥሩ ተልኮ ፋይሉን እያደራጁ መሆኑን፣ በናሙና ከታዩት አሰሪ መ/ቤቶችም ከቀረበው ቃለ መጠይቅ ለመረዳት እንደተቻለው፣
  - ሰራተኞች የጡረታ ጊዜያቸው ሲደርስ እየተቸገሩ መሆኑን እና መ/ቤቶች እራሳቸው የሰራተኞቻቸውን መረጃ አሟልተው የማይልኩ መሆኑን፣

- ኤጀንሲው በጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎች እና አበል ከፋይ ተቋማት እንደዚሁም በአሰሪ መ/ቤቶች ሥራው ለሚመለከታቸው ሰራተኞች ስለሚሰበስቡት የጡረታ መዋጮ አሰባሰብ ማስረጃ አያያዝና አላላክ፣ የጡረታ አበል ክፍያ ለትክክለኛው ባለመብት ስለመክፈል፣ ለአሰሪ መ/ቤቶች የሰራተኛውን ህይወት ታሪክ ማስረጃ አስሞልቶ በወቅቱ ስለመላክ የግንዛቤ ማስጨበጫ አለመሰጠቱ፣

በመሆኑም ከለይ የተመለከቱትን ድክመቶች ለማሻሻል አስተዋጾ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻ ሀሳቦች ለመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ከሚመለታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲያደርጋቸው አሳስበናል፡፡

6.4. በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የቀረጥ ነጻ ንግድ አሠራርና አፈጻጸምን በተመለከተ

- በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉ አካላት፣ ሥራው ላይ ከመሰማራታቸው በፊት የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ሥራ ፈቃድ ማውጣትና በወቅቱ ማደስ ይኖርባቸዋል፡፡ ነገር ግን በኦዲቱ ወቅት፣
  - በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው በመስራት ላይ የሚገኙት የግል የቀረጥ ነጻ ድርጅቶች በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችል የህግ መሰረት እና የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ሥራ ፈቃድ የሌላቸው መሆኑን፣
- በአዲስ አበባ ቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት አስተዳደር ጥር 1994 ዓ.ም ለተገልጋይ ኅብረተሰብ በኪራይ የሚሰጡ ልዩ ልዩ ይዞታዎች አጠቃቀም ሥልት ጥናት ላይ በICAO(International Civil Aviation Organization) የተደገፉ የኤርፖርት የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ውስጥ መንግስታዊ በሆኑ ድርጅቶች ብቻ የሚከናወን ተብሎ የተገለፀ (የኢሚግሬሽን ስራ፣ የጉምሩክ ስራ እና የቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ) ቢሆንም
  - የኢትዮጵያ ሲቪል አቬሽን ባለስልጣን መ/ቤት ሰኔ 26,1994 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሔራልድ ጋዜጣ ቁጥር 248 ባወጣው የጨረታ ማስታወቂያ ላይ የቀረጥ ነጻ መደብር ሱቅ በሚል ያወጣ ሲሆን፣
  - ለዚሁ ጨረታ ነጥብ መስጫ አጠቃላይ እና ቴክኒካል መስፈርት በሚል የተለዩ መመዘኛዎች የተቀመጡ ሲሆን አጠቃላይ መስፈርት ተብሎ የተቀመጠው ተጫራቾች ለቴክኒካልና ለፋይናንሻል ምዘና ከማለፋቸው በፊት ማሟላት የሚጠበቅባቸውን አግባብ ያለው ህጋዊ የቀረጥ ነጻ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥን የሚያካትት ሆኖ ሳለ በዘርፉ ለመሰማራት የሚያስችል የህግ መሰረት እና የቀረጥ ነጻ ንግድ ፈቃድ ሳይኖራቸው እንዲጫረቱ መደረጉ፣

- በዘርፉ ልምድ ሳይኖራቸው ከአስር ዓመት በላይ ልምድ እንዳላቸው ተደርጎ የ37 ዓመት ልምድ ካለው መንግስታዊ የልማት ድርጅት ተወዳዳሪያቸው እኩል 14 ነጥብ በመስጠት ጨረታውን እንዲያሸንፉ በማድረግ ለፈቃድ ሰጪ አካላት(ለቀድሞው የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ ለቀድሞው የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ) ተገቢው የቀረጥ ነጻ ፈቃድ እንዲሰጣቸው የኢትዮጵያ ሲቪል አቬሽን ባለስልጣን በተደጋጋሚ በደብዳቤ በጠየቀው መሰረት ከዛሬ 10 ዓመት በፊት አንደኛው የግል ድርጅት በዘርፉ እንዲሰማራ እድል በመክፈት ቀሪዎቹም(ሁለት የግል ድርጅቶች) በዚሁ አግባብ ሊስተናገዱ መቻላቸው፣

- የተርሚናል ቁጥር ሁለት ግንባታ በተጠናቀቀበት ወቅት በሀገሪቱ ያሉትን ህጎች በመፈተሽ ተገቢው የአስተዳደርና የቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ደህንነት ከማስጠበቅ እና ተገቢውን የፋይናንስ ስርዓት እንዲኖር ለማስቻል የተሰራ ስራም ሆነ የተጠና ጥናት አለመኖሩ፣
- በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 እና 686/2003 መሠረት የቀረጥ ነጻ ንግድ ዘርፍ የቀድሞው የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መ/ቤት የንግድ ሥራ ፈቃድ ከሚሰጥባቸው የንግድ ሥራ ዘርፎች ዝርዝር ውስጥ አለመካተቱ፤
- በሚኒስቴር መ/ቤቱም በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉ አካላት ማሟላት የሚገባቸው መስፈርት አለመዘጋጀቱ፤
- በገቢዎች ሚኒስቴርና በኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን በኩልም የሚያስፈልገውን በቂ የሰው ሀይል መመደብ እንደሚችሉና በቂ ዝግጅት ማድረጋቸው፤ የግል ባለሀብቶች በዘርፉ ቢሰማሩ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ደህንነት ላይ ሊያስከትል የሚችለው ተጽኖ በጥናት ሳይረጋገጥ፣ ሽያጭ ሲፈጸም መብቱ ላላቸው አካላት ብቻ መሆኑ የሚረጋገጥበት ስርዓት ሳይዘረጋ፣ የሽያጭ የአፈጻጸም መመሪያ ሳይዘጋጅ፤ በቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት ፍላጎት ላላቸው ግለሰቦች ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችል የህግ መሰረት ሳይኖር፤ በቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማራውን መንግስታዊ የልማት ድርጅት ለማቋቋም የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 106/85 የቀረጥ ነጻ ንግድ በመንግስት በሞኖፖል ስለመያዙ ወይም በግል እንዳይሰራ የሚከለክል ስለመሆኑ የተቀመጠ

ድንጋጌ የለም በማለት የንግድ ሚ/ር በቁጥር ድ-አ.000171/7780 በ05/07/95 በተፃፈ ደብዳቤ የአስመጭነት የውጭ ንግድ ሥራ ፈቃድ፣ ከክልል የንግድ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ቢሮ የችርቻሮ ንግድ ስራ ፈቃድ ያለው፣ በተለይም በዓለም አቀፍ የአየር ማረፊያ ተርሚናል ውስጥ የኢትዮጵያ ሲቪል አቬዬሽን ባለስልጣን ከመደበው የቀረጥ ነጻ መሸጫ መደብር ውስጥ ሱቅ ለማግኘት የቻለ የንግድ ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው መሆኑ ታውቆ በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም በሚል ባስተላለፈው ትዕዛዝ መሰረት የተፈጸመ መሆኑ፤

- በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል የሚያስችል ፈቃድ ማውጣትና በወቅቱ ማሳደስ ያለባቸው ቢሆንም በቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማራው አልፋራጅ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በአዲስ አበባ ኤርፖርት ተርሚናል ቁጥር አንድ እና ሁለት ውስጥ ላሉት ሁለት ሱቆቹ በውጭ ምንዛሪ ለመገበያየት የሚያስችል ፈቃድ ሳይኖረው፤ በፈቃድ ሰጪና ተቆጣጣሪ አካላትም (የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መስሪያ ቤት) ፈቃድ ያለው ስለመሆኑ ሳያረጋግጡ ከ10 ዓመት በላይ እየሰራ የሚገኝ መሆኑ፣
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ የግል ድርጅቶች በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል የሚያስችል ፈቃድ ለመስጠት የሚፈቅድ ህግ አለመኖሩን በመግለጽ ፈቃድ መስጠት እንደማይችል በደብዳቤ ያሳወቀ ቢሆንም፣ ከኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለስልጣን በተደጋጋሚ በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት ከብሄራዊ ባንክ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖራቸው በውጭ ምንዛሪ ግብይት የሚፈፅሙ መሆኑ፤
- በሌላ በኩል ጥቅምት 20/2002ዓ.ም. በአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት አስተዳደር ከአ/አ ቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት አስተዳደር፣ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ ከአዲስ አበባ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ከኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት በመሆን ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል የሚያስችል ፈቃድ ሳይኖራቸው በወጪ መንገደኞች አዳራሽ እየተፈፀመ ያለውን ህገ - ወጥ የግብይት ስርዓት አስመልክቶ በተደረገ ውይይት፤

- o የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጉዳዩ የሚመለከተው መ/ቤት በመሆኑ፣ የቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት ፈቃድ ሳይኖራቸው በውጭ ምንዛሪ የሚቀበሉ ነጋዴዎች ላይ ቁጥጥር እንዲያደርግ፤
- o ሕጋዊ ፈቃድ ኖሯቸው የሚሰሩ ድርጅቶች ከሽያጭ የሚያገኙትን የውጭ ምንዛሪ እዛው በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ገቢ እንዲያደርጉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለመደብሮቹ ትእዛዝ እንዲያስተላልፍ፤
- o በመንገደኞች አዳራሽ ውስጥ አብዛኛው ግብይት የሚፈጸመው በትራንዚት መንገደኞች በመሆኑ ከግብይት የሚገኘውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በቀላሉ ለመቆጣጠርና ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ገቢ ለማሳደግ እንዲቻል በወጪ መንገደኞች አዳራሽ ውስጥ የሚገኙ የመሸጫ መደብሮች በሙሉ ወደ ቀረጥና ታክስ ነጻ አገልግሎት መስጫ እንዲቀየሩ፤
- ▪ ውሳኔ የተላለፈ ቢሆንም እድሉን በአንድ አጋጣሚ ካገኙት ሶስት የግል ድርጅቶች በቀር በዘርፉ ለመሰማራት የሚፈልጉ አካላትን አለማሳተፉ፤ ውሳኔውም የህግ መሰረት የሌለው መሆኑ፤

- በሁለቱም ተርሚናሎች ውስጥ በሚገኙት የወጪ መንገደኞች አዳራሾች ሁለት አይነት የንግድ አሰራር መኖሩና (ከቀረጥና ታክስ ነጻ እና ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው የሚሸጡ ዕቃዎች ንግድ)ተገቢ ያልሆነ (ህገ-ወጥ) ግብይት እንዲካሄድ ምቹ ሁኔታ መኖሩ ስለታመነበት በባለድርሻ አካላት (የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን) ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችል ተገቢው የግብይይት ስርዓት እንዲዘረጋ ጥናት ቢደረግም ተገቢው የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት በተቀናጀ ሁኔታ ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤
- በዚሁ አዳራሽ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ያልሆኑ አካላትን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ጋር የኪራይ ውል ሲፈጽሙ በሀገሪቱ ገንዘብ ለመገበያየት ሲሆን፣ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳይኖራቸው በውጭ ምንዛሪ የሚገበያዩ መሆኑ፤
- በኤርፖርት ውስጥ በግለሰቦች የውጭ ሀገር ገንዘቦች ግዢ እና ሽያጭ እንደሚፈጸም በተለያየ ጊዜ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ

ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በተደረጉ ጥናቶች የተመለከተ ሲሆን ከመስሪያ ቤታችን ለስራው ወጪ ባደረግነው ገንዘብ አንድ የአሜሪካን ዶላር በ23 የኢትዮጵያ ብር የሚመነዘር መሆኑን ለማረጋገጥ መቻሉ፤

- ሰው እና ጭነት የሚያጓጉዙ የአለም አቀፍ የአየር መንገድ ድርጅቶች እና እቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነጻ ለመሸጥ የተቋቋሙ አካላት የግል ዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ መጋዘን ማቋቋም እና የግል ዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ ማውጣት ያለባቸው መሆኑ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የተመለከተ ቢሆንም የኢትዮጵያ አየር መንገድ የአዋጁ ድንጋጌዎች የሚመለከተው ሆኖ ሳለ፣ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ዕቃዎችን በማስገባት በአየር ላይ (በበረራ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ እና ለሽያጭ የሚቀርቡ ዕቃዎች) ለሚያከማችበት ቦንድድ መጋዘን የጉምሩክ ፈቃድ አለማውጣቱ፤
- ከቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ለተሰማሩ የግል ድርጅቶች የግል ዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ለቁጥጥርና ክትትል አመቺ መሆኑ ሳይረጋገጥ ፈቃድ ተሰጥቶ መገኘቱ፣
- ከ1995 እሰከ ሀምሌ 2002 ዓ.ም ድረስ የግል የቀረጥ ነጻ ንግድ ድርጅቶች የሚጠቀሙበት የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘናቸው በከተማ ውስጥ የነበሩ በመሆኑ እቃዎችን ከመጋዘን በመውጣት ህጋዊ ንግድ ላይ ከፍተኛ ተጽኖ በማሳደሩ ሐምሌ 05/2002 ዓ.ም በቁጥር 50/4/1 በተጻፈ ደብዳቤ በ10 ቀናት ውስጥ ወደ ኤርፖርት ክልል እንዲገባ መወሰኑ፤
- ለግል ድርጅቶቹ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ ሲሰጥ መጋዘኖቹ ያሉበት አካባቢ ለክትትል እና ቁጥጥር አመቺ መሆኑ ሳይረጋገጥ፣ ለክትትልና ቁጥጥር ስራ ተገቢው የሰው ሀይል ሳይመደብ የክትተትልና ቁጥጥር ተግባርን የሚያከናውኑ ሰዎች ምን እንደሚሰሩ የሚገልጽ የስራ መዘርዝር እና እንዴት እንደሚሰሩ የሚገልጽ ማኑዋል ሳይዘጋጅ መሆኑ፤
- ለግል ድርጅቶቹ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ለክትትልና ቁጥጥር አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች ያልተለዩ መሆናቸውን እና በተጨማሪም መጋዘኖቻቸውም ወደ ኤርፖርት ክልል እንዲገቡ ሲወሰን፣ የተዘጋጁ መጋዘኖች ባለመኖራቸው እራሳቸው ኮንቴነር አዘጋጅተው ዕቃዎቻቸውን እንዲያከማቹ በመደረጉ በሙቀት ለብልሽት የተዳረጉ መሆኑ፤

- በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እየተገነባ ያለው መጋዘን ባለበት ሁኔታ ተጠናቅቆ ስራ የሚጀምር ከሆነ በመንገድ ዳር ስለሚገኝ እና አጥር የሌለው በመሆኑ ለቁጥጥር አመቺ አለመሆኑ፣
- የጉምሩክ መጋዘን የስራ ፈቃድ አሰጣጥን ለመወሰን በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 24/1990 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 መሰረት የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ በየበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ከሐምሌ 1 እስከ 30 ባለው ጊዜ ውስጥ ተገቢውን ክፍያ በመፈፀም ሊታደስ እንደሚገባ፤ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ፈቃዱን ያላሳደሰ ድርጅት ደግሞ ከነሐሴ 1 እስከ ነሐሴ 30 ባለው ጊዜ የማሳደሻውን ክፍያ 100% ቅጣት በመክፈል ማሳደስ እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም፣ ሦስቱም የግል ድርጅቶች ከነሐሴ 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃዳቸውን አለማሳደሳቸው፤
- ስለጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የአፈጻጸም በወጣው መመሪያ ላይ ዓለም አቀፍ የአየር መንገዶች፣ እቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲሸጡ የተፈቀደላቸው ድርጅቶችና ሌሎች ከባለስልጣኑ በተሰጠ ፈቃድ መሰረት የሚቋቋሙ የግል የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘኖች አራተኛ ደረጃ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን እንደሚሆን ቢገለፅም
  - ለግል ድርጅቶቹ ፈቃድ የተሰጠበት መስፈርት አለመታወቁ
  - ከመመርያው ውጪ የተለያየ ደረጃ መሰጠቱ
  - የተለያየ ደረጃ ለተሰጣቸው መጋዘኖች አንድ አይነት ክፍያ የሚያስከፍል መሆኑ፤
- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 ላይ የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ማውጫ እና ማሳደሻ ክፍያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ እንደሚወሰን የተገለጸ ቢሆንም ደንብ አለመውጣቱ
- ደንቡ ባለመውጣቱም ከጉሙሩክ መጋዘን ፍቃድ እና እድሳት የሚሰበሰበው ገቢ በ1990ዓ.ም በወጣው ደንብ ቁጥር 24/1990 መሰረት በመሆኑ ባለፉት 3 ዓመታት ማሻሻያ ሳይደረግበት ለመጋዘን ፈቃድ ማውጫ የሚከፈለው ብር 1,250.00 እና ፈቃድ ለማሳደሻ ብር 500.00 ብቻ ሆኖ እንዲቀጥል መደረጉ ፤
- የጉምሩክ መጋዘን የስራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 24/1990 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ-ረ መሰረት በጥንቃቄ

ጉድለት በእቃዎች ላይ ጉዳት ማድረስ፣ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ያልተፈጸመባቸው ዕቃዎች ወደ ባለስልጣኑ መጋዘን በወቅቱ አለማስተላለፍና ሪፖርት አለማድረግ እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያት ለባለስልጠኑ ሹሞች ቀና አገልግሎት አለመስጠት፣ ወይም እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ድርጊቶችን መፈጸሙ ሲረጋገጥ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጣቸውና ፍቃድ የሚሰረዝባቸው መሆኑ ቢገለፅም የኢትዮጵያ አየር መንገድ በተደጋጋሚ ከላይ የተገለጹትን ድንጋጌዎች ሲጥስ ምንም አይነት ማስጠንቀቂያ አለመሰጠቱ እና እርምጃም አለመወሰዱ፤

- የጉምሩክ መጋዘን የስራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣ ደንብ ቁጥር 24/1990 መሰረት ወደ መጋዘን በገቡ እቃዎች ላይ ስርቆት የተፈጸመ ከሆነ የመጋዘን ፈቃድ መሰረዝ እንዳለበት የተመለከተ ቢሆንም የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚያንቀሳቅሰውን ዕቃ የሚያከማችበት መጋዘን ላይ በተደጋጋሚ ስርቆት ቢፈጸምበትም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ አለመሰጠቱ እና አለመቀጣቱ፤
- ከቀረጥና ታክስ ነፃ ዕቃዎች ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ ከመግባታቸው በፊት የዕቃዎቹ ዝርዝር መረጃ (ዓይነትና ብዛት) በጉምሩክ ተጠናቅሮ የማይያዝ መሆኑ ፣
- የአሲኩዳ ሲስተም (ጉምሩክ የሚጠቀምበት የኮምፒዩተር ፕሮግራም) ከተወሰኑ ዕቃዎች በቀር ስለማይጠይቅ የእቃ መጠን ወደ ሲስተሙ ለማስገባት የዕቃዎቹ ዝርዝር መረጃ (ዓይነትና ብዛት) ወደ ሲስተም ለማስገባት የማያስችል ከመሆኑ በተጨማሪ መረጃው በሌላ መንገድ(በመዝገብ፣ በኮምፒዩተር...) እንዲያዝ አለመደረጉ፤
- ከቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ዕቃዎችን ወደ ሀገር በሚያስገቡበት ጊዜ መረጃው የ S መለያ ቁጥር ተሰጥቶት ወደ ASYCUDA (Automated System for Customs Data Analysis) ሲስተም የሚመዘገብ ሲሆን አስር የተለያዩ ዕቃዎች በአንድ ጊዜ አንድ ላይ ቢመጡ ከአስሩ ከፍተኛ የታሪፍ መጠን ባለው በአንዱ የታሪፍ ኮድ ላይ እንዲመደብ የሚደረግ መሆኑ፤
- የጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የአፈጻጸም መመሪያ 40/2002 ገጽ 6 ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባ ዕቃ የሚመዘገብበት መዝገብ እና ኮምፒውተር የመዝገብ ገጽ እና መለያ ቁጥር፣ የዕቃውን ባለቤትና ወኪል ስም፣

ዲክላራሲዮን ቁጥር ወይም የአየር ማጓጓዣ ሰነድ፣ ወደ መጋዘን ገቢ የሆነው ጠቅላላ የጥቅል ብዛት እና የመጠቅለያው ዓይነት፣ የዕቃዎቹ ስያሜ ከጥቅል ብዛታቸው ጭምር፣ ዕቃው ወደ መጋዘን የገባበትና ከመጋዘን የወጣበት ቀን እና የአስረካቢ እና የተረካቢ ስምና ፊርማ መያዝ እንዳለበት የሚያዝ ሲሆን በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መስሪያ ቤት፤ የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ፈቃድ ከተሰጣቸው ጊዜ ጀምሮ ማስረጃዎችን በተሟላ ሁኔታ የማይይዙ መሆኑ፤

- በአየር ማረፊያ ውስጥ ዕቃው ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ ሲገባ ሰነድ ተቀብሎ መፈተሽ፣ የፍተሻ ውጤት ከዲክላራሲዮን አባሪ ሰነዶች ጋር ማመሳከር፣ የፍተሻ ውጤቱ ልዩነት ካለው ለህግ ማስከበር ማስተላለፍ፣ የፍተሻ ውጤቱ ልዩነት ከሌለው መተማመኛ በመፈራረም አንድ ቅጅ ለቀረጥ ነፃ ሱቅ በመስጠት ፋይል ሊደረግ ሲገባ የእቃዎች ፍተሻ ውጤት ከዲክላራሲዮን አባሪ ሰነዶች ጋር ሲመሳከር የሚታዩ ልዩነቶች (ሲጎድል) በሰነዱ ጀርባ ላይ ከመመዝገብ በቀር ለየትኛውም አካል (ለህግ ማስከበርም ሆነ ለስራ ሂደቱ) ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፣
- ይህ ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣ ሲሆን ከ10 ዓመት በላይ የችግሩን መንስኤ በመለየት ለመፍታት ምንም የተሰራ ስራ አለመኖሩ፤
- በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶች ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቧቸውን ጊዜ ያለፈባቸው፤በጉዞ ወቅት መጠነኛ ጉዳት የደረሰባቸው እና ረዥም አመታትን ያስቆጠሩ ዕቃዎች አወጋገድን በተመለከተ የአፈፃፀም መመሪያ እና ለማስወገድ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች ሳይወገዱ ረዥም ጊዜ በሱቅ(በመጋዘን) ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ጊዜ ያለፈባቸው እና በጉዞ ላይ ጉዳት የደረሰበቸው ከቀረጥና ታክስ ነጻ ያስገባቸውን ዕቃዎችን ለተቆጣጣሪው አካል (የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት) እንዲያውቀው ሳይደረግ ከአየር መንገዱ የበላይ ኃላፊ በሚሰጥ ማረጋገጫ ከአየር መንገዱ ሴኩሪቲ፣ ከውስጥ ኦዲት፣ እና ከቤዝ ሰርቪስ ተወካዮች በተገኙበት የሚያስወግድ መሆኑ፤

- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት የቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድን ስርዓት ባለው መንገድ ለመምራት የሚያስችል የሽያጭ አፈጻጸም ሥርዓት እና መመሪያ አለማዘጋጀቱ፤
- ለቀረጥ ነፃ ሱቆችና መብት ላላቸው ተጠቃሚዎች ከቀረጥ ነፃ ንግድ አሰራር ጋር በተገናኘ ያለባቸውን ኃላፊነትና ግዴታ በአግባቡ እንዲወጡ ለማስቻል የግንዛቤ ማስጨበጫ አለመሰጠቱ፤
- ፈቃድ ሰጪ አካላት የሆኑት የቀድሞ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቅንጅት በስራ ላይ ያሉ ህጎችን በመፈተሽ ተገቢውን ጥናት በማድረግ የቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች የሚያከናውኑትን የግብይት ሂደት ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት አለመቻላቸው፤
- በቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት የየቀኑ የዕቃ ሽያጭ ደረሰኝ ቅጅ እና ሪፖርት ለጉምሩክ ማቅረብ፤ የሚቀርበው ሪፖርት ትክክለኛነትም በክፍሉ እና በታክስ ኦዲት ድንገተኛ ኦዲት (surprise Audit) ሊደረግበት የሚገባ ሲሆን የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአየር ላይ ለሚፈጸም ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሽያጭ ማስረጃ (የሽያጭ ደረሰኝ) ለተገልጋዮቹ የማይሰጥ የሽያጭ ሪፖርትም ለጉምሩክ የማያቀርብ መሆኑ፣
- የቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ያስገቧቸውን ዕቃዎች ለዓለም አቀፍ መንገደኞች ብቻ የሚሸጡ ስለመሆኑ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ከአጓጓዥ ድርጅቶች ስም ዝርዝር በመቀበል የማያረጋግጥ መሆኑ፤
- በቀድሞው የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና በኢትዮጵያ አየር መንገድ መካከል ሚያዝያ 1995 ዓ.ም. የተፈጸመ የመግባቢያ ሰነድ መሰረት፡-
    - o የአየር መንገዱ በበረራ ወቅት ጥቅም ላይ የሚያውላቸውና ከቀረጥ ነጻ የሚሸጣቸው ዕቃዎች በጉምሩክ ቁጥጥር እየተደረግባቸው ወደ ተዘጋጀላቸው መጋዘን እንዲገቡ፤
    - o መጋዘኑም በሁለት የተለያዩ ቁልፎች እንዲቆለፍ ተደርጎ ሁለቱም መ/ቤቶች አንዳንድ ቁልፍ እንዲኖራቸው፤
    - o አየር መንገዱ ከላይ የተመለከቱትን ዕቃዎች ወደ መጋዘኑ እንደገቡ ወዲያውኑ ዲክለር እንዲያደርግ እንዲያሳውቅ፤

- o አየር መንገዱ በበረራ ወቅት ጥቅም ላይ ያዋላቸውንና ከቀረጥ ነፃ የሸጣቸውን ዕቃዎች በተመለከተ ለጉምሩክ በየጊዜው መግለጫ እንዲያቀርብ፣
- o በበረራ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉና ከቀረጥ ነጻ የሚሸጡ ዕቃዎች ወደ በረራ እንዲገቡ በሚዘጋጁበት ወቅት ጉምሩክ በቦታው በመገኘት ቁጥጥር እንዲያደርግ፣
- o በበረራ ወቅት ጥቅም ላይ ያልዋሉት እና በቀረጥ ነፃ የልተሸጡት ዕቃዎች በጉምሩክ ቁጥጥር እየተደረገባቸው ወደ መጋዘን እንዲመለሱ ስምምነት ላይ ቢደረስም፣

  የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገባቸው ዕቃዎች በባለስልጣኑ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግበት መሆኑ፤

  - በቀረጥ ነፃ ሱቅና መጋዘን ውስጥ ያሉ ዕቃዎች በሱቅ ወይም በመጋዘን ውስጥ በትክክል ስለመኖራቸው ቆጠራ በማድረግ ውጤቱን ከማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ በመብለጥና በማነስ የተገኙ ዕቃዎች ካሉ በሪፖርት መሰረት ተጣርቶ እርምጃ ሊወሰድበት ሲገባ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት በዘርፉ ከተሰማሩ አካላት በቀረጥ ነፃ መደብር እና መጋዘን ውስጥ ያሉ ዕቃዎች ቆጠራ የማይደረግ፣ ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ የገባ ዕቃ ለባለመብቶች ተሸጦ የቀረውን ዓይነትና መጠን በተመለከተ መረጃ የማይዝ፣ የዕቃዎች ቆጠራ ውጤት ከቀረበው ሪፖርት ጋር እየተመሳከረ ሪፖርት የማይዘጋጅ መሆኑ

የሚሉት በኦዲቱ ወቅት የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም ከለይ የተመለከቱትን ድክመቶች ለማሻሻል አስተዋጸ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻ ሀሳቦች ለገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት በላክነው ሪፖርት በማካተት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲያደርጋቸው አሳስበናል፡፡

6.5. በትምህርት ሚኒስቴር በመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የሚታዩ የሥነ-ምግባር ችግሮች እንዲሁም የሚገጥሟቸው ተቋማዊ እና አካባቢያዊ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን በተመለከተ

- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ለሚገኙ መምህራንና ተማሪዎች የሥነ-ምግባር ደንብና የዲሲፕሊን መመሪያ ሊዘጋጅ፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጥበት እና ስለተግባራዊነቱም ክትትል ሊደረግበት ሲገባ በናሙና በታዩት በዲላ፣ በሀዋሳ፣ በጎንደርና በባህር-ዳር ዩኒቨርስቲዎች የመምህራን የሥነ-ምግባር ደንብ የሌላቸው ሲሆን የተማሪዎች ደንብና መመሪያ ቢኖርም የግንዛቤውን ማስጨበጫ ያላገኙ ተማሪዎች በመኖራቸው መመርያው በትክክል እየተተገበረ አለመሆኑ፣
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የዲላ፣ የሐዋሳ፣ የጎንደርና የባህር-ዳር ዩኒቨርስ ካምፓሶች በተሰበሰበው መረጃ ሰዓት መሰረት አርፍደው ክፍል የሚገቡና የሚቀሩ፣ ፈተና ላይ አይመጣም በማለት ከተማሪው ጋር ተስማምተው የሴሚስተሩን ኮርስ ሳያጠናቅቁ ፈተና የሚሰጡ፣ በወቅቱ በስራ ገበታቸው ላይ ሳይገኙ ቀርተው የፈተና ወቅት ሲደርስ በአጭር ጊዜ ኮርሱን አጠናቀው ፈተና የሚሰጡ፣ የተማሪውን የፈተና ውጤት በወቅቱ የማያሳውቁ፣ (በተለይ ተማሪዎቹ የመጨረሻ ውጤታቸውን የሚያዩት ከእረፍት ሲመለሱ መሆኑ) ተማሪው በትምህርት ገበታው ላይ መገኘቱን የማያረጋግጡ (Class Atendance የማይዙ)፣ ፈተናን እንደ መቅጫ መሳሪያ የሚጠቀሙና ውጤት አሰጣጣቸው አድሎአዊ የሆነ እንዲሁም ለውጤት አሰጣጥ ለሴት ተማሪዎች የወሲብ ጥያቄን እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚያቀርቡ መምህራን መኖራቸው፣
- በናሙና በታዩ የዲላ፣ የሐዋሳ፣ የጎንደርና የባህር-ዳር ዩኒቨርስቲዎች ካምፓሶች ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ የሚሰጠው የማጠናከሪያ ትምህርት (ቱቶሪያል ክላስ) አሰጣጥ በሞጁል ያልተደገፈና መምህራን ባመቻቸው መልኩ የሚያስተምሩት መሆኑ፣
- ለማጠናከሪያ ትምህርት ተብሎ የወጣ ቋሚ ክፍለ ጊዜ ባለመኖሩ ፈተና ሊደርስ አካባቢ የሚሰጥ በመሆኑ መሰረታዊ እውቀት ከማስጨበጥ ይልቅ ፈተና ማለፍን መሰረት ያደረገ እና በተማሪዎች ጭምር የሚሰጥ መሆኑ፣

- በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የማጠናከሪያ ትምህርት የተሰጠው ለአንደኛ አመት ሴት ተማሪዎች ብቻ መሆኑ፣
- የማጠናከሪያ ትምህርት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ኮርሶችን በወቅቱ የመለየት ችግር መኖሩ፣
- የማጠናከሪያ ትምህርት ሲሰጥ የማይገኙ ተማሪዎች መኖራቸውና እንዲገኙ ለማድረግ ስለጠቀሜታው በቂ የግንዛቤ ማዳበሪያ ስራ አለመሰራቱ፣
- የማጠናከሪያ ትምህርቱን ለሚሰጡ መምህራን በቂ ማበረታቻ አለመኖሩ፣
- በናሙና ተመርጠው በታዩት በዲላ፣ በሀዋሳ፣ በጎንደርና በባህር-ዳር ዩኒቨርስቲዎች በሚገኙ ካምፓሶች የሚማሩ የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸው ተማሪዎችን ለመርዳት የሚሰጠው የኢኮኖሚ ድጋፍ የመመልመያ መስፈርት የሌለው ሲሆን፣ ድጋፉ የሚሰጠውም ለሴት ተማሪዎች ብቻ መሆኑ፣
- የኢኮኖሚ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ድጋፍ ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ የበጀት እጥረትና ፈንድ የማፈላለግ ችግር መኖሩ፣
- በናሙና በተመረጡ በዲላ፣ በሀዋሳ፣ በጎንደርና በባህር-ዳር በሚገኙ የዩኒቨርስቲው ካምፓሶች ተማሪዎች ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች ሲገጥማቸው የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ጾታን ያማከሉ፣ ለሥራው ብቃትና ፍላጎት ያላቸው፣ ለማማከር አገልግሎት ብቻ የተመደቡ የሥነ-ልቦና ማማከር ባለሙያዎች እና ጽፈት ቤ/ቶች የሉዋቸውም ወይም ደግሞ በሰው ሃይል እጥረት የሚቸገሩ መሆኑ
- በዲላ ዩኒቨርሲቲ በሶስቱም ካምፓሶች የሥነ-ልቦና ማማከር ባለሙያ አለመኖሩ፣
- በባህር-ዳር ዩኒቨረሲቲ በፖሊ ካምፓስ የሚገኘው ባለሙያ ለብቻው ቢሮ የሌለው በመሆኑ በተማሪዎች አገልግሎት ፅሐፊ ቢሮ ውስጥ ተደርቦ የሚሰራ በመሆኑ አገልግሎቱን ለማግኘት የሚመጣ ተማሪ ሲኖር ሌላውን ሰራተኛ በማስወጣት እየሰራ የሚገኝ መሆኑ፣
- በጎንደር ዩኒቨርሲቲ በማራኪ ካምፓስ ከምትገኘው አንድ የሥነ-ልቦና አማካሪ ባለሙያ በስተቀር በኦዲቱ በታዩት በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች ሴት አማካሪ ባሙያዎች አለመኖራቸው፣
- የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎችን ለሴትኛ አዳሪነት ተግባር አሳልፈው የሚሰጡ ደላሎች (ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች አካላት) በተማሪዎች

ጠቋሚነት እንዲጋለጡ ለጠቋሚዎቹ ማበረታቻ መስጠትና በደላሎቹም ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ የማይደረግ በመሆኑ በናሙና በታዩት በአራቱም ዩኒቨርስቲዎች ካምፓሶች ሴት ተማሪዎችን ለሴትኛ አዳሪነት ተግባር አሳልፈው የሚሰጡ ደላሎች (ተማሪዎች፣ የግቢው ማህበረሰብና የውጭ አካላት) መኖራቸው፣

- በዲላ፣ ሐዋሳና ጎንደር ዩኒቨርስቲዎች የተማሪዎች ስነ-ምግባር ጉዳይ የሚመለከታቸው የሥርዓተ-ጾታ፣ የሥነ-ምግባር፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤቶች፣ ፕሮክተሮችና የጥበቃ ሰራተኞች በቅንጅት የሚሰሩበት መድረክ አለመኖሩ፣ የየዩኒቨርስቲው ሥራ አመራሮችም የሥራ አፈጻጸማቸውን በመገምገም በተገኙ ክፍተቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ የማይወስዱ መሆኑ፣
- የሴትና የወንድ ተማሪዎች መኖሪያ/ዶርም/ የተራራቀ ወይም በአጥር የተከለለ ወይም ጥበቃ የሚደረግለት፤ተማሪዎቹ ለሥነ-ምግባር ችግር እንዳይጋለጡ የዩኒቨርስቲዎቹ ቅጥር ግቢ አጥር ሊኖረው እና በምሽት ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ቦታዎች ሁሉም የኤሌክትሪክ ብርሃን ሊኖራቸው ሲገባ፣
    - በዲላ የዋናውና በጎንደር የማራኪና የቴዎድሮስ ካምፓሶች የሴትና የወንድ ተማሪዎች መኖሪያ (ዶርም) የተቀራረበ፣ (በግምት አስር ሜትር ርቀት ያለው) በአጥር ያልተከለለና ጥበቃም የሌለባቸው (የማይደረግ) መሆኑ
    - በዲላ ዋናውና አዲሱ ካምፓስ፣ በሀዋሳ ዋናው ካምፓስ፣ በጎንደር ማራኪ፣ ቴዎድሮስና አጼ-ፋሲል ካምፓስ፣ በባህር-ዳር ዋናውና ኤፍ. ቢ.ኢ. ካምፓስ ከፊት ለፊት በስተቀር ዙሪያውን አጥር የሌላቸው መሆኑ፣
    - በጎንደር ብሪጅ ኦፍ ሆፕ የሚባል ድርጅት በቴዎድሮስ እና በአጼ-ፋሲል ካምፓስ መካከል በመገኘቱና የግለሰቦችም መኖሪያ ቤቶች በመኖራቸው ምክንያት ከተቋሙ ማህበረሰብ ውጪ ያሉ ሌሎች ሰዎች ግቢውን እያቋረጡ የሚያልፉ መሆኑ፤
    - በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች ተዘዋውረን ባየናቸው ካምፓሶች ውስጥ በምሽት መብራት የሌላቸው ጨለማ ቦታዎች መኖራቸው፣
    - በባህር-ዳር የዘንዘልማ ካምፓስ የሴቶች ዶርም ላይ የተመደቡት ፕሮክተሮች ወንዶች መሆናቸው፣

- ዩኒቨርስቲዎች በአካባቢያቸው የጫት፣ የሺሻ፣ የመጠጥ፣ የጭፈራ እና የመሳሰሉት ቤቶች እንዳይኖሩ ለማድረግ ከከተማ መስተዳድሮች፣ ከፖሊስ አካላት፣ ከማዘጋጃ ቤቶችና ክፍለ ከተሞች ጋር በቅንጅት የሚሰራበት መድረክ ባለመፈጠሩ በዲላ ዩኒቨርሲቲ በአዲሱ ካምፓስ በሀዋሳ ዩንቨርሲቲ ዋናውና የጤና ሳይንስ ካምፓስ፣ በጎንደር ቴዎድሮስና ማራኪ ካምፓስ በባህር-ዳር በዋናው ካምፓስ አካባቢ የጫት፣ የሺሻ፣ እና የመጠጥ ቤቶች እንዲሁም በባህር-ዳር በዘንዘልማና በሀዋሳ በዋናው ካምፓሶች አካባቢ የጫት እርሻዎች መኖራቸው፣

የሚሉት በኦዲቱ ወቅት የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም ከለይ የተመለከቱትን ድክመቶች ለማሻሻል አስተዋጾ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻ ሀሳቦች ለትምህርት ሚኒተሰቴር በላክነው ሪፖርት በማካተት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲያደርጋቸው አሳስበናል፡፡

6.6. በሳይንስ እናቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት

- የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ኘሮጀክት ከ1990 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም ውስጥ የቆላ ዝንብን ከ 25,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ ነፃ ለማድረግ በእቅድ የተያዘ ፕሮጀክት ቢሆንም ከ13 ዓመታት በኋላ የተሰራው በ6,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ ብቻ መሆኑ፣
- በወላይታ ሶዶ እና በዲላ የፕሮጀክቱ ጣቢያዎች የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ከመቀነስ ባሻገር ነፃ የሆነ አካባቢ አለመኖሩ፣ በአርባምንጭ ነፃ የሆነ አካባቢ ቢኖርም የዝንቡ መጠን ካልቀነሰበት ቦታ ለሚፈልሱ ዝንቦች መከላከያ /Barrier/ ተሰርቶ የመቆጣጠር ስራ ባለመሠራቱ ከቆላ ዝንብ ነፃ ሆኗል ለማለት እንደማይቻል በየጣቢያዎቹ ባሉ ባለሙያዎች መገለፁ፣
- ጠንካራ የማኔጅመንት ክትትል ወቅቱን ጠብቆ አለመከናወን፣ በስራ (በትግበራ ወቅት) ያጋጠሙ ችግሮች በሚገባ አለመገለጻቸው፣ የኬሚካሎችና የታርጌቶች (በኬሚካል ተነክሮ ለዝንቦች መከላከያ በዛፍ ላይ የሚሰቀል ጨርቅ) ግዢዎች መዘግየት፣ የሰው ኃይል (የባለሙያ) እጥረት፣ የማቴሪያሎች አለመሟላት ፕሮጀክቱ ባለፉት አስርት አመታት ውስጥ አላማውን እንዳይመታ ካደረጉት ነገሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ መሆናቸው፣

- በ2002 ዓ.ም እና በ2003 ዓ.ም እንስሳት በማይገቡበት አካባቢ መሬት ለመሬትና በአውሮኘላን የኬሚካል እርጭት ለማከናወን በዕቅድ ቢያዝም፤ እስከ የካቲት 2004 ዓ.ም ድረስ ስራው አለመከናወኑ፤
- ከ1990 እስከ 2003 ዓ.ም. ድረስ ባሉት 13 ዓመታት ውስጥ ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ ከመንግስት ብር 129,518,497 የተመደበለት ቢሆንም በሥራ ላይ የዋለው ብር 72,674,931(43.11) ብቻ በመሆኑ ብር 56,843,566 (43%) በጥቅም ላይ አለማዋሉ፤
- ለዕርባታ ማዕከሉና ለመስክ ስራ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣ መድኃኒቶች እና ኬሚካሎች (በፕሮጀክት ማዕከሉ ለዝንቦች እርባታ ክፍል እና ለላቦራቶሪ እንዲሁም ለጨረር ስራ የሚያገለግል) ግዢ በተያዘላቸው ዕቅድ መሰረት አለመከናወኑ፣
- በፕሮጀክቱ የግዢ ሂደታቸው ከተጀመረ ሁለት አመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ለላቦራቶሪ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች፤ ከተጠየቁ ስድስት ወር ያለፋቸው ለመስክ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ማቴሪያሎች ግዢያቸው አለመፈፀሙ፣
- የቆላ ዝንቦች ማምከኛ እና ደምን ከባክቴሪያ ለማፅዳት የሚያገለግል የጨረር (Industrial radiateor Gama ray) መሳሪያ ግዢ የተፈፀመ ቢሆንም ለኢንዱስትሪያል ራዲያተር የሚያስፈልገው ክፍል ግንባታ ስራ ባለመሰራቱ ዕቃው አገልግሎት መስጠት አለመጀመሩ፤ ያልገባ መሆኑ፣ ፡
- በፕሮጀክት ማዕከሉ የንብረት ክፍል(መጋዘን) ውስጥ የተለያዩ ዕቃዎች (በካርቶን የተቀመጡ ማይክሮስኮፖች፣ የታርጌት ጨርቶች …) በተዘበራረቀና ዕቃዎችን ፈልጎ ለማውጣት በማይመች መልኩ መሬት ላይ መቀመጣቸው፣
- አንዳንድ ዕቃዎች ሳይለዩ በካርቶን እንደታሸጉ ለብዙ ጊዜ ያለአገልግሎት መቀመጣቸው፣
- በመስክ ጣቢያዎችም በንብረት ክፍል ጥበት ምክንያት ንብረቶች በተጨናነቀ ሁኔታ ኬሚካሎችና የተለያዩ መድኃኒቶች ከተለያዩ ንብረቶች ጋር ተቀላቅለው መቀመጣቸው፣
- በዲላ ኬሚካሎች ከነ ካርቶናቸው በቢሮ ውስጥ የተቀመጡ ሲሆን፣ ሌሎች ንብረቶች ደግሞ በውጪ/በኮርደር/ ላይ ተቀምጠው መታየታቸው፣

- ወረዳዎች ኬሚካሎችን ከጣቢያዎች በሞዴል 22 ወጪ በማድረግ የሚረከቡ ቢሆንም እራሳቸው ግን ገቢና ወጪ የሚያደርጉት በሞዴል 19 እና 22 ሳይሆን ተከታታይ ቁጥር በሌላቸው ቅጾች መሆኑ፣
- በኦዲቱ ወቅት በታዩት በ3ቱም ጣቢያዎች አገልግሎት ላይ የዋሉ የኬሚካል ዕቃዎች አወጋገድን በተመለከተ ወጥ የሆነ መመሪያ ባለመኖሩ እቃዎቹን አርብቶአደሩ ለሌላ አገልግሎት እንዳያውላቸው በማለት ቆራርጠው በማቃጠል የሚያስወግዱ መሆኑ፣
- በቆላ ዝንብ አካባቢ የሚኖሩ በስራው ላይ ተሳታፊ የሆኑ ብቃት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመምረጥ የሚያገለግል ወጥ የሆነ የመምረጫ መስፈርት ባለመኖሩ ጣቢያዎች እራሳቸው ባስቀመጡት መስፈርት የሚመርጡ መሆኑ፣
- በብልሽት ምክኒያት ከሁለት ዓመታትና ከዚያ በላይ የቆሙ ሁለት መኪኖች እና አምስት ሞተር ብስክሌቶች መኖራቸው፣
- በማዕከሉ ለሚረቡ ዝንቦች የሚያገለግሉ ማቴሪያሎች ሳይሟሉ የእርባታ ስራን መጀመር/መስራት/ የማይቻል መሆኑ እየታወቀ እንደ ሴንሴቲቭ ባላንስ፣ ዲስትለር፣ ፔትሪዲሽ፣ አውቶ ክሌቭ፣ ቴርሞሜትር፣ አልኮል የመሳሰሉት እና ለመስክ ስራ የሚያገለግሉ እንደ ማይክሮስኮፕ፣ ኦፕልኬተር(ኬሚካል ለመርጨት የሚያገለግል) የመሳሰሉት ግብዓቶች እጥረት መኖሩ፣
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት ክፍል/መጋዘን/ እና በእርባታ ክፍል ውስጥ ከተገዙ አምስት አመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ነገርግን ምንም አይነት አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ አምስት ኦቨኖች፣ ሁለት የሙቀት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች (cold room)፣ አምስት ማይሮስኮፖች፣ አንድ የትሪ ማጠቢያ ማሽን (Sterilizer)፣ አንድ የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር መኖራቸው፣
- እነዚህ ንብረቶች በተለያዩ የስራ ክፍሎች እና በፕሮጀክቱ ጣቢያዎች የሚፈለጉ በመሆኑ በተለያዩ የስራ ክፍሎች ተጠይቀው ሳይሟሉላቸው ለረጅም ጊዜ የቆዩ ቢሆንም በንብረት ክፍል እያሉ ለስራ ክፍሎች እንዲሰራጩ አለመደረጉ፣
- ለውሃ ማጠራቀሚያ አገልግሎት ተብሎ ከተገዛ አንድ ዓመት ያስቆጠረ የውሃ ማጠራቀሚያ በመውጫ ስብሰባ ወቅት አገልግሎት እንዲሰጥ

ተደርጓል ቢባልም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አገልግሎት መስጠት አለመጀመሩ፣

- የዕርባታ ማዕከል ውስጥ የሚገኘው የትሪ ማጠቢያ አጠቃቀሙ ባለመታወቁ ምክንያት አገልግሎት ላይ ማዋል እንዳልተቻለ እና ሌሎች ተበላሽተው አገልግሎት መስጠት ያቆሙ እቃዎችን በተመለከተ ደግሞ ዕቃዎቹ ከውጪ በመምጣታቸው እንዴት ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉ የሚያውቅ የባለሞያ ባለመኖሩ ምክንያት እንደሆነ መገለጹ፣
- በፕሮጀክቱ ጣቢያዎች በወላይታ ሶዶ፣ በአርባ ምንጭ እና በዲላ ከላይ የተዘረዘሩ እቃዎች አለመሟላት እና በመሳሪያ እጥረት ምክንያት በገንዲ በሽታ ለተጠቁ ከብቶች በበቂ ሁኔታ ህክምና ለማድረግ አለመቻሉ፣
- በዝንብ እርባታ ክፍሎች ውስጥ ብዛት ያላቸው እቃዎች በእጅ የሚፀዱ ሲሆን በላቦራቶሪ ክፍልም ንፅህናውን የጠበቀ ደም ለዝንቦች መቅረቡ የሚረጋገጠው በተወሰኑ ዝንቦች ላይ ሙከራ በማድረግ እንጂ የቀረበው ደም ሙሉለሙሉ የተጣራ መሆንን ለማረጋገጥ በሚያስችል ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ መሳሪያ አለመሆኑ፣
- የእቃዎች እጥረት መኖሩ ስራን እቃዎችን በመዋዋስ እንዲፈጸሙ በማድረጉ የስራ መዘግየትን የሚያስከትል መሆኑ፣
- በፕሮጀክት ማዕከሉ ለቆላ ዝንብ ዕርባታ ከተሰሩት 7 ክፍሎች ውስጥ ስራ የጀመሩት ሁለቱ ብቻ ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ አንደኛው ክፍል ማርባት ከሚችለው አቅም በታች እየሰራ መሆኑ፣
- እንስሳት በማይገቡበት አካባቢ መሬት ለመሬትና በአውሮፕላን የኬሚካል ርጭት ለማከናወን የሚያስችል ረቂቅ የአካባቢ ጥናት (Environmental risk analysis) ተደረገ ቢሆንም በ2003 ዓ.ም. ለማድረግ በእቅድ ተይዞ የነበረው የርጭት ስራ ቀዳሚ መረጃ የማሰባሰብ እና የመስክ ጉብኝት እስከተደረገበት እስከ የካቲት 2004 ዓ.ም ድረስ ያልተጀመረ መሆኑ፣
- ፕሮጀክቱ በህብረተሰቡ እና በአካባቢው ላይ እያስከተለ ያውን ጉዳት እና እያሰገኘ ያለውን ጥቅም በተመለከተ በተወሰኑ ዓመታት ግምገማ በማከናወን አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ የሚገባ ቢሆንም በ1996 ዓ.ም. ብቻ ከተካሄደው ግምገማ በስተቀር በመርሃ ግብሩ መሰረት በየሶስት ዓመቱ የተደረገ ግምገማ አለመኖሩ፣

- የእንስሳት የኬሚካል ርጭትን በተመለከተ ክብደታቸው ትልቅ ለሆኑ ከብቶች እስከ 20 ሚ.ሊ ሊትር፣ ክብደታቸው ትንሽ ለሆኑ ከብቶች 10 ሚ.ሊ ሊትር እንዲቀባ፤ እንዲሁም የቆላ ዝንቦች በጥቁር ቀለም ስለሚሳቡ ቀለማቸው ጥቁር ለሆኑ ከብቶች በዛ ያለ ኬሚካል እንዲቀቡ መስፈርት ያስቀመጠ ቢሆንም፤ ክብደታቸው አነስተኛ ለሆኑ እና ክብደታቸው ትልቅ ለሆኑ ከብቶች ተመሳሳይ የኬሚካል መጠን መጠቀማቸው፣ ቀለማቸው ጥቁር ለሆኑ ከብቶች እና ጥቁር ቀለም ለሌላቸው ከብቶችም ተመሳሳይ መጠን የሚቀባ መሆኑ፣
- ከብቶችን ስርዓት ባለው መልኩ ለመቀባት የሚያስችል በረት ባለመዘጋጀቱ እና ያሉትም በረቶች በአካባቢው ካሉት የከብቶች ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆናቸው ከብቶችን አብዛኛው የመቀባቱ ስራ ከበረት ውጪ በማሯሯጥ የሚካሄድ በመሆኑ፣ የኬሚካል ብክነትን እያስከተለ መሆኑ፣
- የቆላ ዝንብ ባለባቸው አካባቢዎች የሚደረገው የኬሚካል እርጭት ወቅቱን የጠበቀ እና የጊዜ ገደብ ተቀምጦለት የሚከናወን አለመሆኑ፣
- በወላይታ ሶዶ፣ አርባምንጭና ዲላ ጣቢያዎች በቆላ ዝንብ የማጥፋት ስራ ላይ ለሚሳተፉ የማህበረሰብ አባላት እንስሳት ላይ የኬሚካል አቀባብ፣ ታርጌት ተከላ፣ የገንዲ በሽታ አመጣጥና አወጋገድ ላይ ስልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ እንደሚሰጥ ቢገለጽም ማስረጃ አለመኖሩ፣
- በታርጌት ተከላና በእንስሳት ጀርባ ላይ የኬሚካል መቀባትን በተመለከተ ለማህበረሰቡ ስልጠናዎች እና የግንዛቤ ማስጨበጫዎች የተሰጡ መሆኑ ቢገለጽም ተከታታይነት የሌለው በመሆኑና በተለያዩ ሚዲያዎችና መንገዶች ባለመሰጠቱ ምክንያት የዝንቡ መጠን ትንሽ ሲቀንስ ዝንቡ የጠፋ ስለሚመስላቸው ወይም መዘናጋት በመፈጠሩ ታርጌቶችን በደንብ አለመትከል ወይም ነቅሎ የመውሰድ ችግር መኖሩ፣
- በፕሮጀክት ማዕከሉ ለሚደረጉ የክትትልና ግምገማ ሥራ እንዲሁም የምርምር ጥናቶች በመነሻነት የሚያገለግል የመረጃ አያያዝ ስርዓት መኖር ያለበት ቢሆንም፣
    - በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በዝንብ እርባታ ክፍል ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት የተከሰተውን የዝንቦች መሞት አደጋ መንስኤ እና የተወሰዱ የመፍትሄ ርምጃዎችን፤ እንዲሁም በ2001 ለሙከራ የተለቀቁ ብዛታቸው 8,000

የሚሆኑ የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦች ያስገኙት ውጤትን በተመለከተ የተጠናቀረ መረጃ አለመያዙ፣

- የኘሮጀክት ማዕከሉ በተያዘለት 10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ዓላማውን ለማሳካት ያልቻለበትን ምክንያት የሚያስረዳ መረጃ/ሪፖርት/ አለመቅረቡ፣
- በየሩብ ዓመቱ የሚዘጋጁ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶች፣ በማዕከሉ ሀሙስ ሀሙስ የማራቢያ ክፍሉን በተመለከተ የሚደረግ የግምገማ ስብሰባ (ቃለጉባኤ) እና ሰኔ 2003 ዓ.ም. ስለኘሮጀክቱ ዓለም አቀፋዊ ወርክሾኘ የተደረገውን ስብሰባ የመሳሰሉት መረጃዎች ተጠናቅረው ባለመያዛቸው ለማቅረብ አለመቻሉ፣
- በወላይታ ሶዶ፣ በአርባምንጭ እና በዲላ የሚገኙት ጣቢያዎች እያንዳንዳቸው በስራቸው የሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ ያለውን የከብት ብዛት የሚገልጽ መረጃና ለልማት ጣቢያዎችና ለወረዳዎች የተሰጠውን ስልጠና ዓይነት፣ የሰለጠኑት ሰዎች ብዛት እና የመሳሰሉትን የሚገልጽ መረጃ አለመቅረቡ፣
- የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ስራውን በደቡብ ክልል ሲጀምር ከክልሉ የግብርና ቢሮ ጋር በቅንጅት መስራት የሚያስችለውን የስምምነት ሰነድ በክልሉ ርዕሰ መስተዳደር፤ በክልሉ የግብርና ቢሮ ኃላፊ እና በፕሮጀክቱ ጽ/ቤቱ ኃላፊ ተፈርሞ በወቅቱ ከነበረው የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ይሁንታን ያገኘ ቢሆንም የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በይበልጥ በቅንጅት መስራት ካለበት ከክልሉ ግብርና ቢሮ እና ከግብርና ሚኒስቴር ጋር መረጃዎችን የማይለዋወጥ መሆኑን፣
- ፕሮጀክቱ ሥራወን ከክልሉ ግብርና ቢሮ ጋር በቅንጅት ባለመስራቱ በ2003 ዓ.ም ዓመታዊ ሪፖርት መሰረት የክልሉ የግብርና ቢሮ ፕሮጀክቱ በሚንቀሳቀስበት አካባቢ ብቻ 450,000 በገንዲ በሽታ የተጠቁ ከብቶች ማከሙን በ2003 ዓመታዊ ሪፖረቱ የገለጸ ሲሆን የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ደግሞ በዚሁ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱ ላይ ለ97,625 እንስሳት የገንዲ በሽታ መድሐኒት ሕክምና መስጠቱን መግለጹ ከባለድረሻ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ክፍተት መኖሩን ከማሳየቱም በላይ ስራዉ በቅንጅት ቢሰራ ኖሮ ሊያስገኝ ይችል

የነበረው ጥቅም መታጣቱ፤ በኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም ከለይ የተመለከቱትን ድክመቶች ለማሻሻል አስተዋጸ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻ ሀሳቦች ለለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በላክነው ሪፖርት በማካተት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲያደርጋቸው አሳስበናል፡፡

6.7. በመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም፣ ክትትል እና ቁጥጥር ላይ የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት

- የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የነዳጅ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ለነዳጅ ግዥና አስተደደር ሥራ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ስለ መንግሥት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደር የቁጥጥር ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚያስችል ጥናት ሊያካሂዱ እንደሚገባ በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ የተመለከተ ቢሆንም በኦዲቱ ተመርጠው ከታዩ 11 መ/ቤቶች በ 9ኙ (በግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ በግብርና ሚ/ር፣ በማዕድን ሚኒስቴር፣ በግብርና ምርምር ኢንሲቲትዩት፣ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ የባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እና በኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን የደብረማርቆስ ዲስትሪክት) የበላይ ኃላፊዎች ነዳጅን በአግባቡ ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመጠቀም የሚያስችል ጥናት እንዲካሄድ እና ሥልጠና እንዲሰጥ አለመደረጉ፤
- የግብርና ሚ/ር በ1997 ዓ.ም. ባዘጋጀውን የተሽከርካሪ አጠቃቀም መመሪያ መሰረት የሚሰራ መሆኑ ቢገልጽም ወቅታዊ አለማደረጉ፤ የማዕድን ሚኒስቴር መ/ቤት ለውስጥ አሰራር እንዲያመች በመመሪያ ደረጃ ተዘጋጅቶና በበላይ አመራሩ የጸደቀውን ሠነድ መነሻ በማድረግ እየተጠቀመበት እንደሚገኝ ነገር ግን የሌሎችን መ/ቤቶች ልምድ በመውሰድ የተዘጋጀ ጥናታዊ ሠነድ የሌለው መሆኑ፤

- የመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም፡ የተሽከርካሪ ጥገናና አያያዝን ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት እስከ 2004 በጀት ዓመት መጨረሻ አለማውጣቱ፤
- በናሙና ተመርጠው ከታዩት 11 መ/ቤቶች በ10ሩ የተሽከርካሪዎች ጥገና እና የእንክብካቤ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፤
- የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ለተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚመደበው በጀት በዓመቱ የታቀደውን የመንግሥት ሥራ ለማከናወን በሚያስችል መልኩ በጥናት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ለማረጋገጥ በተደረገው ጥረት በ2002 እና በ2003 የበጀት ዓመታት በኦዲቱ ከተሸፈኑት 10 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በሶስቱ (በማዕድን ሚ/ር፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፤ በኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን በደብረ ማርቆስ ዲስትሪክት) ከ15 እስከ 38.69% አለመጠቀማቸው፤ የጤና ጥበቃ ሚ/ር ደግሞ በ2002 ዓ.ም. ከተያዘለት በጀት በላይ ብር 62,350.8 (7.68%) በጥቅም ላይ አውሎ መገኘቱ፤
- በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች የየሥራ ክፍሎችን የተሽከርካሪ ፍላጎት በማገናዘብ እንደ አስፈላጊነቱ በአንድ አቅጣጫ የሚጓዙ የሠራተኞችን በማቀናጀት ነዳጅን በቁጠባ መጠቀም በሚያስችል ሁኔታ በጥቅም ላይ እያዋሉ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ በናሙና ተመርጠው ከታዩ 11 መ/ቤቶች 8ቱ ለማቅረብ አለመቻላቸው፤
- በማዕድን ሚ/ር ከ2002 እስከ 2003 ዓ.ም. ያለው እና በማዕከላዊ እስታትስቲክስ የባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የስምሪት ሰነዶች ሙሉ በሙሉ አለመገኘታቸው፤ በግብርና ምርምር ማዕከል የጋራ ጉዞን የሚገልጽ መረጃ በስምሪት ክፍሉ የሚያዝ ቢሆንም በአንዱ የጉዞ ጠያቂ ስም ብቻ እየተመዘገበ የሚፈጸምና በሁለት ኮፒ ተሰርቶ አንዱ በመረጃነት እንዲቀመጥ አለመደረጉ፤
- ለመንግስት ተሽከርካሪ የሚሰጥ የነዳጅ እደላ ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንጻር ተገምግሞ በኮታ መወሰኑን እና እንዲሁም ለመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ተሽከርካሪ የነዳጅ ፍጆታ የከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችን ደመወዝ እና ጥቅማጥቅሞች ለመወሰን በወጣው የሚኒስትሮች

ም/ቤት መመሪያ መሠረት የተፈጸመ ስለመሆኑ በናሙና ከታዩት 11 መ/ቤቶች በ8ቱ ማስረጃ ሊቀርብ አለመቻሉ፤

- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ለቁጥጥር እና ክትትል አመቺ የሆነ ወጥ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመዝገቢያ ቅጽ ሊኖር እና በሥራ ላይ ሊውል ሲገባ በናሙና ተመርጠው በታዩት በአስራአንዱም(11) መ/ቤቶች የተለያዩ ቅጾችን (ፎርማቶች) በማዘጋጀት የሚጠቀሙ በመሆኑ ነዳጅ ሲቀዳ የኪሎ ሜትር ንባብ፣ ተሽከርካሪው ሲሰማራ የሄደበት እና የሚመለስበት ሰዓት በተዘጋጁት ቅጾች ላይ ስለማይመዘገብ ወጥነት የሌለው እና ለቁጥጥር የማያመች መሆኑ፤
- እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነት፣ በሞዴልና በዕድሜ ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ ምን ያህል ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል ሊታወቅ እና በዚሁ መሠረት ተግባራዊ መደረግ ሲገባው በናሙና ተመርጠው ኦዲት ከተደረጉ 11 መ/ቤቶች በ7ቱ፣ (በግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ በግብርና ምርምር ኢንስትቱዩት፣ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ በግብርና ሚኒስቴር፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና በኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ደብረማርቆስ ዲስትሪክት) መረጃው ተጠናቅሮ አለመያዙ እና ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- የኪሎሜትር ቆጣሪአቸው /ጌጃቸው/ ለማይሠራ የመንግሥት መ/ቤት ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋ እና በዚሁ መሠረት ክትትል ሊደረግ ሲገባ በናሙና ከተመረጡ 11 የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች በ10ሩ ጌጃቸው የማይሰራ ተሽከርካሪዎች እንዲቆሙ ከማድረግ ወጪ የመቆጣጠሪያ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣
- በናሙና በታዩት በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ 6፤ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ 2፤ በጤና ጥበቃ ሚ/ር 2፤ በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት 17፤ በግብርና ሚ/ር 17 እና በማዕድን ሚ/ር 7 በድምሩ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ 54 ተሽከርካሪዎች ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑ፤
- በመንግሥትና ህዝባዊ ድርጅት ተሽከርካሪዎች ግዥ ሥምሪት አጠቃቀምና ጥገና መመሪያ መሰረት በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ

የሚቀርብበት የአሰራር ሥርዓት በናሙና ተመርጠው ከታዩት 11 መ/ቤቶች በ8ቱ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

- እያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤት በነዳጅ አጠቃቀምና ቁጥጥር የሚታዩ የተለያዩ ችግሮችን በመለየት ለችግሮቹ መፍትሄ በማፈላለግ በወቅቱ እርምጃ ሊወሰድ ሲገባ፣ በኦዲቱ ተመርጠው ከታዩ 11 መ/ቤቶች በ8ቱ ከኮታ በላይ ሲጠቀሙ በነበሩ እና በኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ደብረማርቆስ ዲስትሪክት በ1 ሊትር ከወጣላቸው የኪ.ሜ. ልኬት በታች ያሽከረከሩ አሽከርካሪዎችን በመለየት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን፣
- በግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ተሽርካሪዎች ወጥ /standardized/ እና ወቅታዊ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ ሊያዘጋጅ፤ የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ስልጠና በመስጠት የሰለጠነ እና ልምድ ያለው ባለሙያ እንዲኖር ሊያደርግ እና በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ወቅታዊ እንዲደረጉ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሆኖም በኤጀንሲው የተሽከርካሪ ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ላይ ነዳጅን በተመለከተ ጥቂት መመሪያ ያለ ቢሆንም የነዳጅ አጠቃቀም ዝርዝር መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ እና ነዳጅ እንደ ማንኛውም እስቶክ በማየት የሚታለፍ እንጂ ለብቻ ተነጥሎ ስልጠና እንደማይሰጥ፣
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ (በግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ በገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር፣ በግብርና ሚ/ር፣ በጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ በግብርና ምርምር ኢንሲቲትዩት፣ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ በማዕድን ሚ/ር፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ በባህር ዳር እስታትስቲክስ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እና በኢትዮጵያ መንገዶች ኮርፖሬሽን በደብረ ማርቆስ ዲስትሪክት) በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶችን ወጥነት ባለው መንገድ በማዘጋጀት በጥቅም ላይ እንዲውሉ አለመደረጉ
- በተሽከርካሪ ስምሪት ላይ የሚመደቡ ባለሙያዎች ሙሉ በሙሉ በነዳጅ አጠቃቀም ቁጥጥር ላይ በቂ ክህሎት እንዲኖራቸው የሚያስችል ስልጠና አለመሰጠቱ

- ኤጀንሲው በፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ያሉ ተሽከርካሪዎችን ብዛት፣ ዓይነትና የሚገኙበትን ሁኔታ በተመለከተ መረጃ አለመያዙ፤ እንዲሁም ደግሞ ከነዳጅ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ እስከ አሁን የተደረገ ኦዲት አለመኖሩ የሚሉት በኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም ከለይ የተመለከቱትን ድክመቶች ለማሻሻል አስተዋጾ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻ ሀሳቦች ለመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ መስሪያ ቤት በላክነው ሪፖርት በማካተት መስሪያ ቤቱ ከሚመለታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲያደርጋቸው አሳስበናል፡፡

6.8. <u>በጋራ ልማት እና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች ውጤታማነት</u>

- ኤጀንሲው የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ከግል ባለሃብቶች ጋር በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለመያዝ የተቀመጠ ግልፅ የመምረጫ እና የማወዳደሪያ መስፈርት ሊኖረው እና የመምረጫ መሥፈርቱም ሊተገበርና ስኬታማነቱ ሊረጋገጥ የሚችል መሆን እና በተከራይ ባለሃብቶች እና በጋራ ልማት በሚሳተፉ ባለሃብቶች መካከል የሚጠበቀው ተግባርና ሀላፊነት በህግ ዘንድ ተቀባይነት ባለው መልኩ በኮንትራት ውሉ ላይ በግልጽ እና በፅሁፍ መቀመጥ ይኖርበታል፣
- ይሁን እንጂ በኦዲቱ በተመለከትናቸውና በዚህ ሪፖርት ውስጥ ችግር የተከሰተባቸው ተብለው ከሚቀርቡት በኪራይና በጋራ ልማት ይዞታ ከተላለፉ አንዳንድ የልማት ድርጅቶች አፈፃፀም እንደተረዳነው፤ ኤጀንሲው ከላይ እንደተገለፀው የተሻለ የሥራ ዕቅድ (Business plan) ብቻ ዋነኛ የመምረጫ መስፈርቱ አድርጎ ስለሚወስድ የሥራ ዕቅዱ በተጨባጭ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ወይም የማይችል መሆኑ ስለማይገመገም ተፈፃሚ የማይሆኑ ዕቅዶች በባለሀብቶች ቀርበው የተመረጡ መሆናቸውን፣
- እንዲሁም በኪራይና በጋራ ልማት ለሚያዙ ድርጅቶች ውል ዝግጅት ላይ የሚታዩ ጉድለቶችና የክፍያ ዘመን የሚጠናቀቅበት ጊዜ ለምሳሌ- በኪራይ ለሚያዙ ድርጅቶች የሚሰጠው የእፎይታ ጊዜ ኪራይ ክፍያ በየትኛው ወር እንደሚከፈል በግልጽ የማይቀመጥ መሆኑን፣
- በኪራይ ለተያዙ የልማት ድርጅት በውል ስምምነት ውስጥ የሥራ ዕቅዱን ሊያዘገዩ ወይም እንዳይፈጸም ሊያደርጉ የሚችሉ ስጋት የሆኑ የስጋት

መጠቆሚያ መስፈርቶች (Periodic Risk Assessment) መኖራቸውን በተመለከተ፣

- በናሙና ከተመረጡ በኪራይ ከተያዙ የልማት ድርጅቶች ውስጥ፣ በሲሌ እርሻ ልማት የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ባለመገኘቱ የመንግስት ይዞታ ላይ በአካባቢው ነዋሪዎች ህገ ወጥ የመሬት ወረራ፣ የቤት ግንባታ እና የመሬት ሽሚያ ችግር የተፈጠረና የመፍትሄ እርምጃ አለመወሰዱ፤ እንዲሁም በአካባቢው የመስኖ ውሃ ችግር መኖሩ፣ እንደዚሁም የአርባምንጭ እርሻ ልማት መሬት ለትምህርት ቤትና ለሌሎች አገልግሎቶች ተቆራርጦ እየተሰጠ በመሆኑና የከተማ መስተዳደሩ በሚያደርገው የማስፋፊያ ሥራ ምክንያት የእርሻ ልማቱ በሥራ ዕቅዱ መሰረት መሥራት የተቸገረ መሆኑን፣
- በጋራ ልማት እና በኪራይ ለተያዙ የልማት ድርጅቶች ባለሃብቱ በሚያቀርበው የሥራ ዕቅድ እና የአፈጻጸም ሪፖርት ላይ የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ እቅድ እንዲኖረውና ተግባራዊ እንዲያደርግ የሚያስገድድ የአሰራር ስርዓት ሊኖር እና ተፈጻሚ ሊሆን እንዲሁም በአከባቢውና በመሬት ላይ የሚያደርሱት አሉታዊ ተጽዕኖ ሊገመገም ይገባል፡፡
- ይሁን እንጂ በኦዲቱ፣ ባለሃብቱ በሚያቀርበው የሥራ ዕቅድ ላይ የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ እቅድ እንዲኖረው የሚያስገድድ የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ፣
- የአቢጃታ ሀይቅ ቀድሞ ከነበረበት ይዞታ መጠኑ እየቀነሰ መምጣትና የውሃው መጠን መሸሽ እንዲሁም በሀይቁ ውስጥ የነበሩ የዓሣ ዝርያዎች መጥፋት በአክሲዮን ማህበሩ የሥራ እንቅስቃሴ ምክንያት ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ አክሲዮን ማህበሩ እና የዞኑ ግብርና ፅ/ቤት ተጠይቀው በጥናት የተደገፈ ማስረጃ ሊያቀርቡ አለመቻላቸው፣ በተጨማሪም በሃይቁ እና በዙሪያው ላይ የሚታዩ ኬሚካላዊ እና ስነ ሀይወታዊ ለውጦችን ለማሳየት የሚያስችል የአፈርና የውሃ ምርመራ እና ጥናት ያልተደረገ መሆኑን፣
- በሲሌ እርሻ ልማት እና በአርባ ምንጭ እርሻ ልማት የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች እና የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ በስራ እቅዱ ውስጥ ተካተው በተቀናጀ መልኩ አለመሰራታቸውን ፣ በሪፖርት ልውውጥ እና ዕቅድ

አፈፃፀም ላይ አለመካተታቸውን ከድርጅቶች ስራ አስኪያጆች ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት የተቻለ መሆኑን፣

  - o እንዲሁም የአምቦ ውሃ አክሲዮን ማህበር ድርጅት ፍሳሽ ሰንቀሌ (ደቢስ) ወንዝ ውስጥ የሚገባ ሲሆን ይህም ሊያስከትል የሚችለው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አለመደረጉን፣

- የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ወደ ግል ከተዛወሩ በኋላ በስራ እቅዱ (Business Plan) መሠረት ባለሀብቶች ሥራዎችን እየሰሩ ስለመሆኑ ወጥ የሆነ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ እንዲሁም የተጠናከረ የመስክ ጉብኝት ሊደረግ ይገባል፡፡
- ይሁን እንጂ የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ወደ ግል ከተዛወሩ በኋላ ድርጅቶችን የገዙ ባለሀብቶች በገቡት ውል እና በስራ ዕቅዱ መሰረት እየሰሩ ስለመሆኑ ክትትል አለመደረጉና አንዳንድ ባለሀብቶች የውል ግዴታቸውን በወቅቱ አለመወጣታቸውን፣
- ኤጀንሲው የአቢጃታ ሶዳ አሽ አክሲዮን ማህበርን ለአጋር ባለሃብቱ በሚያስረክብበት ወቅት የርክክብ ሂደቱ በመዘግየቱ ምክንያት የድርጅቱን ምርት ሥራ እንቅስቃሴ በሥራ ዕቅዱ በተመለከተው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በ2003 ዓ/ም የማስፋፊያና የማሻሻያ ሥራዎች አለመሠራታቸው፣
- በሌላ በኩል የሲሌ እርሻ ልማት በቢዝነስ ፕላኑ መሠረት የ2002 በጀት አመት ዕቅድ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብና የእርሻ ልማቱ ተከራይ በቢዝነስ ፕላኑ መሰረት ግዴታውን መወጣት ይችል ዘንድ አቅም እንዲፈጥር ቢወሰንም አለመፈፀሙን፣
- በተጨማሪም የሲሌ እርሻ ልማት ተከራይ የሆነው ሉሲ እርሻ ልማት ድርጅት ከሀምሌ 1/2003 እስከ ታስሳስ 30/2004 ያለው የሥራ ዕቅድ እና አፈፃፀም ሲታይ ሙዝ 7,840 ኩንታል ለማምረት አቅዶ 2,378 ኩንታል (30%)፣ ጥጥ 17,070 ኩንታል ለማምረት አቅዶ 7,167 ኩንታል (42%)፣ በቆሎ 4,500 ኩንታል ለማምረት አቅዶ 1,060 ኩንታል (24%)፣ የተባዘተ ጥጥ 6315 ኩንታል ለማምረት አቅዶ ምንም (0%) እና የጥጥ ዘር 9,730 ኩንታል ለማምረት አቅዶ ምንም (0%) ያላመረተ መሆኑን፣ እንዲሁም ተከራዩ በ2003 ዓ/ም የምርት ዘመን ብር 633 ሺህ ለማትረፍ አቅዶ የብር 1,445 ሺህ ኪሳራ ስላስመዘገበ በ 228% የኪሳራ አፈፃፀም ማሳየቱ፣

- የሲሌ እርሻ ልማት ድርጅት በሬድ ስፔክል ኢትዮጵያ ትሬዲንግ ተይዞ በነበረበት በታህሳስ ወር 2002 ዓ/ም የተመረተ 954.4 ኩንታል በቆሎ እና 136 ኩንታል ማዳበሪያ በመጋዘን ተከማችቶ የሚገኝ ሲሆን ከአንድ አመት በላይ በመጋዘን በመቆየቱ በሙቀትና ቅዝቃዜ መፈራረቅ፣ በአቧራና በአያያዝ ጉድለት እንዲሁም በነቀዝ ምክንያት የተጠቃ በመሆኑ ለምርጥ ዘርነት ዘር የማያገለግል መሆኑ፤
- በተጨማሪም በመጀመሪያው የውል አመት ማለትም ከ23/2001 እስከ መጋቢት 23/2002 ዓ/ም መከናወን የነበረበት 600 ሄክታር ለጥጥ ማምረቻ የሚሆን መሬት ዝግጅት፣ 110 ሄክታር የፍራፍሬ ማልሚያ መሬት ዝግጅት ሙሉ ለሙሉ አለመከናወኑ፣ እንዲሁም ከመጋቢት 23/2001 እስከ መጋቢት 23/2002 ዓ/ም 6,000 ኩንታል ቦሎቄ፣ 30,000 ኩንታል በቆሎ፣ 15,000 ኩንታል ጥጥ፣ 10,000 ኩንታል ሙዝ እንዲመረት ውል ቢገባም ቦሎቄና ጥጥ ምንም ያልተመረተ ሲሆን በቆሎ 4,000 ኩንታል መመረቱ እንዲሁም የሙዝ ምርት መጠንን ማወቅ አለመቻሉ፤
- በጋራ ልማት በተያዘው ሆራይዘን አዲስ ጎማ አክሲዮን ማህበር እ.ኤ.አ. በ2010 ብር 28,817,063 ትርፍ ያሳየና በቀጣይ አመት በ2011 ደግሞ ብር 2,065,335 ትርፍ እንዳገኘ ኦዲት ከተደረገ በትርፍና ኪሳራ ሂሳብ መግለጫ (Income statemenet) የተመለከተ ሲሆን ከፍተኛ የትርፍ መቀነስ ማሣየቱ፤
- የተከራይ ድርጅት የቦርድ ጽ/ቤት በየሶስት (3) ወሩ ስለስራ ሂደት ለኤጀንሲው ሪፖርት ማቅረብ ያለበት ሲሆን፣ በኦዲቱ ወቅት፡-
    - በሲሌ እርሻ ልማት የውል ሰነዱ በሚያዘውና ስምምነት ላይ በተደረሰው መሰረት ወርሃዊ ሪፖርቶች በወቅቱ ማለትም በየሶስት ወሩ እንዲላኩ ቢወሰንም አለመፈፀሙ፣
    - አርባምንጭ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ተከራይ የነበረው ናሪን ኦርሜ ቴክስታይል ግሩፕ በ1998 ዓ/ም (እ.አ.አ ህዳር 2005) ድርጅቱን ተረክቦ ሥራ ከጀመረ ከ3 ወራት በላይ አልፎ የነበረ ቢሆንም ወርሃዊም ሆነ የሩብ አመት ሪፖርቶች ለዳይክተሮች ቦርድ ማቅረብ እንዳለበት በውል ስምምነት ሰነድ አንቀጽ 6.13 ተጠቅሶ ሳለ ሪፖርቶች ወቅታቸውን ጠብቀው አለመቅረባቸው፤

- ሬድ ስፔክልድ ኢትዮጵያ ትሬዲንግ የሲሌ እርሻ ልማትን ተከራይቶ ሥራ ከጀመረበት ከመጋቢት 23/2001 ዓ/ም ጀምሮ ውሉ እስከተቋረጠበት ሚያዝያ 1/2002 ዓ/ም ድረስ ወርሀዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በውሉ መሰረት ለኤጀንሲው ማቅረብ የነበረበት ቢሆንም በ2001 ዓ/ም ሚያዝያ እና ነሀሴ፣ በ2002 ዓ/ም መስከረም፣ ጥቅምትና ጥር ወራት በቀር ተከታታይ ሪፖርት የተላከበት ሁኔታ አለመኖሩን በኤጀንሲው እና በሬድ ስፔክልድ ኢትዮጵያ ትሬዲንግ መካከል የተፈፀመውን የኪራይ ውል አፈፃፀም በተመለከተ ከተደረገ ልዩ ምርመራ ሪፖርት ላይ ለመረዳት መቻሉ፣
- በጋራ ልማት ኢንቨስትመንትና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሂሳብ ሪፖርቶች የትርፍና ኪሳራ ሪፖርት (Income statemenet) እና የሀብት እና እዳ መግለጫ (Balance sheet) ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ሊቀርብና ፈቃድ ባለው የኦዲት ተቋም ኦዲት መደረግ ሲገባው፣ BM (ቢኤም) ኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት የተያዘው በ2002 ዓ/ም ቢሆንም የሂሳብ መግለጫዎች ለኤጀንሲው አለመላኩን እና በገለልተኛ ኦዲተሮች ኦዲት አለመደረጉ፣

* ኤጀንሲው በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨሰትመንት ከግል ባለሀብቱ ጋር በሚያስተዳድራቸው ድርጅቶች ስር ያለው የኃላፊነትና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሁም ውል ቢቋረጥ አፈጻጸሙ በስምምነት ሰነዱ መሰረት ሊሆን ሲገባ፣
* አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበርን ቀደም ብሎ በ1992 ዓ/ም (እ.አ.አ ጥቅምት 2000) ተከራይቶ የነበረው አቲላ ይልድሪም የተባለው ግለሰብ የተለያዩ የመንግስት ዕዳዎች ማለትም የአላቂ እቃዎች ክምችት ዋጋ፣ የኪራይ ክፍያ፣ የኦቨር ድራፍት ክፍያ፣ የሰራተኞች ኢንሹራንስ፣ የስልክና የውሃ ክፍያ እንዲሁም የወለድ ክፍያን ጨምሮ በባለሀብቱ ብር 25,579,395.55 ያልተከፈለ መሆኑን መስከረም 1998 ዓ/ም ቁጥር ዲ.ቦ /111/98 በአርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር የቀረበ የሊዝ ሰነድ ላይ ከቀረበ ፅሁፍ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ ገንዘብ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ታህሳስ ወር 2005 ዓ/ም ድረስ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣
* ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአክሲዮን ማህበሩን በ1998 ዓ/ም ተከራይቶ የነበረው ናሪን ኦርሚ ቴክስታይል ግሩፕ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ለሥራ

ማስኬጃ ብድር ብር 8 ሚሊዮን በየካቲት 30/1998 ዓ.ም የተሰጠው ሲሆን ከ1/07/99 ዓ/ም ጀምሮ በየሶስት ወሩ ብር 1 ሚሊዮን የመክፈል ግዴታ ቢኖርበትም እስከ ህዳር 2005 ዓ/ም ክፍያ ያልጀመረ መሆኑን ለአክሲዮን ማህበሩ ከተፃፈ ደብዳቤ ቁጥር 100/154/7/119/99 ለማወቅ መቻሉ፣

- እንዲሁም ይኸው ተከራይ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ለመለዋወጫ መግዣ እና የቆሙ መሳሪያዎች ተጠግነው ማምረት እንዲጀምሩ የተሰጠውን ብር 8 ሚሊዮን ለተባለው ሥራ ስለመዋሉ እና ስላስገኘው ውጤት ሪፖርት ያላቀረበ መሆኑን ለአክሲዮን ማህበሩ ከተፃፉ ደብዳቤዎች ቁጥር 100/154/7/119/99 እና 100/154/8/127/2000 ላይ ለማወቅ መቻሉ፣
- በተጨማሪም ይህ ተከራይ በገባው የውል ግዴታ መሰረት ኃላፊነቱን መወጣት ባለመቻሉ መክፈል የነበረበትን የኪራይ ክፍያ 760 ሺህ የአሜሪካን ዶላር ባለመክፈሉ በየካቲት 2001 ዓ.ም የኪራይ ውሉ እንዲቋረጥ መደረጉ፣
- አርባምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ሁለት ጊዜ ለተለያዩ ባለሃብቶች በኪራይ ተሰጥቶ ውጤታማ ሊሆን አለመቻሉ፣
- የአዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካን በ1998 ዓ.ም ተከራይቶ የነበረው ናሪን ኦርሚ የኪራዩን ገንዘብ በውሉ መሰረት በወቅቱ አለመመለስ፣ በውሉ መሰረት የመሳሪያዎች ዕድሳት አለመከናወን፣ የተለያዩ ዕዳዎች ማለትም፣የኤክሳይዝ ታክስ (ብር 23.5 ሚሊዮን)፣ የኤሌክትሪክ ክፍያ (ብር 4.1 ሚሊዮን)፣ የቫት ክፍያ (ብር 5.6 ሚሊዮን)፣ የሀገር ውስጥ ገቢ (ብር 3.2 ሚሊዮን) እና የጡረታ ገንዘብ (ብር 474 ሺህ) ያልተከፈሉ መሆኑ፣
- ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባለሀብቱ በገቡት ውል መሰረት አክሲዮን ማህበሩን ለማልማት ባለመቻላቸውና ሃላፊነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ ባለመቻላቸው የሊዝ ውሉ እንዲቋረጥ በማድረግ አክሲዮን ማህበሩ መንግስት እንዲረከበውና ባለሃብቱ ለተጠቀሙበት የመንግስት ሀብት ዋጋ (በንብረት ርክክብ ወቅት የታየ ጉድለት) ብር 37, 870,833 እና በወቅቱ ያልተከፈለ የሊዝ ክፍያ የአሜሪካ ዶላር $1,978,461.66 በድምሩ ብር 72 ሚሊዮን ያልተከፈለ እዳ መኖሩን ለገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከተፃፈ ደብዳቤ ቁጥር 300-220/356/10 እና የኤጀንሲው ጠበቃ ለግልግል ዳኝነት ጉባዔ ካቀረበው የክስ መረጃ ለመገንዘብ መቻሉ፣

- ሬድ ስፔክልድ የተባለው የሲሌ እርሻ ልማት ድርጅት ተከራይ በገባው የውል ስምምነትና የሥራ ዕቅድ መሰረት ሥራውን እያከናወነና ግዴታዎቹንም እየተወጣ ያልነበረ መሆኑ፣ በተጨማሪም ተከራይ ግዴታዎቹን ባለመወጣቱ ምክንያት ለወደፊቱ ሊጣል የሚችለውን ቅጣት የመሸፈን ሃላፊነት ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከተረከበው ንብረት ውስጥ የተጠቀመውና በውሉ መሰረት መከፈል ሲገባው ያልከፈላቸው ግዴታዎች ማለትም የሰራተኛ ደሞዝ፣ የሥራ ግብር፣ የጡረታ ክፍያ፣ የቤተሰብ ህክምና መዋጮ፣ የሰራተኛ ማህበር መዋጮ፣ የመድን ዋስትና መዋጮ፣ የአላቂ እቃዎች ዋጋ እና የኪራይ ክፍያ በድምሩ ብር 1,685,090.22 ያልተከፈለ ዕዳ ያለበት መሆኑ፣
- እንዲሁም በሥራ ዕቅዱ መሰረት ያስቆፈራቸው አራት ጥልቅ ጉድጓዶች በባለቤትነት ጥያቄ ምክንያት ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ታሽገው በመቀመጥ ጥቅም ላይ ሊውሉ አለመቻላቸው፣
- የልማት ድርጅቱ በገባው ውለታ መሰረት በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለተያዙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የኪራይ ክፍያና የመንግስትን የትርፍ መዋጮ በወቅቱ ሊከፍል ሲገባ፣
    - የአምቦ ውሃ አክሲዮን ማህበር አጋር የሆነው ድርጅት ሳብ ሚለር ኃ/የተ/የግ/ማህበር እስከ እ.ኤ.አ ህዳር 2010 መከፈል የነበረበትን የድርጅቱን እዳ ብር 4,499,309 እስከ ታህሳስ 2005 ዓ/ም ድረስ አለመክፈሉ፣
    - የሲሌ እርሻ ልማት ድርጅት ተከራይ ሉሲ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የኪራይ ክፍያ እና ወለድ ብር 1.711 ሚሊዮን እስከ ታህሳስ 2005 አለመክፈሉ፤ በዚሁ ድርጅት የኪራይ ክፍያ መጓተት ከመኖሩም በላይ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ክፍያ፣ የሊዝ ኪራይ ክፍያ እና ሌሎችም የመንግስት ግዴታዎች በወቅቱ ተፈጽሞ ወጤቱ እንዲገለጽለት ቦርዱ ቢወስንም አለመፈፀሙን፣
    - የአደሌ እርሻ ልማት ድርጅት ተከራይ የሆነው አፊያ የምግብ ኮምፕሌክስ የሶስት ሩብ አመት የኪራይ ክፍያ ብር 1,006,416.8 እስከ ታህሳስ 2005 ዓ/ም ያልከፈለ መሆኑ፤

ሰንጠረዥ ፡- በተከራይ እና በአጋር ባለሃብቶች ያልተከፈሉ የመንግስት ዕዳዎች ዝርዝር

ተ.ቁ.	የልማት ድርጅቱ ሥም	ተከራይ (አጋር) ባለሃብት	ያልከፈለው የዕዳ መጠን	የዕዳው ዓይነት
	አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ	አቲላ ይልድሪም	ብር 25,579,395.55	የኪራይ ክፍያ እና ሌሎች እዳዎች
	አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ	ናሪን ኦርሚ ቴክስታይል	760 ሺህ የአሜሪካን ዶላር	የኪራይ ክፍያ
	አዋሳ ጨርቃ ጨርቅ	ናሪን ኦርሚ ቴክስታይል	ብር 72 ሚሊዮን	የኪራይ ክፍያ እና ሌሎች እዳዎች
	ሲሌ እርሻ ልማት	ሬድ ስፔክልድ ኢትዮጵያ	ብር 1,685,090.22	የኪራይ ክፍያ እና ሌሎች እዳዎች
	ሲሌ እርሻ ልማት	ሉሲ እርሻ ልማት	ብር 1.711 ሚሊዮን	የኪራይ ክፍያ
	አምቦ ውሃ አክሲዮን ማህበር	ሳብ ሚለር	ብር 4,499,309	የድርጅቱ እዳ
	አደሌ እርሻ ልማት	አፊያ የምግብ ኮምፕሌክስ	ብር 1,006,416.8	የኪራይ ክፍያ

- የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለግል ባለሀብቶች ከተሰጡ በኋላ ፕራይቬታይዜሽኑ ያስከተለውን አጠቃላይ ውጤት ኤጀንሲው በተወሰነ የጊዜ ገደብ እንዲገምገም አለማድረጉ፤
- የልማት ድርጅት ወደ ግል ባለሀብት ሲዞዋወር በድርጅቱ ውስጥ ያለ ንብረት ለተከራይ ባለሀብት ተቆጥሮና ተመዝግቦ ሊተላለፍ ሲገባ፤
    - በአርባ ምንጭ እርሻ ልማት ድርጅት ግቢ ውስጥ አሚባራ እርሻ ልማት የተረከባቸው የተለያዩ ያረጁ ማሽኖች (ዶዘር፣ የበቆሎ መፈልፈያ የመሳሰሉት) ተቀምጠውና ሳር በቅሎባቸው፣ ዝናብና ፀሃይ እየተፈራረቀባቸው መገኘታቸውን እንዲሁም በእርሻ ልማቱ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ አብዛኛዎች መለዋወጫዎች ጊዜ ያለፈባቸው ከመሆናቸው በላይ እናት ማሽኖቻቸው ከጥቅም ውጭ ሆነው የሚገኙ መሆኑ፤
    - በተጨማሪም አሚባራ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ ከመንግስት የተከራየውን ሎደር እንዲሁም ሌሎች ማሽኖች ለ3ኛ ወገን በማከራየት በ2003/2004 ዓ.ም ብር 2,095,581.27 ገቢ ሰብስቦ የተገኘ መሆኑ ከትርፍ እና ኪሳራ

የሂሳብ ሪፖርት እና በ14/11/2004 ከተፃፈ የመሳሪያ የኪራይ ውል እና ከእርሻ ልማቱ ስራ አስኪያጅ በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ መቻሉ፤

  - o የአደሌ እርሻ ልማት ተከራይ ባለሃብት የሆነው አፊያ የምግብ ኮምፕሌክስ ከመንግስት በኪራይ የተረከባቸውን የእርሻ መሳሪያዎች እና ማሽኖች ወቅቱን የጠበቀ ተገቢ ጥገና ስላልተደረገላቸው ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰባቸው መሆኑ፣

- አሰሪ ድርጅቶች የሥራ ቦታ የደህንነት እና የጥንቃቄ መሳሪያዎችን ሊያሟሉና በሰራተኛው ጤናና ህይወት ላይ ያሉ አሉታዊ ሁኔታዎች ሊፈጥሩ የሚችሉ ነገሮችን ሊያስወገዱ እንደሚገባ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ላይ የተመለከተ ቢሆንም፣
  - o በአቢጃታ ሶዳ አሽ አክሲዮን ማህበር ለእያንዳንዱ ሠራተኛ የመከላከያ መሳሪያ አለመኖር፣ በአክሲዮን ማህበሩ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ በበቂ ሁኔታ እንደሌለና ያለውም ከጊዜው ጋር ያልተጣጣመ መሆኑን እንዲሁም አስቸኳይ ጉዳዮችን ማለትም የእሳትና ሌሎች አደጋዎችን ለማጥፋት እንዲቻል የተፃፈ መመሪያ እንደሌለ፣ በፋብሪካው ለሚሰሩ ሠራተኞች የሚሰጠው ጫማና መሸከሚያ አመቺ ባለመሆኑ ሠራተኛው የማይጠቀምበት ሁኔታ መኖሩ፣
  - o አርባ ምንጭ እርሻ ልማት ድርጅት ስር ባለው ጥጥ መዳመጫ ፋብሪካው ውስጥ ከወለል በላይ ከፍ ብለው ወደሚገኙ የፋብሪካው ማሽኖች ለሚወጡ ሰራተኞች የደህንነት ቀበቶ እና የደህንነት መሳሪያ፤ እንዲሁም ደግሞ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያ እና የእሳት አደጋ ባለሙያ አለመኖሩ፤
  - o በጡረታ ወይም በግል ምክንያት ሥራቸውን መልቀቅ ለሚፈልጉ ሰራተኞች የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ በሚያዘው መሰረት መብታቸው ሊከበርላቸው፤ እንዲሁም አንድ የመንግስት የልማት ድርጅት ወደ ግል ባለሀብት ከተዛወረ በኋላ ነባር ሰራተኞች የጡረታና ሌሎች ጥቅማ ጥቅማቸው ሳይነካ በስራው እንዲቀጥሉ ለማድረግና ባለሀብቱ ከሰራተኛ ማህበራት ጋር በመሆን ሁኔታዎችን ማመቻቸት ሲገባ፤
    - ➢ የሲሌ እርሻ ልማት የ3 ወራት የሰራተኞች የጡረታ መዋጮ አለመክፈሉ፤

- አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮንን ተከራይቶ ከነበረው ከሚ/ር አቲላ ይልድሪም ጋር የነበርውን ክርክር በተመለከተ የተሰጠው የፍርድ ቤት ውሳኔና ትዕዛዝ ላይ ለማየት እንደተቻለው በከሳሽና ተከሳሽ መካከል የነበረው የሊዝ ውል ግንቦት 27 ቀን 1993 ዓ/ም የተቋረጠ ስለሆነ ከህዳር 22 ቀን 1994 ዓ/ም ለሠራተኛው ተከፍሏል የተባለው ደመወዝ ብር 274,414.67 ተከሳሽ ለመክፈሉ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩ፣
- የቢ.ኤም ኢትዮጵያ ድርጅት ወደ ግል ባለሀብት በሚዞርበት ወቅት ሠራተኛው እንዲያውቅ የተደረገበት አካሄድ አለመኖሩ፣

- ኤጀንሲው ከግል ባለሀብቱ ጋር በጋራ ልማት ኢንቨስትመንትና በኪራይ ሊያለማ ያሰባቸውን የልማት ድርጅቶች በተመለከተ የተሟላ መረጃ ሊለይና ሙሉ መረጃን በሚሰጥ መልኩ ማዕከላዊ በሆነ የኤጀንሲው የመረጃ መረብ ላይ ሊያስቀምጥ፤ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ህብረተሰቡ ወቅታዊ መረጃዎችን እንዲያገኙ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ ያለበት በመሆኑ መረጃዎችን የሚያስቀምጥበት የመረጃ መረብ ቢኖረውም እ.ኤ.አ ከ2007 ጀምሮ ከግል ባለሃብቱ ጋር በኪራይና በጋራ ልማት የሚያዙ እና ሊያዙ የታቀዱ ድርጅቶችን ዝርዝር፣ እስከ መቼ በግል ባለሃብቱ መያዝ እንደሚችሉ እና በምን ያህል የኪራይ ዋጋ እና የድርሻ መዋጮ የሚሉትን መረጃዎች በግልፅ አለማስቀመጡ፤ ወቅታዊ የሚደረግበት ሁኔታም አጥጋቢ አለመሆኑ፣ በኦዲት ወቅት የታዩ ግኝቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም ከለይ የተመለከቱትን ድክመቶች ለማሻሻል አስተዋጾ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻ ሀሳቦች ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ መስሪያ ቤት በላክነው ሪፖርት በማካተት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲያደርጋቸው አሳስበናል፡፡

6.9. <u>የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የመንግስት ትርፍ ድርሻ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ ብድር አሰጣጥ፣ አጠቃቀም እና አሰባሰብን በተመለከተ</u>

- ኤጀንሲው ከ2003-2007 ባዘጋጀው እስትራቴጂክ ዕቅድ ውስጥ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ሂሳብ በየዘርፉ በዝርዝር ለምን ያህል

አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች ብድር እንደሚሰጥ እና ምን ያህል የብድር ተመላሽ እንደሚሰብሰብ የልማት ድርጅቶችንና አክሲዮን ማህበራትን የፍላጎት ጥናት መሰረት በማድረግ በስትራቴጂክ እቅዱ ውስጥ አለማካተቱና በየአመቱ ተግባራዊ መደረጉን የማያረጋግጥ መሆኑን፤

- በየበጀት ዓመቱ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር የሚያገኙ የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራትን በተቀመጠው መስፈርት መሠረት በመለየት ሊሰጥ ያቀደውን እና የሰጠውን የብድር ገንዘብ መጠን፣ ብድር የሚያገኙ አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶችን ብዛት፣ የብድር አሰባሰብ እና አጠቃቀምን በተመለከተ እስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት በማድረግ አመታዊ እቅድና የእቅድ ክንውን ሪፖርት የማያዘጋጅ እና በእቅድ ክንውን ሪፖርቱ ውስጥ የታዩ የአፈፃፀም ክፍተቶችንና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን የማያካትት መሆኑ፤
- ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችና አክስዮን ማህበራት በየበጀት አመቱ መክፈል ያለባቸውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ ገቢ እንዲያደርጉ ደብዳቤ የሚጽፍ እና መርሃ ግብር/የጊዜ ሰሌዳ/ አዘጋጅቶ የሚልክ ቢሆንም 28 የመንግስት የልማት ድርጅቶችና አክስዮን ማህበራት ፈሰስ ማድረግ የሚገባቸውን ብር 786,952,679 ገቢ ሳያደርጉ በአማካይ ከ2-3 አመት ያዘገዩ መሆኑን እንዲሁም እያንዳንዱ የልማት ድርጅትና አክሲዮን ማህበር የየበጀት ዓመት የትርፍ ድርሻ፣ ምን ያህል እንደተከፈለና ምን ያህል እንደቀረ ትንተና ለመስራት የሚያስችለውን የሂሳብ ቋት (ledger) ያላዘጋጀ መሆኑ፤
- ኤጀንሲው የመንግስት የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የወሰዱት የብድር ሂሳብ ፋይዳ /ውጤት/ ያስገኘ ስለመሆኑ ከሚያቀርበው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አጠቃቀም ሪፖርት በተጨማሪ የመስክ ጉብኝት /ምልከታ/ የሚያደርግ መሆኑን ቢገልፅም የመስክ ጉብኝት ሪፖርት አለመቅረቡ፤
- የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው አክሲዮን ማህበራት የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ ብድር ለመውሰድ ባቀረበው የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ላይ ብድሩ ተፈቅዶለት ግንባታውን አጠናቆ ወደ ስራ በገባ በዓመቱ አትራፊ እንደሚሆን ያቀረበ ቢሆንም ብር 388,252,933 ፕሮጀክት ለማስፋፋት ወስዶ ፕሮጀክቱ

ተጠናቆ ወደ ስራ በገባ በአመቱ ብር 10,119,088 መክሰሩን፣ የኮስቲክ ሶዳ አክሲዮን ማህበር በ1995 ዓ.ም ብር 6,351,000፣ በ1999 ዓ.ም ብር 5,000,000 ብድር የወሰደ ቢሆንም አትርፎ የማያውቅ መሆኑን እንዲሁም የባቱ ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር በ1997 ዓ.ም ብር 12,440,000 ለማሽነሪና ተሽከርካሪዎች ግዥ ተበድሮ ግዥውን ፈፅሞ ወደ ስራ የገባ ቢሆንም አትራፊ ሊሆን ያልቻለ መሆኑ ለማረጋገጥ መቻሉ፤

- ከ2002 በጀት ዓመት ጀምሮ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈንዱን ማስተዳደር ከጀመረ በኋላ እና በኤጀንሲው ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 730/2004 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 4 ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲያስተዳድር በመንግስት ከተወሰነ ወዲህ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ለተፈቀደላቸው አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች የተፈቀደላቸውን የፈንድ ብድር ሂሳብ በወቅቱ ወደ ባንክ ሂሳባቸው ገቢ በማድረግ የማያሳውቃቸው መሆኑ፤
- የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በ20/08/95 ብር 22,264,000 እና በ15/09/97 ብር 3,965,697 በድምሩ ብር 26,229,697 የተበደረ ሲሆን ከዚህ ሂሳብ ውስጥ ብር 5,550,301 በፈንዱ ላልተፈቀደለት የማሽነሪ (pad roll bleaching) ግዥ፣ ብር 23,055 ለመደበኛ ስራ ማስኬጃና ብር 180,000 ላልተፈቀደ ግንባታ በድምሩ ብር 5,753,356 ከተፈቀደበት ዓላማ ውጭ ወጪ ማድረጉ፣ በ2002 በጀት ዓመት ለኢንቨስትመንት ከተፈቀደለት ብር 5 ሚሊየን ውስጥ ብር 828,964 ከፈንዱ ዓላማ ውጭ ለስራ ማስኬጃ የተጠቀመ መሆኑን፣ ይህንንም በተመለከተ ኤጀንሲው ምክንያቱን በማጣራት አክሲዮን ማህበሩ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ አለማድረጉ፤ ከዚህም በተጨማሪ የኮስቲክ ሶዳ አክሲዮን ማህበር በ1995 በጀት ዓመት በድጋፍ ከተሰጠው ብር 6,351,000 ውስጥ ብር 3,900,000 ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የውል ስምምነት ውጭ ያዋለ መሆኑ በውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት መረጋገጡ፤
- የሸቀጦች ጅምላ ንግድ አስመጪ ድርጅት ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የወሰደውን ብድር በየአመቱ ኦዲት አለማስደረጉ፤ የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር እንደ አሮፓውያን አቆጣጠር በ2010 እና በ2011 በቀረበው የኦዲት ሪፖርት ላይ በድርጅቱ የሂሳብ መዝገብ እና በውጭ ኦዲተር ሪፖርት መካከል እንደ ቅደም ተከተሉ የብር 996,994 እና የብር

325,403 መንስኤው ያልተገለፀ ልዩነት (Unexplained difference) የተገኘ መሆኑ፣ እንዲሁም የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር የፈንዱን ሂሳብ በየበጀት ዓመቱ ሳያስመረምር የሁለት ዓመት ሂሳብ በአንድ ላይ ኦዲት ማስደረጉ፤

- የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት (ጅንአድ) ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በ8/7/2000 በወጪ ሰነድ ቁጥር ወ 084501 የወሰደውን ብድር ብር 50 ሚሊየን እስከ ጥቅምት 30/2002 ዓ.ም ለመመለስ ውል የገባ ቢሆንም ብድሩን በገባው ውል መሰረት ሳይመልስ ለሁለት አመት ያዘገየና ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስም ተመላሽ ያላደረገ መሆኑ፤
- ባቱ ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በ17/2/97 በወጪ ሰነድ ቁ 01.66.21/33 የወሰደውን ብድር ብር 12,440,000 ለማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች መግዣ በሶስት አመት ለመመለስ ውል የገባ ቢሆንም በውሉ መሰረት ተመላሽ ሳያደርግ አራት አመት ያዘገየና ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ ተመላሽ ያላደረገ መሆኑ፤
- ኮስቲክ ሶዳ አክሲዮን ማህበር ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በተለያየ ጊዜ ከተበደረው ብር 22,928,358 ውስጥ ብር 3,666,666 በውሉ መሰረት በወቅቱ ተመላሽ ያላደረገ መሆኑ፣ አዳሚ ቱሉ ፀረ-ተባይ ማዘጋጃ አክሲዮን ማህበር ከተበደረው ብር 12,126,503 ውስጥ ብር 3,031,625.75 የመመለሻ ጊዜው ያለፈ መሆኑ፤
- የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር በተለያየ ጊዜ ከተፈቀደለት የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብር 388,252,933 ውስጥ ብር 35,369,185 እስከ ሰኔ 30/2004 ድረስ መከፈል የነበረበትና የመክፈያ ጊዜው ያለፈ መሆኑ፣
- ሐማሬሳ የምግብ ዘይት አክሲዮን ማህበር በ1998 ዓ.ም በወጪ ሰነድ ቁጥር 560931 የተበደረውን 3 ሚሊየን እስከ ሐምሌ 2001 ተመላሽ ማድረግ የነበረበት መሆኑ፣ እንዲሁም በ8/02/2000 በወጪ ሰነድ ቁጥር 798709 የተበደረውን ብር 10,039,877 ከሐምሌ 2001-04 በየሶስት ወሩ እኩል ክፍያ እየከፈለ መመለስ የነበረበት ሲሆን ገንዘቡን በውሉ መሰረት ተመላሽ ሳያደርግ እንደቅደም ተከተላቸው 6 እና 4 ዓመት ያዘገየ እና ገቢ ያላደረገ መሆኑን፣

- አበቦ እርሻ ልማት ድርጅት ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በ2000 ዓ.ም ከተበደረው ብር 38,290,144 ውስጥ ብር 16,316,057 ለ2 ዓመት ያህል ያዘገየና ገቢ ያላደረገ መሆኑ እንዲሁም ሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ድርጅት ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በ1996 ዓ.ም በወጪ ሰነድ ቁጥር 15697 የተበደረውን ብር 884,000 በአንድ አመት መክፈል የነበረበት ሲሆን ለ7 ዓመት ያዘገየና ገቢ ያላደረገ መሆኑ ከ2004 ዓ.ም የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አጠቃቀም ሪፖርት ለመረዳት መቻሉ፣
- ከዚህም በተጨማሪ ኤጀንሲው ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የተሰጠውን ብድር ከውሉ ውጭ ማራዘም ያለበት መሆኑን የሚገልጽ መመሪያ ሳይኖር በኦዲቱ ወቅት ከታዩት ኮምቦልቻ ጨርቃ- ጨርቅ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የተበደረውን 50,091,133.40 እስከ ሰኔ 30/2004 ማጠናቀቅ ሲገባው እስከ ሰኔ 30/2005 እንዲራዘምለት ማድረጉ፣ የሽቀጦች ጅምላ ንግድ አስመጪ ድርጅት የተበደረውን ብር 50 ሚሊየን ጥቅምት 30/2002 ዓ.ም አጠናቆ መክፈል ያለበት መሆኑ በውሉ ላይ የተቀመጠ ቢሆንም በውላቸው መሰረት ተመላሽ ሳያደርግ እንዲራዘምለት መደረጉ
- ኤጀንሲው በመንግስት ይዞታ ስር የነበሩ አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች ወደ ግል በሚዛወሩበት ጊዜ በውጭ ኦዲተር አስመርምረው ያለባቸውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ ገቢ እንዲያደርጉ ውል ያስገባ ቢሆንም ከሐረር ቢራ አክሲዮን ማህበር ብር 8,362,019፣ ከአምቦ ማዕድን ውሃ ብር 7,806,125፣ ከቦሌ ቡልቡላ ኮንስትራክሽን ብር 2,381,490 በድምሩ ብር 18,549,634 የመንግስት ትርፍ ድርሻ ሂሳብ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ
- ኤጀንሲው በመንግስት ይዞታ ስር የነበሩ አክሲዩን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች ወደ ግል በሚዛወሩበት ጊዜ ያለባቸውን የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ገዢ ባለሀብቶቹ እንዲከፍሉ ውል ያስገባ ቢሆንም አርባምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ብር 10,191,787፣ የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት ብር 11,976,098፣ ታቦር ሴራሚክ ውጤቶች አክሲዮን ማህበር ብር 6,220,831፣ የኢትዮጵያ ቆዳ አክሲዮን ማህበር ብር 11,780,500፣ የሃዋሳ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ብር 4,084,825 በድምሩ ብር 44,254,041 ገዢ ባለሀብቶች በገቡት ውል መሰረት ያለባቸውን የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ተመላሽ ያላደረጉ መሆኑ

- ከዚህም በተጨማሪ በመንግስት ይዞታ ስር በነበሩበት ጊዜ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር የተሰጣቸውና ሳይከፍሉ በፕራይቬታይዜሽን ሂደት ወደ መንግስትና ወደ ግል በመዞራቸው ዕዳው ወደ መንግስት ልማት ድርጅት ባለአደራ ቦርድ የተላለፈባቸው (አደይ አበባ ድርና ማግ ብር 44,339,696፣ አዲስ አበባ ፎምና ፕላስቲክ ፋብሪካ ብር 5,333,331፣ ኢትዮጵያ ቃጫ ፋብሪካ ብር 2,500,000፣ ቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብሪካ 30,000,000፣ ድሬዳዋ ጨርቃ-ጨርቅ ፋብሪካ ብር 7,000,000፣ ጥቁር አባይ ኮንስትራክሽን ብር 14,713,601) በድምሩ ብር 103,886,628 ያልተመለሰ መሆኑ
- ከዚህም ሌላ በኢትዮጵያ መንግስትና ሳይገን ግሩፕ በተባለ የቱርክ ባለሀብቶች ሳይገን ዲማ ጨርቃ-ጨርቅ አክሲዮን ማህበርን ለመመስረት በ2003 ዓ.ም ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የመንግስት ድርሻ ሂሳብ በሚከፈልበት ጊዜ 327,107.8 USD በብልጫ የተከፈለና ያልተመለሰ መሆኑ
- ኤጀንሲው የየድርጅቶቹ ዋና ሰራ አስኪያጆችና የቦርድ ሰብሳቢዎች በተገኙበት የፈንድ አጠቃቀም ግምገም በዓመት ከሁለት ጊዜ በላይ የሚያደርግ መሆኑን ቢገልፅም ከ2001-2004 ባለው ጊዜ ውስጥ የፈንድ አጠቃቀም ግምገማ ሲደረግ የተያዘ ቃለ-ጉባኤ እንዲቀርብልን ጠይቀን የቀረበው በየካቲት ወር 2004 ዓ.ም ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ተሰጥቷቸው ክፍያውን በወቅቱ ካልከፈሉ ድርጅቶች ጋር የተደረገ ስብሰባ አንድ ቃለ ጉባኤ ብቻ መሆኑ፤

  በመሆኑም ኤጀንሲው፡-

  - o የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ፕሮግራምን ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ እንዲያስችለው የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራትን የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ፍላጎት ጥናት በማድረግ በስትራቴጂክ እቅድ ውስጥ ሊያካትት እና ይህንኑ መሰረት በማድረግ አመታዊ እቅድ ሊያዘጋጅ እና ተግባራዊነቱን ሊያረጋግጥ፣
  - o የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት መክፈል የሚገባቸውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ገቢ እንዲያደርጉ ክትትል ሊያደርግ፣

- o የመንግስት የልማት ድርጅቶና አክሲዮን ማህበራት ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የወሰዱት ብድር ውጤት/ፋይዳ ያስገኘ መሆኑን ሊከታተል እና ሊቆጣጠር፣
- o አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች በፕሮጀክት ጥናታቸው በተመለከተው መርሃ-ግብር መሰረት የተፈቀደላቸውን የፈንድ ሂሳብ ገቢ እንዲደረግላቸው ሊያደርግ፣
- o የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት የወሰዱትን ብድር በገቡት ውል መሰረት ተመላሽ ማድረጋቸውን ሊከታተል፣
- o በፕራይቬታይዜሽን ሂደት ወደ ግል ይዞታ የሚዛወሩ የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት ያለባቸውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ እንዲከፍሉ ውል ሊያስገባ እና በውሉ መሰረት ገቢ እንዲያደርጉ

ከባለአደራ ቦርድ እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ፣ ሊከታተልና ሊቆጣጠር እንደሚገባ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

6.10. <u>በግብርና ሚኒስቴር የደን ሀብት ልማት እና ጥበቃ</u>

- የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ፖሊሲ፤ ስራቴጂና አዋጅ በ1999 ዓ.ም የወጣ ቢሆንም ይህን ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ተዘጋጅቶ እና ተጠናቆ ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ፤
- በጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታነት ቀደም ብለው ይዞታዎች በጥናት ላይ በተመሠረተ ሁኔታ የብዝሀ ሕይወት ስብጥራቸው መጠን እንዲጠበቅ ብሎም እንዲጨምር የሀገር በቀል የዛፍ ችግኝ ተከላ ስለመከናወኑም ሆነ የይዞታቸው ስፋት መጠን እንዲጨምር የተደረገ ጥረት ስለመኖሩ እንዲሁም በነባር የተፈጥሮ ደን ሀብትነት ከተያዙት እና በመንግስት ጥበቃ ከሚደረግላቸው በተጨማሪ ተመሳሳይ ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገቡ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች በጥናት ተለይተው እንዲያዙ ስለመደረጉ መረጃ ማግኘት አለመቻሉ፤
- በናሙና ተመርጠው የመስክ ጉብኝት የተደረገባቸው ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶችን በሚመለከት በተሰበሰበው መረጃ መሰረት፡-

- ቅድሚያ የተሰጣቸው የሀገሪቱ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች አብዛኛዎቹ የአስተዳደር ፕላን (Site Mamagement Plan) ያልተሠራላቸው፣
- የአስተዳደር ፕላን የተሠራላቸው ጥቂት ቢኖሩም የቆየ እና ወቅታዊነት የሚጎለው መሆኑ፣
- ዳር ድንበራቸው ተከልሎና ተመዝግቦ በሕግ መሠረት ዕውቅና እንዲያገኙ አለመደረጉ፤
- የብዝሀ ሕይወት ስብጥር መጠናቸው ላይ ጥናት አለመደረጉ፤
- እንዲሁም የደን ቦታዎች ላልተጠና ኢንቨስትመንት የሚሰጡበት ሁኔታ በስፋት መታየቱ እና በተለይ በክልል እና በወረዳ ደረጃ ካለበቂ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ለልማት በሚል ለባለሀብት የሚሰጡበት ሁኔታ መኖሩ ለመገንዘብ ተችሏል፤

- በተለያዩ ክልሎች ከግብርና ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ወደ 5200 ባለሀብቶች ቦታ የወሰዱ ቢሆንም ከዚህ ውስጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የተሰጠው ለ30 ብቻ በመሆኑ እና ቀሪው 5170 በክልሎች የተሰጠ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በክልል ከተሰጡት ቦታዎች ውስጥ ለ5105 ባለሀብቶች 2.1 ሚሊየን ሄክታር መሬት የአካባቢ እና የማኅበረሰብ ተጽዕኖ ሳይጠና የተሰጠ ሲሆን፣ ለ95 ባለሀብቶች ግን የአካባቢ እና የማህበረሰብ ጥናት አለመደረጉን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ ምን ያህል ሄክታር መሬት እንደተሰጠ ለማረጋገጥ መረጃ ለማግኘት አለመቻሉ፤

- በጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች ላይ በስፋት እየደረሰ ያለውን የእሳት አደጋ ለመከላከል የሚያግዙ ተግባራት ባለመከናወኑ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ሊጠበቁ የሚገቡ የተፈጥሮ ደኖች በየጊዜው ከአካባቢው ኅብረተሰብ በሚደርስባቸው ጫና መጠናቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ እንዲሄድ ማድረጉ፤

- የሀገሪቱን የደን ሀብት ሁኔታ የሚያሳዩ ወቅታዊ መረጃዎች በየጊዜው እየተጠናቀሩ የማይያዙ ሲሆን ያሉት መረጃዎችም ከ20 ዓመታት በላይ የቆዩ እና እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ መሆኑ፤

- እንዲሁም የደን ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ ጥቅሞችን በግልጽ የሚያሳይ የመረጃ ቋት አለመኖሩ፤

- በፌደራል ደረጃም ሆነ በክልል ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀምን በተመለከተ መረጃ ለመለዋወጥ የሚችሉበት የአሠራር ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤
- በሀገር አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ ችግኞች የሚተከሉ ቢሆንም የተተከሉበት አካባቢ፣ የቦታው ስፋት፣ ምን ያህልና ምን አይነት ችግኞች እንደተተከሉ፣ የፀደቀው መጠን፣ የታለመለትን አገልግሎት እስኪሰጥ ድረስ እየተደረገ ያለውን ክትትል የሚያሳይ መረጃ ተጠናቅሮ የማይቀመጥ መሆኑ፤
- የዛፍ ችግኞች ከተተከሉ በኋላ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ በቂ ክትትል የማይደረግ ሲሆን ከተከላ በኃላ ችግኞች ለታሰበው ዓላማ ስለመዋላቸው ጥናት አለመደረጉ፤
- የደን መዋቅር ለረጅም ዘመናት በፍጥነት የሚቀያየር እና ያልተረጋጋ እንደነበር፤ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በፌደራል ደረጃ ይህንንም ተግባር ለማከናወን የተመደበው የሰው ኃይል እና ባለሙያዎች የሥራውን ስፋት እና መጠን ያላገናዘበ መሆኑን፤ በክልሎችም የደን ልማት እና ጥበቃን የሚያከናውን አካል በበቂ አደረጃጀት እና ባለሙያ አለመጠናከሩ፤
- በደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ዙሪያ በግለሰብ፤ በማህበርና በባለሀብቶች ደረጃ የሚደረግ ተሳትፎን የሚያመለክቱ መረጃዎችን በማሰባሰብ በአግባቡ ለመያዝ እና ክልሎች በዚህ መልኩ እንዲይዙ የሚደረግ ክትትልና ቁጥጥር አለመኖሩ፤

በመሆኑም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የደን ሀብት ለአንድ ማኅበረሰብ ብሎም ለሀገር ህልውና የሚሰጠው ዘርፈ ብዙ (multi purpose) ጠቀሜታ ከፍተኛ እና በገንዘብ የማይለካ ከመሆኑ አንፃር፡-

- በስፋት እየታየ ያለውን የደን ሀብት መኅሳቆል እና መውደም ለመቀነስ ትኩረት በመስጠት በአግባቡ ለማልማት፣ ለመጠበቅ እና ዘላቂነትን የተከተለ አጠቀምን ለማጎልበት ያወጣቸውን አዋጅ እና ፖሊሲ ለማስፈጸም የሚረዱ አግባብነት ያላቸው ደንብና መመሪያዎች በፌዴራልም ሆነ በክልል ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲዘጋጁ እና ጸድቀው ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ ቀጣይነት ባለው መልኩ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ፤

- የሀገሪቱን የብዝሀ ህይወት ሀብት የያዙ ቅድሚያ የተሰጣቸው የተፈጥሮ ደን ቦታዎችን የመጠበቅ ተግባር ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በየደረጃው የሚገኙ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ ዳር ድንበራቸው ተከልሎ የየራሳቸው ሕጋዊ እውቅና ያለው ይዞታ እንዲኖራቸው እና በማዕከላዊ (core)፣ መከላከያ (buffer) እና መሸጋገሪያ (transition) ዞን ተለይተው የአስተዳደር ፕላን (Site Mamagement Plan) እንዲዘጋጅላቸው፤
- የአካባቢውን ሕብረተሰብ ባሳተፈ ሁኔታ እንደ አስፈላጊነቱ ከአካባቢው ሕብረተሰብ በሚቀጠሩ የደን ዘቦች ጥበቃ እየተደረገላቸው ከህገወጥ ሠፈራ፣ ከደን ጭፍጨፋ፣ በእሳት የሚደርሰውን የደን ቃጠሎ ብዛትና የጉዳት መጠን ለመቀነስ እና ከሌሎች ደኑን ከሚጎዱ ሁኔታዎች እንዲጠበቁ፤
- በተፈጥሮ ደን ይዞታዎች ላይ ጥፋት በፈፀሙ አካላት ላይ ፈጣንና ተመጣጣኝ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ እንዲቻል የፍትህ አካላት ግንዛቤ ዳብሮ ተገቢውን ህጋዊ ድጋፍ የሚያደርጉበት ሁኔታ እንዲመቻች፤
- በነባር የተፈጥሮ ደን ሀብትነት የተያዙ ይዞታዎች የብዝሀ ሕይወት ስብጥራቸው የተጠበቀ እና የተሻለ እንዲሆን እንዲሁም የነበራቸው የይዞታ መጠን እንዲጨምር በጥናት ላይ የተመሠረተ የሀገር በቀል የዛፍ ችግኝ ተከላ እንዲከናወን፤
- በነባር የተፈጥሮ ደን ሀብትነት ከተያዙት እና በመንግስት ጥበቃ እየተደረገላቸው ካሉት በተጨማሪ ተመሳሳይ ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገቡ የተፈጥሮ ደን አካባቢዎችን በጥናት በመለየት ጥበቃ ሊደረግላቸው፤
- ለደን እና ለሌሎች የልማት ተግባራት የሚሆኑ ቦታዎች የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በየደረጃው በማሳተፍ በቅድሚያ ተጠንተው እንዲለዩ፤
- በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አተገባበር ላይ ተገቢው ግንዛቤ እንዲዳብር በማድረግ በልማት ፕሮጀክቶች ላይ የተሻለ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ እንደ አስፈላጊነቱ ማከናወን የሚያስችል ሁኔታን ለመፍጠር ጥረት ሊደረግ እንደሚገባ፤
- በተለይ ለቡና ልማት የተፈጥሮ ደን ይዞታዎችን ከመስጠት ይልቅ በአጭር ጊዜ ሊደርሱ የሚችሉ የጥላ ዛፎችን የደን ይዞታቸው በተመናመነ ቦታዎች ላይ በመትከል ማልማት የሚቻልበት ልምድ እንዲዳብር ጥረት ሊደረግ እንደሚገባ፤ ይህንንም ለማከናወን የሚያስችል አደረጃጀት በሚኒስተር

መ/ቤቱም ሆነ በክልል እና በወረዳ ደረጃ መፍጠር እና እንዲጠናከር መርዳት እንደሚገባ፤

በተጨማሪም የሀገራችን የደን ሀብት ለማልማት የሚወጣው ከፍተኛ ወጪ የተፈለገውን ውጤት ለማምጣ በሚችሉ ተገባራት ላይ እየዋለ መሆኑን ለመከታተል እና አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በወቅቱ ለመውሰድ ብሎም በቀጣይ በተሻለ ሁኔታ ተግባራዊ የሚሆን ዕቅድ ለማቀድ እንዲቻል፤

- የተፈጥሮ ደኑን በተለይም ከፍተኛ የብዝሀ ህይወት ክምችት ይዘው የሚገኙትን ጥብቅ የተፈጥሮ ደን አካባቢዎች ሁኔታን የሚመለከቱ መረጃዎች፣
- በመንግሥት ለደን ልማት ተግባር በተከለሉ አካባቢዎች ላይ በየዓመቱ የተተከሉ ችግኞች አይነት እና መጠን፤ ከተከላ ጊዜአቸው ጀምሮ በየደረጃው የተደረግላቸው እንክብካቤ እና ጥበቃ፤
- ከተተከሉት ጠቅላላ ችግኞች ውስጥ ምን ያህሉ እንደጸደቁ እና በሂደት የሀገሪቱ የተፈጥሮም ሆነ የተተከሉ የደን ሀብቶች እያስገኙ ያለው ጠቀሜታን የሚያሳዩ መረጃዎች በአግባቡ እንዲጠናቀሩ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባ፤

- ከሚመለከታቸው የፌደራል፣ የክልል እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የደን ሀብት የሚመለከቱ አግባብነት ያላቸው መረጃዎች በማያቋርጥና መደበኛ በሆነ መልኩ ልውውጥ ሊደረግ የሚችልበት ሁኔታ ሊመቻች እንደሚገባ፤
- የሀገራችን የተፈጥሮ ደንን ከተጋረጠበት ጨርሶ የመጥፋት አደጋ ለመታደግ የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀምን በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ሊያከናውን የሚችል በተገቢው የአሠራር ስልት እና የሰው ኃይል የተጠናከረ አደረጃጀት ሊኖር እንደሚገባ፤
- በቀጥታ ደንን በማልማት፣ በመጠበቅ እና ዘላቂነትን የተከተለ አጠቃቀም ለመፍጠር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎችም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ /በጥምር ግብርና/ ዛፎችን በመትከል የሚደረጉ እንቅስቃሰዎች በባለሙያ በተደገፈ ሁኔታ እንዲከናወኑ ለማድረግ በየደረጃው በሰው ኃይልም ሆነ በቁሳቁስ የተሻለ አደረጃጀት እንዲፈጠር ጥረት ሊደረግ እንደሚገባ፤

- በአገር አቀፍ ደረጃ የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃ እና ዘላቂነትን የተከተለ የአጠቃቀም ልምድን ከማዳበር አኳያ ከግል፤ ከማህበር፣ ከድርጅት እና ከባለሀብቶች በኩል የሚጠበቀውን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ ተገቢውን ጥናት ማድረግ እና የደን የይዞታ መጠን እና የአጠቃቀም ሁኔታን የሚያሳዩ መረጃዎችን በማሰባሰብ በአግባቡ እንዲያዙ ሊደረግ እንደሚገባ በመግለጽ በኦዲት ሪፖርቱ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቷል፡፡

6.11. የፌዴራል መንግስት ቢሮዎች ሕንጻ ግንባታ

- የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እያከናወናቸው ያሉ እና የተጠናቀቁ የቢሮ ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከተያዘላቸው የጊዜ በጀት በላይ የሚወስዱ መሆኑ፤
- በተያዘለቸው እቅድ መሰረት በስምንት ወራት ውስጥ ይጠናቀቃሉ ተብሎ የግንባታ ስራቸው የተጀመረ ሦስት ፕሮጀክቶች እያንዳንዳቸው ከታቀደላቸው ግዜ በላይ ሁለት ዓመታት በመውሰድ የተጠናቀቁ፤
- በኦዲቱ ወቅት ከታዩ አምስት በግንባታ ላይ ካሉ ፕሮጀክቶች ውስጥ፡-
    - የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስተር ተጨማሪ ብሎክ ህንፃ ግንባታ በጥቅምት 2001 የተጀመረ ሲሆን፣ የዚህ ፕሮጀክት የግንባታ መጠናቀቂያ ጊዜ ሐምሌ 2001 እንዲሆን ታቅዶ የነበረ ቢሆንም እስከ ሰኔ 2004 ድረስ ፕሮጀክቱ እንዳልተጠናቀቀ ለማወቅ ተችሏል፣
    - የፍትህ ሚኒስቴር የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት በሐምሌ 2001 እንዲጠናቀቅ ታስቦ ህዳር 2001 ላይ ተጀምሯል ሆኖም ግን እስከ ሰኔ 2004 ድረስ የተከናወነው የህንፃ ግንባታው 58% ብቻ መሆኑ፡፡



ስዕል 1.ግንባታቸው የዘገየ ፕሮጀክቶች (ምንጭ:የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፋይሎች)

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በኮንትራክተሮች መካከል በተፈረመው የኮንትራክት ስምምነት መሰረት የግንባታ እቃዎች የሚቀርቡት በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ መሆኑ ተገልጿል፡፡ በአዲቱ ወቅት መጠይቅ ከቀረበላቸው የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ምላሽ እንዲሁም በተለያየ ጊዜ ከስራ ተቋራጮች ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከተጻፉ ደብዳቤዎች የግንባታ እቃዎች በወቅቱ አለመቅረብ የኮንስትራክሽን ግንባታዎች በተደጋጋሚ ለወራት እንዲቆሙ ምክንያት መሆኑ፤

- የቢሮ ህንጻ ግንባታዎች መዘግየት ፕሮጀክቶች ከተያዘላቸው የገንዘብ በጀት በላይ እንዲያስወጡ የሚያደርግ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በኦዲቱ ወቅት እንደታየው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የግብርና ሚኒስቴር እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የቢሮ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከተያዘላቸው የገንዘብ በጀት በላይ 8.7 ሚሊዮን ብር ያስወጡ ሲሆን፣ ይህም በአማካይ ሲሰላ የየፕሮጀክቶቹን ወጪ በጀት 20% የሚጠጋ መሆኑ፤

- ፕሮጀክቶች ከተያዘላቸው የጊዜና የወጪ በጀት በላይ የሚከናወኑ በመሆኑ በፕሮጀክቶቹ የስራ ዝርዝር (bill of quantities) እና ለፕሮጀክቶቹ ግንባታ በጥቅም ላይ በዋለው የግብዓቶች መጠን መካከል ሰፊ ልዩነት የሚታይ መሆኑ፤

- ለስታስቲስቲክስ ኤጀንሲ የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት ከመሬት በታች ግንባታ ሥራ (substructure work) በስራ ዝርዝር (bill of quantities) በተመለከተው እና በጥቅም ላይ በዋለው ግብአት መካከል ወደ ግማሽ ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ልዩነት መኖሩ፤
- ለፕሬስ ድርጅት የቢሮ ህንፃ ግንባታ በስራ ዝርዝር (bill of quantities) እና ፕሮጀክት ዲዛይን አለመጣጣም ምክንያት ተጨማሪ 22,434 ኪሎ ግራም ብረት በማስፈለጉ፤ በተደጋጋሚ ያጋጠሙ ተመሳሳይ ልዩነቶች የፕሮጀክት ጽ/ቤቱን የተሻሻለ የስራ ዝርዝር(bill of quantities) ከአማካሪው እንዲጠይቅ ማስገደዱ፤
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከጨረታ በኋላ አሸናፊውን ለማሳወቅ እና ውል ለመፈራረም የሚወስደው ጊዜ በግዥ መመሪያው ላይ ከተቀመጠው ጊዜ በላይ መሆኑ፤ በመንግስት የግዥ መመሪያ አንቀፅ 16 መሰረት ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ የጨረታውን አሸናፊ መግለጽና ውል መፈራረም የሚጠበቅበት ሲሆን ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለማእከላዊ

ስታስቲክስ ኤጀንሲ፣ ለፕሬስ ድርጅት እና ለገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ተጨማሪ ብሎክ ለማሰራት በግንቦት 2002 ጨረታ ካወጣ በኋላ ኮንትራት ለመፈራረም 9 ወራት መውሰዱ፤

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አንዳንድ የግንባታ ፕሮጀክቶችን ለኮንትራክተሮች የመንግስት የግዥ አዋጅ እና መመሪያን ሳይከተል የሚሰጥ መሆኑ፤
- በዚህም ምክኒያት በኦዲቱ ወቅት ከታዩ 8 ፕሮጀክቶች ውስጥ ሶስቱ ካለጨረታ በቀጥታ ለአንድ ሕንጻ ስራ ተቋራጭ የሰጠ መሆኑ፤
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የግንባታ እቃዎች ፕሮጀክቶቹን ለሚገነቡ ስራ ተቋራጮች የሚቀርቡት የተያዘላቸውን የጊዜ ሠሌዳ ጠብቀው አለመሆኑ እና በግንባታ እቃዎች አቅርቦት መዘግየት ምክንያት ግንባታዎች በተደጋጋሚ ከወር በላይ የሚስተጓጎሉ መሆኑ፤

በመሆኑም የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ፡-

- ለግንባታ እቃዎች ፍላጎት እቅድ በማውጣት እና የግንባታ እቃዎች የሚገኙበትን መንገድ ቀድሞ በመፈለግ እንዲሁም ለሚከሰቱ ችግሮች ከሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች ጋር መደበኛ ግንኙነት በመፍጠር እና መፍትሄ በመስጠት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ እና የገንዘብ በጀት እንዲጠናቀቁ ሊያደርግ፤
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጨረታ ካወጣ በኋላ በመንግስት የግዥ መመሪያ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የጨረታ አሸናፊዎችን በወቅቱ ሊያሳውቅ እና ኮንትራት ሊፈራረም እንደሚገባ፤
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚሰሩ የግንባታ ሥራዎች ለማከናወን መወዳደር የሚችሉ ህንጻ ተቋራጮችን ሊያሳትፍ የሚችል ግልጽ የጨረታ ሂደት በማካሄድ እና በማወዳደር የተሻለ ብቃት ላላቸው ተወዳዳሪዎች ሊሰጥ እንደሚገባ፤
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለግንባታ እቃዎችን አስቀድሞ በማከማቸት ለየፕሮጀክቶቹ አግባብ ባለው ጊዜ ለማድረስ የሚያስችል የስርጭት ዘዴ ሊቀይስ እንደሚገባ በመግለጽ በኦዲት ሪፖርቱ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቷል፡፡

6.12. <u>በንግድ ሚኒስቴር ቀጥተኛ ክትትል የሚደረግባቸው የግብርና ምርቶች ውጭ ንግድ ማስፋፊያ ሥርዓት አፈጻጸም እና ውጤታማነት በተመለከተ</u>

- ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች በተለይ ደግሞ ወደ ዘመናዊ ግብይት ያልገቡት ምርቶች ላይ ተገቢውን የጥራት ደረጃ እንዲያሟሉ በየደረጃው በሚገኙ አካላት በየምርቶቹ ባህሪና ዓይነት ከማሳ እስከ ማዕከል ባለው ሰንሰለት ቼክሊስት በማዘጋጀት የሚደረግ የተጠናከረ ወቅታዊ የጥራት ክትትል አለመኖሩ፤
- የንግድ ሚኒስቴር የግብይት አዋጅና ደንብ ላልወጣላቸው ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች የግብይት አዋጅ እና ደንብ እንዲወጣላቸው፤ ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር ምርቶቹ በሚመረቱበት አካባቢ የመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከላት እንዲገነቡ እና ተገቢውን የጥራት ደረጃ እንዲያሟሉ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ አለማድረጉ፤
- የንግድ ሚኒስቴር ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን ጥራት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ የጥራትና ደረጃ ማዕከላት ምርቶቹ በሚመረቱባቸው አካባቢዎች እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ በማድረግ የማዕከላቱን ውጤታማነት መከታተል ሲኖርበት የጥራትና ደረጃ ማዕከላት ወደ ውጭ ገበያ በሚቀርቡ በሁሉም የግብርና የምርት አይነቶች እና የግብርና ምርቶቹ በሚመረቱበት በቅርብ አካባቢ እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ አለማድረጉ፤
- ለንግድ ሚኒስቴር ተጠሪ ከሆኑት መስሪያ ቤቶች አንዱ በሆነው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚላኩ የግብርና ምርቶች ላይ የሚታዩ የጥራት ችግሮች እንዲሻሻሉ በግብይት ስርዓቱ የቀረበው ምርት ያገኘውን ደረጃ እና ምርቱ ያለበትን የጥራት ችግሮች እንዲያሻሽሉ ለአምራች አርሶ አደሮችና ለግብርና ባለሙያዎች የሚደርስበት የግብረ መልስ (feed back) ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ሲገባ የንግድ ሚኒስቴርም ይህ ስርዓት ሥራ ላይ ስለመዋሉ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ ሲጠበቅበት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለውጭ ሀገር ገበያ በአቅራቢዎች የሚቀርበው የግብርና ምርት ያገኘውን ደረጃና በጥራቱ ላይ የታዩ ጉድለቶች እንዲሻሻሉ ለማስቻል ግብረ መልስ (feed

back) ለግብርና ባለሙያዎች እና ለአርሶ አደሮች እንዲደርሳቸው የማይደረግ መሆኑ፤

- የግብርና ምርት ላኪዎች (exporters) ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚገዙት ምርት የኪሎ ጉድለት የሚያሳይ እና በተገዛው የጥራት ደረጃ ልክ የማይደርሳቸው መሆኑ
- የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የግብርና ምርቶች የመገበያያ ዋጋ ከዓለም የገበያ ዋጋ ጋር የማይጣጣም፤ የመጋዘን አገልግሎት አሰጣጡም ቀልጣፋ አለመሆኑ፤
- የንግድ ሚኒስቴር ወደ ዘመናዊ የግብይት ስርዓት ያልገቡና በውጭ ሀገራት ገበያዎች የሚፈለጉ የግብርና ምርት አይነቶችን እና በየሀገራቱ የሚፈለገውን የጥራት ዓይነት እና መጠን በማጥናት መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመተንተንና በማጠናከር ምርቶቹ ሊመረቱባቸው በሚችሉ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች የግብርናና የግብይት ቢሮዎች እንዲሁም ለላኪዎች እንዲደርሳቸው አለመደረጉ፤
- የንግድ ሚኒስቴር ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚላኩ ዋና ዋና የግብርና ምርቶችን የገበያ ፍላጎት እና የዋጋ ትንቢያ ጥናት በማድረግ ውጤቱ ለላኪዎችና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲሰራጭ አለማድረጉ፤
- የንግድ ሚኒስቴር በግብርና ምርቶች የውጭ ግብይት ለተሰማሩ አካላት የተሻለ ተወዳዳሪ እና ውጤታማ ሊያደርጋቸው የሚችል በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ባለሙያ የተደራጀ የመረጃ አያያዝ ስርዓት በመዘርጋት ለዘርፉ የሚያስፈልጉትን የዓለም አቀፍ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመተንተንና በማጠናከር ለላኪዎች፣ በምርት ሂደት እና በግብይት ስርዓቱ ለሚሣተፉ አካላት ፈጣንና ወቅታዊ መረጃ ሊያሠራጭ እና ለዘርፉ የመረጃ ቋት (data base) ማዕከል በመሆን ማገልገል አለመቻሉ፤
- የንግድ ሚኒስቴር በክልል ከተደራጁ የኤክስፖርት ልማት ድጋፍ ኮሚቴዎች ጋር በመሆን በሥራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በወቅቱ እንዲፈቱ ለማድረግ የሚያስችል ወቅታዊ የውይይት መድረክ አለመዘጋጀቱ፤
- የንግድ ሚኒስቴር ለውጭ ንግድ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን በጥራት ለማቅረብ የሚያግዙ ደረጃቸውን የጠበቁ በቂ የጆኒያ፣ የፒፒ ከረጢት እና

የቡና ማስጫ አልጋ ለመሥራት የሚያገለግል ሽቦ አርሶ አደሮች በተመጣጣኝ ዋጋ ከአቅራቢዎች እንዲያገኙ ከጅኒያና ፒፒ ከረጢት አምራች ድርጅቶች ጋር የማቀናጀትና የማስተሳሰር ሥራ ባለመስራቱ አርሶአደሮች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ማድረግ አለመቻሉ እና እጥረት መከሰቱ፤

- የንግድ ሚኒስቴር ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶች በዘመናዊ እና ህጋዊ የግብይት ሥርዓት ውስጥ ገብተው የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ በማሟላት እንዲያቀርቡ ለማስቻል የህገ-ወጥ ግብይትን ለመግታት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል፣ የክልል፣ የዞን እና የወረዳ አካላት ጋር በመቀናጀት የተጠናከረ የቁጥጥር ሥራ አለማድረጉ፤

የሚሉት በኦዲቱ ወቅት የታዩ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

በመሆኑም ከላይ የተመለከቱትን ድክመቶች ለማሻሻል አስተዋጾ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሀሳቦች ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በላክነው ሪፖርት በማካተት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲያደርጋቸው አሳስበናል፡፡

6.13. <u>በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጠው የህክምና አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ</u>

- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች በስራ ላይ የሚውል የተጠናከረ አገር አቀፍ የህሙማን አላላክና አቀባበል /ሪፈራል/ ስርዓት በመዘርጋት በአገሪቷ ያሉ ሆስፒታሎች ተቀናጅተውና ተናበው እንዲሰሩ ማድረግ ወጥ የሆነ የሪፈራል መመሪያ በማዘጋጀት በመመሪያው ላይ ግንዛቤ እንዲሁም ታካሚዎችን መሰረት ያደረገ የህክምና ሥነ-ምግባር መመሪያ (ethical and medico-legal regulation) ሊያወጣ ባለመቻሉ የሪፈራል ሆስፒታሎች የእርስ በርስ ትስስር እና በሆስፒታሎች ውስጥ እና በሆስፒታሎች መካከል ተናቦ የመስራት (inter and intra hospital communication) ሁኔታ አለመኖሩ፣
- ተመላላሽ ታካሚዎች በማንኛውም የስራ ስዓት ሊስተናገዱ፣ በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ዕቅድ መሰረት ታካሚዎች ሆስፒታል በደረሱ በ2 ስዓት ጊዜ ውስጥ አገልግሎት ሊያገኙ እንዲሁም የሆስፒታሉ ሀኪሞች ለሚያደርጉት የጠዋት ስብሰባ የመሰብሰቢያ ስዓት የጊዜ ገደብ

ሊያስቀምጡ ሲገባ የጥቁር አንበሣ ሆስፒታል እና የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ ታካሚዎችን የሚቀበሉት ጠዋት ብቻ መሆኑን፤

- በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት እቅድ መሰረት ሁሉም ታካሚዎች በ2 ሰዓት ውስጥ አገልግሎት የማያገኙ መሆኑ
- በአራቱም ኦዲቱ በተከናወነባቸው የሪፈራል ሆስፒታሎች (በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፣ በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ በጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል እና በጅማ ዩኒቨርስቲ ሪፈራል ሆስፒታል) የዶክተሮች የጠዋት ስብሰባ የሠዓት ገደብ የሌለው መሆኑ፤
- ከስብሰባ በኋላ በሻይ እረፍት ምክንያት ታካሚዎች ከ2 ሰዓት በላይ ዶክተሮችን የሚጠብቁ መሆኑ፣
- በፌደራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ውስጥ የሚገኙ የተመላላሽ፣ የተኝቶ ህክምና እና የድንገተኛ ህክምና ክፍሎችን በቀላሉ ለመለየት በሚያስችሉ ምልክቶች የሌሉዋቸው ሲሆን ያልተማረው የህብረተሰብ ክፍልም በቀለም ቅባቸው (ለምሳሌ ሰማያዊ ለተመላላሽ ታካሚ ክፍል፣ ቀይ ለድንገተኛ ታካሚ ክፍል ወዘተ በመቀባት) ለመለየት እንዲያስችለው በተለየ ሁኔታ አለመቀባታቸው፤
- የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች አገልግሎት አሰጣጥን በበላይነት የሚመራና የሚከታተል የተጠናከረ የሆስፒታል አስተዳደር ቦርድ ሊያቋቁሙ ሲገባ በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የሆስፒታል አስተዳደር ቦርድ ያልተቋቋመ መሆኑ፤ በዚህም ምክኒያት ሆስፒታሉ የውስጥ ገቢውን በቦርድ አስፈቅዶ መጠቀም፣ መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ለመተገበር፣ የሆስፒታሉን እስትራቴጂክ እና አመታዊ እቅድ ማዘጋጀትና ማፀደቅ አለመቻሉ፤
- በተመሣሣይ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የራሱ የሆነ የአስተዳደር ቦርድ የሌለው በመሆኑ፣ አመታዊ እና እስትራቴጂክ እቅዱን እንዲሁም የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱን አዘጋጅቶ በጤና ጥበቃ ስር የሚተዳደሩ ሌሎች የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎችን ብቻ ለሚከታተለው የፌዴራል ሆስፒታሎች ቦርድ የሚያቀርብ መሆኑ፣

- የጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል ስትራቴጂክ እና አመታዊ ዕቅድ የሚያዘጋጅ ቢሆንም በሆስፒታሉ እና በዩኒቨርስቲው መካከል በቅንጅት ተናቦ የመስራት እና የማቀድ ችግር መኖሩ፤
- የትምህርት ሚኒስቴር እና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በስራቸው የሚገኙ የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሚሰጡትን የህክምና አገልግሎት በተቀላጠፈ መልኩ መስጠታቸውን እንዲሁም አስፈላጊ መድሃኒቶችን እና የህክምና መሳሪያዎችን አቅርቦትና አጠቃቀም መኖሩን በቅንጅት ሊከታተሉ ሲገባ
    - የቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ በመደበኛነት የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ድግሞ በአልፎአልፎ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ክትትልና ድጋፍ የሚያገኙ ሲሆን የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ከትምህርት ሚኒስቴር ግን የቴክኒክ ድጋፍም ሆነ ክትትል የማያገኝ መሆኑ፣
    - የጎንደርና የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ ከትምህርት ሚኒስቴር መደበኛ ክትትል አለማግኘታቸው፣
    - የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶችንና የህክምና መገልገያ ቁሣቁሶችን አቅርቦትና አጠቃቀም በመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ እና በመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን አማካኝነት ክትትል የሚያደርግ ሲሆን የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የጅማና የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች በዚህ ዙሪያ ከየትኛውም አካል መደበኛ የሆነ ክትትልና ድጋፍ የማይደረግላቸው መሆኑ፤
- የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ላቦራቶሪዎች ምቹ የሥራ ቦታ እና አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች (‘ሪኤጀንት’፣ ‘አናላይዘር’፣ ‘ኮንስዩሜብልስ’ ወዘተ) ሊኖራቸው፤ የላቦራቶሪ ናሙና አሰባሰብ፣ አያያዝ እና አወጋገድ በተመለከተ መመሪያ ሊኖራቸው፤ እንዲሁም የላቦራቶሪ ክፍል የምርመራ ውጤት እንደደረሰ ለታካሚዎች ሊሰጧቸው ሲገባ የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የላብራቶሪ ናሙና አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ የተለየ መመሪያ የሌለው መሆኑ፣ በቂ የላቡራቶሪ

ክፍል፣ ናሙና መቀበያ ቦታ እና የግብአት አቅርቦት ችግር መኖራቸውን እንዲሁም የ'ኬሚስትሪ ባክአፕ' እና 'ዩፒኤስ' እጥረት ያለበት መሆኑ፣

- በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የላቦራቶሪ ጥራት መመሪያ፣ የላቦራቶሪ ባዮ ሴፍቲ መመሪያ እና ለማህበረሰብ የጤና ላቦራቶሪዎች የጤና እና ደህንነት መመሪያዎች ቢኖሩም በመመሪያው መሰረት ሙሉ በሙሉ አለመተግበሩ፤ እንዲሁም በሆስፒታሉ የላቦራቶሪ ግብዓት እጥረት (reagent, hormone analyzer)፣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች እጥረትና በቂ ቦታ ባለመኖሩ የካንሰር ምርመራ መስራት እንዳልተቻለ መገለጹ፣
- በጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የላብራቶሪ ናሙና አሰባሰብን በተመለከተ ፖሊሲ እና መመሪያ ቢኖርም የሆስፒታሉ ላብራቶሪ የሪኤጀንት እና ማቅለጫዎች አቅርቦት ችግር፣ የላብራቶሪ ቁሣቁሶች እጥረት፣ የናሙና መጓጓዣ ችግር፣ የናሙና መሰብሰቢያ ቅፅ ላይ ሙሉ የሆነ የታካሚ መረጃ ያለመሙላት፣ የናሙና እና የውጤት አያያዝ ችግሮች ማለትም ያለቦታ የማስቀመጥ፣ ቦታውን መቀየር እና የናሙና ውጤት መጥፋት ችግሮች መኖራቸው፣
- በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሚሰጡ ትምህርት እና ስልጠናዎች የህክምና አገልግሎት አሰጣጡን የማይጎዱ ሊሆኑ እና ሆስፒታሎች የህክምና ዶክተሮችን በስራ ሰዓት ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ ሊኖራቸው ሲገባ በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ በጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል እና በጅማ ዩኒቨርስቲ ሪፈራል ሆስፒታል የህክምና እና የማስተማር አገልግሎት ላይ የትኛው ቅድሚያ ማግኘት አለበት በሚለው ዙሪያ ግልፅ የሆነ አሰራር አለመኖር ይህም በህክምና ዶክተሮች መሀከል እያከሙ ማስተማር (ለህክምና አገልግሎት ቅድሚያ መስጠት) ወይንም እያስተማሩ ማከም (ለትምህርትና ስልጠናዎች ቅድሚያ መስጠት) የሚል ግልፅ የሆነ የግንዛቤ እጥረቶች መኖራቸው፤ ይህንንም ለመወሰን የተዘጋጀ ግልፅና ወጥ መመሪያ ያለመኖሩ፤ እንዲሁም ሃኪሞች የስራ ሰዓታቸውን ለሆስፒታሉ አገልግሎት ብቻ የሚያውሉ መሆኑን የሚከታተሉበትና የሚቆጣጠሩበት ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣

- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ ለህክምና አሰጣጥና እና ለትምህርት የተመደበ ስዓትን በተመለከተ የኮሌጁ ሕግ 40% ለህክምና አገልግሎት፣ 40% ለትምህርት እና 20% ለምርምር ሥራ እንዲያውሉ የሚደነግግ ቢሆንም የሐኪሞች የሰዓት አጠቃቀምን የሚገልፅ መረጃ አለመገኘቱ፣ እንዲሁም ሐኪሞችን በስራ ስዓት ለመከታተል የሚያስችል ዘዴ እና አሰራር አለመኖሩ፣
- የተመላላሽ ህክምና ክፍል ሐኪሞች በመደበኛ የሥራ ሰዓት ከሥራቸው የማይገኙበት፣ ዘግይተው የሚገቡበት እና የመውጫ ስዓት ሳይደርስ ቀድመው የሚወጡባቸው ሁኔታዎች በመኖሩ ታካሚዎች የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት ብዙ ስዓት በመጠበቅ እንደሚጉላሉ እና ለተጨማሪ ወጪ የሚዳረጉ መሆኑ(በተለይ ከገጠርና ከሩቅ ቦታ በሚመጡ ታካሚዎች)፤
- ተመላላሽ ታካሚዎች በሆስፒታሉ በተመዘገቡበት ዕለት በስፔሻሊስት ሃኪም የህክምና አገልግሎት ሊያገኙ ሲገባ
  - በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተመላላሽ ታካሚዎች በጠቅላላ ሀኪም ወይንም በሪዚደንት ሀኪም የሚታዩ መሆኑ፣
  - በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የአእምሮ እና የአይን ታካሚዎች በስፔሻሊስት የሚታዩ ሲሆን ሌሎች ታካሚዎች ግን ስፔሻሊስት የማያገኙ መሆኑ፤
- በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ውጤት መሰረት ሁሉም ተመላላሽ ታካሚዎች ስፔሻሊስት፣ ሪዚደንት ሀኪም፣ ጠቅላላ ሀኪም እና ተማሪ ሀኪምን ባካተተ ቡድን እንደሚመረመሩ ቢገልፅም ስፔሻሊስት ሃኪሞች እንደማይገኙ እና ሌሎቹም ቢሆኑ በተሟላ ሁኔታ የማይገኙ መሆኑ፣
- የጅማና የጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች ተመላላሽ ታካሚዎችን ካለ መላኪያ/ሪፈር ወረቀት ስለሚቀበሉ እና የስፔሻሊስት ሀኪሞች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ ህሙማኑ በተማሪ ሀኪም እንደታዩ የሚደረግ መሆኑ፣
- በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ለታካሚዎች አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል በቂ የሆነ የህክምና እና የዲያግኖስቲክ መሳሪያዎች ሊኖሩ እንዲሁም የህክምና መሳሪያዎች ከአገልግሎት በፊትና ከአገልግሎት በኋላ መደበኛ የሆነ የፍተሻ እና የጥገና አገልግሎት ሊደረግላቸው ሲገባ፤ በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል

- o የ ‘ማግኔቲክ ሪዞናንት ኢሜጅንግ’ (MRI) ማሽን የሌለው ሲሆን የኬሚስትሪ ማሽን እጥረት መኖሩ መገለጹ፣
  - o የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች የጥገና ችግር መኖሩን፣ በሆስፒታሉ የህክምና መሳሪያዎች ጥገና ክፍል (bio-medical engineering department) የተቋቋመ ቢሆንም የሚሰጠው አገልግሎት ከሆስፒታሉ ፍላጎት አንፃር በቂ ያለመሆኑ እና የቅድመ መከላከል ፍተሻ አገልግሎት እንደማይሰጥ፣
  - o የአንዳንድ መሳሪያዎች ግዥ ከአንድ አቅራቢ ብቻ የሚፈፀም በመሆኑ የጥገናውንም አገልግሎት የሚሰጠው አቅራቢው ብቻ በመሆኑ ሙሉ የጥገና አገልግሎት ለማግኘት የሚዘገይ መሆኑ፣
- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ እንደ ሦስተኛ ደረጃ ሆስፒታል በቂ የህክምና እና የምርመራ መሣሪያዎች የሌሉት መሆኑ፣
  - o የላብራቶሪ ማሽኖች ለምሳሌ ሆርሞን አናላይዘር፣ ቫይራል ሎድ፣ ፋክስ ካሊበር፣ 5DF፤ ሂማቶሎጂ እና የምርመራ መሣሪያዎች እንደ ‘ሲቲስካን’ (CT-Scan) የተከላ ስራው ቢጀመርም አለመጠናቀቁ፤
  - o የ ‘ማግኔቲክ ሪዞናንት ኢሜጅንግ’ (MRI) በከፍተኛ ወጪ ግዥ ቢፈፀምም የማሽኑ ማስቀመጫ ቦታ ግንባታ ባለመጠናቀቁ ምክንያት ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ ያልተተከለ መሆኑ፣
  - o ማሞግራፍ፣ ቫስኩላር አልትራሳውንድ በቦታ እጥረት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፤
  - o በተመላላሽ ህክምና ክፍል ‘ኤሌክትሮካርዲዎግራም’ (ECG) እና ‘ኢኮካርዲዎግራም’ (ECO-Cardiogram) መሳሪያዎች የሌሉት መሆኑ፤
- በጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል የሕክምና መሣሪያዎች ከተጠቃሚዎች ብዛት አንፃር ሲታይ በቂ አለመሆኑ እና ሆስፒታሉ ለህክምና መሣሪያዎች የጥገና አገልግሎት የሚሰጥ ክፍል በ2004 ዓ.ም ያቋቋመ ቢሆንም ከ2004 በፊት በበቂ ሁኔታ ጥገናዎች እየተከናወኑ እንዳልነበር፣
- በጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆሰፒታል የሕክምና እና የላቦራቶሪ መሣሪያዎች ከተጠቃሚዎቹ አንፃር ሲታይ በቂና ዘመናዊ አለመሆናቸው፣ ከዚህም በተጨማሪ ሆስፒታሉ የጥገና ክፍል የሌለው ሲሆን የሆስፒታሉ

ላውንደሪ ማሽንም ባለመጠገኑ ምክንያት እስከ ግንቦት 2004 አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣

- በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ውስጥ በቂ የመጸዳጃ ቤት፣ የታካሚዎች ማረፊያና የበሽታ መከላከያ (infection prevention) አገልግሎቶች እንዲሁም 24 ሰዓት የውሃ እና የመብራት አገልግሎት ሊኖሩት ሲገባ
  - o የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የኢንፌክሽን መከላከያ ክፍል ያለው፤ ክፍሉም በኢንፌክሽን መከላከያ መመሪያ መሰረት ደረቅና ፍሣሽ ቆሻሻዎችን የተለያየ ቀለም ባላቸው ቅርጫቶች በማዘጋጀት ቆሻሻዎችን የማስወገድ ሥራ እየተሠራ ቢሆንም በሆስፒታሉ የተመላላሽ ታካሚዎችን ቁጥር ያገናዘበ የመፀዳጃ ቤት እና ለታካሚዎች በቂ የማረፊያ ቦታ የሌለው መሆኑ፣ የውሃ አቅርቦት ችግር በመኖሩ ከ6ኛ-8ኛ ፎቅ ውሃ የማይደርስ መሆኑ፣
  - o በቂ ቦታዎች፣ የመቀመጫ ወንበሮች እና ሌሎች አገልግሎቶች ባለመኖራቸው ታካሚዎች ብዙ ጊዜያቸውን ቆመው፤ በጊቢውና በየኮሪደሩ ተኝተውና ተቀምጠው እንዲጠብቁ መገደዳቸው፣
  - o ስትሬቸር ባለመኖሩ ምክንያት የተጎዱ ሰዎች በሰዎች ሸክም ወደ ሆስፒታሉ እንደሚገቡ፣ በተጨማሪም የሆስፒታሉ አስተዳደር የመፀዳጃ ቤቶችን እና የውሃ እጥረትን በጊዜያዊነት ለመቅረፍ ባለመሞከሩ ችግሮቹ እየተባባሱ መምጣታችው፣
- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የኢንፌክሽን መከላከያ ክፍል ያለውና ክፍሉም በኢንፌክሽን መከላከያ መመሪያ መሰረት ደረቅና ፍሣሽ ቆሻሻዎችን የተለያየ ቀለም ያላቸው ቅርጫቶች በማዘጋጀት ቆሻሻዎችን የሚያስወግድ ቢሆንም በሆስፒታሉ ከፍተኛ የመፀዳጃ ቤት ችግር መኖሩ፣
- የጅማና የጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች የኢንፌክሽን መከላከያ ክፍል እና በቂ የመፀዳጃ ቤቶች የሌላቸው እና በኤሌክትሪክ ሃይል መቆራረጥ የሚቸገሩ መሆኑ ፣
- የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች አስፈላጊ የሆኑ መድሃኒቶችን ዝርዝር የሚያዘጋጅ፣ የመድሃኒት አያያዝ ስርዓት የሚከታተል እና የመድኃኒቶችን ግዥ አቅርቦትና አጠቃቀም የሚከታተል ኮሚቴ (DTC) ሊያቋቁሙ ሲገባ የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የመድኃኒትና

ቴራፔቲክ ኮሚቴ በ2003 ዓ.ም ቢያቋቁሙም በሙሉ አቅሙ እየሰራ እንዳልሆነ እንዲሁም በሆስፒታሉ ፋርማሲዎች በቂና አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶች አቅርቦት ችግር ያለበት መሆኑ፣

- በቅዱስ ጳውሎስ፣ በጅማና ጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች በ2003 መጨረሻ አካባቢ ኮሚቴው የተቋቋመ ቢሆንም የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት በሚያስችል ሂኔታ የተደራጀ አለመሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት የተገኙ ዋናዋና ግኝቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖረት አሳስበናል፡፡

6.14. <u>የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት</u>

- በሰኔ 2002 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሠረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች በሚያወጧቸው ጨረታዎች ላይ የጨረታውን ውጤት በጨረታው ላይ ተሳታፊ ለሆኑ ተጫራቾች በሙሉ በእኩል ጊዜ በጽሁፍ መግለጽ እና ለተሸነፉ ተጫራቾች ደግሞ የተሸነፉበትን ምክንያትና አሸናፊ የሆነውን ተጫራች ማንነት መግለጽ ሲኖርበት በኦዲት ወቅት በተካሄደ የዶክሜንት ክለሳና ከኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ ኢንስቲትዩቱ ባወጣው የህንፃ ግንባታ ጨረታ ላይ በጨረታው ለተሸነፉ ተጫራቾች የተሸነፉበት ምክንያት እና የጨረታው አሸናፊ ማን እንደሆነ በጽሁፍ አለማሳወቁ፣
- ኢንስቲትዮቱ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚያስገነባቸው ህንፃዎች በቅድሚያ ጥናት ላይ የተመሠረቱ እና በታቀደው ጊዜ ሳይዘገዩ ቁጠባና ጥራትን መሠረት ባደረገ መልኩ ሊከናወኑ እና ይህንንም ለማሳካት የሚያስችል ብቃት ያለው የክትትል እና የቁጥጥር ስራ የሚያካሂድ አማካሪ ድርጅት ሊመደብለት እና በግንባታ ሂደትም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ወቅታዊ መፍትሔ በመስጠት ኢንስቲትዩቱ ለህንፃ ግንባታው ላወጣው ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም /value for money/ ማግኘት ሲኖርበት በመጀመሪያው ምዕራፍ የሎት አንድ የህንጻ ግንባታን ለማካሄድ ግሬስ ኢንጅነሪንግ ከተባለ ኮንትራክተር ጋር ባደረገው ስምምነት ስራው ውል በተገባ በአራት መቶ ሰማንያ የካላንደር ቀን ተጠናቆ ለመረከብ ቢዋዋልም ስራው ይጠናቀቃል

ከተባለበት ቀን በላይ ስምንት መቶ ዘጠና ሰባት ቀናት ዘግይቶ ጊዜያዊ ርክክብ የተፈጸመ መሆኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት የሚያስፈልጉት በቢዝነስ ኘላኑ ላይ የተገለፁት የምዕራፍ ሁለት እና ሶስት የህንፃ ግንባታዎች በዕቅዱ መሠረት ተግባራዊ ሊሆኑ ሲገባ በኦዲት ወቅት በተካሄደ የዶክሜንት ክለሳና ከኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠየቅ በምዕራፍ ሁለት እና ሦስት የሚካተቱት የኢንስቲትዩቱ ወርክሾኘ፣ የስልጠና ማዕከል፣ ካፍቴሪያ፣ የሠልጣኞች መኝታ ቤት፣ የኢንስቲትዩቱ የመኖሪያ ብሎኮች እና አዳራሽ የግንባታ ስራዎች ያልተጀመሩ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ የሚያከናውናቸው የማሽነሪ እና የላብራቶሪ መሣሪያዎች ግዥ ከህንፃ ግንባታው ኘሮግራም አፈፃፀም ጋር የተጣጣመ መሆን ሲኖርበት በኦዲት ወቅት በተካሄደ የዶክሜንት ክለሳና ለኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ መሠረት ኢንስቲትዩቱ አዲስ በሚያስገነባቸው ህንፃዎች ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጡ ታስበው ከውጭ ሀገር የተገዙ የላብራቶሪ መሣሪያዎችና የልብስ ስፌት ማሽኖች ሀገር ውስጥ ቢገቡም የኢንስቲትዩቱ ህንፃ ግንባታ በመጓተቱ ምክንያት መሣሪያዎችን ገጥሞ ስራ ላይ ለማዋል ባለመቻሉ መሣሪያዎቹ ከሁለት ዓመት በላይ ያለስራ በመቀመጣቸው የዋስትና ጊዜያቸው ማለፉ፣
- ኢንስቲትዩቱ ከአቅራቢ ድርጅቶች የገዛቸውን ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ መሣሪያዎች እና የላብራቶሪ ዕቃዎች እንዲቀርቡለት ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር ባካሄዳቸው የኮንትራት ውል ስምምነቶች መሠረት ድርጅቶቹ ያቀረቡትን መሣሪያዎች የመገጣጠም፣ እንደሚሠራ የማረጋገጥ እና የኮሚሽኒንግ ስራ በኮንትራት ስምምነቱ በተወሰነው ቀን ውስጥ እንዲካሄድ ሊያደርግ እና የማሽን ተከላው ከተጠናቀቀ በኋላም ወደ ሥራ ከመገባቱ በፊት የቴክኒክ ምርመራ ማረጋገጫ መስጠት ሲኖርበት የኦዲት ቡድኑ በኢንስቲትዩቱ ባካሄደው የዶክሜንት ክለሳ እና ቃለ መጠየቅ መሠረት ኢንስቲትዩቱ ከአቅራቢዎች ጋር ባደረገው የኮንትራት ውል መሠረት የተወሰኑ ዕቃዎች በስምምነቱ መሠረት የቀረቡ ሲሆን የተወሰኑት ግን በኮንትራት መሰረት ያልቀረቡ መሆኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ ለጋርመንት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ስልጠና አገልግሎት ከውጭ ሀገር ያስመጣቸውንና በትውስትና በጊዜያዊነት ለተለያዩ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች የሰጣቸውን የልብስ ስፌት መሳሪያዎች በማሰባሰብ ለኢንዱስትሪው የስልጠና ተደራሽነቱን ማስፋፋት ሲጠበቅበት 100 የልብስ ስፌት መሳሪያዎችን ለአልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ በውስት የሰጠ ሲሆን 130 መሳሪዎች ደግሞ ከአደይ አበባ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ጋር በተደረገ ጊዜያዊ ስምምነት በፋብሪካው እንዲቀመጡ የተሰጡ ቢሆንም መሳሪያዎቹ እስካሁን ያልተመለሱ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ ለዘርፉ የኢንቨስትመንት ውሳኔ፣ለገበያ ፍለጋ፣ለምርት ግብይት እና ለመሳሰሉት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን፣ በማደራጀት፣ ወደ መረጃ ማዕከል ማሰተላለፍና እንደ አስፈላጊነቱም ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት ሲገባ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄደው የዶክሜንት ክለሳ በአምስት አመት /2003-2007/ መካከለኛና ከፍተኛ የጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድ ላይ ለዘርፉ ኢንቨሰትመንት ውሣኔ፣ ለገበያ ፍለጋ፣ ለምርት ግብዓት እና ለመሳሰሉት የሚያገለግል የተሟላና ወቅታዊ መረጃ አለመኖሩ፤
- በ2003 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የኢንስቲትዩቱን ድረ-ገጽ በማዘጋጀት መረጃዎችን በመረጃ መረብ የማሠራጨት ሥራ አለመከናወኑ፤
- የመረጃ ዴስክ ወይም ማዕከል አገልግሎት መስጠት አለመጀመሩና በዘርፉ ዋና ዋና ገዢዎችን በተመለከተ የመረጃ ቋት አለመቋቋሙ፤
- በሰው ኃይልና በኢንፍራስትራክቸር አለመሟላት፣ በኢንስቲትዩቱ የህንፃ ግንባታ አለመጠናቀቅ ምክንያት ወቅታዊ የተሟላና ትክክለኛ መረጃ /የመረጃ ዴስክ/ ማደራጀትና መስጠት ያልተቻለ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በአፈፃፀም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች አፋጣኝ መፍትሄ መሰጠት ሲጠበቅበት የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የዶክሜንት ክለሳ በዘርፉ ኢንቨስትመንትን በሰፊው ለመሳብ አለመቻል፣ ወደ ኢንቨሰትመንት የገቡ ፕሮጀክቶች በብድር፣ በመሬትና በመሠረተ ልማት አቅርቦት መጓተት፣ በኮንስትራክሽንና ኮንትራክተሮች አቅም ማነስ እና በመሳሰሉት ችግሮች የተጀመሩት ፕሮጀክቶች በታሰበው ጊዜ መሠረት እንዳልተጠናቀቁ

ለማወቅ ተችሏል፡፡ በ2003 በጀት አመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ሲ.ኤል.ሲ ኢንዱስትሪ ብድር ለማግኘት የወሰደበት ጊዜ ረጅም መሆኑን፣ ራሱ ፕሮጀክቱ ለባንክ ብድር የሚያስፈልጉ ዶክመንቶችን በተጠየቀው መሠረት ፈጥኖ ያለማቅረብ፣ የድርጊት መርሀግብሩ ከሚፈለገው ጊዜ በላይ የተለጠጠ መሆኑ፣ የኤሌክትሪክ አቅርቦት አስመልክቶ ችግር ቢያጋጥም ማረጋገጫ እንዲሰጠውና ይህን ከሚመለከተው አካል ደብዳቤ ለመውሰድ ረጅም ጊዜ መውሰዱ፣ ለስራው የሚያስፈልገውን ጥሬ እቃ ለማቅረብ ከሀገር ውስጥ እጥረት ሲያጋጥመው ከውጭ ለማስገባት እንዲቻል ፈቃድ እንዲሰጠው ፈቃድ ሲጠይቅ ረጅም ጊዜ መውሰዱ፣ በባንኩ በኩል ውሣኔ ለመስጠት ብቃት ማነስ እና ከፍተኛ ክትትል መጠየቅ፣ ተጠንተው የቀረቡ ሰነዶች ለባንክ እንደገና በመታየት ብዙ ጊዜ መውሰዱ ኩባንያው /ኢ.ቱር ቴክስታይል/ የጥናት፣ የሊዝ ውል እና የዲዛይን ሰነዶች በአፋጣኝ ያለማቅረብ፣ የቀረቡትም ቢሆን የተሟላ አለመሆናቸው በፕሮጀክት አፈጻጸም የታዩ ችግሮች መሆናቸው፤

- ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት ላይ እየሰጠ ያለው ምክርና ድጋፍ አጥጋቢ ያለመሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ልማት የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን (ከመሠረታዊ የልብስ ስፌት ስልጠና ውጪ በሌሎች የስልጠና ዓይነቶች ላይ) ለስልጠና አገልግሎት እንዲውሉ የተገዙ ማሽነሪዎች ተተክለው ሥራ ባለመጀመራቸው አለመሰጠቱ፤
- ለ120 የጥጥ መዳመጫ እና የፈትል ክፍል ሠራተኞች፣ለ120 የሽመናና የሹራብ ፋብሪካ ክፍል ሠራተኞችና እንዲሁም ለ120 የማጠናቀቂያ ክፍል ሰራተኞች ስልጠና ለመስጠት የስልጠና ፍላጎት ጥናት ተካሂዶና እቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም ለስልጠና የሚያስፈልጉ ግብአቶች እና በሰው ኃይል አለመሟላት ስልጠናው አለመሰጠቱ፤
- ኢንስቲትዩቱ በመጀመሪያ የውስጥ አቅሙን ስላላደራጀ የፌዴራልና የክልል ጥቃቅንና አነስተኛ የስልጠና ማዕከሎች በሚሰጡት ስልጠናዎች ላይ ድጋፍ ለማድረግ አለመቻሉ፤ በተመሳሳይ መልኩ 700 ባለሙያዎችን

አሰልጥኖ የምስክር ወረቀት ለመስጠት የታቀደ ቢሆንም ስልጠናውን መስጠት አለመጀመሩ፤

- ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ልማት ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናትን በማካሄድ በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶችን ሊያግዝና ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑትንም ሊደግፍ ሲገባ የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የዶክመንት ክለሳ በ2003 የበጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ኢንስቲትዩቱን ከሲትራ ከተባለ ተቋም ጋር በማቆራኘት በኮምቦልቻ፣ ድሬዳዋ እና ክራውን ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ላይ የምርጥ ተሞክሮ ጥናት ማካሄድ አስቦ ቁርኝቱ ተግባራዊ ባለመደረጉ ስራው አለመሰራቱ፤
- በአዲስ ጋርመንት ፋብሪካ ባለፈው በጀት አመት ለስድስት ወር የተከናወነው የቤንች ማርኪንግ ትግበራ ግምገማ ተከናውኖ ቀሪ ሥራዎችን ለማስተካከል የሚያስችል ሁኔታ ባለመኖሩ ቀጣይ ትግበራ ያልተካሄደ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ በጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪዎች የፊዚካል የኬሚካልና ኢንቫይሮንመንታል የፍተሻ አገልግሎት በመስጠት የጥራት ተወዳዳሪነታቸው እንዲጨምር ማድረግ ሲጠበቅበት የሎት ሁለት ህንፃ ግንባታ ባለመጠናቀቁ ለፍተሻ አገልግሎት የተገዙትን መሳሪያዎች ተክሎ ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ አለመቻሉ፤
- ይህን ችግር ለመቅረፍ መሣሪያዎችን በተጠናቀቀው ሎት አንድ ህንፃ ላይ በጊዜያዊነት እንዲተከሉ ማድረጉን፣ ከጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ከሚለቀቁ ፍሳሾች ላይ ናሙና በመሰብሰብ ፍተሻ ለማከናወን እና የመፍትሔ ሃሣብ ለሚመለከተው ክፍል ለማቅረብ የላብራቶሪ መሣሪያዎች ግዥ ሙሉ በሙሉ ባለመጠናቀቁ እና በኢንስቲትዩቱ ያለው ላብራቶሪ ተደራጅቶ አገልግሎት መስጠት ባለመጀመሩ ከኢንስቲትዩቱ ውጪ ያሉ ላብራቶሪዎችን ለመጠቀም መገደዱ፤
- ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ለተሠማሩ ባለሀብቶች ድጋፍ ለማግኘት ከመሄዳቸው በፊት ማሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታ በተመለከተ መረጃ መስጫ አዘጋጅቶ ባለመስጠቱ ባለሃብቶች ለስራቸው የሚስፈልጋቸውን በተለይ ብድር ለማግኘት ማሟላት ስላለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር የማያውቁ መሆኑ፤

- ኢንስቲትዩቱ ለዘርፉ አስፈላጊ የሆኑ የውጭ ገበያዎችን በማጥናትና በማስጠናት የተጠናከረ አዳዲስ ገበያ በማፈላለግ የኤክስፖርት ሥራው ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ ሲጠበቅበት የኦዲት ቡድኑ በኢንስቲትዩቱ ባካሄደው የዶክመንት ክለሳ በተለያዩ የንግድ ትርኢቶች ላይ በመሳተፍ እና የገበያ ጥናት በማድረግ አዳዲስ የገበያ እድሎችን የማግኘትና የማስፋት ልምድ ባለመዳበሩ በአለም አቀፍ ደረጃ ያሉትን አማራጭ የገበያ እድሎች መጠቀም ያለመቻል፣ ለገበያ ፍለጋ የሚያገለግል የተሟላና ወቅታዊ መረጃ ያለመኖር ችግሮች ያሉበት መሆኑ፤
- ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባለሃብቶች በዓለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪ ሆነው ለመገኘት ከመስራት ይልቅ ከፍተኛ ጥረትን በማይጠይቀው የአገር ውስጥ ገበያ ላይ ትኩረት ማድረጋቸው፤
- የውጪ ገበያን መረጃ ለመሰብሰብ እና ለማሰራጨት የሚያስችሉ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች በውጭ አገር አለመኖራቸው፤

በኦዲቱ ወቅት የተገኙ ዋናዋና ግኝቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖረት አሳስበናል፡፡

6.15. <u>የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን</u>

- የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በስትራቴጂክ ዕቅዱ ያቀዳቸውን ተግባራት በዓመታዊ ዕቅድ በማካተት ተግባራዊ ሊያደርግና በየበጀት ዓመቱ በሚያዘጋጀው የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች ውስጥ የሚገለፁ ክፍተቶችን ለማስተካከል የሚያስችል በተሟላ መልኩ የእርምት እርምጃ ሊወስድ ሲገባ
    - o ባለስልጣን መ/ቤቱ በሙቀት ሳቢ ጋዞች ልቀት ምንጮች ጉዳት ላይ ሊወድቁ የሚችሉ የኢኮኖሚ ዘርፎችን የሚለይ ዘገባ እና በዘርፍ መ/ቤቶች የሚገኙ ሰነዶች በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ ሊከሰቱ ከሚችሉ ጉዳቶች የሚያጣጥም የአሰራር ማንዋል ለማዘጋጀቱ፤
    - o በስትራቴጂክ ዕቅዱ ውስጥ ከአጋሮች ጋር በመስራት የአካባቢ ትምህርት በመደበኛ ስርዓተ-ትምህርት ውስጥ እንዲካተት የማድረግ

ስራን ቢያካትትም ይህን ተግባር በዓመታዊ ዕቅዱ ውስጥ በማካተት ተግባራዊ አለማድረጉ፣

- o የባለስልጣኑ የስትራቴጅክ ዕቅድ፣ የዓመታዊ ዕቅዱና የዕቅድ ክንውን ሪፖርቶች ተመጋጋቢ ባለመሆናቸው በየበጀት ዓመቱ ላልተከናወኑት ተግባራት ትኩረት ተሰጥቶት እርምጃ አለመውሰዱ፤

- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የሀገሪቱን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ በየወቅቱ እያዘጋጀ ለመንግስትና ለህዝብ ይፋ ሊያደርግ እንዲሁም በሀገሪቱን የበካይ ነገሮችን መጠን፣ ምንጭ፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚያመለክት የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ ቢያንስ በየአምስት ዓመቱ ሊያወጣ ሲገባ፤
  - o የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በሰኔ 2000ዓ.ም አጠቃላይ የሀገሪቱን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ / Ethiopia Enivronment out look or the state of environment/ ቢያዘጋጅም እስከ 2004 ዓ.ም መጨረሻ ለአካባቢ ምክር ቤት በመላክ ውሳኔ እንዲሰጥበት /Endorsed/ አለማድረጉ፤
  - o በ2004 ዓ.ም ዘገባ ለማዘጋጀት የሚረዳ በአራት አካባቢዎች ላይ ያተኮረ (በአብጃታና ሻላ፣ አባያና ጫሞ፣ ግልገል ጊቤ 2 እና የአፋር የግጦሽ መሬትን በተመለከተ ዓመታዊ የአካባቢ ሁኔታ መግለጫ (Fact sheet) ከማዘጋጀት ውጭ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አጠቃላይ የአከባቢ ሁኔታ ዘገባ በማዘጋጀት ለመንግስትና ለህዝብ ይፋ አለማድረጉ፤
  - o የኢንዱስትሪ ብክለትን ለመከላከል በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 159/2001 ላይ በተቀመጠው መሰረት የሀገሪቱን የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚያመለክት ዘገባ እስከ 2004 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ አላማዘጋጀቱ፤ በዚህም ምክኒያት በአጠቃላይ በአገር አቀፍ ደረጃ የበካይ ነገሮች መጠንና አወጋገድን የሚያመለክት መረጃ አለመኖሩ፤

- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አደገኛ ነገሮችን /ኬሚካሎችን/ ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን በተመለከተ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲና ህግ ሊያዘጋጅ እንዲሁም የፀደቁ የአካባቢ ህጎች በስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል፣

ሊቆጣጠር እና ሊያረጋግጥ ሲገባ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲና ህግ (አዋጅ እና ደንብ) አለማዘጋጀቱ እንዲሁም የፀደቁ የአካባቢ ህጎች በስራ ላይ መዋላቸውን የማያረጋግጥ መሆኑ፤

- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 295/95 በአንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ካዘጋጃቸው 1 የአካባቢ ፖሊሲ፣ 18 ህጎች(አዋጆች፣ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች የማፀደቂያ አዋጆችና ደንቦችን ጨምሮ)፣9 ደረጃዎች እና 5 መመሪያዎች በድምሩ 33 ፖሊሲዎች፣ህጎች፣ደረጃዎች እና መመሪያዎች ውስጥ 29ኙ (88 በመቶ) የአካባቢ ፖሊሲ፣ ህጎችና መመሪዎች ስራ ላይ መዋላቸውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አለመጀመሩ፤
- በባለስልጣኑ የተዘጋጁትን የአካባቢ ደረጃዎች ስራ ላይ መዋላቸውን ለመከታተል የሚያስችል የተደራጀ የፍሳሽ መመርመሪያ ላብራቶሪ በፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የሌለው መሆኑ፣
- በ1995 ዓ.ም በፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በተደረገው የክዋኔ ኦዲት ላይ ስለ አከባቢ ላብራቶሪ ኦዲት ተደርጎ ይሄው ምላሽ የተሰጠ መሆኑ ባለስልጣኑ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ አለመሆኑን ለመገንዘብ ማስቻሉ፣
- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እና የዘርፍ መ/ቤቶች በተፈራረሙት የውክልና ሰነድ አንቀፅ 1 ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ ለመመርመርና ውሳኔ ለመውሰድ የሚያስችል የአካባቢ ህግ፣ደረጃና መመሪያ እንዲሁም የሚያስፈልጉትን ተጨማሪ ሰነዶች ለዘርፍ መ/ቤቶች መስጠት እንዳለበት ቢገለፅም ባለስልጣን መ/ቤቱ ለዘርፍ መ/ቤቶቹ በአካባቢ ዙሪያ የወጡትን እና እስከ አሁን ያልፀደቁ የአሰራር መመሪያዎችንና ደረጃዎች በሶፍት ኮፒ ከመላክ ውጭ መመሪያዎቹን አስፀድቆ እንዲጠቀሙበት አለማድረጉ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪያዎችና ደረጃዎችን ለምሳሌ የባለስልጣን መ/ቤቱ የማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 295/1995 ደንብና የማስፈፅሚያ መመሪያ፣ በወንዞች፣ በሸለቆዎች እና በሐይቆች ዙሪያ ሊኖር ለሚገባው የማይደፈር ክልል (buffer zone) ደረጃ እና ከተሽከካሪዎች የሚወጣው የጭስ ልቀት ደረጃ፣ ለሙቀት ሳቢ ጋዝ ልቀት ደረጃ፣ ለኤሌትሮኒክ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ ደንብ፣

ለውሃ አዘል መሬቶች እና ሐይቆች አጠቃቀም እና እንክብካቤ አዋጅ፣ ለአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ደንብ፣ ለድምፅ ብክለት እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ብክለት ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 159/2001 የአፈፃፀም መመሪያዎችን አለመዘጋጀቱ፤

- ባለስልጣኑ 35 የአካባቢ ህጎችን ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪያዎችና ደረጃዎች ቢያዘጋጅም ለክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች ከ3 እስከ 12 የሚሆኑ ረቂቅ መመሪያዎችን በሶፍት ኮፒ ከመላክ ውጭ የተዘጋጁትን በሙሉ በማፀደቅ አለመላኩ፤
- ኬሚካሎች በአገሪቱ እና በአካባቢ ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ከፍተኛ ቢሆንም የፌዴራል የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችን አያያዝ አጠቃቀምና አወጋገድ /ማምከንን/ አሰመልክቶ መመሪያ በማዘጋጀት ኢንዱስትሪዎች እንዲጠቀሙበት አለማድረጉ፤
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 46 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 37ቱ (80%ቱ) ኢንዱስትሪዎች በፋብሪካው ውስጥ ጊዜ ያለፈባቸውና መወገድ ያለባቸውን ኬሚካሎች እንዴት ማሰወገድ እዳለባቸው፣ የት መወገድ እዳለበት ወይም እንዴት ማምከን እደሚቻል አለማወቃቸው፤ እንዲሁም ደግሞ ከጊዜ ብዛት ምን አይነት ጉዳት እንደሚያደርሱ ግንዛቤ ባለመኖሩ በመጋዘን ቤቶች እና በየፋብሪካዎች ግቢ ውስጥ ብዛት ያላቸው ኬሚካሎች ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑ፤
- በየኢንዱስትሪው መጋዘን ቤቶች ውስጥ የተቀመጡት ኬሚካሎች አንዱ ከለሌኛው ተለይቶ እንዲቀመጥ እና መለያ(label) ያልተደረገባቸው ሲሆን በየቦታው ተደፋፍተውና በሙቀት ምክንያት የቀለጡ/እየቀለጡ መሆናቸው፤
- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ አያያዝን እና ጥበቃን በሚመለከት ለክልሎች ስልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ ሊሰጥ እንዲሁም በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ምርመራና ውሳኔ አወሳሰድ ላይ ለዘርፍ መ/ቤቶች የክህሎት ማጎልበቻ ስልጠና ለመስጠት፤
    - o ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 295/95 በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት ለክልሎች ማድረግ የሚገባውን ድጋፍ ከክልሎች የስራ ሃላፊነት አንፃር በ2002 ዓ.ም በሬዲዮ ፕሮግራም ላይ ለማስተዋወቅ ለ

2 ቀን ባዘጋጀው አውደ ጥናት እና በ2003 ዓ.ም Integrated Environmental Assessment and Reporting ስልጠና ላይ የአማራ፣ የሐረሪ፣ የድሬደዋ እና የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶችን እንዲሳተፉ አለመደረጉ፤

- o እንዲሁም በ2002 ዓ.ም ለ 2ቀን በአየር ንብረት ለውጥና በcarbon neutral climate resilient economy /CNCRG/ ባዘጋጀው የስልጣና ፕሮግራም ላይ የኦሮሚያ፣የደቡብ፣ የአማራ፣ እና የድሬደዋ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶችን እንዲሳተፉ አለማድረጉ እና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጥቶ የማያውቅ መሆኑ፣

- ከዚህም በተጨማሪ የኦሮሚያ፣ የደቡብ፣ የአማራ፣ የሐረሪ፣ የድሬደዋ እና የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች ከ2002-2004 ዓ.ም በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ፣ በአከባቢ አያያዝ ስርዓት፣ በብክለት ቁጥጥር፣ በአካባቢ ኦዲት አደራረግ፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ በተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ እና በአደገኛ ኬሚካሎች አጠቃቀም እና አወጋገድ ላይ በፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ስልጠና ባለመሰጠቱ ክልሎች በስራቸው ላሉት ኢንዱስትሪዎች ስልጠና ለመስጠት እና ክትትል ለማድረግ አለመቻላቸው፤ ይህም የክህሎት ክፍተት በመፍጠሩ ወጥ የሆነ አሰራር በክልሎችና በባለሙያዎች እንዳይኖር ከማድረጉ በተጨማሪ በአካባቢ ህጎችና ደረጃዎች ዙሪያ ለሚነሱ ጥያቄዎች የተሟላ መልስ ለመስጠት አለማስቻሉ፤
- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን 22 የዘርፍ መ/ቤቶች ቢኖሩትም ከነዚህ ውስጥ በዝርዝር ኦዲቱ በተከለሱ የስልጠና ሰነዶች መሰረት በ 9 የዘርፍ መ/ቤቶች እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መጠይቅ ተልኮላቸው ከመለሱት 6 የዘርፍ መ/ቤቶች ውስጥ (ከአንድ የዘርፍ መ/ቤት ውጭ) ለ14ቱ (58%) የዘርፍ መ/ቤቶች በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ምርመራና ውሳኔ አወሳሰድ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የክህሎት ማጎልበቻ ስልጠና ተሰጥቶ የማያውቅ መሆኑ፣
- ከዚህም በተጨማሪ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የኦዲት ቡድኑ በአካል ተገኝቶ ለተመለከታቸው 3 የዘርፍ መ/ቤቶች ባለስልጣኑ ከ 2002-2004 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ (በ 2003 ዓ.ም አንድ ጊዜ በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ላይ ከተሰጠ ስልጠና በቀር) ምንም ዓይነት ስልጠና አለመስጠቱ እና የቴክኒክ ድጋፍም አለማድረጉ፤

- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ከባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ የሆነ የመወያያና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን በማዘጋጀት በቅንጅት ሊሰራ እና የሪፖርት አቀራረብና አደራረግን በተመለከተ ከክልሎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር የመግባብያ ሰነድ (memorandum of understanding) ሊኖረው እንዲሁም የአካባቢ መረጃ ልውውጥን፣ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ስርዓት ሊዘረጋ ሲገባ በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩት 6 የክልል አካባቢ ጥበቃ ቢሮዎች እና በስራቸው ካሉት 46 ፋብሪካዎች እንዲሁም 8 የዘርፍ መ/ቤቶች ጋር ባለስልጣን መ/ቤቱ መደበኛ የሆነ የመወያያና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን በማዘጋጀት በቅንጅት በመስራት ላይ አለመሆኑ፣
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የደቡብ፣ የአዲስ አበባ፣ የኦሮሚያ፣ የድሬደዋ፣ የሐረሪና የአማራ ክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች እና የማዕድን፣ የግብርናና የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር መ/ቤቶች እንዲሁም በሰርቬይ መጠይቅ ተልከላቸው የመለሱት 6 መ/ቤቶች ከፌዴራል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ጋር የሪፖርት አደራረግን በተመለከተ የመግባቢያ ሰነድ /MOU/ የሌላቸው መሆኑ፤
- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ መረጃ ልውውጥን፣ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ስርዓት አለመዘርጋቱ፤
- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአገልግሎት ሰጪ እና የማምረቻ ተቋማት ክትትልን በተመለከተ የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ እዲያሳውቁት፤ እንዲሁም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የጥናት ሰነድ ቅጂና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን የዘርፍ መ/ቤቶች (የሚኒስቴር መ/ቤቶች) ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ እዲልኩለት እና በተሰጣቸው ውክልና መሰረት መስራታቸውን ሊያረጋግጥ ሲገባ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የኦሮሚያ፣ የደቡብ፣ የአዲስ አበባ፣ የድሬደዋ፣ የሐረሪና የአማራ ክልል መንግስታት የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት በመዘርጋት እዲያሳውቁት አለማድረጉ፤
- የአዲስ አበባና የድሬደዋ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች የአገልግሎት ሰጪ እና የማምረቻ ተቋማት ክትትል ሪፖርት ማድረግን በተመለከተ ከፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እንደቅደም ተከተላቸው በ2003

ዓ.ምና በ2004 አጋማሽ ላይ ውክልና ቢሰጣቸውም ለባለስልጣኑ የአገልግሎት ሰጪ እና የማምረቻ ተቋማት የክትትል እና የቁጥጥር ሪፖርቶችን አቅርበው የማያውቁ መሆኑ፣ ሁለቱ ውክልና የተሰጣቸው የከተማ አስተዳደሮች እና ውክልና ያልተሰጣቸው 9ኙም ክልሎች ሪፖርት የማይልኩ መሆኑ፤

- በ2003 ዓ.ም ለውሃና ኢነርጅ፣ ለግብርና እና ለማዕድን ሚኒስቴር መ/ቤቶች (የዘርፍ መ/ቤቶች) ባለስልጣኑ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የጥናት ሰነድ ቅጂና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን በየሩብ ዓመቱ እንዲልኩለት ቢያሳውቅም የውሃና ኢነርጅ ሚኒስቴር የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የጥናት ሰነድ ቅጂ የማይልክ ሲሆን ባለስልጣኑም የዘርፍ መ/ቤቶች በተሰጣቸው ውክልና መሰረት ስራውን ስለመስራታቸው የማያረጋግጥ መሆኑ፤
- የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ለ2 ፕሮጀክቶች፣ የግብርና ሚኒስቴር ለ 9 ፕሮጀክቶች እና የማዕድን ሚኒስቴር ለ38 ፕሮጀክቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የጥናት ሰነድ ገምግመው የይሁንታ ፈቃድ የሰጡ ቢሆንም በውክልናው ሰነድ አንቀፅ 1 ተራ ቁጥር 2 መሰረት የማዕድን ሚኒስቴር ለ 7ቱ ባለፕሮጀክቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሲያካሂዱ የጥቅም ግጭት እንዳያስከትል የሚኒስቴር መ/ቤቱን ወይም የፌዴራልም ሆነ የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ሠራተኞችን ያላሳተፈ መሆኑን በማረጋገጫ ሰሪትፍኬት በፊርማ እንዲያረጋግጡ ከማድረግ ውጭ ለተቀሩት 42 ባለፕሮጀክቶች ያካሄዱት የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ የጥቅም ግጭት የሌለው ስለመሆኑን ሳያረጋግጡ ወደ ስራ የገቡ መሆኑ፤
- ይህም የሆነው የዘርፍ መ/ቤቶች በየ3ወሩ የሚልኩትን ሪፖርት እና የጥናት ሰነድ ቅጂ በሶፍትና በሃርድ ኮፒ ከመቀበል ውጭ ባለስልጣኑ በሰጣቸው የውክልና ሰነድ ላይ በተቀመጡት ዝርዝር ተግባራት መሰረት ስለመሰራታቸው ክትትል ባለማድረጉ መሆኑን ለማረጋገጥ መቻሉ፤
- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ አሃድን (የአካባቢ ነክ ጉዳዩችን የሚከታተል ክፍል) ሁሉም የዘርፍ መ/ቤቶች እና ኢንዱስትሪዎች እንዲያቋቁሙ ሊያደርግ እንዲሁም የስራ ፈቃድ የመስጠት፣ የመተግበር ወይም ክትትል የማድረግ ስልጣን የፌደራል መንግስት የሆነባቸው ወይም ክልል ተሻጋሪ የአከባቢ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ ሊገመግም፣ የይሁንታ ፈቃድ

ሊሰጥ፣ ሊከታተል እና በሰነዱ በተቀመጡ ግዴታዎች መሰረት ስለመስራታቸው ሊያረጋግጥና መቆጣጠር ሲገባው፤

- o በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 3 የሚኒስቴር መ/ቤቶችና መጠይቅ ተልኮላቸው ከመለሱት 6 የዘርፍ መ/ቤቶች ውስጥ በ2003 ዓ.ም የግብርና፣ የውሀና ኢነርጂ እና የማዕድን ሚኒስቴር መ/ቤቶች ብቻ የአካባቢ አሃድ እንዲያቋቁሙ ማድረጉ፣
- o በ2005 ዓ.ም በኢንዱስትሪ፣ በስራና ከተማ ልማት እና በትራንስፖርት ሚኒስቴር መ/ቤቶች ለማቋቋም ጥረት ያደረገ ቢሆንም በ16ቱ (73%) የዘርፍ መ/ቤቶች የአካባቢ አሃድ እንዲያቋቁሙ አለማድረጉ፣
- o እንዲሁም በናሙና ከታዩት 46 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 27ቱ ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ አሃድ ያላቋቋሙ ሲሆን፣ በ16 ቱ ደግሞ ራሱን የቻለ የአካባቢ ነክ ጉዳዩችን የሚከታተል ክፍል ባለመቋቋሙ በኮሚቴ ከሌላ ክፍል ስራ ጋር በተደራቢነት የሚሰራ መሆኑ፣

- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የስራ ፈቃድ የመስጠት፣ የመተግበር ወይም ክትትል የማድረግ ስልጣን የፌደራል መንግስት የሆነባቸው ወይም ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ እንዲገመግሙና በይሁንታ ፈቃዱ መሰረት ስለመስራታቸው እንዲከታተሉ፣ እንዲቆጣጠሩና እንዲያረጋግጡ ለግብርና፣ ለውሃና ኢነርጅ እና ለማዕድን ሚኒስቴር በ2003ዓ.ም አጋማሽ ውክልና የሰጠ ቢሆንም ከ2003 ዓ.ም በፊት የይሁንታ ፈቃድ የተሰጣቸውን ፕሮጀክቶች ዝርዝርና የጥናት ሰነዶች ቅጅዎችን ከውክልናው ሰነድ ጋር ለሚኒስቴር መ/ቤቶቹ ባለማስተላለፉ በአካባቢ ተፅዕኖ ሰነዱ በተቀመጡ ግዴታዎች መሰረት ፕሮጀክቶቹ ስለመስራታቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶቹ ክትትልም ሆነ ቁጥጥር አለማድረጉ፤
- ከ2003 ዓ.ም በፊት በባለስልጣኑ የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ ተገምግሞ የይሁንታ ፈቃድ የሰጣቸው ፕሮጀክቶች ዝርዝር በተደጋጋሚ በኦዲት ቡድኑ ቢጠየቅም ሊቀርብ አለመቻሉ፤
- ከዚህም በተጨማሪ የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣንም እስከ 2004ዓ.ም በአንድ ፕሮጀክት ላይ ብቻ ተከታትሎ በሰነዱ በተቀመጡ ግዴታዎች መሰረት ስለመሰራቱ በማረጋገጥ ቁጥጥር ከማድረግ ውጭ በሌሎች

ፕሮጀክቶች ላይ ክትትል በማድረግ በግዴታው መሰረት ስለመስራታቸው ያላረጋገጠ እና ያልተቆጣጠረ መሆኑ፤

- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ ገምግሞ ፈቃድ ለመስጠት ውክልና ለተሰጣቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች የግምገማውን ውሳኔ በወቅቱ ሊያሳውቅ ሲገባ ባለስልጣን መ/ቤቱ የአካባቢ ተፅዕኖ ዘገባ ገምግሞ ፈቃድ ለመስጠት ውክልና ለተሰጣቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች የግምገማውን ውሳኔ ማሳወቅ እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 295/95 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 5 ቢገለፅም በኦዲቱ ወቅት በአካል ከታዩና ውክልና ከተሰጣቸው የዘርፍ መ/ቤቶች ውስጥ የግብርና እና የማዕድን ሚኒስቴር መ/ቤቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ ቅጅ በሶፍት ኮፒ እና በሃርድ ኮፒ በየሶስት ወሩ ከሪፖርት ጋር የሚልኩ ቢሆንም የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ለነዚህ ፈቃድ ሰጪ ሚኒስቴር መ/ቤቶች የግምገማውን ውሳኔ የማያሳውቃቸው መሆኑ፤
- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ ኦዲት ማድረጋቸውን ሊያረጋግጥ እንዲሁም በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የሰጣቸው ኢንዱስትሪዎችን በአካባቢ አያያዝና አጠባበቅ ዙሪያ ሊከታተልና ቁጥጥር ሊያደርግ ወይም ክልሎች እንዲከታተሉ እና ቁጥጥር እንዲያደርጉ በውክልና ሊያስተላልፍ ሲገባ ባለስልጣን መ/ቤቱ ከ2004 አጋማሽ ወር በኋላ የስርዓት ተከባሪነትን ለማረጋገጥ እና ለመስክ ስራ ባለሙያዎችን ባሰማራበት ወቅት ከስምንት የኢንዱስትሪ ዘርፎች (ጨርቃጨርቅ፣ ቆዳ፣ ሲሚንቶ፣ ኬሚካል፣ ስኳር፣ ብረታ ብረት፣ ምግብና መጠጥ እና ማተሚያ ቤቶች) ውስጥ በሶስቱ ብቻ (በምግብ፣ በኬሚካል እና በብረታብረት ኢንዱስትሪዎች) በ21 ፋብሪካ የአካባቢ ኦዲት ማድረጋቸውን የማረጋገጥ ስራ ቢጀምርም በኦዲቱ ወቅት በኦሮሚያ፣ በአዲስ አበባ፣ በደቡብ፣ በአማራ፣ በድሬደዋ እና በሀረር ክልሎች በናሙና ተወስደው ከታዩት 46 ፋብሪካዎች ውስጥ 40ዎቹ (87%) የአካባቢ ኦዲት ማድረጋቸውን ባለስልጣኑ አለማረጋገጡ፤
- ከዚህም በተጨማሪ ከ40ዎቹ ውስጥ 32ቱ ፋብሪካዎች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማም ሳያስገመግሙ ስራ የጀመሩ መሆኑ፣ ይህም ፋብሪካዎቹ ስለ አካባቢ አጠባበቅ እና ስለ አካባቢ ኦዲት ግንዛቤ እንዳይኖራቸው ማድረጉ፣

- በኦዲቱ ወቅት በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በአዲስ አበባ፣ በድሬደዋና በሐረሪ ክልል ከታዩት 46 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ከፌደራል ንግድ እና እንዱስትሪ ሚኒስቴር የስራ ፈቃድ ያገኙ 33 ፋብሪካዎች ቢኖሩም፤ የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እራሱ ያልተከታተለ ወይም ከአዲስ አበባና ከድሬደዋ ክልሎች ውጭ ለሁሉም የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በየክልላቸው ለሚገኙ በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የተሰጣቸውን ኢንዱስትሪዎች ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ ውክልና ያልሰጠ መሆኑ ታውቋል፡፡ይህም በመሆኑ በ4ቱ ክልሎች ከፌደራል ንግድ እና እንዱስትሪ ሚኒስቴር የስራ ፈቃድ ካገኙ 22 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 18 (82%) ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ አያያዝና አጠባበቅ ዙሪያ ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎባቸው የማያውቅ መሆኑ፤
- በኦዲቱ ወቅት ከተጎበኙት ፋብሪካች ውስጥ 9 ፋብሪካዎች የኬሚካል ማስቀመጫ መጋዘኖቻቸው በቂ አየር የማያስገባ መሆኑ፣ በ 23 ፋብሪካዎች ኬሚካሎች በሰራተኞች ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ እገዛ የሚያደርግ ማቴሪያል ሰፍቲ ዳታ ሺት/Material safety data sheet/ አብሮ አለማስቀመጣቸው፣ በ 9 ፋብሪካዎች ግቢ ውስጥ ከፍተኛ ሽታ ያላቸው የቆዳ ቁርጥራጭ፣ ፀጉር፣ ስላጆችን (slage) እና አደገኛ ኬሚካሎችን ጥንቃቄ ባልተሞላበት ሁኔታ በግቢያቸው፣ በመጋዘኖች አካባቢና ውስጥ ተበታትነው የሚገኙ መሆኑ፤
- በተጨማሪም ፋብሪካዎቹ ወደ አካባቢው የሚለቁአቸው ፍሳሾች በየጊዜው የፍሳሽ ምርመራ /ቴስት/ ሳይደረግ የሚለቀቅ በመሆኑ ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ እንክብካቤ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያገኙ፣ ያላቸውን ክፍተት እንዳያሚሉ እና ያሉበትን ደረጃ እንዳያውቁ እንቅፋት መፍጠሩ፤
- በዘጠኙም ክልሎች የሚገኙ በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የተሰጣቸው ኢንዱስትሪዎች እስከ 2004 ዓ.ም ክትትልና ቁጥጥር ያልተደረገባቸው መሆኑ፤
- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጊዜ ያለፈባቸው በካይ ኬሚካሎች በሰው፣ በእንስሳት እዲሁም በእፅዋት ላይ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ክትትል እያደረገ ለሚመለከተው አካል በማሳወቅና የኬሚካል አወጋገድ መመሪያ በማዘጋጀት የሚወገዱበትን ሁኔታ አለማመቻቸቱ፤

- የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እና ኢንዱስትሪዎች በአደገኛ ኬሚካሎች ዙሪያ ለፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የኬሚካሎቹን አወጋገድ በተመለከተ ሁኔታዎችን እንዲያመቻች ወይም የአደገኛ ኬሚካሎች ህግና መመሪያ እንዲልክላቸው ባለስልጣኑን በተደጋጋሚ ቢጠይቁም የተለየ ሁኔታ ሲኖር ወደፊት የሚያሳውቃቸው መሆኑን ለ2 ድርጅቶች ብቻ በደብዳቤ ከመግጹ በቀር መፍትሄ አለመስጠቱ፤
- በኦዲቱ ወቅት እንደታየው በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በሐረሪ፣ በአዲስ አበባና በድሬደዋ ክልሎች እና የአማራ ገጠር መሬትና የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በየክልሉ ያሉትን የአደገኛ ኬሚካሎች ሁኔታ ለማወቅ ከሰበሰበው ዳታ በተገኘው መረጃ መሰረት በ16 ፋብሪካዎች 314,565 ኪ.ግ፣ 280,207 ሊትር፣ 7,059,523 በቁጥር፣ 140,450 ዶዝ፣ 1,506 ቲዩብ፣ 764 ፓኬትና 25 ጋሎን እንዲሁም የተለያዩ መጠን ያላቸው 5,290 በርሜል፣ 2,373 ጀሪካን፣ 10,578 ከረጢት፣ 527 ካርቶን፣ 9,548 ቆርቆሮ፣ 712 ጠርሙስና 90 ሳጥን ከ1 እስከ 20 ዓመታት ያስቆጠሩ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፉና የሚወገዱ ኬሚካሎች መገኘታቸው፤
- ከእነዚህ ኬሚካሎች ግማሾቹ ለአካባቢና ለሰዎች ጥንቃቄ ባልተደረገበት ሁኔታ የተቀበሩ ወይም በመቀበር ሂደት ላይ ያሉ ሲሆን የተቀሩት ደግሞ በየመጋዘኖች አካባቢ ተቀምጠው በአካባቢው ላይ ጉዳት በማድረስ ላይ የሚገኙ መሆኑ፤ ከእነዚህም ውስጥ ለፍንዳታ የሚያገለግል /ካርባይድ/፣ ክሎሪን ጋዝ፣ የማላታይን ዱቄት፣ ዲዲቲ፣ ሰልፈሪክ አሲድ፣ ሊድ፣ እና ሌሎች ዓይነቶች አደገኛ ኬሚካሎች የሚገኙበት መሆኑ፤
- ከዚህም በተጨማሪ በ 2 ፋብሪካዎች በውስጣቸው የሜሪኩሪና ሰልፈሪክ አሲድ ይዘት ያላቸው የተበላሹ 359 የመኪና ባትሪዎችና 13,384 የፍሎሬሰንት ላምፖች መገኘታቸው እንዲሁም በ5 ፋብሪካዎች ቁጥራቸውና ዓይነታቸው በውል የማይታወቁ ብዛት ያላቸው ኬሚካሎች በየመጋዘኖቻቸው ውስጥ ታሽገው የተቀመጡ እና በየቦታው ተዝረክርከው ዕቃዎቻቸው እየተበሉ፣በአካባቢው ላይ ከፍተኛ ሽታ እየፈጠሩ እና ጉዳት እያደረሱ መሆኑ፤
- አንድ ፋብሪካ ደግሞ ቁጥራቸው የማይታወቅ የመኪና ባትሪና የፍሎሬሰንት ላምፕ በግቢው ውስጥ በማቃጠልና በመቅበር ላይ የሚገኝ መሆኑ፣

- የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ማንኛውም ነባር ፋብሪካ በ5 ዓመታት የጊዜ ገደብ ውስጥ የፋብሪካው እንቅስቃሴ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለማስወገድ የሚያስችል እርምጃ መውሰድ ሲኖርበት የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ነባር ፋብሪካዎች የሚያስከትሉት ሊወገድ የማይችል አሉታዊ ተፅእኖ ሲኖር በደንብ ቁጥር 159/2001 በተቀመጠው የ5 አመት የጊዜ ገደብ ውስጥ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ሊያስወግድ የሚያስችል አስተዳደራዊም ሆነ ህጋዊ እርምጃ ወስዶ አለመገኘቱ፤
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በድሬደዋ፣ በሀረር እና በአዲስ አበባ ክልሎች ከሚገኙት 46 ፋብሪካዎች ውስጥ 35ቱ ነባር ፋብሪካዎች ሲሆኑ ከፋብሪካዎቹ እንቅስቃሴ የተነሳ በሰዎች፣ በእፅዋት እንዲሁም በእንስሳት ላይ በሚከሰተው አሉታዊ ተፅእኖ ላይ ባለስልጣኑ በአምስት አመት የጊዜ ገደብ ውስጥ አሉታዊ ተፅኖው እንዲቀንስ ወይም እንዲወገድ ምንም አይነት አስተዳደራዊም ሆነ ህጋዊ እርምጃ ወስዶ የማያውቅ መሆኑ፤
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ነባር ፋብሪካዎች የሚያስከትሉትን አሉታዊ ተፅእኖ በመከታተል እርምጃ እንዲወስዱ (በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት (BPR) ሰነድ ላይ) ለክልሎች ሃላፊነቱ በመሰጠቱ ክትትሉ በክልሎች የሚደረግ መሆኑን ለአንድ ፋብሪካ በደብዳቤ ከማሳወቁ በቀር የነባር ፋብሪካዎችን ስም ዝርዝር ለክልሎች በማስተላለፍ እርምጃ እንዲወስዱ አለማድረጉ፤
- በህዝብ አቤቱታ እና ቅሬታ መሰረት በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ እና በድሬደዋ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች አሉታዊ ተፅኖውን ለመቀነስ የሚያስችል አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ ጅማሮው ቢኖርም በተቀሩት ስምንት ክልሎች እና በነዚሁ ክልሎች ስራው ተጠናክሮ እንዲሰራ ባለስልጣኑ ጥረት አለማድረጉ፤
- በኦዲቱ ወቅት በስድስቱ ክልሎች የጨርቃጨርቅ፣ የቆዳ፣ የሲሚንቶ፣ የኬሚካል፣ የስኳር፣ የምግብና የመጠጥ፣ የማተሚያ ቤት እና የብረታብረት ኢንዱስትሪዎችን የሚያጠቃልል 46 ፋብሪካዎች ውስጥ 26ቱ ፋብሪካዎች የፍሳሽ ማጣሪያ እና የአቧራና የጭስ መቆጣጠሪያ መሳሪያ የሌላቸው በመሆኑ ከፋብሪካው የሚወጣው ፈሳሽ ቆሻሻ ሳይታከም በቱቦ በመጠቀም ወደ አቃቂ፣ ሰበታ፣ ሞጆ፣ ኮምቦልቻ-ወርቃማ እና አባይ ወንዞች እና ወደ

ገበሬዎች ማሳ ቀጥታ የሚለቀቅ መሆኑን እንዲሁም ፍሳሹ ጉድጓድ በመቆፈር ወደ መሬት ውስጥ እንዲሰርግ መደረጉ ከዚህም ባሻገር የፍሳሹ ውሃ በትነት መልክ ወደ አየር የሚለቀቅ መሆኑን እና ከሲሚንቶ ፋብሪካዎች የሚወጣው ጭስ እና ብናኝም ወደ አየር የሚለቀቅ መሆኑ፤

- የተቀሩት 9ኙ ፋብሪካዎች ደግሞ የመጀመሪያ የማጣሪያ መሳሪያ ቢኖራቸውም በፍሳሽ ማስቀመጫነት የሚጠቀሙበት ገንዳ የሰዎች መኖሪያ ቤቶች ያሉበት እና ከብቶች ሳር የሚግጡበት አካባቢ መሆኑ በተጨማሪም የBOD /Biochemical Oxygen Demand/ እና COD /Chemical Oxygen Demand/ ፍተሻ (Test) ሳይደረግ በፍሳሾቹ ውስጥ የሚገኙ አደገኛ ኬሚካሎች (እንደክሮም፣ ሰልፈሪክ አሲድ፣ ሰሊፋይድ) ደረጃቸው ሳይታወቅ በአካባቢው በሚገኙ ትናንሽ ወንዞች ውስጥ የሚለቀቁ መሆኑ፤
- በፋብሪካዎቹ ግቢ ውስጥ ያሉ የፀጉር፣ የቆዳ ቁርጥራጮች፣ ስላጅ እና ሌሎች ደረቅ ቆሻሻዎች የኬሚካል ይዘት ያላቸው ቢሆንም ለአካባቢው ህዝብ እና ለሰራተኞች ጤና ጥንቃቄ ባልተደረገበት ሁኔታ በግቢው ውስጥ መቃጠሉ እና ተዝረክርኮ መገኘቱ፤

በመሆኑም የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.16. <u>በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል በተደረገው መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሰረት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማነቱን መገምገምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ግኝቶች ማጠቃለያ</u>

- የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የመንግስት መስሪያ ቤቶች መሰረታዊ የአሰራር ለውጥ ተግበራዊ ካደረጉ በኃላ ያስቀመጧቸውን ግቦች ምን ያህል እንዳሳኩ ራሳቸውን እንዲገመግሙ አቅጣጫ ሊያስቀምጥና ተግባራዊነቱንም ሊከታታል ሲገባ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የመንግስት መስሪያ ቤቶች መሰረታዊ የአሰራር ለውጥ ተግበራዊ ካደረጉ በኃላ ያስቀመጧዋቸውን ግቦች ምን ያህል እንዳሳኩ ራሳቸውን እንዲገመግሙ

አቅጣጫ በማስቀመጥ ተግባራዊ እንዲሆን የማድረግና የመደገፍ ሥራ አለመካሄዱ፤

- ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የመንግስት መስሪያ ቤቶችን የአሰራር ሥርዓት ለውጥ ጥናት አተገባበር የሚከታተልበትና የሚደግፍበትን የአሰራር ስርዓት በማውጣት ተግባራዊ እንዲሆን አለማድረጉ፤
- የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር መሰረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ ሥርዓት ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የማበረታቻ ስርዓት ሊዘረጋ እና በሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ሊያደርግ እና የማበረታቻ ስርዓቱም ከውጤትና ከግብ ስኬት ጋር ሊያይዝዝ እና የተቋሙ ስትራቴጂ በሰራተኞች ዘንድ ትኩረት እንዲያገኝ የሚያስችል እና ስርዓቱም በተቋም፣ በቡድን እና በግለሰብ ፈጻሚዎች ደረጃ በትክክል የተዘረጋ እና ፍትሐዊነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ሲጠበቅበት መሰረታዊ የአሰራር ለውጥ ሥርዓት ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል የማበረታቻ ስርዓት አለመዘርጋቱ፤
- የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የሰው ኃይል በቀጣይነት የሚለማበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስልት በመቀየስ ተግባራዊነቱንም ክትትል ሊያደርግ ሲገባ ይህን ለማድረግ የሚያሰችል ስልት አለመቀየሱና ተግባራዊ አለማደረጉ፤
- የተቋማት የመረጃ አሰባሰብ እና ሪፖርት አቀራረብን ቀልጣፋ ከማድረግ ባሸገር ትክክለኛ ግብረ-መልስ ከትክክለኛ ቦታ በተቀላጠፈ መልኩ ለማግኘት፣ የመረጃ ልውውጥን ግንኙነትን የቀለለ እና የሰመረ እንዲሆን ለማስቻል፣ የዕውቀት ለውጥን በማፋጠን የፈጻሚዎችን አቅም ለማጎልበት እና በትክከለኛ መረጃ ላይ የተመሰረተ የውሳኔ አሠጣጥ እንዲኖር ለማስቻል የመንግስት መስሪያ ቤቶች የመሰረታዊ የአሰራር ለውጥ ጥናት ትግበራ በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኮሽን ቴክኖሎጂ (ICT) በሚፈለገው ደረጃ የታገዘ አለመሆኑ፤
- በፌዴራል እና በክልል በሚገኙ ተቋማት ለመሰረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ ጥናት የዋለው ገንዘብ በአግባቡ ለተባለለት አላማ መዋሉን እና የተፈለገውን ውጤት ማስገኘቱን በፌዴራል ደረጃ ሪፎርሙን በሚመራው በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሊታወቅ ሲገባ በፌዴራል እና በክልል የሚገኙ ተቋማት ለመሰረታዊ የአሰራር ለውጥ ጥናት ለማካሄድ እና

የምርጥ ተሞክሮ (Benchmarking) በተለያዩ የዓለም ሀገራት ለማካሄድ የወጣው የገንዘብ መጠን አለመታወቁ እና ገንዘቡ ለተባለለት ዓላማ መዋል አለመዋሉን የሚያሳይ መረጃ አለመኖሩ የሚሉት በኦዲቱ ወቅት የታዩ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

በመሆኑም የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖረት አሳስበናል፡፡

6.17. በኮሜት ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር የጭነት ትራንስፖርት፤ የመለዋወጫ ዕቃ ግዥና የንብረት አስተዳደር የአሠራር ስርዓትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ግኝቶች

- አክሲዮን ማህበሩ ለማጓጓዝ የተስማማቸውን ጭነቶች በውሉ መሰረት ሊያከናውን እና ጊዜን መቆጠብ በሚያስችል መልኩ ዕቃዎችን መጫን፤ ማራገፍ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ሲገባ በመሰረታዊ የትራንስፖርት ቅንጅትና ትርፋማነት መመሪያ ላይ በተቀመጠው መለኪያ መሰረት በዓመት የአንድ ተሽከርካሪ በመጫን ማራገፍ ሂደት አማካይ የጊዜ ቆይታ ቀን 48.75 ቀን (17%) እንደሚፈጅ የተገለፀ ሲሆን ማህበሩ በአራቱ ዓመታት በመጫን ማራገፍ የባከነ ጊዜ እንደቅደም ተከተሉ በመቶኛ 23%፣ 34%፤23% እና 27% መሆኑ፤
- አክሲዮን ማህበሩ በጭነት ትራንስፖርት ዘርፍ ትርፋማና ተፎካካሪ ለመሆን ያሉትን ተሽከርካሪዎች የመለዋወጫ ፍላጎት፣ የጥገና ምልልስ እና የመጫን አቅም ያገናዘበ ጥናት በማካሄድ ወጪን በመቀነስ የተሻለ ተፎካካሪ ሊያደርገው የሚችል ነባር ተሽከርካሪዎችን በአዲስ የሚተኩበት ስትራቴጂ አለማዘጋጀቱ፤
- በመሆኑም አክሲዮን ማህበሩ ካሉት 210 ተሽከርካሪዎች መካከል 93 ማክ ተሽከርካሪዎች ለ20 ዓመታት ያህል ያገለገሉ በመሆናቸው በእርጅና ምክንያት ከፍተኛ የጋራዥ ምልልስ የሚያደርጉ እና የመለዋወጫ ወጪያቸውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ፤

- የመሰረታዊ ትራንስፖርት ቅንጅትና ትርፋማነት መመሪያ መለኪያ የአንድ ተሸከርካሪ የጥገና ቆይታ ስታንዳርድ በአማካይ 73 ቀናት ሲሆን የአክሲዮን ማህበሩ ስታንዳርድ ደግሞ የጋራዥ ቆይታ 76 ቀናት መሆኑ፤
- ከነዚህ ስታንዳርዶች አንፃር የአክሲዮን ማህበሩ አፈፃፀም ሲታይ ከ2002 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ወደ ማዕከላዊ ጋራዥ የገቡ የጭነት ተሸከርካሪዎች የጋራዥ ቆይታ በአማካይ 115 ቀናት ወይም ከስታንዳርዱ 157% በላይ መሆኑ፤
- ለአክሲዮን ማህበሩ የጭነት ተሸከርካሪዎች የጋራዥ ቆይታ መራዘም የመለዋወጫ ዕቃዎች አቅርቦት እና የግዥ መጓተት ዋናው ምክንያት ሲሆን ለሁለት የሲኖትራክ ጭነት ተሸከርካሪዎች ከህዳር 30/2001 ዓ.ም የቀረበ የመለዋወጫ ዕቃዎች ግዥ እስከ ጥር 19/2003 ዓ.ም በመዘግየቱ ተሸከርካሪዎቹ ለሁለት ዓመት ከሁለት ወር በላይ ያለስራ በመቆማቸው አክሲዮን ማህበሩ ተሸከርካሪዎቹ በስራ ላይ ቢሆኑ ሊያገኝ ይችል የነበረውን በአማካይ 2,688,243.48 ብር ገቢ ማጣቱ፤
- ከዚህም በተጨማሪ በመለዋወጫ እጦት ምክንያት 14 ማክ ተሽከርካሪዎቹ የመለዋወጫ ግዥ ተጠይቆ ባለመፈፀሙ ከ10 ወራት በላይ በመቆማቸውና ተጠግነው ወደ ስራ ባለመግባታቸው አክሲዮን ማህበሩ በ10 ወራት ውስጥ ማግኘት የሚገባው ገቢ ብር 1,181,907.132 ማጣቱ፣
- የአክሲዮን ማህበሩ ወጪን ለመቆጠብ እና የተቀላጠፈ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የጭነት ተሸከርካሪዎች በሚሰማሩበት የጉዞ መስመር የደርሶ መልስ ጉዞ ቀን ገደብ ሊኖርና ተግባራዊ ሊደረግ ሲገባ የአክሲዮን ማህበሩ የጭነት ተሸከርካሪዎች የደርሶ መልስ የቀን ገደብ ከአዲስ አበባ ጅቡቲ የተጠናው የደርሶ መልስ ቀነ ገደብ 5 ቀን፣ ከሠመራ ጅቡቲ 3 ቀን፣ ከኮምቦልቻ ጅቡቲ እና ከድሬዳዋ ጅቡቲ 4 ቀናት ሲሆን በሌሎች የጉዞ መስመሮች የተጠና የደርሶ መልስ ቀነ ገደብ አለመቀመጡ እና በኦዲቱ ወቅት እንደታየው የደርሶ መልስ ቀነ ገደብ ወደ 8 ቀናት ከፍ የሚልበት ሁኔታ መኖሩ፤
- የኮሜት ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር በጭነት ትራንስፖርት ዘርፉ ውጤታማ ለመሆን የገቢና የወጪ ዕቃዎችን የማጓጓዝ ስራ ላይ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት መስራት ሲጠበቅበት የተሸከርካሪዎች የደርሶ መልስ አማካይ የጭነት መጠን

(ስታንዳርድ ሎድ ፋክተር) በአክሲዮን ማህበሩ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ እንዲውል የተቀመጠው 70% ሲሆን ማህበሩ ከ2001-2004 ባሉት አራት ዓመታት ለማጓጓዝ ያቀደው አማካይ የጭነት መጠን 56% መሆኑ፤

- አፈፃፀሙ ከ58% አለመብለጡ ደግሞ የአክሲዮን ማህበሩ ተሽከርካሪዎች አብዛኛውን ጊዜ የተመላሽ ጭነት ጉዞ በባዶ ያደርጉ እንደነበረ የሚያሳይ መሆኑ፤
- በገቢና በወጪ ዕቃዎች ላይ የነበረው የአፈፃፀም ደረጃ ሲታይ ደግሞ የገቢ ዕቃዎችን ጭነት የማጓጓዝ አፈፃፀም ከአጠቃላይ የገቢና የወጪ አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር ከ 2001 - 2004 የነበረው ድርሻ እንደ ቅደም ተከተላቸው 95%፣ 91%፣ 89%፣ እና 93% የነበረ መሆኑ፤ በሌላ መልኩ የወጪ ዕቃዎች ጭነትን የማጓጓዝ አፈፃፀም ሲታይ በአራቱ ዓመታት የነበረው ድርሻ 4.2%፣ 8%፣ 8% እና 6.77% በቅደም ተከተል መሆኑ የወጪ ዕቃዎች ለማጓጓዝ በአክሲዮን ማህበሩ ምንም ትኩረት እንዳልተሰጠው እና አብዛኛው ተሽከርካሪዎች ወደ ጅቡቲ ዕቃ ሳይጭኑ በባዶ ይጓዙ እንደነበር የሚያሳይ መሆኑ፤
- የኮሜት ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር በዘርፉ ትርፋማና ተፎካካሪ ሆኖ ለመቀጠል የተጠናከረ የገበያ ጥናት ዘርፍ ሊያቋቁምና የገበያ ጥናቱንም በጭነት ትራንስፖርት ዘርፍ ያለውን ወቅታዊ ገበያ (current market) እምቅና የረጅም ጊዜ ገበያን (potential and long term market) በማጥናት የደንበኞችን ፍላጎት፣ በዘርፉ ያለውን ውድድር በመረዳት ውጤት ሊያመጡ የሚችሉ አማራጮችን ስራ ላይ ማዋል ሲገባ የአክሲዮን ማህበሩ ያቋቋመው የገበያ ጥናት ፍለጋ ቡድን ስራ ያተኮረው የአክሲዮን ማህበሩን የቀድሞ ደንበኞች ለመመለስ በአካልና በስልክ የማግባባት ስራ ላይ እንጂ ዘመናዊ የገበያ ጥናት አካሄድን የተከተለ ጥልቀት ያለው ጥናት አለማከናወኑ፤
- የመንግስት ድርጅቶች የሚያካሂዷቸው የዕቃ ግዥዎች አጠቃላይ የመንግስት ዕቃ ግዥ መሠረታዊ አላማዎችና መርሆዎችን የተከተሉ ማለትም (ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ጥቅም Value for Money ቅልጥፍናና ብቃት፣ ቁጠባ፣ ግልፅነት ተጠያቂነት እና የኢኮኖሚ ዕድገትን) የሚያበረታቱ እንዲሁም የመንግስት ግዥ በአሁኑ ጊዜ የሚመራባቸውን የህግ ሠነዶች መሠረት አድርገው በተዘጋጁ የግዥ

መመሪያዎች መሠረት ሊከናወኑ እና ግዥዎችም በዕቅድ ላይ የተመሠረቱ ሊሆን ሲገባ በግዥ መመሪያ ቁጥር 1/1990 አንቀጽ 17.2 እና በፋይናንስ ደንብ ቁጥር 17/1989 መሰረት የጨረታ አሸናፊው ድርጅት ጨረታውን ማሸነፉ በተገለፀ በ15 ቀናት ውስጥ ውሉን መፈራረም እንዳለበት እና 10% የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ማቅረብ እንዳለበት ይህን ባያደርግ የጨረታ ማስከበሪያው እንደሚወሰድ ቢገለጽም በአክሲዮን ማህበሩ የስራ አፈጻጸም ላይ የታየው ውል የተገባው ሰኔ 29 ቀን 2002 ዓ.ም ሲሆን ውል የተፈረመው መስከረም 27 ቀን 2003 ዓ.ም ከ3 ወር በላይ መቆየቱ አግባብ አለመሆኑ፤

- የግዥ መመሪያው አንቀጽ 13 ቁጥር 7.3 ሪ/4 ላይ የጨረታ ኮሚቴው በመስፈርቶቹ መሰረት የግዥ ውሳኔ ለመስጠት እና አሸናፊውን ለመለየት የአቅራቢውን ድርጅት አቅም አስተማማኝነት ለማወቅ አሸናፊው ድርጅት ለሌሎች ድርጅቶች ተመሳሳይ የግዥ አቅርቦት የፈጸመባቸው ማስረጃዎችን ካሉ አስቀርቦና ማየት፤ እንዲሁም የካፒታል አቅሙን ለመገምገም የንግድ ድርጅቱን በማየት ውል መፈራረም ነበረበት፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ብሉ ቴክ ትሬዲንግ ያስያዘው የውል አፈጻጸም ማስከበሪያ ዋስትና (ባንክ ጋራንቲ) ቀነ ገደቡ ከማለቁ ከ5 ቀን በፊት እንዲራዘም አሳውቁ የሚል ሲሆን በአፈጻጸም የታየው ግን የውል አፈፃፀም ማስከበሪያ ዋስትናው እንዲራዘም የተጠየቀው ቀነ ገደቡ ካለፈ ከ4 ወር በኋላ መሆኑ፤
- የመንግሥት የግዥ መመሪያ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትናን በተመለከተ እንደሚያስቀመጥው የሚቀርበው የዋስትና መጠን ለቅድሚያ ክፍያ ከሚከፈለው ገንዘብ ጋር አቻ መሆን እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሠረት አክሲዩን ማህበሩ ለተሰጠው ቅድሚያ ክፍያ 50% ዋስትናም በዚሁ መጠን እንዲሆን በጨረታ ኮሚቴ መስከረም 10/2003 ዓ.ም በነበረው ስብሰባ የተወሰነ ቢሆንም ማህበሩ ለከፈለው ብር 4.9 ሚሊዩን በብሉ ቴክ ትሬዲንግ የተያዘው ዋስትና 30% ብር 2.7 ሚሊዩን መሆኑና ይሄም በጊዜው ሳይታደስ እንዲቀጥል መደረጉ፤
- በመሆኑም አክሲዮን ማህበሩ በውሉ መሰረት ማለትም ከጥር 27/2003 ዓ.ም ጀምሮ ማሽኑ ባለመረከቡ በወር ውስጥ ከአራት እሁዶች በስተቀር ለ26 ተከታታይ ቀናት ሰርቶ ያስገኝ የነበረው ገቢ በአማካኝ ሲሰላ በቀን

ብር 8827፣ በወር (26 ቀናት) ብር 230,502.00 ለ21 ወራት ለዘገየበት ብር 4,840,542.00 ሲሆን 9% ሕጋዊ ወለድ ብር 914,858.28 በድምሩ ብር 5,755,400.28 ገቢ ማጣቱ፣ በአጠቃላይ አክሲዮን ማህበሩ ቅድሚያ ከከፈለው ብር 4,969,760.84 ጋር ማሽኑን ባለመረከቡ ብር 10,725,161.12 የሚገመት ገንዘብ ማጣቱ፤

- አክሲዮን ማህበሩ የጎማ ግገሮችን ለመፈፀም ባካሄደው ጨረታ የጨረታ አሸናፊ የሆነው ሳያት ኃ/የ/የ/ማ ለግዥ ከተጠየቁት 1194 ጎማዎች ውስጥ 600 ጐማዎች አቅርቦ ቀሪ 594 ጎማዎች በማቅረብ ሂደት ላይ እያለ የውጪ ምንዛሬ ለውጥ ተከሰተ በሚልና የድርጅቱ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው በሚል ምክንያት ቀሪ ጐማዎችን ለማቅረብ አስቸጋሪ ስለሚሆንብኝ ጨረታው ተቋርጦ ለስራ አፈጻጸም ዋስትና ማስያዣ ያስያዙት ገንዘብ ይመለስልኝ የሚል ጥያቄ በ28/12/2002 በደብዳቤ ቁጥር ሳይት/ተክ/3715/2002 በማቅረቡ፤ ለስራው ዋስትና ያስያዙው ብር 631,626.00 የማህበሩን የግዥ መመሪያ አንቀጽ 17.2 ባልተከተለ መልኩ በሦስት ጊዜ ክፍያ መመለሱ ከግዥ መመሪያ ስርዓት አንጻር የጎላ ስህተት መሆኑ፤
- የድርጅቱ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ውል እንዲቋረጥ የቀረበው ጥያቄ በማህበሩ የግዥ መመሪያ አንቀጽ 31 መሰረት ሻጭ ወይም አቅራቢው ጨረታውን ሲጫረት ህጋዊ ሰውነቱ ተረጋግጦ መሆኑን ስለሚገልጽ አክሲዮን ማህበሩ ህጋዊ ሰውነት እያለው ይህንን መፈፀሙ መመሪያውን የጣሰ መሆኑ፤
- የአክሲዮን ማህበሩ ከኢትዮ ኢንቨስትመንት የገዛቸው 15 ስካኒያ የጭነት ተሸከርካሪዎች ከተሽከርካሪው ጋር መምጣት የነበረባቸው ክፍያ የተፈጸመባቸው የድጋፍ ዕቃዎችና መፍቻዎች ባለመምጣታቸው ብር 274,165.44፤ የጐን ቁጥር 79- 002 ስካኒያ ተሽከርካሪ በዋራንቲ ጊዜ የተጠገነበት ወጪ ብር 8137.88፤ ዋጋ ተከፍሎባቸው ያልመጡ መለዋወጫዎች ብር 540,983.55 እና የመለዋወጫ እቃ ማስረከቢያ ለ374 ቀናት የዘገየበት ማካካሻ ብር 569,574.15 በድምሩ ብር 1,392,857.02 ለአክሲዮን ማህበሩ ገቢ ባለማድረጉ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ማጣቱ፤

- በኦዲቱ ወቅት በፕራይቬታይዜሽን እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በ2001ዓ.ም በቀረበው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ በተገለፀው መሰረት የሚሌ ጋራዥ ግንባታ የጨረታ ሰነድ ዝግጅትና የጨረታ አከፋፈት ሲታይ፤
    - o በውሉ አንቀጽ 14 ውል ተቀባዩ የኮንትራት ዋጋውን 10% የውል ማስከበሪያ እንዲያሲዝ የተዋዋለ ቢሆንም ያላስያዘ መሆኑ፣
    - o የጨረታ ሰነድ ሲከፈት የግዥ መመሪያው አንቀጽ 13.7.3. ሐ ተ.ቁ 2 እና 4 የጨረታ ሰነዱ በታሸገ ኢንቨሎፕ እንዲቀርብ ቢያዝም የቀረበ ኢንቨሎፕ ካለመኖሩም በላይ የጨረታ ቃለ ጉባኤ የሌለ መሆኑ፣
    - o የጨረታ ሰነዱ የድርጅቱን ፍላጎት ተረድቶና አስፈላጊ ሥራዎችን ሙሉ በሙሉ ለይቶ የሚሰሩበትን ቁሳቁሶች ጥራትና ዓይነት ያላስቀመጠ መሆኑ፤
    - o በጨረታ ሰነዱ ውስጥ መካተት የሚገባቸው ቴክኒካል መስፈርቶች በትክክል ለጨረታ ግምገማ የሚውሉ መሆናቸው በግልጽ ለተጫራቾች አለመገለጹ፤
    - o የጨረታ ሰነዱ አዘገጃጀት የመሀንዲስ ዋጋ ግምት ያላካተተና በባለሙያ ያልተዘጋጀ ከመጀመሪያው የአማካሪ መሀንዲስ ተሳትፎ የሌለበት በመሆኑ የክለሳ ስራ መጠየቁ፤
    - o የጨረታ ሰነድ ባስከተለው ከፍተኛ ክፍተት የጣሪያ ሥራ ከእንጨት ወደ ብረት መቀየሩ ፤
    - o በመለኪያ አጠቃቀም ምክንያት የተጨማሪ ሥራዎችና የዋጋ ለውጥ መከሰቱ፤
    - o የጨረታው አሸናፊ ከአክስዩን ማህበሩ ጋር ውል ሲፈራረም በ6 ወር ወይም በ180 ቀናት ውስጥ ግንባታውን እንደሚያጠናቀቅ ውል የገባ ቢሆንም ከተቀመጠው ጊዜ በላይ በ3 ዓመት ከመዘግየቱም ባሻገር ስራው በአግባቡ ሳያልቅ አክሲዮን ማህበሩ የተረከበ መሆኑ፤
- በአክሲዮን ማህበሩ የሚፈጸሙ ግዥዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ሊከናወኑ ሲገባ የሲኖ ተሸከርካሪ መለዋወጫ ግዥ ከቴክኒክ መምሪያ የግዥ ጥያቄ ህዳር 30/2001 ዓ.ም ቀርቦ፣ በስፔስፊከሽን ዝግጅት 3 ወር፤ ለጨረታው ጥሪ የቆየበት 30 ቀናት፤ የጨረታ ግምገማ እንዲሰረዝ

የተባለው ውሳኔ የተሰጠበት 1 ወር ከ 8 ቀን፤ ጨረታው ከተሰረዘ 1 ወር በኃላ ግዥው ለ2002 ዓ.ም ተሸጋግሮ፤ ሐምሌ 1/2002 ዓ.ም ጨረታው ተከፍቶ የቴክኒክ ግምገማ ተደርጎ ከ20 ቀን በኋላ ጨረታው ተሰረዘ፤ ባጠቃላይ ግዥው ሳይፈፀም ጥያቄው ከቀረበበት ከህዳር 30/2001 ዓ.ም እስከ ጥር 19/2003 ዓ.ም ድረስ 2 ዓመት ከ3 ወር በላይ መዘግየቱ እንዲሁም የመለዋወጫ እቃ ግዥ ጥያቄው ጥር 17/2004 ዓ.ም ቀርቦ እስከ ህዳር 7/2005 ዓ.ም ድረስ ከ10 ወራት በላይ ግዥ ሳይፈፀም በመዘግየቱ በጥገና እና ማሽን ሾፕ የስራ ሂደት በመለዋወጫ እጦት ምክንያት 14 ማክ ተሽከርካሪዎች መቆማቸው፤

- አክሲዮን ማህበሩ የጥቅል ግዥዎች የሚያከናውንበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ሲገባ በታህሳስ 1 ቀን 2001 ዓ.ም ኦዲትና ኢንስፔክሽን ባደረገው ምርመራ ሪፖርት የአክሲዮን ማህበሩ የመለዋወጫ ዕቃ ግዥዎች በተናጠል ከአንድ ሱቅ ብር 94,800.00 በተደጋጋሚ ግዥ መፈፀሙ ተገልጿል፡፡ ከዚህ ሱቅ በቀን ብር 39,800.00 የሚያወጣ ግዥ ይገዛ እንደ ነበር ይህ ድርጊት ሊታረም ሲገባው አሁንም ድረስ የተናጠል ግዥዎች በብዛት የሚከናወን መሆኑ፤ ይህም ከፍተኛ ግዥዎች የአክሲዮን ማህበሩን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ በጨረታ እና በጅምላ የማይከናወን መሆኑ የሚያሳይ መሆኑ፤
- አክሲዮን ማህበሩ የሚፈፅማቸው ግዥዎችም ሆነ አገልግሎቶች በህጋዊ መንገድ መፈጸም እና ተገቢ በሆኑ ሰነዶች ሊደገፉ ሲገባ ከዋናው መ/ቤት ለጅቡቲ ቅ/ጽ/ቤት የስራ ማስኬጃ በየወሩ ብር 150,000 የሚላክ ሲሆን የአላላክ ሂደቱ ከዋናው መ/ቤት ወደ ሚሌ ቅ/ጽ/ቤት ከተላከ በኋላ ከሚሌ ቅ/ጽ/ቤት ወደ ጅቡቲ በሚሄዱ ሹፌሮች በእጅ የሚላክ መሆኑና፣ ገንዘቡን በጥቁር ገበያ ወደ ጅቡቲ ፍራንክ መንዝረው የሚጠቀሙበት መሆኑ፤
- በአክሲዮን ማህበሩ የሚፈፀሙ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የመለዋወጫ ዕቃ ግዥዎች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ ለመሆናቸው የጥራት ቁጥጥር የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ሲገባ የጐማ የግዥ አፈጻጸም ሲታይ 75000 ኪ.ሜ መሸፈን የሚችል ዋጋው ብር 1,925,000 የሆነ ብሪጅስቶን ጐማ እና 30000 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን 805/250 ፕራይም ዌል ጎማ ዋጋው ብር 1,475,000 የሆነ በሁለቱ መካከል በተደረገ ውድድር ፕራይም ዌል ጎማ በዋጋ 27% ቅናሽ

ቢኖረውም በአገልግሎት 60% ያነሰ ከተጠቃሚው ክፍል /ከቴክኒክ መምሪያ/ 28/02/2001 በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት ጎማዎች ሊሸፍኑ የሚችሉት ከ30000 - 37000 ኪ/ሜትር ሲሆን ከብሪጅስቶን ጎማ ዝቅተኛ በመሆኑ በጨረታ ኮሚቴው ያልመረጠ ሲሆን፣ ይህ የጨረታ ኮሚቴ ያልመረጠውን ፕራይም ዌል ጐማ በወቅቱ በነበሩት ዋና ሥራ አስኪያጅ በተሠጠ ትዕዛዝ መገዛቱን የጎማዎቹ የአገልግሎት ዕድሜ ወይም የሚሸፍኑት ኪ/ሜትር እንደሚፈለገው ሆኖ አለመገኘቱ፤

- እንዲሁም የቦስ ጎማ 18*33 እና 18*25 ግዥዎች ውስጥ በተለይ 18*25 የሆኑት በፎርክ ሊፌቱ ላይ ተገጥመው ሲታዩ ሁሉም የሚፈለገውን አገልግሎት ሳይሰጡ ጎማዎቹ በውስጥ አካላቸው /ግድግዳ/ በኩል በማኮፍከፍና በመፈንዳት ንፋስ መቋጠር ባለመቻላቸው ከጥቅም ውጪ መሆናቸው፤
- አክሲዮን ማህበሩ የውጭና የሀገር ውስጥ መለዋወጫ ዕቃዎችን ግዥ ሲፈፅም የገበያ ዋጋ ዳሰሳ /market survey/በማድረግ በየስድስት ወሩ የተከለሰ የገበያ ዋጋ ዝርዝር /price list/ ማዘጋጀት ሲኖርበት የውጭና የሀገር ውስጥ ግዥ አፈፃፀም ሲታይ የዋጋ መቆጣጠሪያ ስልት የገበያ ዋጋ ዳሰሳ /market survey/ ጥናት እየተደረገ በየስድስት ወሩ የተከለሰ የገበያ ዋጋ ዝርዝር /price list/ የማይዘጋጅ መሆኑ፤
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተከለሱ የግዥ ሰነዶች ውስጥ የመለዋወጫ ዕቃ ግዥ ሲፈፀም የገበያ ዋጋው ብር 12,244.34 ሆኖ በግዥ ሰራተኞች የተገዛበት ዋጋ ግን ብር 27,364.59 መሆኑ ይህም ብር15120.25 (227%) ከገበያ ዋጋ በላይ የተከፈለ መሆኑ፤
- የመንግስት ልማት ድርጅቶች ያላቸውን ንብረት በሽያጭ፤በዝውውር ወይም ማስወገድ ሲያካሂዱ በጥናት ላይ ሊመሰረቱና እና የሚሰጡትም ውሳኔ የድርጅቱን የአጭር እና የረጅም ጊዜ ጥቅምን ያገናዘበ መሆን ሲኖርበት የኮሜት ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር ከአዲስ መካኒካል አክሲዩን ማህበር በ1995 ዓ.ም ያገኘውን የጐማ ማደሻ ማሽን ለግለሰብ በማከራየት ሲጠቀምበት የቆየ ቢሆንም ማሽኑ ያለበቂ ሥራ ረጅም ዕድሜ ያስቆጠረና ተጨማሪ ወጪን እያስከተለ ነው በሚል ለአንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት በካፒታል ዝውውር እንዲፈፀም አክሲዮን ማህበሩ ለፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች

ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በሰኔ 9 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር ኮት አማ/01/83/2001 እና የአንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት ሰኔ 25 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር አከአአድ/ሥድ/0775/01 በተጻፈ ደብዳቤ በጠየቁት መሠረት የተቆጣጣሪ ኤጀንሲው ዝውውሩ እንዲፈፀም በነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓም በቁጥር መልድ 123-223/1540 ማጽደቁ፤

- ይሁን እንጂ የኮሜት ትራንስፖርት አክሲዩን ማህበር በነሐሴ 2001 ዓ.ም ባካሄደው የመሠረታዊ የአሠራር ማሻሻያ ጥናት (BPR) ለተሸከርካሪ ጥገና ደጋፊ የሥራ ሂደት የምርጥ ተሞክሮ /Bench Mark/ ጥናት የተካሄደ ሲሆን በዚህ ጥናት ውስጥ የጐማ ማደሻ ማሽንን አስመክልቶ ከትራንስ ኢትዮጵያ የምርጥ ተሞክሮ ወስዷል፡፡ በተካሄደው ጥናት መሠረትም ትራንስ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የወጪ ማካካሻ ተግባር የሚያከናውነው በጐማ ማደሻ ማሽን መሆኑን እና በዚህ የጐማ እድሣት ሥራ በአራት ሰዓት ጊዜ ውስጥ በአንድ ጊዜ ስድስት ጐማዎችን በማውጣት በአማካይ 24,000 /ሃያ አራት ሺህ/ብር ማዳን እንደተቻለ እና ይህም በአንድ ቀን የብር 48,000 /አርባ ስምንት ሺህ/ ወጪ ለማዳን መቻሉን፣ ለጐማ ማደሻ ማሽኑ የሚያስፈለገውም የጥሬ ዕቃ አቅርቦትም ከኬንያ፣ ከሕንድ እና ከደቡብ አፍሪካ በቀላሉ ሊገኝ እንደሚችል መገለጹ፤
- በ2001 ዓ.ም የአንድ ጐማ ዋጋ ከብር 7,000 /ሰባት ሺህ በላይ የነበረ ሲሆን ከብር 2,500 ሁለት ሺህ አምስት መቶ/ ባልበለጠ ወጪ ጐማዎችን በማደስ /Recapping/ ብቻ ከፍተኛ የጐማ ወጪ ቅነሳ ማድረጋቸው፣ በጐማ ማደሻ ማሽኑ የተጠገነ ጐማ ከ36,000 እስከ 40,000 ኪሎ ሜትር የሚያገለግል ሲሆን ይህ የታደሰ ጐማ ደግሞ እስከ ሶስት ጊዜ እየተጠገነ ሊሠራ እንደሚችል በጥናቱ ከተገኘው መረጃ ለመረዳት መቻሉ፤
- በተመሳሳይ መልኩ የኮሜት ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር ንብረት የነበረው የጐማ ማደሻ ማሽን በቀን 12 ጐማ ማደስ የሚችል በመሆኑ በቀን 48,000 ብር ሊያተርፍ ይችል የነበረ ቢሆንም አክሲዮን ማህበሩ ያለበቂ ጥናት ለአንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት በካፒታል ዝውውር የኮሜት ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር የተሸከርካሪ ጥናት ደጋፊ የስራ ሂደት የBPR ጥናት ቡድን ያካሄደውን የምርጥ ተሞክሮ የጥናት ሪፖርት ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም ለአክሲዮን ማህበሩ ስራ

አስኪያጅ ያቀረበ ሲሆን የBPR ጥናት ቡድኑ ወደ ቀጣዩ ስራ እንዲገባ የተላለፈበትን ቃለጉባዔ ለቦርድና ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የተላከ ቢሆንም በተመሳሳይ ወር ነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓ.ም የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ለአንበሳ አውቶብስ እና ለኮሜት ትራንስፖርት ስራ አመራር ቦርድ ከጥናት ቡድኑ የምርጥ ተሞክሮ ውጤት በተለየ ሁኔታ የካፒታል ዝውውሩ መፈፀሙ፤

- የአክሲዮን ማህበሩ የንብረት አስተዳደር መመሪያ ተከትለው የንብረት ምዝገባ ማካሄድ ሲኖርበት አክሲዮን ማህበሩ የንብረት አስተዳደር መመሪያ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በታገዘ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ምዝገባው እንዲከናወን ቢያዝም ይህ ተግባራዊ ሆኖ አለመገኘቱ፤
- በ2001 በጀት ዓመት በአክሲዮን ማህበሩ የውስጥ ኦዲት በተደረገው የቋሚ ንብረት ቆጠራ ውጤት በስቶክ ቆጠራ እና በሂሳብ ቋቱ መካካል ብር 1,274,922.30 የሚያወጡ የተለያዩ ቋሚ ዕቃዎች በጉድለት የተመዘገበ ሲሆን ይህም ልዩነት በ2000 ዓ.ም በብልጫ ከተመዘገበው ብር 1,101,033.91 ጋር የተካካሰ ቢሆንም የብር 173,888.00 ልዩነት መታየቱ እና እስካሁንም ማስተካካያ ያልተደረገ መሆኑ፤
- አክሲዮን ማህበሩ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የጭነት ተሽከርካሪዎችና መለዋወጫዎችን በንብረት አወጋገድ መመሪያ መሰረት ሊያስወግድ ሲገባ ብር 14,907,848.00 የሆነ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸዉ የቴክኒክ ስራ ማከናወኛ ማሽነሪዎችና መሳሪያዎች በእርጅና እና በቴክኒክ ባለሙያ ተጠንተው አክሲዮን ማህበሩ የማይጠቀምባቸው ወይም በትርፍነት የሚገኙ በመሆናቸው እንዲወገዱ አስተያየት የቀረበ ቢሆንም በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ከ20 ዓመት በላይ በማገልገል ላይ የሚገኙ የማክ ተሽከርካሪዎች ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ለማስወገድ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ተፈጻሚ አለመሆኑ፣ ብር 1,830,454.41 ዋጋ ያላቸው በተሽከርካሪ ጥገና እና ማሽን ሾፕ ዲጋፔ የስራ ሂደት የተመዘገቡ 1533 የተለያዩ መሳሪያዎች በአሁን ሰዓት ያሉበት ቦታ የማይታወቁ መሆኑን፤ በተጨማሪም ዋጋቸዉ ብር 25,065 የሆኑ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ሁለት የበር ላይ የመኪና መፈተሻ መሳሪያዎች ወጪ ተደርገው አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፤

- አክሲዮን ማህበሩም ሆነ ቅ/ጽ/ቤቱ ለስራው በሚያስፈልጋቸው የሰዉ ኃይልና በማቴሪያል የተሟሉ ባለመሆናቸው የመጫን ማራገፍ ስራ በተቀላጠፈ ሁኔታ የማይከናወን መሆኑ፤
- የአክሲዮን ማህበሩ የስራ ሂደቶች በቅንጅት መስራት የሚያስችላቸውን የአሰራር ስርዓት ሊዘረጉ እና ተግባራዊ ሊያደርጉ ሲገባ ከኦፕሬሽናል ዕቅድ በመነሳት ለበጀት አመቱ በክምችት የሚያዘውን የመለዋወጫና ድጋፍ ዕቃ ዝርዝር በመለያ ቁጥር፣ በዓይነት፣ እንዲሁም በመጠን ኢንቬንተሪ ኮንትሮል በዓመቱ መጨረሻ እያዘጋጀ ለቴክኒክ መምሪያ እንደሚያቀርብና ቴክኒክ መምሪያም ዝርዝሩን በማጣራት በክምችት የሚያዝለትን መጠን በመወሰን የተረጋገጠ ሰነድ ለግዥ ክምችትና ንብረት መምሪያ እንደሚልክ ይታወቃል፡፡ ሆኖም፣ ኢንቬንተሪ ኮንትሮል የፍላጎት ጥናት የሚሰራዉ በአብዛኛዉ በቆሙ ተሽከርካሪዎች ላይ ብቻ በመሆኑ ለሌሎች ተሽከርካሪዎች ክምችት እንዲያዝ ቴክኒክ ለግዥ ክምችትና ንብረት መምሪያ የሚልክበት ሁኔታ መኖሩና ለግዥ ክምችትና ንብረትም መለዋወጫዎችን በፍጥነት በመግዛት ለቴክኒክ እንደማያቀርብ እና እነዚህ የስራ ሂደቶች በመቀናጀት ስራውን ባለማከናወናቸው ምክንያት ተሽከርካሪዎች በፍጥነት ተጠግነው የማይወጡና ለብዙ ጊዜ የቆሙ ተሽከርካሪዎች መኖራቸው የሚሉት በኦዲቱ ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

7. የልዩ ኦዲት ስራዎች

በኦዲት ዓመቱ በፍ/ቤቶች ትህዛዝና በተለያዩ አካላት ጥያቄ መሰረት የልዩ ኦዲት ስራዎች ተከናውኖ ሪፖርታቸው ለሚመለከታቸው አካላት የተላኩ ሲሆን፣ የተከናወኑትም ልዩ ኦዲቶች፣

1. የብሔራዊ ሎቶሪ አስተዳደር ጎባ ቅ/ፅ/ቤት የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ማጣራት
2. የኮሜት ትራንስፖርት ድርጅት ሂሳብ
3. የኢትዮጵያ ሲቪል አቬሽን ባለስልጣን

4. የኢትዮ-ጂቡት ምድር ባቡድ ድርጅት የአሮጌ ብረታብረት ሽያጭ ሂሳብ ማጣራት
5. የአክሱም ሐውልት አስመላሽ ብሔራዊ ኮሚቴ ሂሳብ
6. የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት
7. በሴቶች ጉዳይ ሚ/ር የኢ.አ የማገዶ እንጨት ተሸካሚ ሴቶች ማህበር ሂሳብ

ናቸው፡፡

8. ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሰረት እርምጃ ያልተወሰዱ መ/ቤቶች

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡– በ24 መ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱ ሲሆን /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ - 35 ተመልክቷል/ እርምጃ ያልተወሰዱባቸው ነጥቦችና በየመ/ቤቶቹ በየዘርፉ ዝርዝር ሪፖርት መጨረሻ ክፍል ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ እርምጃ እንዲወሰድ ለሁሉም መ/ቤቶች በድጋሚ አሳስበናል፡፡

9. መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮች

መ/ቤታችን በሕገ-መንግሥትና የማቋቋሚያ አዋጁ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ከፍተኛጥረት እያደረገ ቢሆንም፤ በተደጋጋሚ በሚያገጥሙትና መፍትዔ ባላገኙ ችግሮች ምክንያት ያሰበውን ያህል መራመድ አልቻለም፡፡ በሥራ ላይ ካጋጠሙት ችግሮችም መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ኦዲቱን በሚፈለገው መጠንና ጥረት ለማከናወን የሚያስችል በቂ ክህሎትና ልምድ ያለው ባለሙያ ለመቅጠር አለመቻልና ከፍተኛ ልምድ ያለቸው ሠራተኞች ከደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቀሞች ማነስ ጋር በተያያዘ መ/ቤቱን መልቀቃቸው መቀጠሉ፣

- ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ሂሣባቸውን በወቅቱ ዘግተው ለኦዲቱ አለማቅረብና አንዳንድ የስራ ኃላፊዎች ለልዩ ልዩ ማብራሪያዎችና ለሚጣሩ ጉዳዮችና ለመዉጫ ስብሰባዎች ሲፈለጉ በወቅቱ አለመገኘት፤
- ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሚቀርበው የስራ አመራር ሪፖርት ላይ በወቅቱ ምላሽ አለመስጠት፣
- ኦዲት ተደራጊዎች በሚሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረት በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድና የቀጣዩ ኦዲት የስራ ጊዜ አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ፣

ዋና ዋናዎች ናቸው፡፡

10. የመፍትሔ እርምጃዎች

እየተወሰዱ ከሚገኙት የመፍትሄ እርምጃዎች፣

በየወቅቱ መ/ቤቱን የሚለቁትን ለመተካት በየሩብ ዓመቱ ቅጥር በማከናወን ለመሙላት ጥረት እየተደረገ ሲሆን፣ ለኦዲት ባለሙያዎች የሙያ አበል እንዲያገኙ ለም/ቤቱ ጥያቄ ቀርቦ ምላሽ እየተጠባበቅን ነው፡፡

የኦዲት ተደራጊዎችንም በተመለከተ በተለያዩ መድረኮች በማነጋገር ለኦዲቱ ስራ የሚያደርጉትን ትብብር እንዲያጠናክሩ የግንዛቤ መፍጠርና አስፈላጊነቱን የማሳመን ስራዎች ተከናውኗል፡፡

11. ማጠቃለያ

በሪፖርቱ እንደተመለከተው በ2004 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተካሄደው ኦዲት በሂሳብ ምርመራ ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የተያዙትን ጨምሮ የኦዲት ሽፋኑን 96.12% ደርሷል፡፡ የኦዲት ዕቅድ ክንውናችንም የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት 100% እና የክዋኔ ኦዲቱም 17 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችን ለማውጣት ታቅዶ 17ቱም ሲጠናቀቁ ሌሎች በዳሰሳና ቅኝት ደረጃ የሚገኙ 10 ክዋኔ ኦዲቶች ወደ ቀጣዩ ዓመት የተላለፉ ስለሆነ፤ውዝፍ የኦዲት ሥራ ባለመኖሩ ወቅታዊ የኦዲት መረጃን ማመንጨት ተችሏል፡፡

በዚህ ረገድ የተገኘው ውጤት የሀገራችንን የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት የተሻለ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያመለክት ቢሆንም፤ በኦዲቱ ሂደት በየመ/ቤቱ በተደጋጋሚ የሚታዩት ዋና ዋና ግድፈቶች በአፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድባቸው

ይገባል፡፡ ዝርዝር ሪፖርቱ በሁለት ጥራዝ ተዘጋጅቶ፤ የእያንዳንዱ ክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ሪፖርት በ17 ጥራዝ ለአፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት የተላከ በመሆኑ፤ ም/ቤቱ በመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኩል በጥልቀት መርምሮ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በተጨማሪም እርምጃ ሳይወሰድባቸው ከዓመት ወደ ዓመት የሚተላለፉ የሠነድ ሂሣቦች፣ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚፈጸሙ ግዥዎች፣ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ በየዓመቱ የሚታዩ ተመሳሳይ ችግሮችና ከውስጥ ገቢ አሰባሰብና ሪፖርት አደራረግ አንፃር የሚታዩ ችግሮች፤ እንደዚሁም ከመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮችና በሚቀርቡት የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የማይወስዱ አካላትን፤በተለይም ኦዲት ተደራጊዎች በጊዜ ገደብ የታጠረ የማስተካከያ መርሀ-ግብር መንደፍና የሚሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሀሳቦችን ተግባራዊ ማድረግ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ የም/ቤቱ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም ቋሚ ኮሚቴዎች የክትትልና ቁጥጥር ፕሮግራም በመንደፍና በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በመታገዝ የግድፈቶቹን መንስኤዎች በማጣራት ከሥረ መሠረቱ ለማስወገድ የተጀመረው አሰራር የበለጠ ተጠናክሮ ሊሠረበት ይገባል፡፡

በመጨረሻም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የቀረፃቸውን የአሠራር ማሻሻያዎችና ስትራቴጂዎችን በሚገባ በመተግበር ይበልጥ እንዲጠናከርና የምክር ቤቱን የክትትልና የቁጥጥር ተግባር በተሻለ ደረጃ እንዲያግዝ ሁሉን አቀፍ ድጋፍና ክትትል እንዲደረግልን እንጠይቃለን፡፡

የ2004 በጀት ዓመት የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ኦዲት አፈጻጸምና ዋና ዋና ግኝቶች

1. መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት በመንግሥት በጀት እና በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን፣ በመንግሥትና በውጭ ሀገር መንግሥት ድጋፍ የሚከናወኑትን ፕሮጀክቶችን፣ እንዲሁም የዕርዳታ ሂሳቦችን ኦዲት እንደሚያደርግ ይታወቃል። ሆኖም በመ/ቤቱ የአቅም ውስንነት የተነሳ ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የዕርዳታ ሂሰቦች በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና ከመ/ቤቱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በማስደረግ ላይ ይገኛል። በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት ተደርገው በሚቀርቡ ሪፖርት መነሻነት መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች አስፈላጊው ማሻሻያዎችና እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊው ድርጅት፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ የበላይ መ/ቤቶች በደብዳቤ አስፈላጊውን ማሳሰቢያ በመስጠት ውጤቱን ከሌሎች ኦዲት ጋር ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያቀርባል፡፡

በዚሁ መሠረት የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በተከናወነው ኦዲት የተገኙ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች ቀጥለው ቀርበዋል።

2. የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2004 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት

2.1 የኮርፖሬሽኑ ዓላማ

የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የተቋቋመው በአዋጅ ቁጥር 126/1969 ሲሆን የመንግሥት የሆኑ ወይም አብዛኛው ድርሻቸው በመንግሥት ለተያዘ የማምረቻና የማከፋፈያ እና የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ሂሣብ ኦዲት ማድረግና የኦዲት ሙያን ማዳበር ሲሆን፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ራሳቸውን ችለው በአዋጅ ቁጥር 25/1984 እንዲተዳደሩ ከተወሰነ ወዲህ ግን፣ የኦዲት ሥራውን

በጨረታ ካሸነፈ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንም ሆነ የግል ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

2.2 የኦዲት ሪፖርት ዝግጅትና ስርጭት

የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ኦዲት ሪፖርቶችን ለድርጅቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ወይም ለሥራ አመራር ቦርድ ሲልክ በግልባጭ ለተመርማሪው ድርጅት ያሳውቃል፡፡

በተጨማሪም ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርቱን ተመልክተው አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኙና ክትትል እንዲያደርጉ በግልባጭ እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

አንድ የፋይናንስ ኦዲት ከተከናወነ በኋላ የሚዘጋጁት ሪፖርቶች ሁለት ዓይነት ሲሆኑ እነርሱም አጭርና ረዥም /ዝርዝር/ ሪፖርት በመባል ይታወቃሉ፡፡

በአጭር ሪፖርት የሚሰጡ አስተያየቶች ዋና ዓላማ በአንድ ድርጅት ተዘጋጅተው የቀረቡ የሂሣብ መግለጫዎች በአለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን የኦዲት ደረጃዎች መሠረት በማድረግ በቂ በሆነ ናሙና /በአልፎ አልፎ የኦዲት ዘዴ/ በመጠቀም ኦዲት ከተደረጉ በኋላ መግለጫዎቹ ትክክለኛውን የፋይናንስ ሁኔታ ማሣየት ወይም አለማሳየታቸውን በመግለፅ ኦዲተሩ አስተያየት የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡

በረጅም ሪፖርት ላይ የሚሰጡ አስተያየቶች በኦዲቱ ወቅት የተደረሰባቸውን የገንዘብና የንብረት ጉድለቶች፣ የቁጥጥርና የአሠራር ድክመቶች በመጠቆም እነዚህን ጉድለቶችና ድክመቶች ለማስወገድ ምን ዓይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በመግለጽ የማሻሻያ ሃሣብ የሚሰጥበት ነው፡፡

2.3 የሥራ ዕቅድና ክንውን

ኮርፖሬሽኑ በ2004 በጀት ዓመት በዕቅድ የያዛቸውና ያከናወናቸዉ የሂሣብ ምርመራ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ተ.ቁ.	መግለጫ	የ2004 በጀት ዓመት		የ2003 በጀት ዓመት
		ዕቅድ	ክንውን	ክንውን
1	የአምራች ድርጅቶች ኦዲት መምሪያ	162	158	177
2	የአገልግሎት ሰጪና የማከፋፈያ ድርጅቶች ኦዲት መምሪያ	78	76	76
	ድምር	240	234	252

ወጪ የሆኑት 234 ሪፖርቶች /ይህ ቁጥር የአንድ መ/ቤት ድርጅት የሁለትና ከዚያ በላይ ሂሳባቸው የኦዲት የተደረጉትን አንድ በአንድ በመቁጠር የተወሰደ ነው፡፡/

ሪፖርቶቹም በኦዲት አስተያየት ሲተነተኑ፤ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቃፊታ የሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው 114፤ ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው 103፤ አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት የተሰጠባቸው 4 እና የልዩ ሪፖርቶች 13 ናቸው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኮርፖሬሽኑ በመንግስት ጥያቄ የሁለት የፈረሱ ድርጅቶችን ሂሳብ እያጣራ ሲሆን፤ ከዚህም በበጀት ዓመቱ ብር 747,492.00 ገቢ አግኝቷል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የ2004 ክንውን በሪፖርት ብዛት ከዕቅዱ ጋር ሲነፃፀር በ6 ሪፖርቶች በቁጥር የሚያንስ ሲሆን ከ2003 በጀት ዓመት ክንውን ጋርም ሲነፃፀር በ18 ሪፖርት ወይም በ7% ማነስ አሳይቷል፡፡ ይህም ምክንያቱ የሰው ኃይል በመሳሳቱ፤ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ በነበረው የሰው ኃይል ዕቅዱ በመነደፉ ነው፡፡

2.4 <u>የኮርፖሬሽኑ የሰው ኃይል ሁኔታ</u>

በ2003 በጀት ዓመት መጨረሻ የሠራተኛው ብዛት 116 የነበረ ሲሆን፣ በ2004 በጀት ዓመት፣ ከምድብ ሥራቸው ላይ የጠፉ 2 እና በፈቃዳቸው የተሰናበቱ 1 በመሆኑ፤ በ2004 በጀት ዓመት መጨረሻ 113 ሠራተኞች እንደነበሩ ታውቋል።

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የነበረው የሰው ኃይል በሙያ ሲተነተን ፕሮፌሽናል ኦዲተሮች 75፣ የአስተዳደር 37 እና አንድ የትምህርትና ስልጠና ሠራተኞች ሲሆኑ፤ በፆታም ሲታይ 62 ወንድና 51 ሴት እንደሆኑ ታውቋል፡፡

2.5 የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ

ኮርፖሬሽኑ ከተቋቋመበት ዓላማ አንደኛው የኦዲት ሙያ በይበልጥ የሚዳብርበትንና አገሪቷ በዚህ ሙያ ረገድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሷን እንድትችል የሚደረገውን ጥረት ማገዝ እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡

በዚህም መሠረት በእንግሊዝ አገር ከሚገኘው አሶስዬሽንስ ኦፍ ሠርቲፋይድ አካውንታንትስ (ACCA) የሚሰጠውን የተልዕኮ የሙያ ትምህርት የድርጅቱ ኦዲተሮች እንዲከታተሉ በገንዘብና በጊዜ እንዲሁም በመጻሕፍት እየረዳ 24 ሠራተኞችን በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በአገር ውስጥ ባሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን በትርፍ ጊዜአቸው ለሚማሩ ሰራተኞች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተገቢውን ድጋፍ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

የኦዲት ሙያ ያለ ቀጣይና ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ሊከናወን እንደማይችል በዓለም አቀፍ ደረጃ የታመነበት በመሆኑ፤ ኮርፖሬሽኑ በዚህ ረገድ ለሠራተኛ የሚሠጠው ሥልጠና ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

2.6 የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ

የኮርፖሬሽኑ የገቢ ምንጭ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት በመስጠት የሚያገኘው ገቢ ሲሆን፤ በተጨማርም ከሂሳብ ማጣራትና ከሕንጻ ቢሮዎች በሚገኝ ኪራይ ነው፡፡ በ2004 በጀት ዓመት በዕቅድ የያዘውና አገልግሎቱን አከናውኖ ያገኘው ገቢ፣ እንዲሁም ሥራውን ለማከናወን ያቀደው ወጪና በአግባቡ ወጪ ያደረገው ሂሣብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የ2004 የፋይናንስ ዕቅድና ቅንውን

መግለጫ	ገቢ ብር	ወጪ ብር	ትርፍ ብር
ዕቅድ	12,836,750	8,693,232	4,143,518
ክንውን	13,998,601	9,841,546	4,157,055
ክንውን በመብለጥ /በማነስ/	1,161,851	1,148,314	13,537

የ2004 የዕቅድ ክንውን ከ2003 ጋር ሲነፃፀር እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

የበጀት ዘመን	ገቢ ብር	ወጪ ብር	የተጣራ ትርፍ ብር
2004	13,998,601	9,841,546	4,157,055
2003	11,555,444	7,816,982	3,738,462
ልዩነት በመብለጥ	2,443,157	2,022,564	418,593

በሰንጠረዡ እንደተመለከተው የ2004 የገቢና ወጪ ክንውን ከ2003 ጋር ሲነፃፀር ከፍ ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡

3. በ2004 በጀት ዓመት በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉት የመንግስት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 82 ሲሆኑ በኢትዮጵያ መንግስትና በውጭ መንግስታት የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ደግሞ 150 በድምሩ 232 (ይህ ቁጥር በአንድ በጀት ዓመት የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረገው መ/ቤት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርብ ዓመቱን ብቻ እንደ አንድ በመቁጠር የተወሰደ ነው) ናቸው፡፡

በእነዚህ ሪፖርቶች የተሰጠው በኦዲት አስተያየት ዓይነት ሲተነተን፣ ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Unqualified opinion) የቀረበበት 87፣ ነቀፌታ ያለበት አስተያየት (**Qualified** opinion) የቀረበበት 142፣ አቋም የማይወሰድበት አስተያየት (Disclaimer opinion) የቀረበበት 2 እና ተቀባይነት የሚያሳጣ የኦዲት አስተያየት የቀረበበት 1 በድምሩ 232 ናቸው፡፡

4. ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች

በ2004 በጀት ዓመት በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች ሂሣባቸው ኦዲት ተደረጎ ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን ከደረሱን የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ጉልህ የሆኑ የየድርጅቶቹ ድክመትና የሂሣብ አያያዝ ጉድለቶች የተነሳ የኦዲት ሪፖርቱ ውጤት አቋም ለመውሰድ የማይቻልና ተቀባይነት የሚያሳጣ ነው ተብለው በኦዲተሮች አስተያየት የተሠጠባቸው ድርጅቶች ሁኔታና ከሁለት ዓመት በላይ ሂሳባቸውን ኦዲት ያላስደረጉ ድርጅቶች ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.1 ተቀባይነት የሚያሳጣ የኦዲት አስተያየት የሰጠባቸው

ተቀባይነት የሚያሳጣ የኦዲት ሪፖርት የተሰጠባቸው ድርጅትና ይህንን እንዲያሰጥ የደረሱ ጉልህ የሆኑ የየድርጅቶቹ ድክመትና የሂሣብ አያያዝ ጉድለቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.1.1 የኢትዮጵያ ማዕድን ልማት አ.ማ.

ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የተጠናቀቀው የአክስዮን ማሕበሩ ሂሣብ በኮካብ ሞገስና ጓዶቹ የተመሠከረላቸው የሂሣብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ኦዲት ተደርጎ የቀረበው ኦዲት አስተያየት ቀጥሎ የተመለከተው ነው፡፡

- በሂሣብ መግለጫው የተመለከተው የመነሻ ካፒታል ሂሣብ አክስዮን ማሕበሩ ሲመሠረት በወቅቱ የነበረውን የተሰብሣቢ ሂሣብ ተከፋዮችና የክምችትና የተጣራ ሂሣቦችን በትክክል ያልተንፀባረቁ መሆኑ በቀድሞ ኦዲተሮችም ትክክል አለመሆኑ በመገለጹ ፣
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የክምችት ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ከመዝገብ ጋር ሣይገናዘብ የምዝገባውን ውጤት ብቻ በሂሣብ መግለጫው በመካተቱ ፣
- አክስዮን ማሕበሩ በአፋር የጨው አምራቾች አክስዮን ማህበር 83.33% የአክስዮን ድርሻ ቢኖረውም እንደዋና ባለድርሻነቱ አጠቃሎ የአፋር የጨው አምራቾች ማህበርን ሂሣብ መግለጫዎችን አጠቃሎ ያላስገባ እና የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ (consolidated financial statement) ያላዘጋጀ በመሆኑ፣

- የተሰብሣቢ ሒሣብ 52,138,550 ለረዥም ዓመታት የቆየና ምንም መጠባበቂያ ያልተያዘለት እና የተከፋይ ሒሣብ ብር 24,642,297 ለረዥም ጊዜ ምንም እንቅስቃሴ የሌለው ለምን እንዳልተከፈለ ወይም ስለተደረገው ትክክለኛነት በቂ ማብራሪያ ያልተሰጠው መሆኑ፣
- በሒሣብ መግለጫው የሚታየው በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ ሥራዎች በትክክል በዝርዝር ያልተመዘገበ በመሆኑ፣
- በሰኔ 30/2001 የተመለከተው ተሰብሣቢ የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) በምዝገባው እና ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተገለፀው መካከል የብር 920,319 ልዩነት መኖሩ እና፣
- ከልማት ባንክ የተገኘው የረዥም ጊዜ ብድር በተመለከተ ስለትክክለኛነቱ ከባንኩ ማረጋገጫ ባለመሰጠቱ፣

በድርጅቱ ተዘጋጅታው ለኦዲት የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች የኢ.ማህበሩን የስራ እንቅሰቃሴ፤ የገንዘብ ምንጭና አጠቃቀም፤በአለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝ መርሖዎች መሰረት እንደሚያሳዩ ኦዲተሮቹ አስተያያታቸውን ሰጥተዋል ፡፡

ከዚህ በኋላ በደረሰንና የተወሰዱ እርምጃዎች እንዲገለፁልን ለጠየቅነው ጥያቄ በተሰጠው ምላሽ የተጠቀሱት ችግሮች አንዳንዶቹ እንደተሰተካከሉ ገልጸው ሌሎች ማስተካከያዎችም ለማድረግ የተዘጋጀውን መርዓ-ግብር አያይዘው ልከዋል ፡፡ በዚህ 2005 ዓም ሰኔ 30/2002 ዓ.ም የተጠናቀቀው የኢ.ማ ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ የደረሰን ሲሆን የተወሰኑ ማስተካከያዎች እየተደረጉ እንደሆነ ቢገለፅም በኦዲት ሪፖርቱ ተመሳሳይ አስተያየት መቅረቡ ተውቋል፡፡

4.1.2 የቡና ተክል ልማት ድርጅት

ሰኔ 30/2001 ዓ.ም የተጠናቀቀው የድርጅቱ ሂሣብ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ የቀረበው የኦዲት አስተያየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በሰኔ 30/2000 ዓ.ም የተመለከተው የቋሚ ንብረት ሂሣብ በዋጋ ወይም በግምታዊ የዋጋ ሥልት (valuation) የተመለከተ ሲሆን በዓመቱ መጨረሻ የተመለከተው ከዋጋው በላይ ትርፍ ብር

150,368,912 ነፃ በሆነ ባለሙያ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ስለትክክለኛነቱ ማጣራት ባለመቻሉ፣

- ዓመታዊ የቋሚ ንብረቶች ቆጠራ ቢከናወንም ከንብረትና ሂሳብ ምዝገባዎች ጋር ባለመገናዘቡ በሂሣብ መግለጫው የተመለከተው የቋሚ ንብረቶች ዋጋ ብር 153,447,605 ሁሉም በአካል ስለመኖራቸው ማረጋገጫ ያለመኖሩና እና በዓመቱ የተከናወነው የቴፒ ቡና ልማት የዶዘር ግዥ ብር 5,776,312 በሂሣብ የተካተተ ቢሆንም ለሌላ ሦስተኛ ወገን የተላለፈ መሆኑ፣
- በሊሙ ቴፒና በበቃ ቡና እርሻዎች ያልተለየ ቅንስናሾች ተብሎ በወጪ ሂሳብ የተያዘው ብር 166,605,821.00 እስካሁንም ባለመጠራቱ፣
- በሂሳብ መግለጫው የተመለከተው ጉዞ ላይ ያሉ ዕቃዎች ሂሳብ ብር 6,110,576.00 ትክክለኛነት ለማመን አስተማማኝ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት አለመኖሩ፣
- በሂሳብ መግለጫው የተመለከቱት የረጅም ጊዜ ተቀማጭ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ሚዛን ትክክለኛነት የሚያመላክት ምንም ማረጋገጫ በለማግኘታችንና ለረጅም ጊዜ ሳይጣራ የቆየ የጥሬ ገንዘብ ጉድለትና የባንክና የጥሬ ገንዘብ ማስተካከያዎች ሳይጣሩ የቆዩ በመሆናቸው፣
- የተለያዩ ሕጋዊ ግዴታዎችን ባለመወጣት የተከተሉ እዳዎችና ብድር፣ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ወለድ ሂሣቦች፣ ከመዝገብ እንዲሠረዙ ተጠይቆ የተፈቀደውና በበጀት ዓመቱ ከመዝገብ የተሠረዘ ብር 789,628,002 እና የገ/ኢ/ል/ሚ/ር የረዥም ጊዜ ብድር ከወለድ ጋር ብር 780,535,762 ከመዝገብ ሲሠረዙ ያልተለየ ልዩነት ብር 6,603,239 እና ብር 99,964,797 እንዴት ሊከሰት እንደቻለ በቂ ማብራሪያ ማግኘት አለመቻሉ፣
- በእርሻ ጣቢያውና ድርጅቱ ዋና መ/ቤት መካከል የተከናወኑ የሂሣብ ልውውጦች ተሰሰብሣቢ ሂሣብ ልዩኑት ብር 36,281,235 ያልታረቀ /unreconcile difference/ ማብሪሪ ያልተሠጠበት መሆኑ፣

- በብልጫ የተከፈለ የትርፍ ድርሻ /dividend/ ብር 6,198,125 እና የትርፍ ግብር ተመላሽ ብር 19,761,634 ትክክለኛነት ላይ በቂ መረጃና ማብራሪያ የተሰጠ ባለመኖሩ፣
- የተዘጋጁት የሂሣብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የድርጅቱን ሀብትና ዕዳ፣ የሥራ እንቅስቃሴና የገንዘብ ፍሰቱን ያሚያሉ ብሎ አስተያየት ለመስጠት እንዳስቻላቸው ገዳጸዋል፡፡
- ከዚህ በተጨማሪ በሂሣብ መግለጫው ጋር በተያዘው ማብራሪያ ውስጥ ቀጥሎ ስለነበረው ሁኔታ የበበቃ የቴፒና የሊሙ ቡና እርሻ ልማት ድርጅቶች ወደ ግል ድርጅት የዞሩ ስለመሆናቸው ተጠቅሷል፣ እንዲሁም የሂሳቡ ኦዲት በሶስት ዓመታት ወደ ኋላ የቀረ መሆኑና በኦዲተ ሪፖርቱ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ የተወሰደ እርምጃ እንዲገለጽልን ለተጠየቀው ጥያቄ አንዳንድ ማስተካከያዎች ተደርገው ከ2002-2004 ያለው ሂሳብ ኦዲት እየተደረገ መሆኑ በተሰጠን ምላሽ ተገልጿል፡፡

5. ስለልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች የሂሳብ አያያዝና ንብረት አጠባበቅ በተመለከተ

የልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች አጠቃላይ የሂሳብ አያያዝ፣ ንብረት አጠባበቅና አስተዳደርን በተመለከተ በኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ችግሮችና መፍትሔያቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡

5.1 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

- በርካታ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ የሌላቸው፤ ያላቸውም ምዝገባቸው ያልተሟላ፣ አንዳንዶች ደግሞ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶችን አንድ ላይ መዝግበው መገኘታቸው፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መዝገብ ቢይዙም የግዥ፤ ሽያጭንና ዝውውርን በተመለከተ የተሟላ መረጃ ካለመመዝገባቸው የተነሳ መዝገብ የሚታየው የዋጋና የአገልግሎት ቅናሽ ሂሳብ በዋናው መዝገብ ጋር በየወቅቱ ባለመመሳከሩ በሁለቱ መዝገቦች መካከል ልዩነቶች እንደሚያጋጥሙ፣

- በመዝገብ የተዘረዘሩት ንብረቶች በእውን መኖራቸውንና ተገቢው እንክብካቤ የሚደረግላቸው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል የቋሚ ንብረት ቆጠራ እንደማይደረግና የተደረገም ከሆነ ከመዝገቡ ጋር የማይገናዘብና ልዩነት ከተገኘም እንዲታረቅ የማይደረግ መሆኑ፣
- በውርስና በተለያዩ መንገድ ቋሚ ንብረቶች ከአንድ ድርጅት ወደ ሌላ ሲዛወሩ በተገቢው መንገድ ርክክብ የማይካሄድና በሰነድ ያልተደገፈ በመሆኑ ምክንያት ቋሚ ንብረቶች በተረካቢውም ሆነ በአስረካቢው ድርጅት የሂሳብ መዝገብ ውስጥ በትክክል የማይመዘገቡ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ለቋሚ ንብረቶቻቸው የገዙት የመድን ዋስትና በቂ ያልሆነና በአደጋ ጊዜ ሊደርስ የሚችለውን ጥፋት ሙሉ በሙሉ ሊሸፍን የማይችል ሲሆን ሌሎች ደግሞ ለንብረቶቻቸው የመድን ዋስትና ያልገቡ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የንብረት መጥፋት የተከሰተ መሆኑ ለመረዳት ቢቻልም ንብረቱ የጠፋበት ምክንያት ተጣርቶ እንዲተካ እንደማይደረግ በኦዲት ወቅት ታይቷል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶቹ በንብረት ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዲያደርጉና የንብረት ሂሳባቸው ትክክለኛውን ሂሳብ ለማንጸባረቅ እንዲቻል አስፈላጊውን ሁሉ እንዲደረግ በየኦዲት ሪፖርቱ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

5.2 በመጋዘን ያሉ እቃዎች

- በመጋዘን ያሉ እቃዎች (stock) በሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ ላይ ቆጠራ የማያደርጉ ወይም ከፊል ቆጠራ ብቻ ማድረጋቸውና ሌሎች ደግሞ ቆጠራ ቢያካሂዱም የቆጠራውን ውጤት ከሂሳብ መዝገቡ ጋር ተገናዝቦ ልዩነት ካለ አስፈላጊውን ማስተካከያ የማያደርጉ መሆኑ፤
- አንዳንድ ድርጅቶች በመጋዘን ያሉ እቃዎች እንቅስቃሴ የሚከታተሉበት መቆጣጠሪያ መዛግብት (stock card) እንደማይዙ፤ ሌሎች ደግሞ አሟልተው የማይመዘግቡና የምዝባ ስህተቶች ልዩነት ሲያጋጥሟቸው ጉዳዩን ሳያጣሩ በተሰብሳቢ ወይም ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ የሚይዙ መሆኑ፣
- በብዙ ድርጅቶች ውስጥ በብልሽትና በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ ሳይውሉ ለረዥም ጊዜ ተከማችተው የቆዩ እቃዎች መኖራቸውና

በአንዳንድ ድርጅቶችም እነዚህ እቃዎች በዝርዝር ተመዝግበው ባለመያዛቸው ለእቃዎች መጠባበቂያ ተብሎ በመዝገብ የሚታየው ሂሳብ ትክክለኛነት ለመገመት የማይቻል መሆኑ፣

- ከሀገር ውጭ በሚገዙ እቃዎች እስከሚደርሱ ድረስ በጉዞ ላይ ያሉ እቃዎች በሚል ሂሳብ ውስጥ እስከ 6 ወር ያህል ጊዜ ብቻ መዝግቦ መቆየት የሚቻል ቢሆንም በበርካታ ድርጅቶች በጉዞ ላይ የሚገኙ እቃዎች ተብሎ ከሁለትና ከዚያ በላይ ዓመት የሚቆዩና አንዳንዶቹም በሰነድ ያልተደገፉ ሂሳቦች፣ የጠፉ ወይም የተበላሹ እቃዎች ከሆኑም በወቅቱ የመድን ካሳ ያልተጠየቀባቸው መሆኑ፣
- በእቃ ግመጃ ቤት ውስጥ ከረዥም ጊዜ በፊት አንዳንዱም ከውርስ ጊዜያቸው ጀምሮ በምርት ዕደት የነበሩ ወይም ለሌላ አገልግሎት ያልዋሉና በየጊዜው ምንም እንቅስቃሴ የማያሳዩ ለረዥም ጊዜ በመቆየታቸው የተነሳ ጥቅም ላይ ወይም በምርት ተግባር ስለማይውሉ እነዚህ ዓይነት ንብረቶች የመጠባበቂያ ሂሳብ እንዲያዝላቸው ወይም ከሂሳብ መዝገብ ውስጥ እንዲቀነሱ የማይዳረግ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት በተደጋጋሚ የተገኙ ናቸው፡፡

በመሆኑም ድርጅቶቹ በክምችት እቃዎች ላይ የሚያደርጉት ቁጥጥር እንዲጠናከርና የታዩት ችግሮች ላይ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰድ በየኦዲቱ ሪፖርት ማስገንዘቢያ ተሰጥቷል፡፡

5.3 <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

- አብዛኞቹ ድርጅቶች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ሳይሰበስቡ ከዓመት ዓመት ስለሚያሸጋግሩ ተሰብሳቢው እየበዛና ጊዜው እየረዘመ በሄደ ቁጥር ባለእዳዎችን በውዴታ ወይም በሕጋዊ መንገድ ለማስከፈል ችግር መፍጠሩና ድርጅታቸው በውዝፍ ያሉትን ሂሳቦች ገቢ እንዲደረጉለት ተገቢውን ጥረት የማያደርጉ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ተሰብሳቢ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ከማን መሰብሰብ እንዳለባቸው የማይታወቁ መኖራቸው፣እንዲሁም ድርጅቶቹ የሂሳብ ግንኙነት ካላቸው መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የተሟላ አድራሻ ባለመያዛቸዉ በኦዲት ወቅት የተመረጡ ድርጅቶችን

በዓመቱ መጨረሻ የነበረው ሂሳብ በቀጥታ ከድርጅቶች ለማጣራት /ማረጋገጫ ለማግኘት የሚደረገው ጥረት አልተሳካም፣

- በብዙ ድርጅቶች ለሠራተኞች ብድርና የቅድሚያ ደመወዝ ብድር መስጠት የተለመደ ቢሆንም አንዳንድ ድርጅቶች ስለአወሳሰዱ፣ አፈ‌ቃቀዱና አሰባሰቡ መመሪያ የሌላቸው መመሪያ ያላቸውም ቢሆኑ በትክክል ስለማይተገብሩ ከፍተኛ የመንግሥት ገንዘብ በሠራተኞች ስም በተሰብሳቢ ይታያል፡፡ ከዚህም ሌላ ብድር ያለባቸው ሠራተኞች ከመ/ቤቱ ሲሰናበቱ ወይም ወደሌላ ድርጅት ሲዛወሩ ያለባቸውን እዳ እንዲከፍሉ ወይም እንዲጣራ ስለማይደረግ ለረዥም ጊዜ የቆዩ የብድር ሂሳቦች ሲንከባለሉ የሚታዩ መሆኑ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለአንድ ባለእዳ ሁለትና ሶስት ወይም ከዚያ በላይ የሂሳብ ቋት ስለሚከፈት የሂሳቦች መመሰቃቀልና አለመስማማትን የሚያስከትል ሆኖ ይታያል፡፡

በመሆኑም በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ ቁጥጥር እንዲጠናከር፣ ሊሰበሰቡ የሚችሉ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲሰበሰቡ ይህም ካልተቻለ ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካል ጋር በመመካከር ሂሳቡ እንዲሰረዝ በማድረግ ሂሳቦቹ ትክክለኛው የድርጅቱን የተሰብሳቢ ሂሳብ ገጽታ የሚያሳዩ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚገባ በኦዲቱ ሪፖርት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

5.4 <u>በባንክና በካዝና ያለ ገንዘብ</u>

- አንዳንድ ድርጅቶች የሚሰበስቡትን ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ገቢ የማያደርጉና ከዚህም ገንዘብ ላይ ክፍያዎች እንደሚፈጽሙ፣ በርካታ ድርጅቶች በባንክ ያላቸውን ሂሳብ በየወሩ ከባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ ጋር በወቅቱ በማገናዘብ እንደማያስታርቁ፣ የባንክ መዝገባቸውና የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ መካከል ልዩነት ቢያጋጥም እንኳ የልዩነቱን መንስኤ እንደማያጣሩና አንዳንዶችም ምንም እንቅስቃሴ የሌላቸው የባንክ ሂሳቦች ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ መኖሩ፣
- በርካታ ድርጅቶች በሂሳብ ዘመኑ መጨረሻ በካዝና የነበረውን ጥሬ ገንዘብ እንደማይቆጥሩ፣ ቢቆጥሩም በዓመቱ መጨረሻ የሚደረገው የጥሬ ገንዝብ

ቆጠራ ከመዛግብቱ ጋር በማመሳከር ልዩነቱ ካለ እንደማያጣሩ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች በባንክ ያለውን ሂሳብ በትክክል ለመቆጣጠር ከባንክ የሚላከውን ወርሃዊ የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያና ዓመታዊ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከሂሳብ መዝገብ ጋር ማስታረቅና ልዩነቶችና ስሕተቶችን እንዲሁም አላግባብ ወጪ የሆኑ ሂሳቦች ሲኖሩ ወዲያውኑ ተከታትሎ አስፈላጊውን እርምጃ እንደወስድ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች ተገልጾላቸዋል፡፡

5.5 <u>ተከፋይ ሂሳቦች</u>

- በርካታ ድርጅቶች ለመንግሥት መክፈል የሚገባቸውን ግዴታዎች ማለትም ከሰራተኞች ደመወዝ የተቀነሰ የሥራ ግብር፣ የጡረታ ማዋጮ እንዲሁም የሽያጭና የንግድ ትርፍ የታክስ ሕጉ በሚያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው እንደማይከፍሉ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ተካፋይ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩና ለማን መክፈል እንዳለባቸው የማይታወቁና ለረዥም ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩ የረዥም ጊዜ ብድሮች እንዳሉባቸውና ከአበዳሪዎች ጋርም በየጊዜው የሂሳብ መግለጫዎች ስለማይለዋወጡ በኦዲት ወቅት ከአበዳሪዎች /ተከፋይ ድርጅቶች/ ማረጋገጫ በሚጠየቅበት ጊዜ መልስ የማይሰጡ ቢሰጡም ድርጅቶቹ አለን ከሚሉት ሂሳብ ጋር ከፍተኛ ልዩነት የሚታይ መሆኑ የሂሳቦቹን ትክክለኛነት አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች የተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ በየወቅቱ እንዲከፍሉ ትክክለኛነቱንም እንዲያጣሩ በተላከላቸው ሪፖርት ተገልጿል፡፡

5.6 <u>ስለ ሂሳብና የሰነድ አያያዝ</u>

- አንዳንድ ድርጅቶች ውስጥ ቫውቸሮች በሂሣብ ሠራተኞች ከተዘጋጁ በኋላ አግባብ ያለው የሥራ ኃላፊ ተመልክቶት ትክክለኛነታቸውን መርምሮ ሳያፀድቅ በሂሣብ መዝገብ እንደሚመዘገቡ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለሂሣብ ሠነዶች የሚያደርጉ ቁጥጥር አናሳ መሆኑና በማተሚያ ቤት ቁጥር ተሰጥቶአቸው የሚወጡ ሰነዶች እንቅስቃሴ እየተመዘገበ ቁጥጥር እንደማይደረግ፣ ከክፍያ ሠነዶች ጋር የተያያዙ የወጪ ደጋፊ ደረሰኞች የተወራረዱ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ምንም

ዓይነት ምልክት እንደማይደረግባቸውና በአንዳንድ ሂሣቦችም የአርዕስት አመዘጋገብ ስህተት እንደሚታይ ታውቋል፡፡

የዚህ ዓይነት አሠራር የድርጅቶችን ገንዘብ ለብክነት የሚዳርግ፣ የሂሣብ ሠነዶችን በሚፈለጉበት ጊዜ በቀላሉ ለማግኘት ስለማይቻል፣ ሠነዶች በጥንቃቄ እንዲያዙና ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ እንደማገባ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች ሪፖርት ተልኳል፡፡

6. በመንግሥትና የልማት አጋሮች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ

በመንግሥትና የልማት አጋሮች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ የሂሳብ አያያዛቸው በአጠቃላይ አጥጋቢ ሲሆን በአብዛኛው የተሰጠው የኦዲት አስተያየትም ነቀፌታ የሌለበት (clean opinion) እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

ሆኖም በአብዛኛዎቹ ፕሮጀክት ፈፃሚዎች ትኩረት ያልተሰጣቸውና በተደጋጋሚ በሥራ አመራር ሪፖርት ላይ የሚጠቀሱ በኦዲት ሪፖርቱም መሠራት የማሻሻያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የተለየ የባንክ ሂሳብ እንዲኖራቸው ለሚጠይቁ ፕሮጀክቶች ለብቻ የባንክ ሂሳብ አለመክፈትና በየወቅቱ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ አለማዘጋጀት፣
- በባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ እና በባንክ መዝገብ መካከል የሚታዩ ልዩነቶች መንስኤ አለማጣራት፣
- ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ በሳጥን እንዲቀመጥ የሚደረግ መሆኑ፣
- በዓመቱ መጨረሻ የሚታየውን የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ አለማድረግ እና ወይም የቆጠራውን ውጤት ከመዝገብ ጋር አለማመሳከር፣
- በበርካታ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ መጠን ያለው ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖር እና በዕድሜ ተተንትኖ አለመገለጽ፣
- አልፎ አልፎ በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ ክፍያን በወጪ መመዝገብ የሚታዩ መሆኑ፣
- ቅድሚያ ክፍያና ተሰብሳቢ ሂሳቦች ሳይወራረዱ ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ መሆኑ፣
- የአንዱን በጀት ዓመት የፕሮጀክት ወጪ ለሌላው በጀት ዓመት የመመዝገብ ሁኔታ የሚታይ መሆኑ፣

- ከዋናው መ/ቤት የሚተላለፈው የገንዘብ መጠንና በፈፃሚ ቅ/ጽ/ቤት/መ/ቤት ገቢ የሆነው /የተመዘገበው ሂሳብ መካከል ልዩነት መኖሩ፣
- በአንዳንድ ፕሮጄክቶች ለበጀት ዓመቱ ከተመደበው በርካታ መጠን ያለው ገንዘብ ሥራ ላይ ሳይውል ወደ ቀጣይ ዓመት የሚዞር መሆኑ፣
- በፕሮጀክት ሂሳብ የሚገዙ ቋሚ ዕቃዎች ምዝገባ የማይካሄድና መለያ ቁጥር በአግባቡ የማይሰጥ መሆኑ፣

ከቀረቡት የኦዲት ሪፖርቶች መረዳት ተችሏል፡፡

በመሆኑም በየፕሮጀክቶቹ የሚታዩት የሂሳብና ንብረት አያያዝ ግድፈቶች በኦዲት ሪፖርቱ መሠረት ማስተካከያ ሊደረግባቸውና የሚደረገው ቁጥጥር ሊጠናከር ይገባል፡፡

7. የችግሮቹ ምክንያቶችና መፍትሄያቸው

7.1. የችግሮቹ ምክንያቶች

በሂሣብ አያያዝና ቁጥጥር ረገድ ለሚታዩት ችግሮች ምክንያት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በብዙዎቹ ድርጅቶች ተገቢውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት አለመዘርጋትና ካለም ተግባራዊ አለማድረግ፤
- የድርጅቶች የበላይ ኃላፊዎችና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በውጭ ኦዲተሮች የሚሰጡ የእርምትና የማሻሻያ ሃሣቦች ላይ ተገቢውን እርምጃ አለመውሰድ ናቸው፡፡

7.2. ችግሮቹን ለማቃለል ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃች

- የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በማንኛውም ድርጅት መዋቅርና የአሠራር ፕላን ውስጥ መዘርጋት ያለበት ሲሆን፣ የድርጅቱ ገንዘብና ንብረት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ማንኛውንም የምዝበራና ብኩንነት ሁኔታ ከምንጩ ለመከልከል፣ የድርጅቶች የሂሣብ መዛግብትና ሠነዶችና መረጃዎች አስተማማኝ መሆናቸውን ለማረጋገጥና የሥራ ቅልጥፍናና የውስጥ እንዲኖር ለማድረግ፣

- ማኔጅመንቱ የሚያውቃቸውና ከበላይ አካል የሚወጡ መመሪያዎች ሁሉ ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ስለሚረዳ ተገቢ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

ኦዲት ተደራጊ ድርጅቶች በውስጥም ሆነ፤ ከውጭ ኦዲተሮች የሚሰጡ ማሻሻያ ሃሣቦችን ተግባራዊ ማድረግና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶችም አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡